# ከንጥቂያ ባሻገር

## የገቢር መጽሃፍ



3 መቅድም፤ ¡DESPÓJATE! እራሳችሁን አንፁ! መናፍስታዊ መሳሪያዎች ለንጥቂያ፤ በሩበን ጌስታምቢዴ-ፈርናንዴዝ

7 ምስጋና

9 የንጥቂያ ጉዳዮች፤ ግብዣ፤ በጽኑ አረሞች የምርምር ቡድን

15 የጽኑ አረሞች ፍጭት፤ በጽኑ አረሞች የምርምር ቡድን

33 ወፍራም ደም፤ በናኦሚ ሪንኮን ጋላርዶ

53 ብርሃን፣ ነበልባል፣ ጉጉል፤ በሲልቪያ ዳስ ፉዳስ

75 በወንዝ ዳርቻ፤ በሮሽታ ቱግሩል

97 ዴስፒና፤ በኢፔክ ሃምዛኦግሉ

121 የወረቀት አውድማ፤ በጃኒን ጀምበሬ

145 የኦፖስም ጽናት፤ በናኦሚ ሪንኮን ጋላርዶ

169 መቆርቆር እና መሆን፤ በብርሃኑ አሻግሬ

193 መደምደሚያ፤ በዘመናችን ባለው የሉላዊ ደቡብ ወቅታዊ እውነታ ላይ የቀረበ ሂሳዊ ቁዘማ፤

በኤልሳቤጥ ወልደጊዮርጊስ

197 አባሪ፤ ጽኑ አረሞች አብሮ የመስራት ፕሮቶኮል፤ በጽኑ አረሞች የምርምር ቡድን

205 ከንጥቂያ ባሻገር የትግበራ ካርዶች









# ከንጥቂያ ባሻገር

# ከንጥቂያ ባሻገር

## የገቢር መጽሃፍ

K. Verlag
2021

አኔተ ባልዳውፍ የማህበራዊ ጉዳዮች ተመራማሪና አስተማሪ ናት። ስራዎቿ እና ፍላጎቷ በሥነጥበብ አስተምህሮ (የማስተማር ዘዴ) እና የከተማ ቦታ/መሬት ፖለቲካዊ ግንኙነት የሚያጠነጥኑ ሲሆን፤ የትብብር የሥነጥበብ ፕሮጀክቶች ላይ በመሳተፍ የረጅም ጊዜ ተሞክሮ አላት። ከብዙዎቹ እንዲህ ያሉ የትብብር ፕሮጀክቶች አንዱ ስፔስስ ኦፍ ኮመኒንግ የሥነጥበብ ልምምድና የለውጥ ራዕይ (Spaces of Commoning. Artistic Practices and Visions of Change) የተባለው ከ ስቴፋን ግሩበር፣ አኔተ ክራውስ፣ ሆንግ-ካይ ያንግ፣ ማራ ቬርሊክ፣ ቭላድሚር ሚለር፣ ጁልያ ቬገር፣ እና ሞይራ ሂል ጋር በ 2017 የሰራችው ስራ ነው። በቪዬና የስነ ጥበብ አካዳሚ ፕሮፌሰርና የ PhD in Practice ፕሮግራምን በዋነኛነት ከሚመሩት ሁለት ምሁራን ውስጥ አንዷ ናት።

ብርሃኑ አሻግሬ የሥነጥበብ ባለሙያና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአለ ሥነጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት ውስጥ በረዳት ፕሮፌሰርነት ደረጃ ያስተምራል። ስራዎቹ በዋነኛነት የከተማ ቦታዎችን በማዘመን ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩ የማያስተማምኑ የኑሮ ሁኔታዎች ላይ ያተኩራሉ። የሚሰራቸው ፕሮጀክቶች ሂደትን ያማከሉና በአብዛኛው ከስቱዲዮ ውጪ የሚከወኑ ናቸው። ብርሃኑ ስራዎቹን በኢትዮጵያና በሌሎች የተለያዩ የዓለም ክፍሎች ያቀረበ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት በቪየና የሥነጥበብ አካዳሚ ውስጥ የ PhD in Practice ፕሮግራም ተማሪ ነው።

ሲልቪያ ዳስ ፋዳስ (የትውልድ ስሟ ሲልቪያ ሳልጉዌሮ) ተቀማጭነቷ በደቡብ ፖርቹጋል የሆነች ፊልም ሰሪ፣ አስተማሪና ተመራማሪ ናት። በቪዬና የስነ ጥበብ አካዳሚ የ PhD in Practice ፕሮግራም ተማሪና ኒውዮርክ በሚገኘው የኩኒ ሴንተር ፎር ፕሌስ ካልቸር ኤንድ ፖለቲክስ የድህረ ምረቃ ማዕከል ጎብኚ ተመራማሪ ናት። የጥናት ፍላጎቷ የሲኒማ ጥበብ ውስጠ ባህሪና ፖለቲካ የሚያተኩር ሲሆን፤ በተሰባበረና ዕረፍት የለሽ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሲኒማን እንደ እብሮነትን መፍጠሪያ ዘዴ በማሰብ ዙሪያ ያጠነጥናል።

ኢፔክ ሃምዛኦግሉ በቪዬና እና ኢስታንቡል የምትኖር የሥነጥበብ ባለሙያ፣ ፊልም ሰሪ እና ተመራማሪ ናት። ስራዎቿ ቦታ፣ የአጋጣሚ ግንኙነት፣ እንጉርጉሮ እና የተለያዩ የትርክት አይነቶች ላይ የሚያተኩሩ ሲሆን፤ አጫጭር ፊልሞችን በዋነኛነት ትጠቀማለች። ኢፔክ የኩዊር ፌሚኒዝም፣ የታሪክ ዶሴ ፖለቲካ (politics of the archive)፣ ባልንጀርነት፣ በጋራ የዕውቀትን የመመስረት (collective knowledge production) ሂደትን ማዕከል ያደረጉ የስብስብ ፕሮጀክቶችን አስተባብራለች። ከእነዚህ ስብስቦች ውስጥ “ff. Feministisches Fundbüro” (2015), Hayırlı Evlat (2017) ይገኙበታል።



ጃኒን ጀምበሬ በቪዬናና በበርሊን ተቀማጭነቷን ያደረገች የሥነጥበብ ባለሙያ፣ ፊልም ሰሪና ተመራማሪ ናት። በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የክዋኔ፣ የትምህርት፣ የቪዲዮ እና የድምፅ ፕሮጀክቶችን በመስራት ላይ ትገኛለች። ስራዎቿ ስጋዊነትና አካል (sensuality and body) ላይ የሚያተኩሩ ሲሆን የስነ ፆታ፣ ዘር፣ የመቻል ፖለቲካ (abelism) እንዲሁም ውክልና እና የትርጉም (translatability) ጥያቄዎች ያሳስቧታል። በተጨማሪም የጥናት ፍላጎቷ አካላዊ እውቀት (embodied knowledge)፣ ስጋዊ ተዋረዶች (sensual hierarchies)፣ የአለመቀነባበር (dissonance) ንድፈ ሀሳብን እንደ ማሰቢያ መሳሪያነትና ከልዩነት ጋር ለመኖር መጠቀምን ያካትታሉ።



ናኦሚ ሪንኮን ጋላርዶ በሜክሲኮ ሲቲ ተቀማጭነቷን ያደረገች የሥነጥበብ ባለሙያ፣ የባህል ሰራተኛና ተመራማሪ ናት። ሂሳዊ አፈ ታሪካዊ ዓለምን የመስራት ፕሮጀክቶች በመፈብረክ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አውድ ውስጥ ምናባዊ የሆኑ አማራጭ ዓለሞችን በስራዎቿ ትፈጥራለች። ስራዎቿና የጥናት ፍላጎቷ ከኢ-ቅኝ ግዛታዊ ፌሚኒዝም (decolonial feminism)፤ ኩዊር ኦፍ ከለር ክሪቲክ፣ ህዝባዊና ሙከራዊ ሙዚቃ (popular and experimental music)፤ የትያትር ጨዋታ (theatre games)፤ ዲ.ዋይ.አይ ሥነውበት (D.Y.I aesthetics)፤ አውዳዊ ክብረበዓላዊነት (vernacular festivities)፤ እደ ጥበብ ስራ፣ እልም አስተኔ (fantasy) እና ግምታዊ ልብወለድ (speculative fiction) ጋር ይዛመዳል፤ ይዋሀዳልም። በቪዬና የስነ ጥበብ አካዳሚ የ PhD in Practice ፕሮግራም ጨርሳለች። ከ Miembro del Sistema Nacional de Creadores de Arte 2019-2022 del Fondo Nacional para La Cultura y las Artes የገንዘብ ድጋፍ አግኝታለች።



ሮሽታ ቱግሩል ተቀማጭነቷን በዲያርባኪር ያደረገች በይነ ዲስቺፕሊናዊ የሥነጥበብ ባለሙያና ተመራማሪ ናት። የስራዋ ዋና ትኩረትም በምርምር ላይ በተመሰረተ መልኩ የማንነትና የቦታ/ሥፍራ ጥያቄዎችን ታጠናለች። ፕሮጀክቶቿ በቦታና በማንነት መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት በፎቶግራፍና፣ በስዕልና ድምፅ ኢንስቶሌሽን (audiovisual installation) ይመረምራሉ። በእንስሳት ህክምና ኤም ኤስሲ ዲግሪዋን በማርዲን አርቱክሉ ዩኒቨርስቲ ካጠናቀቀች በኋላ ኤም ኤዋን በስነ ጥበብ ትምህርት በ 2016 አግኝታለች። በአሁኑ ጊዜ በቪዬና የሥነጥበብ አካዳሚ የ PhD in Practice ፕሮግራም ተማሪ ናት።



ሩቢን ጌስተምቢዴ ፈርናንዴዝ ምርምሮቹ እና ምሁራዊ ተግባራቱ የሚያተኩሩት በምልክታዊ ድንበሮች እና በባህላዊ ምርቶች ተለዋዋጭነት እና በመንነት መታወቂያ ሂደቶች ውስጥ ያሉ ትምህርታዊ አውዶች ዙሪያ ላይ ናቸው። ሩበን (ከኤሚ ክራሄ እና ቢ እስቴፋን ከርፔንተር፣ 2018) ጋር በመሆን በዘር ማንነት እና በስነጥበብ ትምህርት ዙሪያ የተዘጋጀው የፓልግራቭ የእጅ መጽሐፍ ተባባሪ አዘጋጅ ነው። የንድፈ-ሀሳባዊ ሥራው የሚያተኩረው በፈጠራ፣ በቅኝ ግዛት እና በአንድነት መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ነው። ሩበን በኦንታሪዮ የትምህርት ጥናት ተቋም የሥርዓተ ትምህርት እና ፔዳጎጂ ፕሮፌሰር እና የሥርዓተ ትምህርት ጥናት መጽሔት ዋና አዘጋጅ ነው።

ኤሊሳቤጥ ጊዮርጊስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በነጥበባት ኮሌጅ እና በአፍሪካ ጥናት ማዕከል ውስጥ የስነጥበብ ታሪክ ፣ ሂስ እና ቲዎሪ ተባባሪ ፕሮፌሰር ናት። በተጨማሪም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር የሚገኘው የዘመናዊ ስነጥበብ ሙዚየም፤ የገብረ ክርስቶስ ደስታ ማዕከል ዳይሬክተር፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነጥበባት ኮሌጅ ዲን እና እንዲሁም የኢትዮጵያ ጥናት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር በመሆን አገልግላለች። በርካታ ኤግዚቢሽኖችን አደራጅታለች፣ የብዙ ህትመቶች አርታኢ እና ደራሲ ሆና የሰራች ሲሆን፤ እንዲሁም በርካታ አለምዓቀፍ ሙያዊ ግብዣዎችን እና ሽልማቶችን ተቀብላለች። ኤልሳቤጥ የዘመናዊነት ሥነ ጥበብ በኢትዮጵያ (Modernist Art in Ethiopia) የተባለ መጽሐፍ በኦሃዮ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ, 2019 አሰትማለች።



ስሜነህ አያሌው አስፋው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ውስጥ የታሪክ ተመራማሪ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት በደቡብ አፍሪካ በሚገኘው በኬፕታውን ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካ ጥናት ትምህርት ክፍል የዶክትሬት ትምህርቱን እየተከታተለ ይገኛል። ምርምር የሚያደርግባቸው መስኮች አብዮትን፣ የከተማ ማህበራዊና ባህላዊ ለውጥን፣ ዘመናዊነትን፣ ህዝባዊ አመፅን እና ባህልን ያካትታሉ። በሙዚቃ፣ በማህበራዊ ታሪክ፣ በፖለቲካ ንቃተ-ህሊና፣ በፖለቲካ ማንነት ግንባትና በከተማ ታሪክ ላይ የተለያዩ ጥናቶችን ያደረገ ሲሆን የጥናት ስራዎቹም ታሪካዊና ስፍራዊ ትኩረት አላቸው።

# ከንጥቂያ ባሻገር

# ከንጥቂያ ባሻገር

## የገቢር መጽሃፍ

K. Verlag
2021

### መቅድም

# ¡DESPÓJATE!
# እራሳችሁን አንፁ!
# መናፍስታዊ መሳሪያዎች ለንጥቂያ

በሩበን ጋዝታምቢዴ-ፈርናንዴዝ

ማንጻት ወይንም despojos ፖርቶ ሪኮ በልጅነቴ በማድግባቸው አመታት በጣም የተለመደ ነገር ነበር። በልጅነቴ አያቴ ለማንኛውም-ለትንሹም ለትልቁም በሽታ ዴስፖዮስ ፍቱን መድሃኒት ነው ብላ ማንኛውም በሽታ ላለበት ሰው ስታዝዝ በደንብ ትዝ ይለኛል። ሰዎች መጥፎ እድል ከገጠማቸው ዴስፖዮስ መጠቀም ክፉ ነገርን ያስወግዳል። ጥንዶችም ችግር ከገጠማቸው ዴስፖጅ ነው መድሃኒቱ። ጉንፋንም ከጠና በዴስፖዮስ ድራሹ ይጠፋል። ለአያቴ ዴስፖዮስ ደንቃራን፣ መጥፎ ስሜትን፣ ክፉ መናፍስትን፣ ቡዳን፣እርግማንን፣መተትን ሁሉ ያስወግዳል፤ ያርቃል። እራስን ማንፃት ዴስፖሃርሴ (Despojarse) ይባላል። ራስንም ከእርኩስ መንፈስ ይጠብቃል ከደዌም ይፈውሳል።

በፖርቶ ሪኮ የሚገኙት ዴስፖዮስዎች ግን የሚያንጹ እና የሚፈውሱት ብቻ አይደለም። ሌላው አይነት የዴስፖዮስ ንጥቂያ (dispossession) ነው። ዴስፖዮስ በስፖኛ መንጻትም ንጥቂያም ማለት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ብንወስድ የአሜሪካ ጦር በዚህች አገር የምትገኘውን ቪኩዌስ የምትባለውን ከተማ ሶስት አራተኛ ክፍል የተለያዩ ከፖርቶ ሪኮ ነጥቆ የአካባቢውን ተፈጥሮ እና ፖርቶ ሪካኖችን እጅግ የሚጎዱ የጦር ትያትሮችንና ልምምዶችን ሲያካሂድ ነበር። በ 1982 የፖርቶ ሪኮ የቅኝ ግዛት አስተዳድር የቪላ ሲን ሚየዶን ነዋሪዎች መሬት እና መኖሪያዎች ለሃገረ-መንገስቱ ጥቅም ነው በሚል ሰበብ ነጥቋቸዋል። ባለፉት አስርት አመታትም ትልልቅ ባንኮችና ባለሃብቶች የሃገሪቱን ኢኮኖሚ በንጥቂያ አደህይተው ነዋሪዎቹንም ለክስረት ዳርገዋቸዋል። የኢኮኖሚው ውድመትም የአገሩን ሰው አቅም በመሟጠጥ በቅርብ ግዜ ለተከሰቱ የተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭ ከማድረጉም በላይ ከዚህ ጥፋት እንዳያንሰራሩ አድርጓቸዋል። አያቴ አሁን ብትኖር ፖርቶ ሪኮ የሚያስፈልጋት ዴስፖዮስ (መንፃት) እንጂ አውዳሚ የቅኝ ግዛት ንጥቂያ አይደለም የምትል ይመስለኛል። ነጻ የሚያወጣው የሚያንጻው እና የሚያነጻው የመናፍስት እና የቅዱሳን ዴስፖዮስ ወደ ህይወት መንፈስን የሚመልስ ዴስፖዮስ ነው ፖርቶ ሪኮ የሚያስፈልጋት ትል ነበር።

የአያቴን ዴስፖዮስ ለመጠቀም መሳሪያዎች ያስፈልጋሉ። ምንም በሽታን ከሚፈውሱ እጽዋቶች የተሻለና የበለጠ የፈውስ መንገድ የለም። እነዚህ አያቴ ዴስፖዮስ የምታዘጋጅባቸው እፆች ናና፣ጤና አዳም፣ የለውዝ ዛፍ፣ ጦስኝ፣ ባህር ዛፍ እና ፅኑ አረሞች ናቸው። እንደነዚህ አረሞች ሁሉ የዚህ መፅሃፍ ፀሃፊዎች ለዴስፖዮስ የሚያገለግሉ የተለያዩ መሳሪያዎችን ያቀርቡልናል። እነዚህ የፍጥረት ትሩፋት የሆኑ የዚህ መፅሀፍ ፀሃፊዎች የሚያቀርቡልን እሳቤዎችና ተግባራት እራሳችንን ከቅኝ ግዛታዊ ሀይልና ንጥቂያ እንድናነፃ የሚያግዙን በዴስፖዮስ ንጥቂያ ላይ የሚዘምቱ የሚያነፁ ዴስፖዮስዎች ናቸው። እነዚህ መሳሪያዎች ፍሰቱን ለመዝጋት ሳይሆን ለመክፈት የሚያገለግሉና ሊያጠፉ የሚመጡትን የቅኝ ግዛት ሃይሎች ለመታገልና ለመሞገት የሚውሉ ናቸው። የቺክሲዋ ምሁርና የመብት ተሟጋች ሲልቪያ ኩስኳንኩዊ እንደምትለው የእነዚህ መሳሪያዎች አላማ "የሞቱትን የማያስፈልጉትን እና ፍሰቱን የዘጉትን ለማስወገድ እንደ ኤሌክትሪክ ሀይል የደመቀ ከተለያዩ ተቃርኖዎች ጋር አብረን እንድንኖር የሚያግዘን፤ እንዲሁም ዘልቆ እንደሚገባ ጨረር ከላይ ከሚታየው ክፍል ባሻገር የነገሮችን መሰረት እንድናስተውል የሚያደርግ ራእይ ነው"[1] (ይህ በዚህ መቅድም ፀሃፊ ከስፖኛ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመ ሲሆን ከእንግሊዘኛው ወደ አማርኛ የተመለሰ ነው)።

በቪያና ከተማ ባህልና ስነ ጥበብ ስራ ላይ ከተሰማሩት የዚህ መፅሃፍ ጻሃፊዎች ጋር በነበረኝ የውይይትና የመማማር ቆይታ አንድ ላይ ሆነን የጋራ ዴስፖዮስ (የመጽዳት ተግባር) እና ልምምድ አድርገናል። በዚህ ሂደት የተለያዩ እውቀቶችንና የአስተሳሰብ ማእቀፎችን ነቅሶ በማውጣት በጋራ ፈጠራዊ አጋርነትን (creative solidarity) ለመገንባት ጥረናል። አላማችንም ራንጎአቶ

ህላሳኔ እንደሚለው "ንጥቂያን እና የተነቀሉ ትርክቶችን ለመታገል የሚያስችሉ አዲስ ትርክቶችን"[2] ለማከማቸት ሁኔታውን ለማመቻቸት ነው። ይህ መጽሃፍ የተግባር መሳሪያዎች ማጠራቀሚያ አቁማዳ ከመሆን ባሻገር በድንገተኛ መንገድ የሚፈጠሩ የራስ ማንነት እንቅስቃሴ እና ዑደትን ለማከማቸት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ቋት ነው። ይህም ማን እንደሆንን እና እንዴት አብረን እንደምንሰራ እንደገና የምንተርክበት መሳሪያ፤ እንዲሁም የአብሮነትና የአጋርነት አስተምህሮት (pedagogy) መተግበሪያ ዘዴዎች ቋት ነው። የትግበራ መሳሪያዎቹ የተቃኙት እነዚህ የስነ-ጥበብና የባህል ባለሙያዎች ከመጡባቸው አካባቢዎች እና ማህበረሰቦች ውስጥ ነው። አላማቸውም ወፍራም ጠንካራና የረጋውን የቅኝ ግዛት ሂደት ለመፍታት የተቀረጹ አስተምህሮዎች ለመሆን ሳይሆኑ ይልቁንም ኩሲካንኩዊ እንዳለችው በቅኝ ግዛት ቅራኔ ውስጥ ሆኖ የፈወስን በር በመክፈት፥ ሃይሉን በማነቃቃት፥ ድንቅ መናፍስታዊ እና ከሰው በላይ የሆኑትን አካላትን አዲስ ምትሃታዊ ራእዮች በመጋበዝ፥ ጸረ-ቅኝ ግዛታዊ ጽናትን በመገንዘብ ህዝቦች ከንጥቂያ የተረፉበትን/የሚተርፉበትን የትግል ሂደት ለመሰነቅ ነው።

እነዚህ የጋራ ፈጠራ የሆኑ መመሪያዎች ከአዳዲስ አፈ ታሪኮች ጋር እንድንወያይ ይቀሰቅሱናል፤ ድንቅ ተፈጥሮ ያላቸው አካላት እና ህያዋን ጋር በወንዞች ውስጥ እንድንሄድ፣ ክፍተቶችንና ስንጥቆች በመፈለግ ቅኝ ግዛት ያሳጣንን ነገሮች በስሜታችን አንፅረን በፍርስራሽ ውስጥ የተውልንን መርዛማ ቅሪት እንደገና ለመፈተሽ እንድንችል ይረዱናል። እነዚህ የፈጠራ ሰዎች እንካችሁ የሚሉን የትግበራ መሳሪያዎች የምንነጻበትን አስማታዊ ዴስፖዮስ ነው። ይህ አስማታዊ ዴስፖዮስ ከቅኝ ግዛት ነጠቃ እና ነቀላ መላቀቅን የመጨረሻ ግቡ ያደረገ ሳይሆን፤ ከቅኝ ግዛታዊነት ሃይልና ተፅእኖ የሚያነጻ፤ በንጥቂያ ውስጥ ሆኖም በቺክሲ (ch'ixi) ተጋድሎ እና እምቢተኝነት መንፈስ፤ "ውድመትን የሁከትና የአደጋ ጊዜን የሚያመጣ፤ ነገር ግን ምጡቅ የሆነን ነጻነት የሚተፋ ገሞራ (magma) የሚያመነጭ"[3] ነው። እነዚህ የመለወጥ ሂደት (metamorphosis) መሳሪያዎች ሲሆኑ የመለወጥ ሂደቱ ፈጠራዊ እና በፊት የተለመዱ ዘዴዎችን በአዲስ መልክ የሚቃኝ የአናርኪስት ፌሚኒስቶች አፈ-ታሪካዊ፣ እንስሳዊ እና መናፍስታዊ ዘዴዎችን የሚጠቀም ነው። እነዚህ መሳሪያዎች ቅፅበታዊ የፊልም (cinematographic) ዘዴዎችን በመጠቀም ባልተጠበቁ ቦታዎችና ስፍራዎች የተነጠቁ፥ የጠፉ እና በለቅሶና በዋይታ የተረሱትን የሚያስነሱ መሳሪያዎች ናቸው። ሃሜት እና ነውርን በማስታወስ እንደ ጽኑ አረም አዲስ ዘርን በማፍራት አሰቃቂ ከሆነው የቅኝ ግዛት መቃብር ውስጥ ህይወትን ለማትረፍ፥ ለማዳንና ለመንከባከብ የተመለሱ መንፈሶች ናቸው። ቁስሉ ሙሉ በሙሉ ባይሽርም ህመሙ እንዲጠፋ የሚያደርጉ፤ እንደ ትላኩዋቼ ሞት እንኳ የማያቆመውን ህይወት እንደገና ነፍስ እንዲዘራ፣ ህልውና እንዲቀጥል ያደርጋሉ።

1 Silvia Rivera Cusicanqui, *Un mundo ch'ixi es posible. Ensayos sobre un presente en crisis* (Buenos Aires: Tinta Limón, 2018), 152–53; translation by the author.

2 Rangoato Hlasane in personal communication with the author, 26 February 2020.

3 Rivera Cusicanqui, *Un mundo ch'ixi es posible,* 44; translation by the author. For an English version of the text, see Project Bibliography in this volume.



**“የመነጠቅ ተቃራኒ አለመነጠቅ አይደለም። ማከማቸትም አይደለም። አለመርሳትም አይደለም። ግዘፍ መንሳት ነው።”**

— Angie Morrill, Eve Tuck, and the Super Futures Haunt Qollective,
“Before Dispossession, Or Surviving It”



# ምስጋና

እያንዳንዳችን እና ሁላችንም በጋራ በፈታኝ ጊዜያት ላሳየነው የመጋራት መንፈስ፣ ለቁርጠኝነታችንና ለአብሮነታችን እናመሰግናለን።

ለጋስ የባልንጀርነት ሂስን ላበረከቱልን ለኢፒፋኒያ አሞ አዳሬ፣ ሩበን ጋዝታምቢዴ ፈርናንዴዝ፣ አንጄላ ማሊቶፖሎስ፣ ማርጋሪታ ፓላሺዎስ እና ኢቭ ተክ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ሁሉም በዚህ ጉዟችን አብረውን ተጉዘዋል። ኢፒፋኒያን ስለስፍራ ትምህርትና ፅንሰ ሃሳብ ያላቴን ዕውቀት ስላካፈለችን እናመሰግናለን። ሩበንን ትኩረታችንን ወደ አጋርነት ሁኔታዎች እንድናደርግ ስለረዳን እናመሰግናለን። አንጄላን በስራችን እንቅስቃሴ ውስጥ ተለዋዋጭ የሆኑ መመለሶችን እንድናጤንና እውቅና እንድንሰጥ ስለረዳችን እናመሰግናለን።, ማርጋሪታ ደግሞ የስሜትና ምኞትን ሃያልነት ስላሳየችን እናመሰግናለን። ኢቭን የግል ስራዎቻችንን እንዴት የጋራ ከሆኑ ምርምሮች ጋር እንደምናቆራኝ መንገዶችን ስላመላከተችን እናመሰግናለን። የእናንተ ያልተቆጠበ ድጋፍና እንክብካቤ ተጨምሮበት ፕሮጀክቱ እንዲያብብ እና ፍሬ እንዲያፈራ ሆኖአልና ከልብ እናመሰግናለን።

የኦስትሪያ ሳይንስ ፈንድን ፕሮጀክቱን በገንዘብ ስላገዘን እናመሰግናለን። በቪዬና የስነ-ጥበብ አካዳሚ የረዱንን አንድሪያ ቢ. ብራይድትን፣ ማይክል ግላንዝን፣ አኒና ሙለር ስትራስኒግን፣ ዱንያ ራይትነርን፣ ሬናታ ሎሬንዝን፣ ሞይራ ሂልንና የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤቱን የፒኤችዲ እጩዎችን (በተለይም በእግር ጉዟችን አብረውን የተጓዙትን) እናመሰግናለን። ስቴፋኒ ሶሪያልን የሕብር ዝማሬ ቡድን ለመመስረት ባደረግነው ጥረት ስላገዘችን እናመሰግናለን። ናኦኮ ካልትሽሚትን የፊልም ስክሪኒንግ በሙሞክ ኪኖ እንድናዘጋጅ ስለጋበዘን እናመሰግናለን። ራፋል ሞሩሲዊስዚን የመጀመሪያውን የአርትኦት ስራ ስለሰራልን እናመሰግናለን። ኬ. ቬርላግን እና በተለይም አና ሶፊያ ስፕሪንገርን ይህን እትም እውን እንዲሆን ስላደረጉ እናመሰግናቸዋለን።

ሩበን ጋዝታምቢዴ-ፈርናንዴዝን እና ኤልሰቤጥ ጊዮርጊስን ለሚነሽጡት የመቅድም እና የመደምደሚያ ፅሁፎቻቸው እናመሰግናለን።

ናኦሚ፤ ሮዛሊዳ ዲዮኒቺዮ፣ ማሻ ጎዶቫናያ፣ ክላውዲያ ሎፔዝ ቴሮሶ፣ ኦሊቭር ማርቲኔዝ ካንድት፣ ጃኒያ ኤስትራዳ እና Instituto de Artes Gráficas de Oaxaca (IAGO) ታመሰግናለች።

ብርሃኑ፤ ውድ ባለቤቱን ሊያ ግርማንና ሁለቱን ልዕልት ልጆቹን ዲና እና ማያ ብርሃኑን ያለገደብ ለሰጡት ፍቅር፣ መረዳትና እገዛ ያመሰግናቸዋል። በተጨማሪም፤ በጥናቱ ሂደት ውስጥ ከጎኑ ለነበሩ የስራ ባልደረቦቹ፣ ጉዋደኞቹ እና ቤተሰቦቹ ምስጋና ያቀርባል። በመጨረሻም፤ ይህንን መፅሀፍ ወደ አማርኛ በመተርጎም ሂደት ውስጥ ላደረገው ሙያዊ አስተዋፅኦ እና ላጋራው ባልንጀራዊ መንፈስ፤ ስሜነህ አያሌውን ያመሰግናል።

ኢፔክ፤ ሴሚል ሀምዛኦሉ፣ ላውራ ኒችን፣ ማሉ ብሉሜን በዚህ ፕሮጀክት ዘመን ያለገደብ ለለገሷት አለሁ ባይነታቸው፤ ወላጆቿን ደግሞ ለፍቅራቸውና ለዕርዳታቸው ታመሰግናቸዋለች።

ሲልቪያ፤ ብርቱና ለጋስ የሆኑትን በአሌንቴዥ ያገኘቻቸውን ሰዎች፤ በተለይም ጆኤል ጋዛሪያንን፣ ሁሊዮ ሄንሪኬን እና የትሮቪስካይስና ሳኦ ሉዊስ መንደርተኞችን ታመሰግናለች።

ሮሽዳ፤ የፍቅር አጋሩዋ የሆነውን ሙርዶክ ማክሌኦድን ለሰጣት ጠቃሚ ምክርና እገዛ፤ ቤተሰቧን በተለይም አባቷንና እናቷን በትምህርት ላይ ባለችባቸው ጊዜያት ሁሉ ለሰጧት እገዛና ማበረታታት ታመሰግናቸዋለች።

ጃኒን፤ ኒኮል ሱዙኪን፣ ፊሊፕ ካቦ ኮፕሴልን፣ ሬጂና ሳሬይተርን፣ ኢኦቶ ኢ.ቪ. እና በርሊን ፖስትኮሎንያልን ታመሰግናለች።

አኔት፤ ኢቭ ተክን እና ሲልቪያ ፌዴሪቺን ዘላቂ ለሆነው አብርሆታቸው፤ እንዲሁም ጓደኞቿንና ቤተሰቧን ለእገዛቸው ታመሰግናቸዋለች።

**ከፊት ለፊት ያለው አስደሳች እና ፈታኝ ተግባር በእግር መጓዝ እና ዓለማትን እንደ ምርኮኛ ሆኖ ማውራትን ያካትታል። ዕውቀቶችን እና ዓለሞችን በማቋቋም ረገድ የፍጥረታትን ሕያውነት እና የነገሮችን ብዝሃዊነት በመረዳት ሁሉንም እንደ እኩዮች የሚዳሰሱበት ዓለም መፍጠር።**

— Juanita Sundberg, “Decolonizing Posthumanist Geographies”



# የንጥቂያ ጉዳዮች ግብዣ
# (the wilfull weeds research group)

ከንጥቂያ ባሻገር ቅኝ ግዛት ካስከተለው ዘረፋ እና ጥፋት እንዲሁም ከቅኝ ግዛት ስንጥቆች መካከል የሚያድጉ፣ የሚያብቡ ብርቱ እፅዋት ናቸው። በአለም ዙሪያ የተለያዩ ብዝሀ አቀፍ ሁለንተና (pluriverse) እንዲተርፍና እንዲያብብ ትግሎች በተበራከቱበት ዘመን፤ እነዚህን ትግሎች የምንቀላቀለው በቅኝ ግዛት የተነጠቁ ማህበረሰቦች አለምን እና ህይወትን ለመሥራት (World Making) የሚያስችላቸውን የታመቀ ኃይል እና ችሎታ በመመርመር ለሌሎች የግብዣ እጆችንን እየዘረጋለን ነው።

ከንጥቂያ ባሻገር የገቢር መፅሀፍ አካባቢ-ተኮር የሆነ የስነ ጥበብ ጥናት ውጤት ነው። እኛም በተለያዩ የነጠቃ ፖለቲካ ያጐሳቆላቸው የአለም ክፍሎች የምንገኝ የስነ-ጥበብ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች ነን። ይህ ፕሮጀክት የጋራ በሆነው ጉዟችን እና ተመክሯችን አማካኝነት የተፈጠረውን ሙያዊ ትስስር በመጠቀም እና የምንጋራውን ዕውነታ  በማጤን፤ የሚያገናኘንን የህይወት ውል ለማጠናከር በሚጥር መልኩ የተቃኘ የስነ-ጥበብ ጥናት ውጤት ነው። እራሳችንን “እኛ” ብለን ስንጠራ በደቡባዊ የአለም ንፍቀ ክበብ የሚደረጉ ትግሎች አካልነታችንን ለማበከር እንጂ በመካከላችን ያሉ ብዝሀ-ማንነቶችን ለመካድ ብሎም የአጋርነት ፖለቲካችን ያሉበትን ተግዳሮቶች ባለመረዳት አይደለም። በዚህ ስብስብ ውስጥ የምንገኝ የስነ-ጥበብ ሰዎች እና ተመራማሪዎች ብዙ ልዩነቶች ካሏቸው ከሲኖፕ /ቱርክ/፤ ኦክሳካና ዛካቴካስ /ሚክሲኮ/ ፣ አዲስ አበባ /ኢትዮጵያ/ ዲያልባኪር / ኩርዲስታን/፣ አሌንቴዦ /ፖርቱጋል/፣ በርሊን /ጀርመን/ የመጣን ነን። ተገናኝተን ይህንን ስብስብ የፈጠርነውም በአንዲት ነጭ ኦስትሪያዊ ኘሮፌሰር ተጋብዘን በቪየና የስነ ጥበብ አካዳሚ (Acadamy of Fine Arts Vienna) ሲሆን ስብስባችን እንዲቋቋም የገንዘብ እርዳታ ያደረገውም ተቋዋም የኦስትሪያ ሳይንስ ፈንድ (FWF) ነው።  የገንዘብ ድጋፉም የተደረገው ንጥቂያ፡ ድህረ-ተሳትፎ የስነ-ጥበብ ገቢር እና የመሬት የአስተምህሮ ዘይቤ (DisPossession Post-Participatory Aesthetics and the Pedagagy of Land (2018-2020) በማለት በሰየምነው የሁለት ዓመት ኘሮጀክት ነው (2018-2020)።

ስለ ንጥቂያ (Dispossession) በመጀመሪያ እንድናጠይቅ የረዳን “ንጥቂያ፤ ክዋኔ በፖለቲካ ውስጥ” (Dispossession: The performative in the political) የተባለው መጽሀፍ ነው። በዚህ ስራቸው ጁዲት በትለር እና አቴና አታናሲዩ ንጥቂያ ጥንድ ትርጉምን እና እንድምታን ይይዛል ሲሉ ይከራከራሉ። አንደኛ ንጥቂያ እንደ መሬት፣ ሰዎች፣ ፍላጐቶች፣ መብቶች፣ እና ማህበረሰባዊ ግንኙነቶች በኀይል የሚገፈፉበትን ሁኔታ ሲያመለክት፤ በሌላ በኩል ደግሞ፤ ንጥቂያ የሰዎች ግንኙነት እና መስተጋብር የሚመሰረትበትን የኀይል አውድ እንዲሁም በዚህ የኀይል ግንኙነት አመካኝነት የሚገነባው የጭቆና ስርዓት ሁሌ የሚጠየቅና የሚሄስ የማንነት ግንባታ ሂደት እንደሆነ የሚያመለክት ንድፈ ሃሳብ ነው ብለው ይሞግታሉ[1]።

በስብሰባችን ውስጥ ውይይታችንን የጀመርነው ከመጣንባቸው አካባቢዋች ያገኘናቸውን የተለያዩ ተመክሮዎችን በመለዋወጥ ነው። የዋናነት ከተወያየንባቸው ጉዳዬች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡- መንግስት መር የሆነ የማፈናቀል ፖለቲካ፣ የኒዎ-ሊቡራል የመሬት ነጠቃ፣ በከተማ እድገት ውስጥ ያለው የድሆች መፈናቀል (gentrification)፥ ደህንነትን ምክንያት ያደረገ የመንግስት ቁጥጥር ስርአት (Securitarian governmentality) ፣ እንዴት የሰዎች እና ሰው ያልሆኑ አካላት በአዲስ አይነት የባርነት እና የቅኝ ግዛት አሰራሮች ግዘፍ እንደሚሰጣቸው እና ግዘፍ እንደሚነሱ (becoming materialized and dematerialized) እና ስርዓታዊ በሆነ መልኩ አለማችን የወረሰችው የሀይል ግንኙነት እንዴት የሰዎችን ግንኙነቶች እንደሚያደራጅ ተወያይተናል። በውይይታችንም እነዚህን ሁኔታዎች እንደ አይነተኛ የመነጠቅ  ገጽታዎች ነቅሰን በማውጣት በተለያዩ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ አጋርነቶችን ለመመርመርና በመፈለግ ተሰማርተናል።

በመቀጠልም ገዢ የሆኑ አውሮፖ-ተኮር እሳቤዎች እና የእውቀት ዘዴዎች ተፅዕኖ ውስጥ ብንሆንም፤ ከነሱ ባሻገር ለማሰብ ያስችለን ዘንድ ከደቡብ ንፍቀ ክበብ በወጡ የእውቀት አደረጃጀት ዘዴዎችና እሳቤዎች፤ እንዲሁም አገር በቀል እውቀቶችና ልምዶች ላይ መመስረትን እና በነሱም መታገዝን የትግላችን ዋና መሳሪያ አደረግን ። ይህንንም ለማሳካት በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ነባራዊ ሁኔታዎችን በመመርመር ለምንኖርበት አውድ የሚስማሙ ንድፈ ሀሳቦችና የእውቀት ደርዞችን እንዲሁም የማሰቢያ እና የስሜታችን ማሰሪያ ማዕቀፍ ለማድረግ ጣርን። ለዚህ ጥረታችን የቦቬንቱራ ዲ ሶሳ ሳንቶስን Epistemologies of the South: Justice against Epistemicide የተባለው መፅሃፍ የግንዛቤ

1 Judith Butler & Athena Athanasiou, *Dispossession: The Performative in the Political* (Cambridge: Polity, 2013).

አድማሳችንን አንድናሰፋና ብዝሀ-አቀፍ ሁለንተናን እንድንተልም በእጅጉ ረድቶናል። ይህም ስራ በአብሮነት መንፈስ የተቃኙ የተለያዩ የእውቀት ደርጆችን፥ የመኖር ፍልስፍናዎችን እና ፖለቲካዊ ማንነቶችን በጥልቀት እንድንመረምር አግዞናል[2]።

በእጅጉ የተዛባ የኀይል ግንኙነት በሰፈነበት፥ የመንግስት የሀይል እርምጃና አዲስ አይነት የእጅ አዙር ፋሽስታዊ ፖለቲካ በተንሠራፋበት እና ድንበር ዘለል ነጠቃ በሚበረታታበት ዓለም፤ የትኞቹን ታሪኮች መስማትና



ማዳመጥ ያሻናል? በመጥፋት አፋፍ ላይ ያሉ የህይወት ተሞክሮዎችን እና ታሪኮችን እንዴት መልሰን በኑሮአችን ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ ማዋል እንችላለን? የተጨቆኑ ታሪኮችንና እውነታዎችን ፈልፍሎ አውጥቶ በመተረክ፤ በፍርሀት፣ በሰቆቃ እና በተስፋ መቁረጥ ብቻ ያልተቃኙ ወደፊቶችን እንድናልም የሚያስችሉ ህይወትና አለምን የመስራት መንገዶችን እና ዘዴዎችን ማመቻቸት እንዴት ይቻለናል? እንዴትስ አዲስ አይነት በጐ ግንኙነቶች ለመፍጠር እንችላለን? ብሎም ቁጭት፣ እንቢተኝነት እና በጐ ምኞት የወለደው አዲስ ትልም እንዲፈጠር እንዴት አስተዋፆ ማድረግ እንችላለን? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎችን እንድንጠይቅ ረድቶናል።

የአብሮነት ጉዞአችንን የጀመርነው በአንዷ አጋራችን ሲልቪያ ዳስ ፋዳስ መሪነት በተዘጋጀ የአጭር ጊዜ ጉዞ ወደ አሊቴንዣ /ፖርቱጋል/ በመሄድ ነበር። በመጀመሪያ ሲልቪያ ዳስ ፋዳስ በአንድ የአናርኪስት ዞባ ቡድን (commune) ላይ ያደረገችውን ጥናት እና አድናቆቷን በቦታው ላይ በተገኘንበት አጋራችን። በዚሁ ጉዟችንም አገልግሎት መስጠት ያቆመ አንድ የድሮ የማዕድን አውጪዎች ከተማንም ጎበኘን። በአንድ ጥቁር ሀይቅ ዳርቻ እንዲሁም፤ በማይነጥፍ ስግብግብነት ምክንያት ህይወት በጠፋበት ባዶ፣ ህይወት አልባ፣ ጉድጓድ አፋፍ ላይ ሆነን በፀጥታና በአርምሞ ቆዘምን። በዚያው ምሽት በአቅራቢያ በሚገኝ ትንሽ ከተማ ውስጥ በማዕድን አውጭዎች የተከናወነ ባህላዊ ዘፈንና ዳንስ ተመለከትን። ይህ ሽማግሌና ወጣት ማዕድን አውጭዎች ክንድ ለክንድ ተያይዘው የሚወዛወዙበት ትርኢት በአካባቢው ላይ የተደረገው ዝርፊያ ህይወትን እንዳላስቀረና እንቅስቃሴን እንዳላቆመ አስተማረን። በአጠቃላይ በቆይታችን ውስጥ ጥሩ የስራ፥ የመማማር እና የመዝናናት ጊዜን አሳለፍን።

ቪየና ከተመለስን በኋላ "የቢሆን" ፍለጋችን የእግር ጉዞዎችን እስከታለ። በእግራችን ተጓዝን፣ ተወያየን፣ ትንፋሻችንን ሰበሰብን ፍለጋችንን እና ጉዟችንን ቀጠልን። ንባቦቻችን የእግር ጉዟችንን እንድንቀጥል አነቃቁን። አብረን ከቅርብና ከሩቅ አጋሮቻችን ጋር ተጓዝን። የብዙሃን መጓጓዣዎችን በቀላሉ ለማግኘት ብንችልም በቪየና ደኖች እና በዳኒውብ ወንዝ ዳርቻ ላይ በአግራችን ተጓዝን። ሌሎች ሰዎችንም አብረውን እንዲጓዙ ጋበዝን። በእግር ጉዟችን የአካባቢውን ድምፅ በጥልቀት አዳመጥን፣ እንጉዳዮችን ለቀምን፣ ሽርሽር ሄድን፣ አብረን አነበብን፣ በተለያዩ አካባቢዎች ያሳለፍናቸውን ማለፊያ የህይወት ተሞክሯችንን ተጋራን።

እንድ ጓዳችን 'ስንቅ' በመባል የሚታወቅ በጉዞ ወቅት ስለሚያዝ ምግብ እና ይህም ምግብ ሰዎች በጉዞአቸው ውስጥ ከሚያገኙዋቸው ባይታዋሮች ጋር የሚቋደሱት ምግብ መሆኑን አጫወቱን፤ ይህንን በማሰብም የሚበላ ነገር እንዲዘጋጅ አመቻቹልን፤ በላንም። የእግር ጉዟችንን ባደረግንበት ቀንም እኒሁ አጋራችን በቪዛ ምክንያት ከኦውስትሪያ ወደ አገራቸው መመለሳቸው የግድ ሆነ። በቀጣዩ ቀን ባደረግነው የእግር ጉዞም ጓዳችን ስለ "ስንቅ" ባህል እና በጉዟችን ውስጥ አዳዲስ ግንኙነቶችን ስለመፈለግ ጥቅምና ዋጋ የፃፉልንን ደብዳቤ አነበብን፤ በቀኑም ከጐናችን አለመሆናቸው በአለም ላይ ስላለው እኩል ያልሆነ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት እንድናስተውል አስገደደን። ለአንዳንዶቻችን ከአደጋ ነፃ የሆነ እንደልብ የመንቀሳቀስ እድል በዋዛ የሚገኝ አለመሆኑንም አስታወሰን። በየጊዜው የአካዳሚውን ቢሮ ለቀን የምናደርገው ተመሳሳይ የእግር ጉዞ አይምሯችንን እና አካላችንን ቃኝቶ በተለየ መልኩ እንድናስብ/

↑ Mushroom Picking, Vienna, 2019; photo by the Willful Weeds Research Group

2 Boaventura de Sousa Santos, *Epistemologies of the South: Justice against Epistemicide* (Boulder: Paradigm Publishers, 2014).



እንዲሰማን ረድቶናል።

በማይጋብዘው የቪየና የስነ-ጥበብ አካዳሚ ቢሮ ቁጥር #A4239A ውስጥ በመደበኛነት በመገናኘት ስለ ኘሮጀክቶቻችን ሂደትና እድገት አንወያይ ነበር። ብዙ ጊዜያችንን እናጠፋ የነረው በጠረጴዛ ዙሪያ በመሰብሰብ፣ ላኘቶፖቻችን ላይ በመስራት፣ ማስታወሻዎችን በመለጠፍ፣ ፅሁፎችን ጮክ ብለን በማንበብ፣ ባለሙያዎችን በመጋበዝና በመወያየት፣ ስለ ስራዎቻችን በመነጋገር፣ በጣም ብዙ ማስታወሻዎችን በመውሰድ ነበር። ቀስ በቀስ የጋራ ንድፈ-ሀሳቦችን ሰብስበን፡- የገደል መስመር (abyssa line) ብዝሃ አቀፍ ሁለንተና (pluriverse) ፣ ማሰብ/መስማት (thinking/feeling) ፣ ማለፊያ ህይወት (good living / buen vivr) ፣ ፍርስራሾች (ruins)፣ ጭራቆች (monsters)፣ መናፍስት (ghosts)፣ . . . ይህንንም የንድፈ ሀሳብ ስብስብ የኛ "ምሕዋር" (firmament) ብለን ሰየምነው። ይህ የፅንሰ ሃሳብ ስብስብ ከተለያዩ ንባቦች የተገኘ ሲሆን ለጋራና ለነፍስ-ወከፍ ስራዎቻችን አቅጣጫን ሰጥቶናል። የጥናት መስኮቻችን እና የመጣንባቸውን አከባቢዎች ባስተናገዷቸው ንጥቂያዎች አይነትና መጠን እንዲሁም ባካሄዱዋቸው የተቃውሞ ዘዴዎች ልዩነቶች ያሏቸው ቢሆኑም በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ተሞክሮዎች መካከል ልንገነባው ያለምነው ገና ያልጠና ያልጠነከረ ድልድይ የግንኙነቶቻችንን ድር ሲሰራ ማየት ጀምረናል። የታይግረስ ወንዝን እያዩ ታጉስ ወንዝ ላይ ምን እየሆነ እንዳለ አለማሰብ አይቻልም። የተደቆሱ የደቀቁ የዛካቴካስ ተራራዎችን እያዩ፤ የአዲስ አበባን ግዙፍ የህንፃና መሰረተ ልማት ግንባታዎች እና ያስከተሉትን የማህበራዊ ህይወት ውድመት አለማሰብ አይቻልም፣ እነዚህ ኩነቶች በቁስ፣ በጊዜና በቦታ መካከል ያለውን ጥልቅ ቁርኝት እንድንማር፣ በዝርዝር እንድንገነዘብ አድርገውናል። በሩቤን ጋዝታምቢዴ-ፈርናንዴዝ፣ አንጌላ ሜሊቶፖሎስ፣ ማርጋሪታ ፖላሲዩስ እና ኢቭ ተክ ወርክሾፖች ውስጥ በተፈጠሩ የትኩረት ዕይታዎች ልዩ፥ የማይመሳሰሉና የማይገናኙ በሚመስሉ ኩነቶች መካከል ጥልቅ ቁርኝት እና ትስስር እንዳለ እንድንገነዘብ ረድተውናል።

በቪየና እየሰራንበት ባለንበት ጊዜ እንኳን ሁላችንም የኘሮጀክቱ ልብ ወይንም ልቦች ሌላ ቦታ እንዳሉ እንገነዘብ ነበር ። ኘሮጀክቱ ወደተለያዩ አካባቢዎች እንድንጓዝ አድርጐናል። ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ተሸጋግረናል፤ የልባችን ምኞት ቤታችን ወደ ሆነው አካባቢያችን ሄደናል፤ እንደገናም ወደ ቪየና ተመልሰናል። ምንም እንኳን በቪየና ለመቆየት ሁላችንም ቪዛችን የሚያስችለን ቢሆንም ይህ አውሮፖዊ የእውቀት ማዕከል ደቡባዊ ማንነታችንን፣ የቆዳችንን ቀለም፣ ስደተኛ አካላችንን /ሰውነታችንን/ በደስታ የሚቀበል ቦታ አልነበረም። የገደሉ መስመር (the abyssal line) በቡድናችን መሀል በማለፍ ማህበራዊ ግንኙነታችንን አደራጅቷል፣ ግንኙነቶቻችንን ወስኗል መንገዶቻችንን እና መስተጋብሮቻችን የተለያዩ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። የግሎሪያ አንዛልዳው የማቋረጫ፣ መተላለፊያ (crossing) ንድፈ-ሀሳብ ያደረግናቸውን ብዛት ያላቸውን መመላለሶችና መተላለፎች እንድናጤን ረድቶናል። የመተላለፍ ግንዛቤያችን ከሰሜን ወደ ደቡብ የአለም ክፍል ባደረግናቸው መሸጋገሮች፣ ጉዞዎች፣ በጉዞዎቻችን ባጋጠሙን መልክዐ-ምድሮች እና ተሞክሮዎች እንዲሁም ባገኘናቸው ሰዎች በሰራናቸው እና ዋጋ በምንሰጣቸው ጓደኝነቶች የተቃኘ ነው። አንድ ቦታ ብቻ መቸከልን ከመምረጥ ይልቅ የተለያዩ አለሞችን መኖር ተቃርኖንና እርግጠኛ መሆን አለመቻልን ማጥናት ማጠየቅና እርስ በርስ መሠራራትን መርጠናል[3]።

ለኛ ቪየና በጊዜያዊነት ለተቀመጥን የስነ-ጥበብ ሰዎች "እኛ" ከሚለው መንፈስ ፈቀቅ ብለን "እኛን" እንድንመረምር ያደረጉን ጊዜያት ጥቂት አይደሉም። እነዚህ ያሳደጉን የለወጡን ጊዜያት ከመሆናቸውም ባሻገር ጉዟችንን እንድንቀጥል፣ ግንዛቤያችንን እንደናሳድግ እና እርምጃዎቻችንን እንድናጤን ረድተውናል። ከአንድ ነጥብ ወደ ሌላ ያደረግንናቸው እንቅስቃሴዎች የተለያዩ ቦታዎችን እንድንመረምርና ስራችን ባጋጠሙን ነገሮች እንዲዳብር አድርገዋል። ገጠመኞቻችን የቁጭትና የምኞትን ሀይል አሳይተውናል። ቁጭት ባንድ ጎን እና ምኞት በሌላ ከተለያየ ግብረ ገባዊ (ethical) ስፍራ የሚመነጩ የአለም ግንዛቤዎች ናቸው[4]። ቁጭት ከስሜት (affect) የሚመነጭ ኢፍትሐዊነትን የሚገዳደር የእምቢተኝነት የቁጣ መንፈስና የሰው ልጅን ክብር ለማጐናፀፍ የሚጥር "በሰው ልጅ የመጠቃት ስሜት" ላይ የሚመሰረት ሲሆን፤ ምኞት ደግሞ በኢቭ ተክ ቃላት "በበደልና ተስፋ መቁረጥ ስሜት የሚገፋ ግን ደግሞ ተስፋና ራዕይን የሰንቀ ብሎም የህይወት ተሞክሮ ላይ የተመሠረተ የጥበብ ውልድ ነው። ምኞት ያልተቋጨ ገና ያልተሳካ ብሩህ ህልም ነው[5]።"

ከመብት ተሟጋቾች፣ ከፌምኒስት ቡድኖች፣ ከተለያዩ ንጥቂያን ከሚታገሉ ክፍሎች፣ የራስ-ገዝ አስተዳደርን ለመጐናጸፍ ከሚጥሩ ሀይሎች፣ የህይወት ጥሪያቸውን ከነሱ በላይ ለማሳካት ለሚተጉ፥ የህዝባዊ ስፍራዎችን ለጋራ እንጉርጉሮና ፈውስ እንዲውሉ ለማድረግ የሚታገሉ ቡድኖች ፣ አዲስ አይነት ታሪክን እና ትልምን የሚወጥኑና የተጠቂነት መንፈስን የማይቀበሉ አርቲስቶችና የመብት ተሟጋቾች ጋር አጋርነትን ከመመስርታችን ባሻገር ስራችንን ለነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች መታሰቢያ እንዲሆን አበረክተናል። ስለዚህ ይህ መጽሀፍ እንደዚህ ላሉ ፍቅራቸው

3 Gloria E. Anzaldúa, *Borderlands / La Frontera: The New Mestiza* (San Francisco: Aunt Lute Books, 2012).

4 de Sousa Santos, *Epistemologies of the South*.

5 Eve Tuck, "Suspending Damage: A Letter to Communities," *Harvard Educational Review* 79, no. 3 (Fall 2009): 417.

ላልተመለሰላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የተሰጠ ስጦታ ነው። ጥረታችን ያለፈውን ዘመን በምናብ በመከሰት እና በእንጉርጉሮ ፈውስን ማግኘት፣ የመጪውን ዘመን አማራጮች በመመርመር የተሻለ አለምን መፍጠር፣ የአለምን መርዝ አዲስ ትርክቶችን በማሰራጨት ማርከስ እና መጪውን አለም ለመፍጠር የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን መታጠቅ ነው። የየግላችንን መንገድ ከተጓዝን በኋላ አንድ ላይ ለመምጣትና እንደገና ለመገናኘት እነዚህ መሣሪያዎች ያስፈልጉናል። አንድ ላይ ሆነንም ታሪኮቻችንን ለማሰራጨት በህብር ሙዚቃ ፅኑ አረሞቻችንን ለመትከል እና ለማብቀል እነዚህ መሣሪያዎች ግድ ይሉናል።

የግል የስነ-ጥበብ ምርምር ፕሮጀክቶቻችንን ለመስራት የየግል መንገዶቻችንን ጠርገናል፤ የትግበራ መሣሪያዎቻችንንም (Tools) አንፀናል፤ ። እነዚህ መሣሪያዎቻችንን የተለያዩ የስነ-ጥበብ ሰዎች፣ የመብት ተሟጋቾች እና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በየወርክሾፖቻችን ሞክረናቸዋል። በመቀጠልም፤ ተሞክሮዎቻችንን በመጠቀም መሣሪያዎቹን ለሚጠቀሙባቸው ክፍሎች የተሻለ ትርጉም በሚሰጣቸው ሁኔታ ከልሰናቸዋል። በመሆኑም፤ ለአዲስ ህይወትና አለም ቅመራ ውለው ንጥቂያን ለሚገዳደሩ የተለያዩ ትግሎች እንዲመቹ ሆነው ተደራጅተዋል። በሂደቱ ውስጥም፤ የተለያዩ የተለመዱ አስተሳሰቦችን እና መስተጋብሮችን ለመስበር የሚያግዙ መመሪያዎች እና የመማሪያ ዘዴዎችን በመፈለግ እና በመመርመር ሂደት ውስጥ የዳበሩ የአስተምህሮ ዘዴዎችን፣ ጨዋታዎችን እና የገቢር መፃህፍትን አግኝተናል፤ አጥንተናል።



ይህ መጽሀፍ በተለያዩ የተወሰኑ የአለም አካባቢዎች ላይ የተደረጉ የስነ-ጥበብ ጥናቶችን አካትቶ ሰንዷል። የእያንዳንዱ ፕሮጀክት መግቢያ ሥፍራ ተኮር የሆኑ የመስክ ጥናት ውጤት ሃተታዎችን የያዘ ነው። መግቢያውንም ተከትሎ የጥናቱ ውጤት የሆኑ የተግባር መሳሪያዎች (tools) እና የነሱን የገቢር ዝርዝር ይዘወል። እነዚህም የጥናት ውጤቶች በአጋጣሙን፣ በተመለከትናቸው የመኖርና የመቀጠል ጥረቶች፣ ተቃውሞዎች፣ የጽናት ተምሳሌቶች እና እንቅስቃሴዎች ፣ የሰው ልጅ ክብር ማሳያዎኛ፥ የሰው ልጅ ደስታ ተምሳሌቶች የተቃኙ እና የተነቃቁ ስራዎች ናቸው። እነዚህም የፈጠራ ችሎታ ማሳያዎችና የሰው ልጆች ከተለያዩ ህይወቶች (species) ፣ የጊዜ ቀመሮች (temporalities)፣ የህልውና ዘዴዎች፣ አስተሳሰቦች፣ ስሜቶች ጋር ላላቸው ግንኙነቶች ምሳሌ ናቸው። ከእኛ ለእነሱ እና ለእናንተ የተሰጡ አበርክቶዎች ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ገቢር ተሳታፊዎች እጅ መሳሪያዎቹ እና ተግባራቱ በንፉስ መሪነትና በእናንተ አነቃቂነት እንደወላንሳ እንደሚበሩ ተስፋ እናደርጋለን።

ከንጥቂያ ባሻገር የገቢር መጽሐፍ የሰባት አካባቢ ተኮር ጥናቶች ግንዛቤን ይሰጣል። ተስፋችን ከተለያዩ ድንበር ዘለል ምኞቶች እና የትግል ስልቶች ጋር መጽሐፉ ንበት ይኖረዋል የሚል ነው። “ወፍራም ደም” (Heavy Blood) ባለችው የናኦሚ ሪንኮን ጋላርዶ ፕሮጀክት አርቲስቷ በቬታግራንዴ ዛካቴካስ /ሜክሲኮ/ ከሚገኙ መናፍስቶች ጋር በመሆን የአካባቢውን ብክለት ለመበቀል እንዴት እንደሚቻል ልታሳየን ትሞክራለች። “ብርሃን፣ ነበልባል፣ ጉጉል” (Luz, Blaze, Fulgor) በተባለው ስራዋ ሲልቪያ ዳስ ፋዳስ ደግሞ የአንድ ረጅም የአናርኪስቶች ዞባ ቡድን ታሪክን በማጥናት በአሌንቴዦ /ፖርቹጋል/ ያለው የራስ-ገዝ ህይወት ጋር ያለውን አስተጋብትኦ ታጠናለች። ሮዥታ ቱግሩል ደግሞ “በወንዙ ዳርቻ” (Around a River) በተባለው ፕሮጀክቷ የታይግረስና የዩፍራተስ ወንዞችን ሁኔታ እና በአንድ በመጥፋት ላይ ባለች በላይኛው የሜሶፖታሚያ ክፍል ባለ ግድብ ውስጥ በምትኖር የኤሊ ዝርያ ላይ በማተኮር ይከተላል። ኢፔክ ሃምዛኦሉ ደግሞ “ዴስፒና” (Despina) በተባለው ፕሮጀክቷ ሰዎችና መናፍስትን በማጣመር የቱርክ ከተማ በሆነችው ሲኖፕ ውስጥ የሚገነባው የኑክሌር ሀይል ማመንጫ እንዴት የከተማይቱን እጣ ፈንታ እንደሚወስን ታውጠነጥናለች። ብርሃኑ አሻግሬ ደግሞ “መቆርቆር እና መሆን” (Care and Become) በተባለው ፕሮጀክቱ የሃዘን ልምዶችና ባህሎች እንዴት ወደ ስነ-ውበት፣ የአስተምህሮ እና የፖለቲካ ዘዴዎች ሊቀየሩ እንደሚችሉ እና በአዲስ

↗ Walking together to a deserted open-pit mine in Mina de São Domingos, Corte do Pinto, Alentejo/Portugal, 2018; photo by the Willful Weeds Research Group



አበባ ከተማ /ኢትዮጵያ/ ታሪክ ዙሪያ ላሉ ማህበራዊ ቀውሶችና አለመግባባቶችን ለማከም ስለሚያስፈልጉ የጋራ ፈውስ ሂደቶችን ለመፍጠር የሚያስችሉ መንገዶችን ይመረምራል። ናኦሚ ሪንኮን ጋላርዶ በሌላኛው “ጽኑ ኦፖስም” (Opossum Resilience) በተባለው ፕሮጀክቷ በኦክሳካ /ሜክሲኮ/ የሚደረገው ፀረ-ንጥቂያ ትግል የተዳቀለ የሜሶ-አሜሪካን አፈ-ታሪክ ለመተለም እንደሚረዳ ታሰላስላለች። ጃኒን ጀምበሬ ደግሞ “የወረቀት አውድማ” (Paperlands) በተባለ ፕሮጀክቷ የጀርመን የቅኝ ግዛት ዶሴን (archive) በመመርመር በአፍሪካውያን በ1880 እና በ1914 መካከል የተፃፉ ደብዳቤዎችን በማጥናትና በእነዚህ ደብዳቤዎች የተገለጹ ተቃውሞዎችን በመሰነድ በነዚህ አፍሪካውያን እና በኋላ በሚመጡ የፀረ-ቅኝ ግዛት ትግሎች መካከል ያለውን ቀጣይነት ታሳያለች። በመጨረሻም “የፅኑ አረሞች ሁከት” ብለው የጥናቱ ስብስብ አባላት አንድ ላይ ባዘጋጁት ፅሁፍ በአውሮፖ የሚገኝ የቅኝ ግዛት ታሪክ ያለው ተቋም ስለ ነጠቃ፣ ምኞትና ቁጭት ለማጥናት የመቻሉን ቅቡልነት ያጠይቃሉ።

ምንም እንኳን መጽሀፉን በእንግሊዝኛ ብንጽፈውም የጥናት ወርክሾፖቹ እና በውስጣቸው የተደረጉ ገቢሮችና መሣሪያዎች የተዘጋጁት በተለያዩ ቋንቋዎችና ማህበራዊ ዕሴቶች ነው። እንግሊዝኛ የማናችንም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ባይሆንም ኢምፔሪያል ታሪክ ስላለው አልያም በሌላ ምክንያት ሁላችንም በጋራ የምንግባበበት ቋንቋ ነው። ይህን ፕሮጀክት ወደ መጽሀፍ ለመቀየር ስናስብ በእንግሊዝኛ ማሳተሙ “የመመለስ” መሻታችንን የማያንፀባርቅ እና ምኞታችንን የማያደርስ ሆኖ አገኘነው። በመሆኑም መጽሐፉ በተለያዩ ብዙ ቋንቋዎች እንዲታተም ተስፋችን ቢሆንም እስከዚያው ድረስ ግን ወደ አማርኛ ፣ ኩርዲሽ፣ ፖርቹጋልኛ፣ ቱርክኛ እና ስፖኒሽ እንዲተረጐም አደረግን።

ከንጥቂያ ባሻገር የገቢር መጽሀፍ ለአሳታፊ የስነ-ጥበብ ፕሮጀክት መመሪያ አይደለም። ተሳትፎን መጠየቅ ማለት የልምምዱን አውድ እኛ ወስነን የታሪኩን ኩነት አና ሂደት እኛ በቀመርነው መልኩ እንዲፈስ አድርገነዋል ማለት ይሆናል። የኛ አላማ እና ተስፋ ከዚህ በተለየ ያዘጋጀናቸው መሳሪያዎች እና ገቢሮች እንዲያነሳሱና




እንዲያነቃቁ ነው። ማነሳሳት (initiation) ከዳንስ /ውዝዋዜ/ እና የክውን ጥበባት የተዋስነው ጽንሰ ሃሳብ ነው[6]። ማነሳሳት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ መምራትንና መከተልን ያገናኛል። ተስፋችን ከንጥቂያ ባሻገር የገቢር መጽሐፍ ገቢሩን ሲመራ እና ሲከፍት እንዲሁም በክፍተቶች መካከል በሚገባበት ጊዜ እንኩዋ የተሳታፊዎችን ፍላጎትና ምላሽ እንዲከተል ነው። የዚህ መጽሀፍ አላማ የምድር፣ የውሃ፣ የአየር፣ የእህል እና በሰዎች ህይወትና በተፈጥሮ መከከል ያሉ የተቀደሱ ትስስሮችን የሚያጎለብት የህይወትና የአለምን ስራ እንደ ኦድሪ ሎርድ አባባል “እንደ አመጽ መቀሰቅስ” ነው። ይህ ስራ ሄትሮ-ፖትሪያርካል፣ ዘር-ተኮር እና ካፒታሊስታዊ አመክንዬ ላይ የተመሰረቱ አለምን እንደ ንብረትነት የሚመለከቱ ገዢ አስተሳሰቦችን የሚቃወሙ ትግሎችን ይጋብዛል ከነርሱም ጋር የአጋርነት ጥያቄን ያውጃል።

በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ መሳሪያዎች እና ገቢሮች በተለያዩ ቦታዎች ሞክረናቸዋል። እናንተም የኛን ከመሬት ጋር እና በመሬት ዙሪያ ያሉ ብዝሃ ትስስሮችን የማስታወስ፣ በአዲስ መልክ የማሰብ፣ የማጠየቅ እንዲሁም እንደገና የመተረክ ጥረት እንድትቀላቀሉን ለመጋበዝ፣ ለማነቃቃት እና ለመነሸጥ ይህን መጽሐፍ አዘጋጅተናል። አሁን ተስፋችን የተወደዳችሁ አንባቢዎቻችን የመጽሐፉን ጉዞ ወዳልተጠበቁ ስፍራዎች እንድትወስዱት ነው። እንድታሳድጉት!

*SPROUT!*

↖ Signs at the deserted open-pit mine in Mina de São Domingos, Corte do Pinto, Alentejo/Portugal, 2018; photo by the Willful Weeds Research Group

6 Lepecki, André. “From Partaking to Initiating: Leading Following as Dance’s (A-personal) Political Singularity.” In *Dance, Politics and Co-immunity.* Edited by Stefan Hölscher & Gerald Siegmund. Berlin and Zurich: Diaphanes, 2013. 21–38.

በደረቅ ቢሮዎች ውስጥ፤
ዝምታ ስለ ውጥረት ያወጋል፤
ከዚያም ድምፆች በዝማሬ ሲገናኙ፤
ጫጫታው እሳት ሆኖ ይነግሳል።



# የጽኑ አረሞች ፍጭት



## በጽኑ አረሞች የጥናት ቡድን

ቪዬና/አስትሪያ

ብዙዎቻችን ያሁን ጊዜ ችግርን የመጪውን ጊዜ ጥሩ ተስፋ በምናባችን በመሳል ልንወጣው፣ ልናልፈው እንሞክራለን። የወደፊቱን ጨለማ ሊጋርዱ የሚችሉ ያሁን ክስተቶችን ለማቆም እንሞክራለን። መጪውን ጊዜ የተሸለ ለማድረግ እንዲሁም ለመጪው ትውልድ ስንል የአሁኑንና ያለፈውንም ጊዜ ለማጽዳት እንሞክራለን። ከችግር ጋር መቆየት እንዲህ አይነት ግንኙነት ከመጪው ጊዜ ጋር መመስረትን አይጠይቅም። እንዲያውም ዛሬን ከልብ መሆን የአሁንን ችግር ለመፍታት ይጠቅማል። አሁንን ከልብ ሆኖ መኖር ማለት በፍፁም ገነት እና ፍፁም ሲኦል መካከል ሆኖ ያለፈ ጊዜን ወይም የአለም ፍፃሜን እና ድህነትን አምጪ በሆነ ነገ መካከል ያለ ከንቱ አላፊ ጠፊ ህይወት ሳይሆን እንደ ሟች ፍጡር ያላለቁ ቦታዎች፣ ጊዜዎች፣ ጉዳዮች እና ትርጉሞች አካል ሆኖ መኖር ማለት ነው።

— Donna J. Haraway, *Staying with the Trouble*

“ትግሉን የምታካሂዱበት ዘይቤ፣ ትግሉ ሲያልቅ የሚኖራችሁን ማንነት ይወስናል።”

— Taiaiake Alfred, *Wasáse*





ወደ እዚህ ወደ ቪዬና ያመጣንን ያልተገመተ የግብዣና የምክረ ሀሳብ ጽሁፍ ቀስት እናስታውስ። እስቲ አብረን እናንብብ፣ የአገር በቀል የመሬት አስተምህሮ መንገዶችም አብርሆት ይስጡን፣ እነኝህ አብርሆቶችን እንዴት ከየራሳችን ልዩ ልዩ ሁኔታዎችና አውዶች ጋር ልናስማማ እንደምንችል እናስብ፣ አብረን እንጻፍ፣ እንዝፈን፣ ችግሮቻችን ቸል እንበል፣ ሌሎች ቦታዎችን በምናባችን እንከስት፣እናጥና፣ እንመርምርም።

ቪየና ሳለን የስራ ክፍላችንን ለቀን የምንወጣባቸው ጊዜያት አስታወሳችሁ? የአና ሲንግን ጽሁፍ ጮክ ብለን እያነበብን፣ እንጉዳይ ለመልቀም ወደ ጫካ የሄድነውን፣ የዳኒዬብን ወንዝ ዳርቻ ማእበል እየናጠው በማያስተማምን ሁኔታ የኦጋዋ ፕሮ ኮሌክቲቭን ሳንቲዙካ ፔዛንትስ ኦፍ ዘ ሰከንድ ፎርትረስን (Sanrizuka - Peasants of the Second Fortress by the Ogawa Pro Collective) ስናይ፣ በድፍረት ይሁን በደካማነት በወረቀት ጭንብል ተከልለን ሙዚየም ውስጥ ለመዝፈን ስንሞክር አስታወሳችሁ?

↑ The Willful Weeds Research Group in Portugal, 2018; photo by the Willful Weeds Research Group

በወርሐ መስከረም በአሌንቴገ ፖርቹጋል ደረቅ ምድር የኢትዮጲያን አዲስ አመት ያከበርነውን ታስታውሳላችሁ? በጋራ ማብሰላችንን፣ መደነሳችንን፣ የእግር ጉዞ ማድረጋችንን አስታውሳችሁ? ምንም ውሃ ጉድጓድ ውስጥ ባለመኖሩ የከተማዋን ነዋሪዎች ጭንቀት ታስታውሳላችሁ? ካርታዎችን፣ አስቸጋሪ ንድፎችን እና የማይቻሉ መርሃ ግብሮችን ስንጋፈጥስ ታስታውሳላችሁ?

በአሮጌው የማእድን ቁፋሮ ስፍራ ያደረግነውን የእግር ጉዞ አስታወሳላችሁ? የአካባቢውን የሚያሰክር የኬሚካል ቅሪት መርዛማነት ከመንደሩ ነዋሪዋች ደግነትና ወዳጅነት ጋር ሲነጻጸር የሚሰጠውን ስሜትስ? ግማሽ ውሃ በያዘው ግድብ ዳርቻ ያሳለፍነውን ጊዜስ? በቁፋሮ የተሞላ ቦታ ላይ ላፍታ በራሳችን አለም የጠፉንበትንስ ጊዜ? ውሃ ውስጥ ድንጋይ መወርወር፣ ያለአላማ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ፣ አንድላይ ሆነን ምን እየሰራን እንደነበርስ? ይህንን ሁሉ ውጣ ውረድ ማሳለፋችንን አዲስ ዓለም የመስራት ሂደት ነበር ያልነው።

እነዚያ ቀጣይነት የነበራቸው ማቋረጦች ለኛ ምን ማለት ነበሩ? የለውጥ ንድፈ ሃሳባችንን ጠብቀን መቀጠል ችለናል? ወይስ ህይወታችንን ለመለወጥ አዳዲስ ንድፈ ሀሳቦችን አግኝተናል? ስጦታን ለማበርከትስ ተችሎናል? በእረፍት እጦት በመደነቅ ብሎም በእያንዳንዳችን ማንነት፣ በሌሎች ህይወት እና ተግባር ተነጥቀናል።

ስንት ግዜ እንደ ቡድን ተለያይተናል? እንደገናስ እንዴት ለመመለስ ቻልን? ስላልተነገረው ምን አደረግን (ወይስ ምን አላደረግንም)? ስለማይፈለገው የሃይል ተዋረድስ? ስላልተሳኩ ተስፋዎችስ? ችግሮች ቢኖሩም ለመጋራትና ለመተሳሰብ መርጠን ነበር? ይህን ስናደርግስ አብረን በገነባነው ትርጉም ትልቅ ደስታን አገኘን? ግትር በሆነው አንድ ላይ የመሆን ምኞት፤ ከብቻ ይልቅ አንድ ላይ የመስራት ፍላጎትና በተቋም ውስጥ ሆኖ ይህን ማድረግ የሚፈጥረው የሀሰተኛነት ስሜት ተቃርኖስ? ልዩነት እንዳለ አለመርሳት፤ የልዩነት ውጤት ሳይሆን በልዩነት ውስጥ መኖር መፈለግ ቢሆንስ። ልክ እንደ አረም።

“እዛ” እኔ እየተወጠርኩበት የነበረውን ነገር “እዚህ” ለማምጣት የሚቻለው እንዴት ነው? “እዛ” የኔ ጉዳይ የነበረን ነገር እንዴት “እዚህ” የሁላችን ጉዳይ ማድረግ እንችላለን? በባህሩ ላይ ያለውን ጭጋግ በመግለጥ ነው የምጀምረው ወይስ ባህሩ ላይ ያንዣበበውን አደጋ አና እውነታ በመግለጽ? በባህሩ ላይ የመዋኘትን አስደሳችነት ነው ወይስ የባህሩ ሙቀት ወይም ቅዝቃዜ እንዴት እንደሚያውክ ነው የማወራው? እንዴትስ ነው “የእዛን” ማህበራዊነት ፣ አብሮነት፣ መሬት፣ ስነምህዳር ወደ የእዛዎች “እኛ” የቪየና ህብረት ማምጣት የምንችለው? የእነዚህ እነዛዎችስ ጉዳዮች ለሁላችን ግድ እንዲሉ እንዴት ማድረግ ይቻለናል? ይህን ለማሳካትስ ምን አይነት ቋንቋ ነው የምንጠቀመው? ስለ ንጥቂያ እንዴትስ ነው የምናወራው? ዶና ሀራዌይ እንዳስጠነቀቀችን “ስለአንድ ነገር ለማሰብ ምን አይነት ነገርን እንደምንጠቀም ማወቅ ወሳኝ ነው” (“It matters what matters we use to think other matters with”)[1]። እንዴት ነው አንድ ላይ እዚህ በቪየና ስብስባችን የፈጠርነውን “የእኛነት” ስሜትና መተሳሰብ ወደ እኔ መልሰን “እዛ” ካሉ ማህበረሰቦች ጋር ለማጋራት የምንችለው?

1 Donna J. Haraway, *Staying with the Trouble: Making Kin in the Chthulucene* (Durham and London: Duke University Press, 2016), 12.



## “የት ነን? የት? የት የሚባል ነገርእማ አለ፤ ምክንያቱም እኛ አለን፤ ነበርን-በግትርነት። አንቺ ከሆንሽ፣ አንተ ከሆንክ እና እኔ ካልሆንኩ እኛ እነማን ነን?”

— Etel Adnan, *There*

ይህ ልምምድ እርስ በእርስ የመተሳሰብ አንዱ ለሌላው ስራ የማሰብ ተግባር ነው። ጉዳዩ ከምንላቸው እይታዎችና ስፍራዎች የመማር ሂደት ነው። በአውሮፓ ውስጥ ቪዛ፣ ገንዘብ እንዲሁም ተቀባይነትን ከሚሰጥ የትምህርት ማዕከል ወደእነዛ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ወደሚገኙ ቦታዎችና ሀገሮች እንደ ባህል ሰራተኛ (እንደ አርቲስት/ተመራማሪ) መመለስ። የምንመለሰው አቅምን ሰንቀን ሌሎች ትርክቶች እና አለማትን ለመፍጠር ካለን ምኞት እና ድልድይ ለመሆን ካለን ሃላፊነት የሚመነጭ ስሜት ነው። ወደ እነዛ ሌላ እውነታዎች ሲመለሱ በአውሮፓ የተለመደ ምቾትንና የቅንጦት ህይወትን በቀላሉ ለመርሳት ሊያስቸግር ስለሚችል እንደገና እንዴት መራመድ፣ እንዴት በሰው ፊት ማውራት፣ እንዴት መልበስ፣ መቼ እንደምንወጣ፣ መቼ ቤት መሆን እንዳለብን እንደገና መላመድ ሊያስፈልግ ይችላል።

አንዳንዴ አብሮ መስራት፤ ካለን ነገር በተጨማሪ ሌላ ነገርን የሚፈልግ ውስብስብ ጉዳይ ነው። የተወሳሰበ ከመሆኑ የተነሳም፤ ቀጣይነት ያለው የመማር ሂደት ነው። ታዲያ እንዴት አድርገን ነው አብረን ስንሰራ ጠቃሚ የሆኑ የመተግበርና ምላሽ የመስጠት መንገዶችን የምናዳብረው? የእርስ በርስ ግንኙነቶች ሊያስከትሉ የሚችሉት ውጥረቶችም እብሮ መስራትን ከባድ ሊያደርጉት ይችላሉ። ነገር ግን አንድ ላይ ሆኖ መስራት ደግሞ ሁልጊዜ ጠቃሚ ሃይል የሚነሳሳበትን ሁኔታ ይፈጥራል-ይሄም ሃይል ከተጋመደ የስብስብ መንፈስ ውስጥ የሚፈጠር ነው። ውጥረቶችና አለመግባባቶችም እንደ አብሮነት ሁሉ አስፈላጊ መሆናቸው ይሰማናል። የዚህ የጋራ ትግል አካል መሆን ትልቅ ጥቅም አለው። በዚህ ሂደት ውስጥ ማለፉ እና ሂደቱ ለሚሰጠው ጥቅም ምስክር መሆን ያንፃል፤ ያጎለብታል።

“እኛ” የማያስተማምን በጊዜያዊ አጋርነት ላይ የተመሰረተ በአጋጣሚ አንድ ላይ በሚመጡ ሃይሎች የተቀመረ ያልተረጋጋ ስብስብ ነን። “እኛ” የ”እኛ”ን (አለ)መቻሎችን፣ ዘለቄታዊ ሊሆንም ላይሆንም የሚችል ቅጽበታዊ አብሮነትን፣ እንዲሁም አንዳንዴ የምንወደው በሌላ ጊዜ የማንፈልገው ስብስብ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን። በፕሮጅክታችን መጀመሪያ የአንድ የስራ ባልደረባችንን በቪዛ ችግር ከሃገር መባረር አይተን በሌሎች ላይ ሚደርስ ያየነውን የኢሚግሬሽን መኮንኖች ወከባ፣ እንዲሁም የየእለት የመንገድ ላይ ማፍጠጦችን ካስተዋልን በኋላ ቪዬና ሁላችንንም ሊቀበል የሚችል “የጋራ ቦታ” ይሆናል የሚል ቅዠት እልነበረንም። ለአንዳንዶቻችን “እኛ” ስንጫወት፣ ተያይዘን የእግር ጉዞ ስናደርግ ወይም የኢትዮጲያን ባህላዊ ውዝዋዜ ስንማር ላፍታ ብቅ ብሎ የታየ ነፀብራቅ ወይም ብልጭታ ነው። ላፉታም ቢሆን “እኛ” ከወረቀት የተሰራ ጭምብል (mask) ስናጠልቅ፣ ምንም እንኳ ድምጾቻችን ሰው ፊት ቆሞ የሚዘመርባቸው ባይሆኑም በድፍረት ግን ደግሞ በሀፍረት የህብረት ዝማሬ ሰዎች ፊት ቆመን ስንዘምር፣ የተሰማን ስሜት ነው። በእፍረታችንም ቢሆን ላፍታ ቆይታ በሌሎች መነጠቅን ፈቀድን።



በምንሰራበት ቢሮ ውስጥ ስለ ጥናት ቦታዎቻችን የነበረው ዝርዝር ገለጻ አንዳንዴ በከባድ ዝምታ የታጀበ ነበር። ዝምታው ሁላችንም ስለእያንዳንዳችን የጥናት አውድ ግንዛቤ አልባ መሆናችንን ያሳየንና አብሮነታችን እያንዳንዳችንን ከሌላችን የሚያራርቅ የሚመስል፤ የተለየ አይነት ከሌሎች መኖር የሚመነጭ የመነጥቅ ስሜትን የፈጠረ ሁኔታ ነበር። የቅኝ ግዛታዊ ሽብርና የጉልበት እርምጃ ባደራጀው የእውቀት ማእቀፍ የደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ሕብረተሰቦች በማይጠቅም የእውቀት ማጋበስ እንዲጠመዱና እርስ በርስ ያላቸውን ቁርኝቶች እንዳያጠኑ እና እንዳያስተውሉ ከማድረጉም በላይ በመካከላችው ያሉትን ልዩነቶችና ግንኙነቶች እንዳያስተውሉና ቁርኝታቸው እንዳይጎለብት አድርጓል። እንድንናገር እንጋበዛለን ግን ማነው የሚያደምጠን? እንዴትና ለምን አላማ እንደምንናገር ሁልጊዜ ግልጽ ላይሆን ይችላል። በዚህ ሂደት ውስጥ አላማው መነጠቅ ከነበረ፤ ይኸው ብዝሀነት ባላቸው የእርስ በርስ መተላለፎች ተነጥቀናል። (አንደንድ ጊዜ እነዚህ መተላለፎች የደማን ያህል ይሰሙናል፤ ከብዙ ማቋረጦች በሁዋላ የምንመለስበት ቦታ እንደሌለንና በቋሚነት መመለስ የምንችለው ወደ መናፈቅ አለም ብቻ እንደሆነ ይሰማናል)። የጋራ ስፍራ ላይ ለመድረስ በምናደርገው ጥረት አንዳንዴ ጥልቀት የሌለው የጋራ መቆሚያ ስፍራን እንድንመርጥ ያስገድደናል።

ይህ ጥናት ከኦስትሪያውያን ግብር በተሰበሰበ ገንዘብ የተደገፈ ፕሮጀክት ነው። ለዚህ ፕሮጀክት ገንዘብ ከለገሱት ኩባንያዎች አንዱ አንድሪትዝ ኤጂ የተባለው የኦስትሪያ የምህንድስና ኩባንያ ነው። ይህ ኩባንያ መቀመጫው በግራትዝ ሲሆን አንድ አርቲስት እንደገለፁት “ተፈጥሮን እንደ ጦር መሳሪያ” የሚጠቀመው በኩርዲስታን ለሚገነባው ግድብ የደህንነት አገልግሎት ይሰጣል። ይህ ግድብ የአካባቢውን መንደሮች በጎርፍ ያጥባል፣ ቤቶችን ያወድማል፣ ስነ ምህዳሩንና ቅርስን ያጠፋል። ሌላው ለዚህ ፕሮጅክት ገንዘብ ያዋጣው ኩባንያ በቪየና የሚገኝ ኦኤምቪ የተባለ የኦስትሪያ የዘይትና የጋዝ ኩባንያ ሲሆን፤ ኩባንያው በኒውዚላንድ ጠረፍ በሚገኙ የማኦሪ ግዛቶች ዘይትና ጋዝ ከከርሰ ምድር ያወጣል። እነዚህን ውስብስብ ተቃርኖዎች ለመጋፈጥና ለእነርሱም መፍትሄ ለማግኘት የሚያስችል ችሎታም ሆነ ክህሎት እንዲሁም ራእይ አልነበረንም።

በደምብ እየተዋወቅን በመጣን ቁጥር ግንኙነታችን ሳቅና ጨዋታ የታከለበት እየሆነና ቀለል እያለ ይመጣ ጀመር። በተደጋጋሚ ባልጠበቅነው እውቀት መደነቅ ጀመርን። እኛ መሃል ሀሚነግበርድ ምን ማየት እንደምትችልና እንደማትችል የሚያውቅ ይኖራል ብሎ ማን ይገምታል? ላንቃችን እስከሚነቃ ጮክ ብለን እንድንዘምር ምን እንደሚረዳን (ለምሳሌ ከመዘመራችን በፊት በመጮህ እና በመዝለል) ወይም በጉዞ ወቅት ከውሻ ጥቃት እንዴት እራሳችንን መከላከል እንደምንችል (ለምሳሌ በቀኝ እጅ ድንጋይ ይዘን) የሚያውቅ ይኖራል ብሎ ማን ገመተ። አንዳንዶቻችን ታዋቂ ዘፋኝ አንዳንዶቻችን ደግሞ የዳንስ ችሎታ እንዳለን በመቀራረባችን ተማርን። ከመሃላችን አንዷ ህልመኛ እንደነበረችና የራሷን UFO ከቡሽ ዛፍ አጠገብ አቁማ እንደነበር ተረዳን። አንዳችን ከሌላችን ለመማር ሞከርን። ልዩነታችንን እና የየግላችን መለያ የሆኑትን ነገሮች አደነቅን።

አንዳንዴ በስብሰባዎቻችን ወቅት በምርምር ስፍራዎችቻችን ለሚገኙት የመጣንባቸው የህብረተሰባችን ክፍሎች የነበረንን መስጠትና ቃልኪዳን የረሳን

ይመስል ስራዎቻችን ግላዊ ሁሉን ልሰብስብ ባይ የአርቲስት ማንነት ውጤት ተደርገው የታዩባቸው ጊዜያትም ነበሩ። ስራዎቻችን ውስብስብ የስነ ጥበብ አስተዋጽኦዎች እንደሆኑና ስለ ሥነ ውበትና ዘርፈ ብዙ የሆነ የስነ ጥበብ ዓለምን የመስራት ችሎታ ውይይትን የሚጋብዙ መሆናቸውን ማሳየቱ ሁልጊዜም አስቸጋሪ ጥረት እንደሆነ ተረዳን።

የጋራ ቋንቋ ለመፈለግ ታገልን። አንዳንዶቻችን አካዳሚያዊ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ልምምድ ያለን ስንሆን ሌሎቻችን ደግሞ ይህ አልነበረንም። አንዳንዶቻችን በአደባባይ የመናገር ችግር የለብንም ሌሎቻችን ይህ ልምምድ ስለሌለን ቢያንስ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቸገርን። ውስጣዊ ተዋረዶች ጋር ታገልን። በመነሻችን በተለይ የተጠናከረ ማእከል እንዳለና ሌሎች ዳር እንደቆሙ ተሰማን በሁለቱ መሃከል ያለው ክፍተት ሰፊ ሆኖ ታየን። አለመታየታችን ተገቢውን አድናቆትና ትኩረት እንዳላገኘ ተሰማን። እቅድ አውጥተን በተወሰነለት ጊዜ ሳናከናውን የቀረንባቸው ጊዜዎች አንድ ሃሳብና ቦታ ላይ እንደተቸከልን ተሰማን። ብዙዎቻችን በቡድን የሚሰሩ ስራዎችን ሰርተናል፤ ነገር ግን እንደ አርቲስቶችና የግላችንን ሰዋሰውና ቃላት ወደፊት እንድንገፋ በመሰልጠናችን የተነሳ ከሌሎች ጋር አብሮ መስራት ሁሌ ቀላል አልነበረም። አሁን በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ በማይመች የእንጨት ወንበር ላይ ተሰፍተን ተቀምጠን ፊት ለፊታችን ባሉ ላፕቶፖቻችን ላይ አፍጠን እልፎ አልፎ ወደ አውናዊው (virtual) አለም ጉብኝት እንድንሄድ እድል ሰጠን። በየመስክ ጥናቶቻችን ያስተዋልናቸውን ተቃርኖዎች፤ ሰሜንና ደቡብ፣ ተቋማዊ ማዕከል እና ዳርቻዎቹ፣ ዜግነትና ነዋሪነት የመሳሰሉት ጉዳዮች ፊታችን ተመላለሱብን።

በክፍል #A4239A በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን በደቡብ ንፍቀ ክበብ ባሉ የተለያዩ ማህበረሰቦች መሃከል ድልድይ የመስራት እምቅ ሀይል እንዳለ ጭላንጭል አየን። እውቀትና ዘዴ (strategy) ከአንዱ ወደአንዱ የሚዘዋወሩባቸውን ሁኔታዎች በጉጉት እየተጠባበቅን ድንበር ዘለል የሆነ ፋይዳ ያላቸውን አለምን የመስራት ትልሞችን አሰብን።

ምን ማለት ነው በመነጠቅ ላይ የሚያተኩርን ፕሮጅክት አብዛኞቹ የፕሮጀክቱ ቡድን አባላት ከደቡባዊ ንፍቀ ክበብ የመጡ በሆኑበት ሁኔታ በሰሜናዊው ንፍቀ ክበብ የተወለደች ፕሮፌሰር ስትመራው? በዚህች ነጭ "የፕሮጀክቱ መሪ" በተዘጋጀ የጥናት ንድፍ ማእቀፍ ውስጥ የጥናት ቡድኑን ማቋቋምስ ምን ማለት ነው? ይህች ሰው ለፕሮጀክቱ ገንዘብ ካገኘች በኋላ አምስት አርቲስቶች / ተመራማሪዎች ቡድኑን እንዲቃላቀሉ ሲጋበዙ በደግነት የተደረገ ግብዣ ወይስ በመጠነ ሰፊ ነጠቃ ላይ የተመሰረተ ከሰሜን ተነስቶ ወደ ደቡብ የሚፈነጥቅ የገዢ ሀይል መገለጫ? አግባብ ባልሆነ የትብብርና የውስጥ ስርዓት በደቡብ እያሰረጹ የሰሜኑ ኮርፖሬሽኖች የደቡቡን ሃብት ማውጣትና መውሰድ ምን ማለት ነው? የሰሜኑ ዩኒቨርስቲዎችም እነዚህን "ሌሎች" እውቀቶች እየወሰዱ ከዚያም ከልብ በሆነ መንገድ እነዚህን እውቀቶች ተቋማዊ ተፈጥሯቸውንና ይዘታቸውን ከመሰረቱ እንዳይጠይቁ በደቡብ የሚገኙ ማህበረሰቦችን መከልከልስ?

አንድን የጥናት ቡድን በጥናት ሂደቱ ውጣ ውረድ ውስጥ መምራት እና በተመሳሳይ ጊዜ የራስን (ምእራባዊ) የእውቀት ማዕቀፍ ውሱንነትና አለማወቅ



የማጠየቅ ስራን ባንድ ላይ ማከናወን ይቻላል? የናጥት ቡድኑን መምራትና በተመሳሳይ ሰዓት ግሎሪያ ዌከር እንደምትለው የራስን "ነጭ ንጽህና" ኢንፌክሽን ማለትም የራስን ጥቅምና መብት ለመገንዘብ አለመፈለግን መመርመር ይቻላል?[2] ስለዚህ የዚህ የቤት ስራ አላማ ለፈተና መዘጋጀት ሳይሆን ህመም ባልበዛበት መልኩ መውደቅን ለመማር ነው። እንዴት ተጠያቂ መሆን እንደሚቻል ለመማር ነው። መቼ መናገር እንደሚገባና መቼ ማዳምጥ እንደሚያስፈልግ ለመማር ነው። ቡድኑን የህመም ማእበል ከእግሩ አንስቶ ሊጠርገው ሲያስገመግም እና ለአፍታ የሚያርፍበት ቦታ በመፈለግ ንዴት በነጻነት መንሳፈፍ ሲጀምር ለቡድኑ ማሰብና መጠንቀቅን ለመማር ነው። ጭንቀት እንደ ተላላፊ ቫይረስ መሰራጨት ሲጀምር ለራስ ማሰብን ለመማር ነው። ቅርበትና ርቀትን ለክቶ መንቀሳቀስን ለመማር ነው። ውጥረትን ለመቆጣጠር ስንሳሳት ይቅርታ ማለትን ለመማር ነው። የመምህራንና የተማሪዎችን ጥንቅር የሚያንጸባርቅ ዩንቨርሲቲ የመፍጠርን ሂደትን ለመማር ነው።

በመስክ ጥናት ስፍራዎቻችን ስንሄድ የምናገኛት የደቡባዊው ንፍቀ ክበብ ፀሃይ በቪዬና ቢሮ የነበሩን ትግሎች እንዲወገዱ ታደርጋለች። እነዚህ ቦታዎች በአንድ ጊዜ ለምለምና አሳዛኝ፣ ቆንጆና አስፈሪ፣ ወግ አጥባቂና ለአዲስ ሁኔታዎች ክፍት የሆኑ፣ ምቹና እንግዳ ተቀባይ እንዲሁም የተጎሳቆሉ ስፍራዎች ናቸው። የድብቅ መቃብሮች በሞሉበት በዚህ ከባቢ የነባር ህዝቦች እምቢተኝነት የስነ-ምግባር ኮምፓስ ማዕከሎች የሆኑበት፣ ብዙ የደስታ ክብረ በአላት ከወታደራዊና ልዩ ታጣቂ ሃይሎች ጎን ለጎን የሚከበሩባቸው አካባቢዎች ናቸው። ክብርን ለማስመለስ የሚደረጉ በቁጭትና ንዴት የታጀቡ የአካባቢ ወረራን ለመመከት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱባቸው ስፍራዎች ናቸው። ከሰሜናዊው ወደ ደቡባዊው ንፍቅ ማቋረጥ ለሰሜኑ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ልምምዶችን (ሰሜናዊው ንፍቅ ላይ ከመኖር የሚመጣ የአገልግሎቶች አለመቋረጥ የሚያመጣውን መሞላቀቅ) መርሳትን ይጠይቃል። ነገር ግን ሁሌም በሰሜናዊው ንፍቀ ክበብ የሚኖረው የደቡብ ሰው ጋር የሚቆይ ቁስል በሰሜኑ የሚፈጠረው የየእለት የበታችነት ስሜት ነው። ወደ ደቡባዊ ንፍቅ መመለስ እንዴት ንቁ መሆን እንዳለብን እንደገና መማር ያስፈልጋል፣ የእለት ተእለት ህይወት ተገማችነት የማጣትን (unpredictability) አደጋ ለመቀበል ክፍት መሆን፣ ላፕቶፕ እና የባንክ ካርድ አለመያዝ፣ አትክልትን በጸረ ባክቴሪያ ማጽዳትንና የሚጠጣ ውሃን መግዛት፣ ለረጅም ሠአታት በትራፊክ ቆሞ መጠበቅን፣ እራስን መቆጠብ በተፈጥሮ የተሰጠ ሳይሆን በልምድ የሚገኝ መሆኑን መቀበል፣ የምንወዳቸውን ሰዎች በየእለቱ ለከፍተኛ አደጋ ተጋላጭነት የተዳረጉ መሆናቸውን ሳይዘገይ መገንዘብና ነገሮች በፍጥነት መጥፎ አቅጣጫ ሊይዙ እንደሚችሉ እንደገና መማርን ይሻል። በእነዚህ ሁሉ የተቃረኑ እውነታዎች ውስጥ ከሰሜን ወደ ደቡብ/ ከደቡብ ወደ ሰሜን ማቋረጥ የሚጠይቀው ወደ ሌላ የተቃርኖ ስብስብ ውስጥ መሻገርን ነው። የራስ አቋምና ለራስ የሚኖር አመለካከት እንዲሁ የሚዋልል ይሆናል። በአውሮፓ የትምህርት ጥቅም እና ምቾት ለተወሰነ ጊዜ መቆየት እንደ ቅንጡም እንደ ከሃዲም ሊያስወስድ ይችላል።

ለማወቅ አስቸጋሪ የሆነ ግርምቢጥ አለም ነው። በኩርዲሽ ተራሮች ላይ ሆኖ "የብላክ ሆል" ፎቶ ማየት ትንሹን አይምሮ በመደነቅ ይሞላዋል። ይሄ የሆነው

2 Gloria Wekker, *White Innocence: Paradoxes of Colonialism and Race* (Durham: Duke University Press, 2016), 1–29.

በኑክሌር አስፈራርቶ የሚፈልጉትን ለማግኘት ስለሚደረግ ጥረት ስንሰማ ነው። ይህች ፕላኔት የሚያስደንቁ ነገሮች ቡፌ ናት። አስደናቂ፣ አናዳጅ፣ አነቃቂ፣ አሰቃቂ፣ ... እና አዎ እኛ ስድስት ፈቃደኛ አእምሮዎች በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን አለም የምታልፍባቸውን ለውጦች ስንከተል ነበር። የብዙዎች መፈናቀልና የፖለቲካ ትግሎችን እንዲሁም የስነ መህዳራዊ አደጋዎችና የተፈጥሮ ነጻነት ጋር ተፋጠናል። እነዚህን ጉዳዮች በተለያየ ቋንቋ እና መረዳት ስንወያይ እኛም የራሳችንን መለወጥ አይተንበታል።

እንዴት አድርጎ ነው ሃሜት ከሲኖፕ፣ አዲሰ አበባ፣ ዲያርባኪር፣ አሌንቴዠ፣ በርሊን፣ አክሳካ ወይም ቪዬና ሊመጣ የቻለው? ይደንቃል።







↑ The Willful Weeds researchers' choir performance at mumok kino in Vienna, 2019; photos by Pat Blashill; courtesy of the photographer

መሳሪያ

# በሕብር መዘመር

የሕብር ዝማሬ ሰዎች በአንድ ላይ እንዲሰባሰቡ ያደርጋል። ምኞታቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ትርክታቸውን የሚያሰላስሏቸውን ጉዳዮች እንዲያጎሉና እንዲያብራሩ እድል ይሰጣቸዋል። በዝማሬ ቡድን ውስጥ አንዱ ያንዱ ዘይቤ (ቅላጼ) ውስጥ ይገባል፤ በተመሳሳይ ጊዜም ለተለያዩ (እርስ በርስ ለሚጋጩ) ገለፃውች ቦታ ይሰጣሉ። በርካታና የተለያዩ ድምጾችን በምልዓት እንዲብራሩ ይፈቅዳል። የዝማሬ ቡድን ውስጥ ሁሉን ለኔ የሚለው ግለሰብ ጁዲት በትለርና አቴና አታናሲዩ እንደሚሉት በሌሎች ውስጥና በኩል እየተንቀሳቀሰ ይጠፋል ወይም ይነጠቃል።[1]

የዝማሬ ቡድን ከብዙሃኑና ከብዙሃኑ ውስጥ በሚኖሩ ልዩነቶች ህይወቱን ይቀዳል። ሳይዲያ ሀርትማን እንደምትለው የዝማሬ ቡድን ሚናቸው አናሳ ለሆኑትና እይረቡም ተብለው ለተጣሉት እንዲሁም "ትርፍ" ለተባሉትም፣ ስም ላልተሰጣቸው ለብዙዎቹ ይቆማል።[2] የብቸኛው ጀግና ተቃራኒ እንደመሆናቸው የቡድን ዘማሪዎች ታሪካቸው ያልተዘመረላቸው እንዲያውም ብዙ ጊዜ የተረሡ ህይወታቸው ተራና የተለመደ ተብሎ የሚወሰድ እካላት ስብስብ ናቸው። በተጨማሪም አንደ ጥንታዊው የግሪክ ትራጄዲ የቡድን ዘማሪዎች የሂስ ሰጭ አካላት ስብስብ ናቸው። ጭምብል ያደረጉ ግን ፊት የሌላቸው ግለሰቦች የድርጊቱ አካል አይደሉም ነገር ግን እየተገለጠ ላለው ድራማ መልስ ለመስጠት ያልተስተዋሉ ነገሮች ላይ ትኩረት እንዲያርፍ ስለሚያደርጉ እንደ ቁጣና ሃዘን የመሰሉ ስሜቶች ማስተላለፊያ ቱቦዎች ሆነው ያገለግላሉ። ከትግሎች ውስጥ የተወለዱ የተለያዩ የቡድን ዘማሪዎችን የሚያያይዟቸው ነገሮች ዜማዎች፣ ጽሁፎች፣ ስለ ናፍቆት፣ ቁጭት፣ መከራ እና እኒህን አንድ ላይ የመተረክ ምኞት ሲሆን፤ የቡድን ዘማሪዎቹ ደግሞ ማዕድን አውጪዎችን፣ እስረኞችን እና ሌሎች ቅሬታ አቅራቢዎችን ያጠቃልላሉ። አንድ ላይ ሲዘመሩ ትግሎችና ናፍቆቶችን በእያንዳንዳችን ሰውነት ውስጥ በማስረፅ ማጋራት፣ ማጉላትና ከነባራዊ ሁኔታችን ጋር በማስተጋባት ልንለውጣቸው እንችላለን። ዜማዎች ብዙ ጊዜ ተደጋጋሚ እና ወደ ሌላ አለም መንጥቀው የመውሰድ አቅም ያላቸውና ስሜትን የሚያነሳሱ ናቸው። መናፍስቱን በህይወት ከአደጋ ተጠብቀው እንዲቆዩ የሚያደርጉ መድሃኒቶችም ናቸው።

ፓውሎ ፍሬሬ እንደሚያስተምረን በጋራ መማር በመጀመሪያ የራስን አለማወቅ መቀበልን ይጠይቃል። የሆነ ነገር ልታስተምሩ ከሆነ እናንተም አዲስ ነገር መማር አለባችሁ። ይህ እያደረጉ የመማር አይነተኛ ማሳያ ነው። የምርምር ቡድኑ "የፅኑ አረሞች የዝማሬ ቡድን" የሚባል ቡድን አቋቋመ። ይህ ቡድን የተወለደው በአሌንቴዦ (ፖርቱጋል) በተመለከትነው የማዕድን አውጪዎች የዝማሬ ትእይት በመነጨ አድናቆት ነው። እነኝህ የማዕድን አውጪዎች ውስጥ የተመለከትነው ስስነት፣ ጽናት እንዲሁም የህብረት መንፈስ መነሳሳትን ፈጥሮልናል። የዝማሬ ቡድኑ እንዴት አንድ ላይ መሰብሰብ እንዳለብን ለማሰብ እና ለመመርመር አስችሎናል። በተጨማሪም እንዴት ባለ መንገድ አብሮነትን መገንባት እንደሚገባን አቅጣጫ ሰጥቶናል። ድምጻችንን በአንድነት በጉልህ መንገድ እና በተብራራ መልኩ እንድናሰማና ብዝሃነታችንን እና ልዩነታችንን ባከበረ ሁኔታ ቡድናችንን እንድንሰራ አስተምሮናል። ከዳንስና የክዋኔ ጥበባት መምህርና ተዋናይ ስቴፋኒ ሶውሪየል ጋር አብረን ሰርተን ነበር። እርሷም በዝማሬያችን የመጀመሪያዎቹ የልምምድ ሰዐቶች ትመራንና ታበረታታን ነበር። ግጥሙን አብረን ጻፍን። ጭንብል የለበስነውም የየራሳችን ማንነት ለመደበቅ (ለመንጠቅ) ሳይሆን የእያንዳንዳችንን የጥናት ቦታ ነጠላነትና ልዩ ማንነት ወደ ዝማሬ ቡድናችን ለማምጣትና አብሮነታችንን ለማወጅ ነው። የመጀመሪያውን ህዝባዊ ትእይንት (ትርኢት) በሙሞክ ኪኖ ቪየና ሞደርን አርት ሙዚየም ለተመልካች አሳየን። ትእይንቱን ያቀረብነው "ንጥቂያ፣ ፅኑ አረሞች እና ከፍርስራሾች ውስጥ አለምን መስራት" በሚል ካዘጋጀነው የፊልም ትዕይንት መግቢያ ላይ ነበር።

(1) Judith Butler & Athena Athanasiou, *Dispossession: The Performative in the Political* (Cambridge: Polity, 2013), 1–10.
(2) Saidiya Hartman, *Wayward Lives, Beautiful Experiments: Intimate Histories of Social Upheaval* (New York: W.W. Norton, 2019), 475–80.

ገቢር

# የዝማሬ ቡድን መመስረት

የዝማሬ ቡድን መመስረት አደጋው አንድ አይነት ያልሆኑትን ነገሮች አንድ አይነት ማድረግ ነው፤ ልዩነቶችን ለስምምነቶች ሲባል መሸፈን። ከቡድን መሪ ወይም ኮንዳክተር ጋራ ለመስራት ከወሰናችሁ መዘምራኑን የመምራት ሚና ከባድ ሃላፊነት ነው። ግለሰቦችንም ቡድኑንም በደንብ ማወቅ የሚጠይቅ ስራ ስለሆነ የመሪዋ ሚና በስልጣንና በበላይነት መምራት ሳይሆን በእውቀት ላይ ተመስርቶ የማገልገል አመለካከት መላበስን ይጠይቃል። የዝማሬ ቡድኑን ያለመሪ ለማቋቋም መወሰንም ተመሳሳይ ተግዳሮቶች አሉት። ነገር ግን ተግዳሮቶቹ ባንድ ሰው ላይ ሳይሆን በሁሉም ትከሻ ላይ ያርፋሉ። ይሄ ሁሉም ሰው በትኩረት እንዲከታተል እና አንድ ላይ ለመዘመር መንገዶችን (እየደጋገሙም ቢሆን) መፈለግን ይጠይቃል።

### ሰዎች ማግኘት

- የዝማሬ ቡድን ለመመስረት አብሮ ለመዘመር ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ማግኘትና መሰባሰብ ያስፈልጋል።

### ማሟሟቅ

- ሰውነታችሁን አሟሙቁ ተንቀሳቀሱ፣ መንጋጋችሁን አንቀሳቅሱ፣ ጡንቻዎችሁን ዘረጋጉ፣ ከንፈሮቻችሁን አንቀሳቅሱ
- በስፍራው የሰውነት አካል ግንኙነቶችን መርምሩ፤ በስፍራው ያሉትን የሰውነት አካል የርቀትና የቅርበት ግንኙነቶች አጢኑ
- የአተነፋፈስ ልምምድ አካሂዱ፤ ከአጭር ወደ ረጅም ትንፈሳ ሂዱ
- በተለያየ የድምጽ ከፍታና ክልል ዘምሩ





ገቢር

### መዝሙሩን መምረጥ/ማዘጋጀት

- ቀድሞ የነበረ ዘፈን (ዝማሬ) መዘመር ከፈለጋችሁ ለምሳሌ the Hildegard von Bingen (በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አንድ ላይ ሆነው የሚያዜሙበትን የዝማሬ እንቅስቃሴ) ወይም አዲስ ዝማሬ መፍጠር ከሆነም ወስኑ:- ለምሳሌ ለስራችሁ እንደ ሞዴል የሚያገለግል የዘፈን (ዝማሬ) ድርሰት ምረጡ።
- ዝማሬያችሁን የሚመራውን የምት አወቃቀር ለዩ ወይም እንደአማራጭ ቃላት ቆርጣችሁ ለጥፉ-ለምሳሌ በተደጋጋሚ ሙከራ ወይም (በጋራ) የነጻነት ፅሁፍ ልምምደች ወቅት የተገኙ ቃላትን በወረቀት ላይ በምታችሁ ጋር አቀናጇቸው።
- በወረቀት ላይ የተቀናጀውን ፅሁፍ ከቅላጼ ጋር አጣምሩት። በፊት የነበሩ ቅላፄዎችን ተጠቀሙ ወይ አዲስ ፍጠሩ።

### ዝማሬውን ለማቅረብ መዘጋጀት

- ስለውጤቱ ብቻ ሳትጨነቁ ትርጉም በሚሰጣችሁ መንገድ ተለማመዱ
- ዝግጅታችሁን የት ማቅረብ እንደምትፈልጉ በጥንቃቄ ወስኑ
- ዲአይዋይ (DIY) አልባሳትና ጭንብሎችን ዲዛይን አድርጉ፤ ለልዩነቶችም ዕድል ስጡ።
- ለዝግጅቱ ድራማተርጂ አዘጋጁ
- ድፍረታችሁን አክብሩ

↻ Rehearsal of the Willful Weeds researchers' choir performance with Stefanie Sourial, 2019; photos by the Willful Weeds Research Group



↗ Choir masks by the Willful Weeds Research Group; reproduced with permission of the artists

ADDITIONAL REFERENCES


- Adnan, Etel. *There: In the Light and the Darkness of the Self and the Other*. Sausalito: Post-Apollo Press, 1997.
- Alfred, Taiaiake G. *Wasáse: Indigenous Pathways of Action and Freedom*. Toronto: University of Toronto Press, 2005.
- Haraway, Donna J. *Staying with the Trouble: Making Kin in the Chthulucene.* Durham: Duke University Press, 2016.
- Morrill, Angie, Eve Tuck, and the Super Futures Haunt Qollective. "Before Dispossession, Or Surviving It." *Liminalities: A Journal of Performance Studies* 12, no.1 (2016): 1–20. Online at: liminalities.net/12-1/dispossession.pdf.
- Sundberg, Juanita. "Decolonizing Posthumanist Geographies." *Cultural Geographies* 21, no.1 (2014): 33–47. Doi: 10.1177/1474474013486067.

የመሬት ክፍት ቁስል
ሊተነፈስ የማይችል የተበከለ አየር
ለቅሶ ጩኸት ከዋሻው
አፏን ስትከፍት ስትቃትት



# ወፍራም ደም



ናኦሚ ሪንኮን ጋላርዶ

ዛካቴካስ /ሜክሲኮ/

“ኤክስትራክቲቪዝም ወይንም ቡጥቦጣ ካፒታሊዝም በአሜሪካ አህጉራት ከንጥቂያ፣ ብድር፣ በሀይል ማፈናቀል ጋር የሚሰራውን የኢኮኖሚ ስርዓት ይመለከታል። በሀይል እርምጃውም የነባር የአሜሪካ ህዝቦችን እና አፍሪካዊ ዝርያ ያላቸውን ሰዎች ማህበራዊ ህይወት ያደራጃል እንዲሁም መሬታቸውን እና ሌሎችን ሀብቶቻቸቸውን ይነጥቃል። አድሎአዊ የዘር ካፒታሊዝም [የሚባለውን ንድፈ ሀሳብ] በታሪካዊ ሂደት የአፍሪካ ዝርያ ያላቸውን እና ነባር የአሜሪካ ህዝቦችን ጥገኝነት እንዴት እንደመጣ የሚያሳይ ሲሆን ኤክስትራክቲቪዝም ደግሞ በሰው እና በስነ-ምህዳር ላይ አድሎአዊ የዘር ካፒያሊዝም ያስከተለውን ቁሳዊ ተጽኖ ላይ ያተኩራል” (...) “ወህኒ ቤቶችን እና የደህንነት ስርዓት መረብን ከመዘርጋት ባሻገር አንዱና የአድሎአዊው የዘር ካፒታሊዝም በደቡብ የዓለም ንፍቀ ክበብ ውስጥ ራሱን የሚያስቀጥልባቸው ዋነኞቹ ዘዴዎች ግዙፍ ነጣቂ ኘሮጀከቶችን [Mega-extractive projects] ፣ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ አቅም እና ሀብት የሚጠይቁ ትልልቅ ግድቦችን፣ የማዕድን ማውጫዎችን በመገንባት እና ኤንሪኬ ዱሴል እንደሚለው ዘመናዊነትን እንደ ዓለም አቀፍ የአገዛዝ ዘዴ በመመስረት ወይም ‘የሀሰት ልማታዊነትን’ [developmentalist fallacy] በመጫን ነው።”

— Macarena Gómez-Barris, *The Extractive Zone*



“በዘር የተቃኘ የነጠቃ ፖለቲካ፣ ማፈናቀል፣ አድሎ፣ አካባቢዎችን፣ ሠዎችን ማርከስ መፈብረክና መጣል፣ ሀብትንና የሴቶችን ስነ-ተዋልዶዋዊ ጉልበት መበዝበዝ ሉላዊ ደቡባዊነት (ወንዳዊነትን ጨምሮ) የሚመረትባችው ሁኔታዎች ናቸው። በቅኝ ግዛት ዘመን ተራሮች ተንደዋል፣ ወንዞች ያለመንገዳቸው እንዲፈሱ ተደርገዋል፣ ደኖች ተመንጥረዋል፣ ወድመዋል፣ ተክሎች እንስሳትና ሠዎች ከቦታቸው ተፈናቅለዋል። ሠዎች አካባቢያቸውን የመለወጥ እና በራሳቸው አምሳያ መስራታቸውን ስለማያቆሙ የድህረ-ቅኝ ግዛት ርዕዮተ ዓለምም ተመሳሳይ የልማት አመክንዮን ይዞ ቀጥሎአል።”

— Françoise Vergès, “Like a Riot”



↑ Vetagrande in the Mexican state of Zacatecas; photo by Naomi Rincón Gallardo, 2018



በቬታግራንዴ /ዛካቴክስ/ የደቀቀ ኮረብታ አካባቢ በእግሬ ተጓዝኩ። ከፊል በረሃማ በሆነው መልክአ ምድሩ መደምሰስና በኮረብታው ለሁለት መገመስ ደነገጥኩ አጥንቴ እንደደረቀ ተሠማኝ። ትልቅ የተከመረ የደቀቀ ዳለቻ አፈር ወደተበከለ የመቃብር ቦታነት እየተለወጠ ነው። የደቀቁትን ብናኞች በሳንባዬ ተነፈስኩ። ስራመድ ያደረግኩት ጫማና ጂንስ እሾህ እና ስንጥር ይይዛሉ። የተቃጠሉ ቁልቋሎች በየቦታው ይታያሉ። የሚያብረቀርቁት የማዕድናት ቁርጥራጮች እንኳን አያፅናኑም። መንገዴን ግን ቀጠልኩ። አሻግሬ ስመለከት በግራ በኩል በመናፍስት የተወረረ የሚመስል የቅኝ ግዛት ዘመን ትንሽ ከተማ፤ በቀኝ ደግሞ ለአዲስ መጭ ማዕድን አውጪዎች የተሠሩ ቤቶች አንድን ሀይቅ ከበው ቆመዋል።

ቬታግራንዴ ማለት በስፓኛ “ጥልቅ የደም ስር” ማለት ነው። የሚገኘውም ከዛካቴካስ ሀገረ ግዛት ዋና ከተማ በጥቂት ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ ነው። ዛካቴካስ የተቆረቆረችው በስፔይን ቅኝ ገዢዎች በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን ከዛ ጊዜ ጀምሮ “የማዕድናት እርግማን” በክልሉ ተሠራጭቶ ይገኛል። የአካባቢው ሠዎች “የማዕድናት እርግማን” ብለው ዛካቴከስን የሚጠሯት የ500 አመት ዝርፊያን ያስተናገደች በብር፣ ዚንክ፣ መዳብ፣ እንዲሁም ሌሎች ማዕድናት ሀብታም የሆነች አካባቢ ስለሆነች ነው። በአዲስ መልክ የተደራጀ በአሜሪካና ካናዳ ኩባንያዎች የሚመራ የንጥቂያ (extractivism) ኢንዱስትሪ በ21ኛው መቶ ክፈለ ዘመን ተጠናክሮ በመጀመሩ የአካባቢውን ሠው ማዕድናትን በመቆፈር የአካባቢውን ትሩፋት የመጠቀም እና የመሸጥ መብቱን ከልክሎታል።

ይህ ነጣቂ አድኋዊ ጣልቃ ገብ የዘር ካፒታሊዝም በሠዎች እና በስነ ምህዳራቸው ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል።[1] ከዚህ የሚገኘው ትርፍም ወደ ሰሜኑ ንፍቀ ክበብ ይሄዳል። የአካባቢው መንግስት ህጋዊ ግን ኢፍትሀዊና ብልሹ አሠራሩን ለልማት ሲባል መደረግ ያለበት ነው በማለት ያስተባብላል። ሠሜኑ ትርፉን ያገኛል ደቡቡ ደግሞ ብክላውን፣ መፈናቀሉን፣ ህገወጥ ወታደራዊነትን፣ የሠዎች መጥፋትን፣ የአካባቢ ውድመትን ያገኛል። በአካባቢው ብክላ የተነሳ ፎሪው ያለጊዜው ይሞታል። በዚህም የተነሳ “ጥልቅ የደም ስር” የምትባለው ዛካቴካስ ደም አልባ ትልቅ ክፍት ቁስል ሆናለች።

የቅኝ ግዛት የሀይል እርምጃና ግፍ፣ ነጠቃ እንዲሁም በገፍ እየጠፋ ካለው ህይወት ጋር ተዳምሮ የሠው እና ሠው ያለሆኑ መናፍስትን እንዲቀሠቀሱ ብሎም ንጥቂያ አውድማ ያደረገው ስፍራ ላይ እንዲሰፍሩ አድርጓቸዋል። “ወፍራም ደም” የነዚህን በቬታግራንዴ (ዛካቴክስ) የተበከሉ ፍርስራሾች መሀከል እያጉረመርሙ ከአካባቢው የሚውጡ መናፍስት እና ፍጥረታትን ታሪክ የሚተርክ ስራ ነው። እነዚህን መናፍስት ታሪኬ ውስጥ ያስገባኋቸው በደቀቁት ኮረብቶች ላይ ስራመድ፣ በአካባቢው የሚገኙ ቤተ መዛግብትን፣ ሚውዜም እና የፎቶግራፍ ስብስቦችን ስጐበኝ፣ ጋዜጦችንና የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎችን ሳነብ፣ ጋዜጠኞችን፣ የመብት ተሟጋቾችን እንዲሁም የአካባቢውን ሙዚየም መስራች የነበረውን አሁን በህይወት የሌለውን ሰው ሚስት ቃለ መጠየቅ በማድረግ ነው። የ“ወፍራም ደም” ተረኮች በቀጥተኛ መስመር ላይ የሚፈሱ አይደሉም። ያልቀኑ የቪዲዮ ትርክቶች ናቸው። ስድስት ንዑስ-ምዕራፎች አላቸው። እንዚህ:- ም:- ሳንባዎች፣ ትንቢት፣ ሀሚንግ በርድ[2]፣ ባለ መዳብ ጥርሷ ሴት፣ የማዕድናት እርግማን እና ወፍራም ደም ናቸው።

1 Macarena Gómez-Barris, *The Extractive Zone: Social Ecologies and Decolonial Perspectives* (Durham: Duke University Press, 2017), xvii.
2 በአሜሪካ አህጉራት የምትገኝ ሹል እና ረጅም መንቁር ያላት ወፍ።



↑ Sketches for *Heavy Blood* by Naomi Rincón Gallardo, 2018



“ጭራቅ ምንድነው? (ጭራቅ በደል የደረሠበት ፍትህ የሚሻ መንፈስ ነው)። ጭራቆች ምን ሲሆን ነው የሚያስቸግሩት? (ጭራቆች የሚያስቸግሩት በደላቸው ሲረሳ ነው። ጭራቆች የሚያስቸግሩት ሲካዱ ነው። ሆኖም የጭራቆችን ነገረ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት አይቻልም።) እንዴት ነው ግን ጭራቆችን ለማጥፋት የሚቻለው? (ጭራቆችን ለወዲያኛው ማጥፋት አይቻልም። ጭራቆችን ለተወሠነ ጊዜ ገሸሽ ማድረግ ማባረር ብቻ ነው የሚቻለው። ወደ ህይወታችን የሚገቡበትን በራቸውን ለዘለቄታው መዝጋት አይቻልም።)

— Eve Tuck & C. Ree, “A Glossary of Haunting”

## ሳንባዎች

አንድ ተዋናይ ሁለት ገፀ-ባህሪያትን ይላበሳል-ማዕድን አውጪና የስልክ ወሲብ ስራ ላይ የተሰማራች ሠው። በትይዩ ስክሪኖች ላይ ሁለቱም ገፀ-ባህሪያት ይታያሉ። የሚገኙትም በአንድ ወለሎቹ የሻገቱ በዛጉ ቁሳቁሶች የተመላ ሙዚየም ውስጥ ነው። የማዕድን ሠራተኛው አካላዊ ጉልበት የሚጠይቅ እንቅስቃሴ ያደርጋል፣ በከባድ ሁኔታም ይተነፍሳል። የስልክ ወሲብ ሰራተኛዋ ደግሞ የተለያዩ ቅላፄዎችን ታወጣለች። የእርካታ ድምፅ እንዲሁም የመታፈን ድምፅ። የመደብ፣ የዘር እና የፆታ ጥገኝነታቸው የላብ አደር ሳንባቸው ውስጥ ይገባል። ሁለቱ ገፀ-ባህሪያት አተነፋፈሳቸው ይፈጥናል። መተንፈስ እስኪያቅታቸው ይተነፍሳሉ። በመጨረሻም መተንፈስ ሲሳናቸው ጥቁር ነገር ይተፋሉ።  ፍርግርግ ብረት-ሽቦ የለበሱ መንትያ ምስሎች የታፈነ የሳክስፎን ድምፅ ያወጣሉ።





↑ Video stills, *Heavy Blood* (HD video, 18'46"), by Naomi Rincón Gallardo, 2018





↑ Bárbara Lázara in *Heavy Blood* (HD video, 18'46"), by Naomi Rincón Gallardo, 2018

## ትንቢት

የማዕድን/የስልክ ወሲብ ሠራተኛ ድምፅ መቅጃ ቴፕ ይዘው በረሃ ውስጥ ይታያሉ። አንድ ድምፅ ትንቢት ይናገራል።

> አያቶቻችን ምን ይሉ እንደነበር ካስታወሳችሁ፣ የመጨረሻው ሰዓት ላይ ጨለማ ይሆናል ደም የጠማቸው ያላገቡ ሴቶች ወደ ምድር ወርደው ይበሉናል።  ከዛም አለሙ ይለወጣል። ጭምብል እና ከቁልቋል የተሠራ ዊግ የለበሱ ምስል ከአውድማው እና ከበረሃው ይወጣሉ።[3]

እኒህ ምስል የሜሶ አሜሪካ አማልክት የሆነችውን ትዚትዚሚሚን ይመስላሉ። የትዚትዚሚሚ የማይጠግብ መንፈስ እና የማይረካ ሀይል በሜሶ አሜሪካ አፈ-ታሪክ የሚገለጠው የህይወት ዑደትን እንደገና ለመለወጥ ነው። የማዕድን/የስልክ ወሲብ ሠራተኛዋ ጭምብል ትለብስና ከሌሎች ባለ ጭምብሎች ጋር ትቀላቀላለች። እየሳቀችም የመዳብ ጥራሿን ታሳያለች።[4]

3 ከ Annals of Juan Bautista ሡተወሠደ ዝርው ትርጉም። ይህ መፅሀፍ በናሁዋት ቋንቋ (በሜሶ አሜሪካ የሚገኙ የናሃው ህዝቦች) ፅሁፍ በ16ኛው መቶ ክ/ዘመን የተገኘ ነው።

4 This passage is adapted from *Annals of Juan Bautista,* a compilation of texts written in *náhuatl* (the language of the Nahua people in Mesoamerica) from the sixteenth century.



↑ Video still, *Heavy Blood* (HD video, 18'46"), by Naomi Rincón Gallardo, 2018

## ሃሚንግ በርድ

አንዲት ሃሚንግበርድ በቼታግራንዴ የማዕድን ፍርስራሾች ውስጥ ትኖራለች። በሜሶ አሜሪካ ንፅርኦት አለም ሃሚንግበርድ በጦርነት ጊዜ የወደቀች የወሲባዊነት ተምሳሌት ስትሆን መሬትን ከሰማይ/ከጠፈር የምታገናኝ ቅዱስ ፍጥረትም ናት። ዘዴኛዋ ሠው ሠራሽ "የወፍራም ደም" ሃሚንግ በርድ የአበባ ማር ወለላን እየመጠጠች የቀድሞ መኖሪያዋ ስለፈረሰባት በበረሃ ለመኖር ተገድዳለች። አቅጣጫ ጠፍቶባት በስክሪኑ ላይ ወደሚታየው እየጠፋ ወዳለ አንድ አረንጓዴ መሬት ትበራለች። ወደ አንድ ዋሻ ገብታም የመዳብ ጥርስ ያላትን ሴት ታገኛለች። በእነዚህ ሁለት የተለያዩ ፍጥረታት መካከል (interspecies) ወዳጅነት ይጀምራል።

| | |
|---|---|
| Flecha | ቀስት |
| Espina sangre | ደም እሾህ |
| Borracha de miel | በማር መስከር |
| Inmóvil en el aire | አየር ላይ የማይንቀሳቀስ |
| Zumbando sortilegios | ድግምት ማነብነብ |
| | |
| Nómada | ዘላን |
| Vuelo vibrador | የሚነዝር በረራ |
| Libando el nectar | ወለላውን በመምጠጥ |
| En intercambio mutuo | ለቅፅበታዊ ሞት |
| Para una muerte pasajera | የውስጥ ትኩሳት |
| | |
| Picaflor | ሃሚንግ በርድ |
| Caldera interior | የወደቀች ጦረኛ |
| Guerrero caído en combate | በሚውለበልቡ ክንፎች የሚመሩ |
| Alas batientes que guían | በአስማት የሚጠፉ የሚመስሉ |
| A los que desaparecieron como por magia | ግራኝ |
| | |
| Zurda | ከተለያየ ስፍራ ሲያዩት የሚለዋወጥ ድንጋይ |
| Piedra tornasol | በትንሽ ፈለግ የምትመለስ |
| Dardo que se desplaza | ወደ ቀደመው መልክዓምድሯ |
| A sus paisajes natales | የተበከሉ ፍርስራሾች የደቀቁ ኮረብታዎች |
| Ruinas tóxicas y cerros triturados | በመብረር |
| | |
| Vuelan | ረጅም መንገድ |
| Larga ruta | እንደገና ከሞት በመነሳት |
| Los resucitados | በድርቁ ለመሞት |
| Que mueren en la sequía | ከዝናቡ ጋር ወደ ህይወት ለመመለስ |
| Y reviven con las lluvias | |
| | በረሃ መጣሁ ላይህ |
| Desierto | ለምትቃጠለው ሴት |
| Vine a buscar | የመዳብ ጥርስ ላላት |
| A la mujer que se quema | አለምን ለምታጠፋው |
| La de los dientes de cobre | ጭራቅ |
| La destructora telúrica. Monstruo | |

## ባለ መዳብ ጥርሷ ሴት



ባለ መዳብ ጥርሷ ሴት የጥልቅ ስሜታዊ ድምጿን አስተጋብኦ በመላ ሠውነቷና የድንጋይ ግድግዳ ባለው ዋሻ ውስጥ ትፈልጋለች። በድምፅ መቅረጫው ራሷን ትቀዳለች። የሜሶ አሜሪካ አማልክት የሆነችውን በዋሻ ውስጥ የምትኖረውን ትላንቴፑዚላማን ታስታውሳለች። ትላንቴፑዚላማ ከዋሻዋ የምትወጣው የልጅና የአዋቂ ልብና ደም አምሮቷን ለመወጣት ብቻ ነው። ትላንቴፑዚላማ ከብዙዎች የሜሶ አሜሪካ የምድር ፍጥረታት ውስጥ አንዷ ስትሆን የእነዚህ አማልክት የማጥፋት ችሎታና ሀይል የህይወት ዑደትን (ህይወትና ሞትን) ለማደስ ይጠቅማል። ባለ መዳብ ጥርሷ ሴት የተጐዳ መሬትን ድምፅ እያወጣች ጉምጉም ትላለች። ታላዝናለች።

↑ Bárbara Lázara in *Heavy Blood* (HD video, 18'46"), by Naomi Rincón Gallardo, 2018



## የማዕድናት እርግማን



ባለ መዳብ ጥርሷ ሴት እንግዳ የሆነ ሽርሽር በግራጫው የደቀቀ ድንጋይ በበዛበት ክፍት የማዕድን ጉድጓድ ውስጥ ስታደርግ ትታያለች። ፍራሽ ላይ ተቀምጣ ቀይ ነገር እየጠጣች፤ በኘላስቲክ ጠርሙስ ውስጥ የውሃ ፒፓ እያጨሠች በስካር ትናውዛለች፤ እያጨሠች ታስላለች። በፈራረሰው መልክዓምድር ውስጥ ሆና በአፏ በምትወስደው መጠጥና በምታወጣው ጭስ ትዝናናለች። የራሷን ድምፅም በድምፅ መቅረጫው ትቀዳለች። የመጠጥና የማጨስ ተግባሯን ትዚትዚሚሚዎች /ጥርሳማ ብልቶች/ ያጅቧታል። ሁሉም አንድ ላይ ሆነው ለበቀል ያላቸውን ጥማት ለመቁረጥ ይዘጋጃሉ።



↑ Video still, *Heavy Blood* (HD video, 18'46"), by Naomi Rincón Gallardo, 2018

↖ Bárbara Lázara in *Heavy Blood* (HD video, 18'46"), by Naomi Rincón Gallardo, 2018



↑ On the set of *Heavy Blood,* by Naomi Rincón Gallardo, 2018; photo by Angélica Canales



## ወፍራም ደም

የትዚትሚሚዎች /ጥርሳማ ብልቶች/ ቡድን በበረሃው ላይ ሳክስፎን ይጫወታሉ ከበሮ ይመታሉ። ባለ መዳብ ጥርሷ ሴት ራስን መከላከልን በሚያሳይ የዳንስ እንቅስቃሴ ታጅባ ትዘፍናለች:-

Desde las ruinas
Nuestras vidas al acecho
Por el expolio
Portadoras del desecho
Desde las ruinas
Aguantando la rapiña
Desde las ruinas
En defensa expulsiva

Sangre pesada
Resiste, persiste
Sangre pesada
Necea, perrea
Sangre pesada
Más deseante que deseable
Sangre pesada
Durable e indomable.

Inhala
Exhala
Liba!
Escupe!
Deglute!
Muerde!
Arranca!

*Blue grabbing!*
*Land grabbing!*
*Pussy grabbing!*

Aunque sedientas seguimos escupiendo
Aunque chimuelas vorazmente mordemos
Aunque explotadas viviendo en exceso
Agazapadas lamiéndonos los dedos
Muertas fallidas comiéndonos las uñas
Intoxicadas con hambre de venganza

በፍርስራሹ መሃል
ተኝተን እንጠብቃለን
ቆሻሻ ብካይ ተሸካሚዎች ነን
እንከላከላለን እናስወጣለን
ወፍራም ደም

አንገዳደራለን እንፀናለን
ወፍራም ደም
በትጋት በጥንካሬ እንቆያለን
አንደንሳለን
ወፍራም ደም
መፈለግ ሳይሆን እንፈልጋለን
ወፍራም ደም

ፅኑ እና የማይሸነፉ
ወደ ውስጥ መተንፈስ
ወደ ውጭ መተንፈስ
መምጠጥ! መትፋት!
መዋጥ! መንከስ!
ማጥፋት!
ሰማያዊውን መቀማት!
መሬትን መቀማት!
ሴትነት መቀማት!
ደርቀን የተሠነጣጠቅን ብንሆንም እንተፋለን
ጥርስ ባይኖረንም ተስገብግበን እንነክሳለን
ብንበዘበዝም ከልክ ባለፈ መንገድ እንኖራለን
ጊዜያዊ መጠለያ ፍለጋ ጣቶቻችንን እንመጣለን

ያልተሳካልን አስከሬኖች
ጥፍራችንን እናኝካለን
በበቀል ረሃብ አንሠክራለን






መሣሪያ

# መናፍስትና ጭራቆች በተገፈፉ መልክዓምድሮች

ባለ መዳብ ጥርሷ ሴት--ጭራቅ መሆን እንዴት ነዉ?

ባለ መዳብ ጥርሷ ሴት:- በሰውነቴ ውስጥ ልባቸው የሚመታ ግን የሞቱ የተሠወሩ ሠዎች እንቅስቃሴ ይሠማኛል፣ ለመጋጥ የማይመጡት ፍየሎች፣ የጥፉት ሠብሎች- አልፋልፋው፣ ባቄላው፣ አጃው፣ በቆሎው፣ የፒር ፍሬ ለእንስሳት መኖነት የምንጠቀመው እነዚህ ሁሉ ይሠሙኛል። ቆዳዬ ተገፍፏል። ቀድሞ መሬቱን ይሸፍኑ የነበሩ ተክሎች አሁን የሉም። አንዳቸውም አልተረፉም። ጥርሶቼ እና ድንጋዮቼ ተነቃንቀዋል። ጥልቅ የሆኑት የውሃ ጉድጓዶቼ እንኳን ተመርዘዋል። አጥንቴ ደርቆ ይሠማኛል። በሳይናይድ እና በሜርኩሪ ውስጥ ተዘፍቄያለሁ። ደሜ በእርሳስ አማካኝነት ረግቷል። የደም ስሮቼን "ስትራቴጂክ ሀብት" ብለው ይጠሯቸዋል። በእነርሡ ፋንታ የታሸገ ውሃ የሠጡኛል። ግን እዚህ ያለሁት ስለ ህመሜ ለመናገር አይደለም። የመጣሁት እንደእኔ ያሉ ሌሎችን ለመመልመል ነው። ምክንያቱም እኛ የጦር ሀይል ነን። በዚህ ሁሉ ጭካኔ ውስጥ ሆነን ኘሮግሬስ (ስልጣኔ) ላይ እንቅፋት ለመፍጠር መላ እንዘይዳለን። በዚህ ሁሉ ጭካኔ በዚህ በብካይ መሬት ውስጥ ሆነን ጊዜያዊ መጠለያ እንፈልጋለን፤ ልናደርሠው የምንችለውንም በቀል እና ጥፋት እናሰላስላለን።

መናፍስትና ጭራቆች የጉልበት እርምጃና ማህበራዊ ጥፋት ባለበት ቦታ ሁሉ ይመጣሉ።(1) እንስሳት፣ የተለያዩ የህይወት አይነቶች፣ የተገደሉና የተሠወሩ ሠዎች ለመደመጥና ለመሠማት መንገድ የፈልጋሉ። በንጥቂያ መልክዐ-ምድሮች ሞት በህይወት መጨረሻ የሚመጣ ሳይሆን ከህይወት ጋር ሁሌ አብሮ የሚኖር ነገር ነው። እነዚህ መናፍስትና ጭራቆች ሲመጡ እንዴት ነው ቦታ አዘጋጅተን የምንቀበላቸው?

የመናፍስት አለም ለሠው ልጅ መንፈስ ብቻ መኖሪያ ቦታ አይደለም። አጥፊ የሠው ልጅ እርምጃ፣ ሀይልና ጭካኔ ሠው ያልሆኑ መናፍስትንም ይፈጥራል ይጠራል። የብዝሀ ህይወት ከምድር ላይ መጥፋት ብዝሀ መናፍስቶች በምድር ላይ እንዲሠፍሩ ምክንያት ይሆናል። በንጥቂያ ዞኖች እና በአሮጌ ኢንዲስትሪዎች ላይ ይሰፍራሉ። ከዚያ ይነሳሉ። እንደማይፈለጉ ችኮ-የማይጠፉ አረሞች እንደገና መልሰው መላልሰው ይበቅላሉ። በመናፍስት በተወረሩ ፍርስራሾች መሃል የተሠወሩ ህይወቶች ውል ይገኛሉ። መናፍስቱም የሚያንፀባርቅ መናፍስታዊ ብርሃናቸውን ይለቃሉ። ብርሃናቸውም እንግዳ ከሆነው አየር ጋር ይናበባል።

(1) Avery F. Gordon, *Ghostly Matters: Haunting and the Sociological Imagination* (Minneapolis: University of Minnesota Press, 2006).

## ገቢሮች

የሚከተሉት ገቢሮች ህይወትን እና አለምን ለመስራት ለሚደርጉ ጥረቶች መናፍስቶችን እና ጭራቆችን ለመጋበዝ ለሚፈልጉ እንዲያግዙ ተዘጋጅተዋል። እነሆ:- መናፍስቶችና ጭራቆችን አለምን በመስራት ጥረት ውስጥ መጋበዝ (2)

ተቀባይ፡ መንፈስ በሰፈረበት አካባቢ ለሚኖሩ ግለሰቦችና ማህበረሰቦች

### ለመናፍስቱና ለጭራቆቹ እውቅና መስጠት

- ስራ የምትሰሩበት፣ ጥናት የምታካሂዱበት ወይም የምትኖሩበት ቦታ በእግር ተመላለሱ። ይህን ማድረግ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ግምት ውስጥ ክተቱ።
- ይህን አካባቢ ለመመስረት/ ለመቆርቆር እነማን እንደተበደሉ አንደተጨቆኑ አጣሩ። የአካባበውን ታሪክ የሚያውቁ ሰዎችን አናግሩ፣ ቤተ መዛግትን ጐብኙ፣ አንብቡ ማስታወሻም ውሰዱ።
- በአካባቢው የሚገኙ ምልክቶችን፣ አስተሳሰቦችን ቅሪቶችን በማጥናት በቀደመ ጊዜ የኃይል እርምጃ የተፈፀመ ያለፈ ቢመስልም ውሉ እስከ አሁን የሚመዘዝ የንጥቂያ እና የጭካኔ ታሪክ ፈልጉና ለይታችሁ አውጡ። እንዴት የመገፈፍ፣ የብዝበዛ እና የጭቆና ታሪክ ይህ ቦታ ላይ ተጽእኖ አሳደረ? በቃል የማይነገሩ/ የማይባሉ ነገሮች ነገር ግን በስሜት የሚገለጹ ምልክቶችን አስተውሉ እውቅና ስጡ። እንዲህ አይነት ስሜቶችን በተቻላችሁ ዝርዝር ከትቡ፤ ምን እይነት ስሜት እንደሆኑ እንዴት ልታውቁዋቸውና ልትደርሱባቸው እንደቻላችሁ እና እንዴት የቀደመ ታሪክ ምልክት እንደሆኑ አጢኑ። ማስታወሻም ውሰዱ።
- የአካባቢውን ሰው እና ሰው ያልሆኑ መናፍስት ለይታችሁ እወቁ። እንዴት ነው እውቅና እድንሰጣቸው የሚጠይቁን? ምን አይነት የስሜት ቀመር ያስመዘግባሉ? ያዘኑ ወይስ የተናደዱ፣ የሚቃትቱ ወይስ ለመበቀል ሴራ የሚሸርቡ ናቸው ብላችሁ ጠይቁ። ማስታወሻም ውሰዱ።

### መናፍስቱና ጭራቆቹ የሚመጡበትን ሁኔታ እና ስፍራ አመቻቹ

- ከላይ የተዘረዘረውን በመመልከት ከሙታን እና ከመናፍስት ጋር የምትነጋገሩበትን መድረክ አዘጋጁ። መናፍስቱንና ጭራቆቹን ለመቀበልም ንግግርና ድግምት አዘጋጁ። ሊማርኳቸው የሚችሉ፡ ቁሳቁሶችን አዘጋጁ። ሊያዩዋቸው የሚፈጉ ሰዎችን ዝርዝር አውጡ። ሲመጡ ለመቀበል አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጉ / ድምጽ፣ ሽታ፣ በስክሪን ላይ የሚታዩ ምስሎች መብራት ወዘተ.../
- በምናባችሁ ለመከሰት ሞክሩ። የተለያዩ ምስሎችን ከተለያየ ቦታ ሰብስቡ። ኮላጆችና ስኬቾችን አዘጋጁ። ስሪታቸውን /የልስላሴ፣ ሻካራነት፣ ወዘተ. . . መጠናቸውን/ ሽታቸውን፣ የክብደት መጠናቸውን፣ ልኬታቸውን፣የእፍጋት (density) መጠናቸውን አስቡ።
- እንቅስቃሴያቸውን እንደምትከተሉ ሁሉ የተለያዩ የካሜራ እንፃሮችን ሞክሩ። የተለያዩ ድምፆችን ቅዱ፣ የነሱን ድምጽ እና ቅላፄን የሚከተል/ የሚመስል ድምፀታዊ ከባቢ (Sonic atmosphere) ፍጠሩ። ጥያቄዎቻቸውን በጉልህ ፃፉ።
- ከላይ የተዘረዘሩትን አንድ ላይ በማምጣት መናፍስትን የመጥራት ምትሀት፣ ወደፊቱን ለማየት ድግምት እና የምናባዊ ግንኙነት ልምምድ አድርጉ።

(2) See also, Janine Jembere's chapter "Paperlands" in this volume, 121–43.

ADDITIONAL REFERENCES


- Galeano, Eduardo. *The Open Veins of Latin America: Five Centuries of the Pillage of a Continent.* Translated by Cedric Belfrage. London: Monthly Review Press, 1997.
- Tuck, Eve & C. Ree. "A Glossary of Haunting." In *Handbook of Autoethnography.* Edited by Stacy H. Jones, Tony E. Adams, and Carolyn Ellis. Walnut Creek: Left Coast Press, 2013. 639–56.
- Vergès, Francoise. "Like a Riot: The Politics of Forgetfulness, Relearning the South, and the Island of Dr. Moreau." *South Magazine* 9 (documenta 14 #4). Online at: documenta14.de/en/south/25_like_a_riot_the_politics_of_forgetfulness_relearning_the_south_and_the_island_of_dr_moreau.


CREDITS


*Heavy Blood*, by Naomi Rincón Gallardo. HD video, 18'46", 2018. Shot in Vetagrande, Zacatecas, Mexico. Performers: Lady of the Copper Teeth – Bárbara Lázara; Toothed Vaginas Ensemble – Karina Rivera, Azalia Morales, and Rosalba Lira; Hummingbird – Naomi Rincón Gallardo. Lyrics and Texts: Naomi Rincón Gallardo. Musical Composition: Federico Schmucler. Cinematography: Dalia Huerta. Drone: David del Hoyo. Direct Sound: Elda Ortiz y Servando López. Photo documentation: Angélica Canales. Choreography: Marta Sponzilli. Production assistants: Fernando Salcedo and Eric Nava. Masks: Jorge Luis Guerrero and Abelardo Piña. Seamstress: Emilia Robles. Special thanks to the research group FWF/PEEK "DisPossession: Post-Participatory Aesthetics and the Pedagogy of Land." *Heavy Blood* was commissioned by XIII FEMSA Biennial "We Have Never Been Contemporary." Zacatecas, 2019. All film stills and photographs in this chapter: reproduced courtesy of Naomi Rincón Gallardo, the artist.

በአመፀኞች ምድር
በተለየ መንገድ ለመኖር ጥረት
በለውጥ ውስጥ ባሉ ማህበራት
በራስ ገዝ ነፃነት ለመኖር መጠራት



# ብርሃን ነበልባል ጉጉል (ፉልጎር)




ሲልቪያ ዳስ ፉዳስ

አሌንቴዦ/ፖርቹጋል

“በዚያ ምንም ነገር በበፊቱ አውድ አይኖርም። እኛ የስደት ኑሮ ትሩፋት ተካፋዮች ነን።የራሳችን ቋንቋ የራሳችን ነፃነት ያለን ። (ይህንን ነጻነታችንን) በክፍት ቤት እንዲሁም በተዘጉ ደጆች ውስጥ ተለማምደነዋል ። ከሁሉም መንፈሶች ጋር አብረን ኖረናል ። በዚያ አገር የደብዛዛ ድንበሮች እና ገጽታዎችን መጥፋት ጭላንጭል ተመልክቻለሁ።”

— Maria Gabriela Llansol, *The Geography of Rebels Trilogy*

“እኛ በአለም አቀፋዊ የካፒታሊስት ስርአት ሙሉ ለሙሉ የተዋጥን አካላት አይደለንም፤ ሆነንም አናውቅም። ከዚህ ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌለን ሁሉ መኖር የትግላችንን አቅጣጫ ወደ ከባድና አስቸጋሪ ወደሆነው የራስ አገዝ የነፃነት ኑሮ አቅጣጫ ይወስዳል። ሙሉ ለሙሉ መዋሃድን ፍፁም የማይቻል በሚያደርግ የገዢ ስርአት ተፅእኖ ምክንያትም ይሁን ተግዳሮቶቹን ሁሉ ተቀብሎ የራስ አገዝ ነጻነትን መምረጥ ህይወትን በተለየ መልክ መኖርን ይጠይቃል። ይህንንም ኸርበርት ማርኩሰ የተለየ የህይወት ማህበር (“organs for the alternative”) ይለዋል”

— Avery F. Gordon, *The Hawthorn Archive*






አሌቴንዦ በወንዝ ስም የተሰየመ አካባቢ ነው። ከወንዙ ባሻገር ያለውን ቀድሞ ኤንትሬ-ቴዦ-ኤ-ጉዋዲያና የሚባለውን በታጉስ እና ጉዋዲያና ወንዞች መካከል የሚገኘውን የየብስ ክፍልም ያካትታል። ይህ ክልል በደቡብ ፖርቹጋል የሚገኝ ሲሆን በሰሜን የታጉስ ወንዝ በምእራብ የአትላንቲክ ውቅያኖስ በምስራቅ የስፔይን የየብስ ክፍል እና በደቡብ ደግሞ የጉዲያና ወንዝ እና የኤልግሬቭ ክልል ያዋስኑታል። በቫሌ ዴ ሳንቲያጎ በ1917–1918 አንቶኒዮ ጎንዛልቬዝ ኮሪያ በተባለ አናርኪስትና ጓዶቹ ተቋቁሞ የነበረው የራስ ገዝ ዞባ (commune) ተምሳሌትነት በመነሳሳትና ይህንንም በአሁኑ ሰዓት በአሌቴንዦ በምስረታ ላይ ካለ ዞባ ሀሳብ ጋር በማጣመር ይህንን የፊልም ስራ አቀርብላችኋለሁ። በአንቶኒዮ ጎንዛልቬዝ ኮሪያ የተቋቋመው ራስ አገዝ ማህበር “የብርኃን ዞባ” ይባላል። የኔ የምናብና የቀን ህልም ውጤት የሆነው ዞባ ደግሞ “የጉጉል ዞባ”[1] (“የፉልጎር ዞባ”)[2] እለዋለሁ[3]።

ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ “ብርሀን ዞባ” የሰማሁት በ2017 ክረምት ከሳራ ቻንግ ያን ጋር የዞባውን ፍርስራሾች የጎበኘን ግዜ ነው። አንድ በፎርናልሃስ ቬልሃን የሚገኝ ቡና ቤት ገብተን የአካባቢውን ሰዎች ስለ “ብርሃን ዞባ” ጠየቅን። እነሱም ስለ ዞባው የሚያውቁትን እና የሰሙትን ከነገሩን በኋላ ዞባው ወደነበረበት አቅጣጫ አመላከቱን። የዞባውን አጥር ከፍተን ተመለከትን አዳመጥን ከዚያም በጥቁርና ነጭ ፊልም ቀረጽነው። በዚያው አመት በጋ እንደገና ወደ ዞባው ከሊሳ ትሩማን ጋር ተመለስኩ። ነገር ግን ዞባው የነበረበት ስፍራ ለስምንት ግለሰቦች ተከፋፍሎ በእነርሱ ንብረትነት እንደተያዘ ተረዳን። እነዚህን አዲስ ባለቤቶች ከዞባው ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው መሆኑንም ተገነዘብን። ከነርሱ አንዳቸው ይባስ ብለው ንብረታቸውን አቋርጠን ማለፍ ከለከሉን። በዚህም ተስፋ ቆርጠን ወደመጣንበት እየተመለስን ሳለ አንድ ቀጭን መንገድ ላይ እራሳችንን አገኘን። ይህም መንገድ ወደ ትላልቅ መስኮች እና ወዳልጠበቅናቸው ግንኙነቶች መራን።

↑ Frame enlargement from Sílvia das Fadas, *Light, Blaze, Fulgor* (2019) showing a tree shadow at the Commune of Light, Vale de Santiago

1 ጉጉል የሚያበራ ማለት ነው።

2 “ፉልጎር በፖርቹጋልኛ የሚማርክ ደማቅ ብርሃን ማለት ሲሆን ተምሳሌትነቱም ከቀደመው ጊዜ እና ታሪክ የተለየ ዘመንን የሚያበስርና ለግፉአን ያልተጠበቀ እድል እና ግንኙነት የሚፈጥር ዘመን ነው”

3 Sílvia das Fadas, *Auguries for a Non-Hierarchical Framing and Flourishing*; volume in the series "Die Frau mit 50 Füssen," eds. Cristina Gómez Barrio & Wolfgang Mayer (Stuttgart: Akademie der Bildenden Künste, 2019), 33.



↑ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2017) showing the Commune of Light in half-moon and a crack in the ruin's walls

እንደገና በ2018 ከፅኑ አረሞች ቡድን ጋር ወደ ዞባው ተመለስኩ። ከቡድኑ አባላት ጋር ሆነን ከዞባው በአጭር ርቀት ላይ ከሚገኘው ቫሌ ደሳንቲያጎ ከተማ ወደ ብርሃን ዞባ በእግራችን ተጓዝን። ከማንም ተቃውሞ ሳይገጥመን ዞባው ወደ ነበረበት ስፍራ ገብተን ቁጭ ብለን አወራን ፀሃይ እስክትጠልቅም በዚያው ቆየን። ስለ መጪው ዘመን ምልክት ለማግኘት ወደ ዞባው እንደገና በ2019 ተመለስኩ። በዚህ ጊዜ ሮበርት ብራት አብሮኝ ነበር። ሮበርት የዞባውን ፍርስራሾች ድምጽ ሲቀዳ እኔ ደግሞ በሁለት የፊልም ጥቅል (አንዱ ጥቁርና ነጭ ሌላው ደግሞ ባለቀለም) በመጠቀም የምስል ቀረፃ አደረግኩ። በዞባው ሆነንም በባታልሃ የአናርኪስት ጋዜጣ እንደገና የጎንዛልቬዝ ኮሪያን ደብዳቤዎች ጮክ ብለን አነበብን። በዞባው በተመለስኩ ቁጥር የማውቀውን ያክል ታሪኩን ለሌሎች እናገራለሁ። ዞባው የነበረበትን ስፍራ ጥሰን በገባን ቁጥር ዞባው የተመሰረተበትን ሃሳብና መንፈስ እንዳከበርን ይሰማኛል። ይህን ባደረግን ቁጥር ዞባውን የአናርኪስት ማህበሩን አባላት፥ ስምየለሽዋን ሴት፥ በተመሰረተ በጥቂት ግዜያት የፈረሰውን እና በዞባው ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች እየዘከርን ነው ብዬ እስባለሁ።

ከዞባው ፍርስራሽ ተነስቼ በህይወት ያጌጠውን ክልል ወንዞቹን፥ ዛፎቹን፥ ድንጋዮቹን ህይወት ያላቸውን ሁሉ ነገሮች ተከትዬ በእግሬ ተጓዝኩ። ንጥቂያ የሌለበትንም ነገን በምናቤ ሳልኩ፥ ተመኘሁ፥ ተነበይኩ። ብሎም ከሌሎች ጓደኞቼ እና የማንተዋወቅ መንገደኞች ጋር በመሆን አንድ ዞባ መገንባት ጀመርን። ይህን ዞባ የኛ ባልሆነ ቤት ውስጥ የፅናት መንፈስን እና እንግዳ ተቀባይነትን ባስተማረንና በለገሰን አንድ ሰፈር ውስጥ መሰረትን። ለእኔም ከዛ ጊዜ ጀምሮ ፊልም መቅረጽ ከእለት ተእለት ህይወቴ ጋር የተቆራኘ ተግባር ሆነልኝ።

የፊልም ሰሪዋ “እኔ” ወደ ተስፋን የሰነቀ “እኛ” በፊልሙ ሂደት ይለወጣል። ፊልሙ ስለምን እንደሆነ ምን ሊሰራ እንደሚችል አናውቅም። ይህም የመጀመሪያው የለውጥ ሂደት (Metamorphosis) ነው። ሌሎችም ይከተሉታል።





↑ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2019): Way of the trees in Arraiolos; Way of the river in Troviscais; Way of the stones in Cromeleque dos Almendres; Stone's Drawing in Mina de São Domingos; Way of the serpent in Pego Ferreiro; Way of the sea; Fishermen's Trail; and, The no way of extraction in Zambujeira do Mar










↑ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2018 and 2019): Sever River and Flauta de Luz, both in Pego Ferreiro; Cork Trees in Arraiolos; and, Girl with Mask at the Fair of Joy in São Luís

ብርሃን፥ ነበልባል፥ ጉጉል ሙከራ ነው። የተለዋጮች (Mutants) እና የለውጥ ሂደት (Metamorphosis) አካል ነው። በምኞት የሚመራና የሚዘወር የህይወት ልምምድና ክዋኔ ነው። የስልጣን ተዋረድና ልዩነትን ለመደምሰስ የሚደረግ ሙከራ ነው። ሙከራው የሚመጣው ግን ከአንድ የአለም ክፍል ነው። ከቁርጥራጮች ህልውና ካላቸው አካላትና ከተፈጥሮ የተውጣጣ የጎንዮሽ ጥናት ውጤት ነው። አንዳንዶቻችን ይህ ሙከራ ከሚደረግበት የአለም ክፍል የመጣን አይደለንም ነገር ግን በአመጸኛ ምህዳሩና በውስብስብነቱ እንከየፋለን። የጉጉል ዞባ የሚወለደው ከአቅምና ከጉልበት መስክ ነው። ውልደቱም ቅጽበታዊ፣ ከቁጭትና እምቢተኝነት፣ ድህነትን፣ ንጥቂያን፣ብዝበዛን ከመታገል ጠንካራ ስሜት እና ያለፈውን እንደገና ለመኖር ከመወሰን የሚመጣ ፍላጎት ነው። እዚህ ክልል ውስጥ የማያቆም የሃይል እርምጃ፤ ረጃጅም አጥሮች፣ የግል ንብረቶች፣ የመአድን ፕሮጀክቶች፣ የቀነጨሩ አየሩን፣ አፈሩን፣ ውሃውን የሚበክሉ የእይታ አድማሳችንን የሚያጣብቡ የመቃብር ቦታ የሚመስሉ ኦሊቮች፣ አልመንዶች፣ የስደተኛ ወረቀት የሌላቸው ሰራተኞች፣ ዘረኝነት፣ የተመረዙ ወንዞች፣ የተራቆቱ



የተሸረሸሩ መሬቶችን እናያለን። ሆኖም ከዚህ ሁሉ የነጠቃ ስርአት ጎን ለጎን በጎ ህይወትን ለመምራት የሚደረግን ጥረት እናገኛለን። ይህን ጨካኝ ስርአት ለመሞገትና ለመገዳደር እራሳቸውን በአዲስ መልክ ለመፍጠር የሚሞክሩ አካሎች (Bodies) እናገኛለን። እነዚህ ግፉአን አካላት ከመሬት ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች ያጠናክራሉ፣ ይህን በማድረግም ግዞት፣ ንጥቂያን ላለመቀበል እራሳቸውን ያዘጋጃሉ። ነቀላን፣ አለማብቀልን፣ አለመትከልን ይቃወማሉ፤ ማህበራቸውንም ያጠናክራሉ። የራስ አገዝ ዞባዎቻቸውንም ይገነባሉ፣ እራሳቸው ያበቀሉዋቸውን ዘሮችም ያሰራጫሉ፣ ግጥምን ይተረጉማሉ፣ እንግዳ ተቀባይነትን ይለማመዳሉ። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ግን በነጣቂው ስርአት ውስጥ ለመሆን እየተገደዱ ባለበት ሁኔታም ጭምር ነው። አቨሪ ጎርደንን በመጥቀስ ያህል "ነፃነት ለባርነት የማይዳረጉበት አሰራርን የሚያዳብሩበት ሂደት ነው።"[4] አብሮነታችን ህይወትና አለምን በመስራት ክር የተገመደ "የተግባር እርምጃን የርስበርስ መረዳዳትን እና የመጪውን አለም ማህበር የሚተልም ፖለቲካን (አርቆ) የሚመለከት ነው።"[5] ልምምዳችንን በቅርብ ግዜ የነሸጡ እና ያገዙ በአሌንቴጆ የታተሙ ሶስት ስራዎች ጆርና ማፓ፣ ፍላውታ ደሉዝ እና አይዴያ ናቸው። እነዚህ ስራዎች አመጸኛ የሆኑ የአለም አቀፋዊነት ዘርን በመርጨት ሰዎች ለተግባር እንዲዘጋጁ ንቃተ ህሊናቸውን አሳድገዋል። ከእነዚህ ትግሎች እና ሃሳቦች ጋር ልዩነታችንን ጠብቀን አጋርነትን እንመሰርታለን። የምንመሰርታቸው አብሮነቶች እና ትብብሮች በእሴት ላይ የተመሰረቱ ዝምድናዎች ናቸው። አንዱ ትብብርና ግንኙነት ወደ ሚቀጥለው ይመራል። ወዳጅነትና ባልንጀርነትንም ያዳብራል። ይህን ወዳጅነት እውቅና በመስጠት እና በማጤን ፊልማችን ውሉን ይከተላል።

እንዘጋጃለን! ፍሬድ ሞተን እንደሚለው "በመሰራት ላይ ያለውን ልናየው የመጣነውን እያየን መቆየት እንፈልጋለን። ክህሎት፣ችሎታ አይቆሙም ግን የሁላችንም የሆነው "የኔ" የኛ ይሆናል። የጋራ ይሆናል።"[6] ፊልማችን በመሰራት ያለ፣ የሚቀጥልና ለወዳጅነት፣ ለባልንጀርነት ምስረታ መሳሪያ ሆኖ በጋራ እንዲያገለግል የተሰራ ነው። ፊልሙ የተለያዩ አቅጣጫዎችን ይይዛል በጉጉል (በደማቅ መብራት) እየተመራ ያልተጠበቀ አቅጣጫ እየወሰደ ለስልጣን ተዋረድ ቁብ በሌለው ማእቀፍ ውስጥ ሆኖ የማበብና የማደግ እድል ይኖረዋል።

የራስ አገዝ ስልተ-ምርት እና ስርጭትን እንለማመዳለን በተግባር ላይም እናውለዋለን። ፊልሙን የመቅረጽና አርትኦት የማድረጉን ሂደት በተቆራርጠ የድርሰት ጽፍሁ በቅድሚያ ባልተዘጋጀበት መንገድ የሚከናወን ይሆናል። የፊልም ስራው ሂደት እንክብካቤና ዋጋ የመሰጣጠት ግንኙነት ላይ የተመሰረተ እንዲሁም ብሬሰን እንዳስተማረን[7] ባለማወቅና በከፍተኛ የማወቅ ፍላጎት ላይ የተገነባና ያልተጠበቀ ውጤትን ለማየት ድፍረት ያለው ነው። ብርሃን፣ ነበልባል፣ ጉጉል የሚቀርበው በተለያዩ አውዶች ውስጥ ይሆናል። በሲኒማና ቲያትር ቤቶች ውስጥ እና ውጪ፣ በመስኮች፣ ሰዎች በማይኖሩባቸው ወይንም በማይጠቀሙውዋቸው ህንጻዎች፣ በሰው ሰራሽ ዋሻዎች (Grottos)፣ በተለያዩ የግል እና የህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች፣ በጨለማ እና ከውድድር ገበያው ውጪ ባሉ የተለያዩ አውዶች ውስጥ ይቀርባል። በሂደት ላይ ያለው ይህ ፊልም ጊዜያዊ ደማቅ ራስ አገዝ ህብረቶችን የመፍጠር እምቅ ሃይል እና ከሌሎች ተመሳሳይ ማህበራት ጋር የሚናበብ ተሞክሮ ልምምድ ይኖረዋል።

መጠበቅ አቁመናል። አሁን በሚለመልም መንገድ እየኖርን ነው። ይህም ሁለተኛው የለውጥ ሂደታችን ነው። ሌሎች ይከተላሉ።

4 Avery F. Gordon, *The Hawthorn Archive: Letters from the Utopian Margins* (New York: Fordham University Press, 2018), 49.

5 Simon Springer, *The Anarchist Roots of Geography: Towards Spatial Emancipation* (Minneapolis: University of Minnesota Press, 2016), 94.

6 Fred Moten, "Come On, Get It!," *The New Inquiry* (19 February 2018); online at: thenewinquiry.com/come_on_get_it.

7 Robert Bresson, *Notes on Cinematography* (New York: Urizen Books, 1977).








# የእግር መንገድ እንደ ዝግጅት መሳሪያ

ብዙ ጊዜ በእግሬ እንዳልሄድ ተነግሮኛል። ሩቅ ነው፣ አደገኛ ነው ወይም እንደሴት በእግሬ በመሄድ ጥቃትን በራሴ ላይ እንደምጋብዝ ተመክራያለሁ። ከሊዝበን (ፖርቹጋል) ወደ ሎስ አንጀለስ (አሜሪካ) ከሄድኩ በኋላ ግን የእግር መንገድ እራስን የመግለጫ መንገድ እንደሆነ ተገነዘብኩ። በእግር መጓዝ በዚህ ብዝሃ አቀፍ አለም የራስን ቦታ የማግኛ መንገድ እንደሆነ ገባኝ። በአሁኑ ጊዜ አሌንቴዦ ብሰራም ከዚያ አካባቢ አይደለሁም። ሆኖም በዚያ በእግር መጓዝን መርጫለሁ የስሜት እና አካል መግለጫ ዘዴ አድርጌም ተቀብየዋለሁ። በዚህ ዘዴ ከመሬት ጋር ያለኝን ትስስር እና ከእርሷ ምን ልማር እንደምችል ግንዘቤን አግኝቻለሁ። ለመሬት አይነተኛ ትኩረት በመስጠት መሬት ላይ እየደረሰ ያለውን ገፈፋ እና ብዝበዛ እንዲሁም መሬት የምትሰጠውን ብዝሃ ህይወት ተገንዝቤያለሁ። ብቻዬን ቪዲዮ ካሜራና ድምጽ መቅረጫ ይዤ በእግር በመንቀሳቀስ በቅርብ ግዜ ከ”እኔ”ነት ወደ “እኛ”ነት እንደምለወጥና የሰዎች የመናፍስት እና የሌሎች ፍጥረታትን ማህበርን እንደምቀላቀል ተረድቻለሁ።

ምንም እንኳን በአንድ አይነት መንገድ ባይሆንም የእግር ጉዞ በየቀኑ ሊደረግ የሚችል በየትኛውም ከተማና መልክአ ምድር ላይ ሊከናወን የሚችል እንቅስቃሴ ነው። የእግር መንገድ በአንዳንድ አካባቢዎች ነጻነትን የማወጃ መንገድ ተደርጎ ቢታይም በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ አደጋን ሊያስከትል የሚችልና በጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባ እንቅስቃሴ ነው። የእግር ጉዞ በየእለቱ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፤ ነገር ግን ሆን ብለን እና አቅደን የሚያመጣውን ስሜት ከተላበስነው (Intentionally embody) የአብሮነት ፖለቲካን የምንከውንበት መሳሪያ ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው ብቻዋን ወይም ከሌሎች ጋር በእግር ልትሄድ ትችላለች። ሰዎች ከመሬትና ከሌሎች ሰዎች፣ በአንድ ተልእኮ ወይንም በሲቪል አመጸኝነት (Civil disobedience) ከሌሎች ጋር በአጋርነት ወይም አብሮ በመሆን (Co-presence) በእግር መግዋዝ ይችላሉ። ሰንድበርግ የተባሉ ሰው እንደሚሉት አብሮ በእግር መጓዝ “የአጋርነት የመረዳዳት እና የውለታ፣ የመደማመጥ፣ የመነጋገር እና የማድረግ ዘዴ ነው። ከነባር (Indigenous) ማህበረሰቦች ጋር ግንኙነት እና መስተጋብርን ለማጎልበት የሚደረግ የእግር መንገድ ደግሞ ሰዎችን ምሁራዊ የፖለቲካ ማንነት ያላቸው እና ዓለምን በመስራት ገቢር ላይ ባልደረቦቻችን አድርገን እንድናውቃቸው ያደርገናል። የእግር ጉዞን እንዴት አይነት የግንኙነት ዘዴ ሊከተል እንደሚሻ ግን ከሰው ሰው የተለያየ ሊሆን ይችላ።”(1)

ይህ ፕሮጀክት እንደጥናት ልምምድ ስለ እግር መንገድ ከገጣሚዎች፣ ከቀን ህልመኞች፣ ከአመጻኞች፣ ከመብት ተሟጋቾች፣ በእግራቸው ሮጠው ካመለጡ ባሮች፣ ከወንበዴዎች፣ ከማሪን ማህበሮች፣ ከሱሪያሊስቶች፣ ከሲትዌሽኒስቶች ተምሮዋል። ከStalker-Observatoir Nomade ከተባሉ በጋራ የከተማዎችን ድሃና አሳቻ ስፍራዎችን በእግር ከሚጓዙ ቡድኖች፣ እንደ “Walk exchange” ያሉ የእግር መንገድ ፕሮጅክቶች (እነዚህ የእግር ጉዞ አስተምህሮ ዘዴን እና የእግር መንገድ ጥናት እና ስልጠና የሚያዘጋጁ፣

Walking lab ከሚባሉ ያልተለመደ አይነት የእግር ጉዞ ዘዴዎችን ከሚያዘጋጁ የረጅም ጊዜ ጥናት ቡድን፣ ከፌሚንስት ኒው ማቴሪያሌዝም (Feminist new materialism) ከኩዊር ቲዎሪ፣ ከክሪቲካል ሬስ ቲዎር አብርሆትን አግኝቷል።

በመጨረሻም የእግር መንገድ ጥናታችን አንድ ላይ ተሰብስበው የእግር ጉዞ በማድረግ ሰልፍ፣ ተቃውሞና አመፅን ባካሄዱ ሰዎች ተበረታትቷል/ተነሳስቷል። የእግር መንገድ እንደ ተቃውሞ ዘዴ በሴቶች ትግሎች ዘንድ የሚነሳ የልምምድ ዘዴ ነው። የፊልም ምሁሯ ትሪንህ ቲ ሚንህ-ሀ እንደምትለው የእግር መንገድ ከሃሳብ ባለፈ ፈጠራን የተመላ የአካል ገለጻ ስለሆነ በክዋኔ “የተሰወሩትን” የሚቀሰቅስ ልምምድ ነው ትለናለች። (2) የእግር ጉዞ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:- Algerian Mothers of the Disapproved (የአልጄሪያ የተሰወሩ ልጆች እናቶች)፣ Las Maders de Plaza Demogo (በስፔን ስልጣንን የጠየቁ እናቶች)፣ በአሜሪካ የአፍሪካ-አሜሪካዊያን ሴቶች በሞንትጎመሪ ተቃውሞ አውቶብሶች ላለመሳፈር በማቀድና በማደራጀት የዘር አድሎን ተገዳድረዋል።

የእግር መንገድ ክዋኔን በመላበስ የሚገኝ ምናባዊ ምስልን፣ ንግግርን እና ግንኙነትን በተግባር የመትከልና የመተርጎም እንቅስቃሴ ነው። በግንኙነት ላይ የተመሰረተ ስሜታዊ ልምምድ ነው። የእግር ጉዞ ከሰዎች ባሻገር ያሉ ህልውናወችን በማወቅ ላይ የተመሰረተ ተግባር ነው። የምንራመድበትን መሬት ካወቅነው እና ከተንከባከብነው እንጠብቀዋለን። የእግር መንገድ አይነተኛ የሆነ የዝግጅት ተግባር ነው። የመጥፋት አደጋ ለተጋረጠበት ነገ አይነተኛ መሳሪያ ነው።

(1) Juanita Sundberg, “Decolonizing Posthumanist Geographies,” *Cultural Geographies* 21, no. 1 (2014): 33–47; doi: 10.1177/1474474013486067.
(2) Trinh T. Minh-ha, *Lovicidal: Walking with the Disappeared* (New York: Fordham University Press, 2016).



↻ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2019): A walk with the Willful Weeds Research Group in the almost empty dam of Monte da Rocha (left page) and evidence of a severe drought in Alentejo (right page)





ገቢር

# እንደገና ይራመዱ

በእግራችሁ ሂዱ። በመራመድ ውስጥ ያለው የእውቀት ፍለጋ በመንፈስ ይምራችሁ፤ ለተፈጥሮ እና ለተለያዩ የሃይል ግንኙነቶች ትኩረትን ስጡ። ለእግር መንገዳችሁ የሚያስፈልጓችሁን ነገሮች እንደየ ሁኔታው ሊለያዩ ይችላሉ። ስለዚህ የሚከተሉትን መመሪያዎች ከግምት ውስጥ ክተቱ። ዝርዝራቸውንም አዘጋጁ፡-

- የምትደርሱበትን ቦታ ብዙም ሳታስቡ የእግር መንገዳችሁን የምትጀምሩበትን ቦታ ወስኑ
- በእግር ጉዟችሁ ብዙ ነገር አትያዙ መሮጥ ካስፈለጋችሁ በነጻነት እንድትንቀሳቀሱ
- ጥልቅ የእግር ጉዞ ትኩረትን እና ጥልቅ ማዳመጥን ስለሚሻ ህዋሶቻችሁን አንቁ
- የምትራመዱበት ሁኔታ ለደህንነታችሁ አስጊ ካልሆነ የቀን ህልም ለማለም ራሳችሁን ክፍት አድርጉ። ጉዟችሁ ስለሚወስደው ሠዓት ብዙ አትጨነቁ።
- በእግር መንገዳችሁ ስለ ቁሶች ለአፈሩ፣ ለዘሮች፣ ለዛፎች፣ ለአሸዋው፣ ለኮብል ድንጋዩና አስፋልቱ ትኩረቱ ስጡ
- ለአካላችሁ እና ስጋ ለበስነታችሁ አትኩሮት ስጡ
- እርሳስ ፣ ወረቀት እና የማስታወሻ ደብተር ያዙ። ስእልም ሳሉ

በእያንዳንዱ እርምጃችን አለሙ ወደኛ ይመጣል
በእያንዳንዱ እርምጃችን አበባ በእግራችን ስር ታብባለች
በእያንዳንዱ አርምጃችን ማንነታችን ይከፈትልናል
የአለሙን ስጦታዎችንም እንቀበላለን
እንዴት በአዲስ መንገድ እንደምንራመድም እንማራለን።
— Trinh T. Minh-Ha & Jean-Paul Bourdier, “L’autre marche / The Other Walk”



ገቢር

# እራስን ለመግዛት መራመድ

- በምድር ላይ በወፍ ዘራሽ የሚበቅሉትን አዝርዕት ለማወቅ እና እነርሱንም ለመለየት በእግር መጓዝ
- የእግር ጉዟችሁን አካባቢውን እና በመስክ ላይ የሚበቅሉትን አዝርዕቱን ከሚያውቁ ሠዎች/ሠው ጋር አድርጉ። አለዚያም ስለዚህ ጉዳይ የሚያስተምራችሁ መፅሀፍ ያዙ
- ከአደጋ ወይም ከጥቃት መከለላችሁን ካረጋገጣችሁ አጥሮች፣ ድንበሮች፣ የግል ንብረቶችን ጥሳችሁ አቋርጡ
- የሚበሉ ፍራፍሬዎችን ልቀሙ በህብረት የምትመገቡትን ምግብ አዘጋጁ
- ይህንን በሌላ የዓመቱ ወቅት እንደገና ድገሙት
- የራስዎን አካል እና የሰውነት አካልነት ከግምት ውስጥ ያስገቡ።
- አንዳንድ ሊሆኑ የሚችሉ ቀጣይ ደረጃዎች፤ የአትክልት ስፍራን ማደራጀት ይጀምሩ፣ ወይም ክሬ የዘሮችን ክበብ በሉ; የአካባቢ ዘሮችን በመሰብሰብ፣ በመዝራት፣ በማፅዳት፣ በመለየት፣ በማከማቸት እና ዘሮችን ከሌሎች ጋር በመጋራት ይማማሩ።



↑ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2019): Corema album or the edible and almost extinct Portuguese Crowberry Shrub in Zambujeira do Mar





ገቢር

## ለመጠገን የእግር መንገድ

- የእግር ጉዞ በምታደርጉበት አካባቢ ያሉ በግንባታ የተደመሠሡ ሠፈሮችን (gentrified neighborhoods)፣ የተበከሉ ወንዞችን፣ ነዳጅ የሚወጣባቸውን ስፍራዎች፣ የማዕድን ቁፋሮ ቦታዎችን፣ ወንዞችን እና አንድ ተክል ብቻ የሚበቅልባቸውን መስኮችን (monoculture fields) እና የመሳሰሉትን የመነጠቅ ምልክትና ሁኔታዎችን ለዩ
- ለእግር ጉዞ የመረጣችሁትን ስፍራ የሚያውቁ የተለያዩ ሰዎችን ለጉዟችሁ ጋብዙ
- ዋና ዋና ቦታዎች ላይ ቁማችሁ አካባቢውን አስተውሉ። ማለፍ ካለባችሁ ጥላችሁ እለፉ፤ ግን እራሳችሁን እና ሌሎችን ለአደጋ እንዳታጋልጡ ጥንቃቄ ውሰዱ
- እንዴት ለአደጋ የተጋለጠውን ስነ-ምህዳር እንደምትንከባከቡና እንደምትጠብቁ በግል እና በህብረት አስቡ ተወያዩም
- ከአካባቢው ጉዳት ባሻገር ያልተነገሩ፣ የታፈኑ የፅናት፣ የተጋድሎና የትቃውሞ ታሪኮችን ፈልጉ። እነዚህንም ታሪኮች አሠራጩ
- አንዳንድ ሊሆኑ የሚችሉ ቀጣይ እርምጃዎች፤ የጋራ እርምጃ መውሰድ፣ ሁለቱንም ፈውስን እና አረመኔነትን ከግምት ያስገቡ።





“በአሁኑ ጊዜ የዓለም መልከዓ ምድሮች በፍርስራሾች የተሞሉ ናቸው። ሆኖም እነዚህ አካባቢዎች እየሞቱ እንደሆነ ቢነገርም አሁንም ህይወት አላቸው። ሠዎች የማይኖሩባቸው መስኮች አንዳንድ ጊዜ ብዝሃነት ያላቸው ህይወቶች እና ባህሎችን በውስጣቸው ይዘው ይገኛሉ። እንዲህ ባለ የተጐዳ አለም ህይወትን በፍርራሾች መሀል ከመፈለግ ውጪ ሌላ አማራጭ የለም። የመጀመሪያ ተግባራችን የማወቅ ፍላጐትን መቀስቀስ ነው። በልማት ትረካዎች ሳንዋጥ ቋጠሮዎችን እና የልብ ምቶችን በየቀዳዳው መፈለግ ያሻናል።”

— Anna Tsing, *The Mushroom at the End of the World*

↖ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2018): Ruins of the railway workshops in Mina de São Domingos; toxic waters of the open-cast pit in Mina de São Domingos; and, a dead bird

መሳሪያዎች

# ተንቀሳቃሽ ሲኒማ

ተንቀሳቃሽ ሲኒማ የተፈለገበት ምክንያት የፊልሙን የለውጥ ሂደት ለሌሎች ለማሳየትና ለማጋራት ከመነጨ ምኞት ነው። ይህ ብርሃን፣ ነበልባል፣ ጉጉል የተባለ ፊልም የመጨረሻ ውጤት ለአሌንቴዦ ሠዎች እና ማህበረሠብ የቀረበ እነርሱንም ቃለ መጠይቅ በማድረግና በመቅረፅ የተዘጋጀ ነው።

በሶስተኛው የሲኒማ (Third Cinema) እንቅስቃሴና በነፃነት ትግል ዘመን የሲኒማ መፈንጠቂያን (Projector) ይዞ ሲኒማ ወዳልደረሠባቸው ቦታዎች መሄድ የተለመደ ነበር። የፊልም ስብስቦች/ቡድኖች (collectives) በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ ይህንን መሣሪያ ወደተለያዩ ቦታዎች በመውሠድ ውይይትን በመቀስቀስ ለስር ነቀል ለውጥ አስተዋፅኦ ያበረክቱ ነበር። በዚህ ረገድ የለንደን የሴቶች የፊልም ቡድን በ1970ዎቹ፣ የአጋዋ ሺንሱኬ ስብስብ (1967-1987) እና የግሩፖ ዜሮ በፖርቹጋልኛ ቋንቋ የተዘጋጁ ፊልሞችን በማቅረብ ለነፃነት ትግል አስተዋፃኦ አድርገዋል። እንደሚያድጉ አረሞች ተንቀሳቃሽ ሲኒማ በከተሞች፣ በአደባባዮች፣ በአትክልት ቦታዎች፣ በመስኮች፣ በመሸታ ቤቶች ፣ በማህበራት፣ በማዕድን ማውጫ ስፍራዎች፣ በሠው ሠራሽ ዋሻዎች፣ በበረቶች፣ በድልድዮች ፣ ለጋራ ጥቅም በሚውሉ ስፍራዎች እና በተተው ህንፃዎች ፍሬን የማፍራት እና የመባዛት እምቅ ሀይል አላቸው። በቤት ውስጥ በኮምፒውተር ስክሪን፣ በስልክ እና ቴሌቪዥን የምናገኘው ሲኒማ በተለይም ሲኒማን በጋራ፣ በማህበር ከመመልከት አንፃር ሲታይ የመነቀል እና የመለየት ተምሳሌትነቱ የጐላ ነው።

ተንቀሳቃሽ ሲኒማ ስፋት ላለውም ሆነ በትንሽ ስፍራ የሚደረግን ውይይት በመቀስቀስ፣ በህብረት ተሠብስበው ለሚገኙ ሠዎች ማቅረብና ማሠራጨት ሠዎች ሀሳባቸውንና ተቃውሟቸውን እንዲያደረጁና እንዲገልፁ ያስችላቸዋል። የፊልሙ ይዘት ሠዎች በአካባቢያቸው አንገብጋቢ ነው ብለው የሚያስቡትን ስራ የውሃ፣ የመሬት ነጠቃ፣ አድሎ እና የመሳሠሉትን ጉዳዮች የሚያነሳ ሊሆን ይችላል። ተንቀሳቃሽ ሲኒማ የሲኒማ ተመልካቾች የማንነት ስሪት ላይ ከፍተኛ ትፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ብሎም ልማዳቸውን የመለውጥ አቅም እንዳለው እናምናለን። ከዚህም ባሻገር የሲኒማ ምናባቸውን በማሳደግ ምንም እንኳ በጊዜያዊነት ቢሆንም የጐንዮሽ ግንኙነታቸውን ሊያዳብር ይችላል። ሀሳባቸውን እና አላማቸውን እንዲጋሩም ያግዛቸዋል።





ገቢር

# ወፍ ዘራሽ ሲኒማ

ተንቀሳቃሽ ሲኒማ ቅፅበታዊ እና ከሠዎች እና ከስፍራዎች ጋር ቀጥተኛ አጋርነትና አብሮነትን ሊፈጥር ይችላል።
ተቀባይ:- ማንኛውም ሰው ተጋብዟል

ዝግጅት

- የፊልም ማስፈንጠሪያ ወይንም ማጫወቻ ያለው ዲጂታል ማስፈንጠሪያ
- ማስፈንጠሪያው የሚቆምበት ነገር
- ድምፅን የሚያጐላ መሳሪያ
- ተንቀሳቃሽ ስክሪን፣ ነጭ ግድግዳ ወይንም ነጭ ወረቀት
- መቀመጫ ወንበር ፍራሽ የእህል ጆንያ/ማዳበሪያ
- ፊልሞች



ክፍል አንድ

ወፍ ዘራሽ ሲኒማው የሚታይበትን ቦታ ማዘጋጀት፣ ቁሳቁሶችን ለመውሠድ መኪና ወይም ማንኛውንም የዕቃ ማጓጓዣ ማዘጋጀት

ክፍል ሁለት

ፊልም በምታሳዩበት ቦታ አጋርና ደጋፊዎችን ፈልጉ። ለአካባቢው አግባብ የሆነ እና ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ግንኙነት ያለው ፊልም ምረጡ። በስማ በለው እና የሚስብ ማስታወቂያ በመለጠፍ ፊልሙን ሠዎች እንዲመለከቱት ጋብዙ። አንድ ወይም ብዛት ያላቸውን ፊልሞችን አሳዩ። ውይይትን አበረታቱ። የሠዎችን የተለየና የተቃውሞ ሀሳብ አስተናግዱ። ከተቻለ ምግብና መጠጥ በጋራ ተካፈሉ።

ክፍል ሶስት

ይህን ሌላ ቦታ ድገሙ። ፊልሙ ወደታየባቸው ቦታዎች በመደበኛነት ተመላለሡ።

ሊታሠብባቸው የሚገቡ ነገሮች

ፊልም ለማሳየት ተቋማዊ በሆነና ውስብስብ ዝግጅትን በሚጠይቅ (ከቀበሌ አስተዳደር ከፊልም አከፋፋዮች ጋር ውል መፈራረም እና የተለያዩ አስተዳደራዊ ደንቦችን በማድረግ) መሰናዶና ወፍ ዘራሽና ቅፅበታዊነት ባለው መንገድ፤ እንዲሁም ከሠዎችና ከቦታ ጋር አጋርነትን ለመፍጠር የሚሞክር ሲኒማን በማሠናዳት መካከል ምርጫ ማድረግ ያስፈልጋል።



↻ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2019): Impermanent Location of Commune of Fulgor, Troviscais; a fig leaf with food in São Luís; and, dwellers of Troviscais (Mr. Heliodoro, Mrs. Jozilia & Mr. Lebrinha) at Café Santa Bárbara







መማሪያ

# መጠባበቅ (Anticipation)

የዚህ መማሪያ ዋና ግብ በሂደት ላይ ያለ ህይወትንና እዚሁ በመሃላችን ያለን አለማዊና የሚያብብ ህይወትን መጠባበቅ (anticipation) ነው። ይህ መማሪያ በመሃላችን ያሉ ግን ደግሞ ሁልጊዜ ግልፅ ያልሆኑ ነገሮችን እንድናስተውልና ሳናስበው የሚፈነዳ እና በለውጥ ሂደት ላይ ያለውን የነባራዊውን አለም እይታችንን የማብራት (የማድመቅ) ሀይል አለው። በማህበራዊ ትምህርት ውስጥ ብዙ ቅፅበታዊ ውልደቶች (improvisations) እና ጊዜያዊ ምልክቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በመሆኑም መጠባበቅ ለ____________________ __________ መዘጋጀት ነው። መጠባበቅ በኤቨሪ ኤፍ ጎርደን (በኽርበርት ማርኩሠ አማጭነት) ቃላት “የተለየውን አማራጭ ለማግኘት አካላትን ማብቀል” (3) ነው። ይህን ሁኔታ ጊብሰን ግራሃም ደግሞ “በማናገር ወደ ህይወት ማምጣት” (4) ይለዋል። እኔ ደግሞ የመጪውን ጊዜ ድምፅ መፈለግ (searching for auguries) እለዋለሁ።

የመጪውን ዘመን ድምፆች ከመልክዓ ምድሩ በመቅዳት እኛ ለይተን የምናያቸው የምናናግራቸው፣ የምናቅዳቸው፣ የምናመርታቸው፣ የምንፈጥራቸው ምስጢራዊ ምልክቶት ናቸው። ሌሎችም ሊለዩዋቸውና እውቅና ሊሠጧቸው ይቻላቸው ይሆናል። የመጪው ዘመን ድምፆች ከአማራጭ ኢኮኖሚዎች እና የራስ አገዝ ልምምዶችና ተግባሮች ጋር ሊያያዙም ይችላሉ። ለምሳሌ ወንበዴዎች እና አርብቶ አደሮች ምልክቶችን ለጓደኞቻቸው ይተዋሉ - እዚህ ጋር ያለውን ውሃ መጠጣት ትችላላችሁ፣ እዚህ ጋር መጠለያ ታገኛላችሁ፣ እዚህ ያለው ፖሊስ ጨካኝ ነው ወዘተርፈ። እነዚህን የመሠሉ የመጪው ጊዜ ምልክቶች አለምን የመስራት ልምምዶች የተከለሉ ፅሁፎች እና የታመቀ ሀይል ያላቸው የግፉአን ታሪኮች ናቸው።

(3) Avery F. Gordon, *The Hawthorn Archive: Letters from the Utopian Margins* (New York: Fordham University Press, 2018), 375;

(4) J.K. Gibson-Graham, “Imagining and Enacting a Postcapitalist Feminist Economic Politics,” *Women’s Studies Quarterly* 34, no. 1/2 (2006): 72–8.





↑ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2018): Auguries I, Vale de Santiago; Auguries II, Arneiro; Auguries III, Panóias; Auguries IV, Arneiro; Auguries V, Ourique

ጥንቆላ፣ ሰዋዊ ያልሆኑ የሠው ልጅ ፍርሀቶች
ይህ የመዝሙሮች ድርድርና ርቀት
በመአከሉ ተሰራጭቶ፤ የህግ አይነቶች
ነዋሪውን ለመግደል፤ በጊዜ የሚገጥሙ ርቀቶች።
ፍርስራሾች መከለያ ናቸው፤ መዝሙሮች ደግሞ
አጥንቶች።

— Sean Bonney, *Our Death*



Activity

# ደብዳቤ እንደ ቀስት

ደብዳቤ ቀስት ነው:- ስጦታ--የጊዜ አንክብል። አድርጐትን (agency) ይሸከማል። አንድን ሠው ወይም አንድን ነገር ለመድረስ ያለን ፍላጐት ያሳያል። ይህ ደብዳቤ የመፃፍ ልምምድ ምን አይነት አለም ውስጥ ለመኖር እንደምትፈልጉ፣ እንዴት መኖር እንደምትሹ እና ይህንንም አለም/ህይወት በመጠበቅ መንፈስ ሆናችሁ በተቻላችሁ ዝርዝር እና ግልፅነት የምኞት አለም እንድትገልፁ ይረዳል።

ተቀባይ:- የቀን ህልም አላሚዎች፣ ትሁት የማይኮፈሱ ሠዎች እና በእነዚህ አይነት ሠዎች መሃከል ያለ ማንኛውም ሠው።

ዝግጅት
ደብዳቤዎቹ ከሚከተሉት በየትኞቹም መንገዶች ሊቀርቡ ይችላሉ- በፅሁፍ፣ በስዕል፣ በተቀረፀ ድምፅ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል። እንደምትመርጡት አይነት ደብዳቤውን የማቅረቢያ ዘዴ ወረቀትና እስክሪፕቶ፣ ድምፅ መቅረጫ፣ ካሜራ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ኮምፒውተር እና የመሳሰሉት ሊያስፈልጉዋችሁ ይችላሉ።

ክፍሎች

- ደብዳቤዎች ምን አይነት ቃላትን መምረጥ እንደሚፈልጉና ደብዳቤውን ለማቅረብ ተገቢውን መሳሪያ ምረጡ
- ተቀባይ ምረጡ
- ደብዳቤያችሁን ፃፉ። ጠብቁ። አስቡ
- ደብዳቤያችሁን ለተቀባይ ስጡ
- ተቀባዮች ደብዳቤያችሁን ካነበቡ በኋላ ስለ ምኞት አለማችሁ የፃፉችሁትን ጮክ ብለው ያንብቡላችሁ።
- ደብዳቤያችሁ ሲነበብላችሁ ምን ተሠማችሁ? የፃፉችሁት አለም ልትኖሩ ከምትፈልጉበት አለም እንዴት የተለየ እንደሆነ አስቡ። ይህንን ክፍተት ለመሙላት ምን መደረግ አለበት?

ሊታሠቡ የሚገባቸው ነገሮች
ይህ ገቢር በአንድ ክፍል ውስጥ በተወሠኑ ሠዐታት ሊከወን ይችላል። ረዘም ያለ ጊዜ ሊወሰድም ይችላል። ይህ ከሆነም በሚከተሉ መንገዶች ሊከፋፈል ይችላል። ደብዳቤውን የመፃፊያ ጊዜ- ደብዳቤውን የመላክ/የማጋራት ጊዜ- የመቀበያ/የማንበቢያ ጊዜ - ለደብዳቤው በተለየ መንገድ መልስ የመስጫ ጊዜ



↑ Frame enlargements from *Light, Blaze, Fulgor* (2019): A sound letter from Commune of the Fulgor in Troviscais; A griffon vulture's flight in Portas do Rodão


ADDITIONAL REFERENCES

- Bonney, Sean. *Our Death*. Oakland: Commune Editions, 2019.
- Boudry, Pauline & Renate Lorenz. *Moving Backwards*. Geneva: Skira, 2019.
- Brenez, Nicole & Isabelle Marinone. *Cinémas libertaires: Au service des forces de transgression et de révolte*. Villeneuve d'Ascq: Presses Universitaires du Septentrion, 2015.
- Debuysere, Stoffel. *Figures of Dissent: Cinema of Politics / Politics of Cinema*. Ghent: Mer. Paper Kunsthalle, 2016.
- Llansol, Maria Gabriela. *The Geography of Rebels Trilogy*. Dallas: Deep Vellum, 2018.
- Minh-Ha, Trinh T. & Jean-Paul Bourdier. "L'autre marche / The Other Walk." In Trinh T. Minh-Ha, *D-Passage: The Digital Way*. Durham: Duke University Press, 2013. Doi: 10.1215/9780822377320-007.
- Smithson, Robert & Nancy Holt. *The Writings of Robert Smithson: Essays with Illustrations*. New York: New York University Press, 1979.
- Tsing, Anna. *The Mushroom at the End of the World: On the Possibility of Life in Capitalist Ruins*. Princeton: Princeton University Press, 2015.

ARTWORKS & FILMS

- Akerman, Chantal, director. 1977. *News from Home*. Carlotta Films.
- Aurand, Ute, director. 2004. *Half Moon for Margaret*. Ute Aurand Filmproduktion.
- Baudelaire, Eric, artist. 2014. *Letters to Max*. Poulet-Malassis, La Région Île-de-France; LUX Artist's Moving Image.
- Carasco, Raymonde, director. 1979. *Tarahumaras 78*. Raymonde Carasco.
- Costa, Pedro, director. 2006. *Colossal Youth*. Momento Films.
- Diop Mambéty, Djibril, director. 1999. *La Petite Vendeuse de Soleil*. California Newsreel Productions.
- Fishinger, Oskar, director. 1927. *Walking from Munich to Berlin*.
- Mackenzi Kent, director. 1961. *The Exiles*.
- Mateus, Marta, director. 2018. *Farpões Baldios / Barbs, Wastelands*. C.R.I.M. Produções, Sociedade Óptica Técnica.
- Muñoz, Jeannette, director. Since 2005. *Envíos*.
- Ogawa Productions, director. 1986. *The Sundial Carved with a Thousand Years of Notches—A Magino Village Tale*. Ogawa Productions.
- Rey, Nicolas, director. 2012. *Molussy, Differently*.
- Rivette, Jacques, director. 1974. *Céline et Julie Vont en Bateau*. Films du Losange.
- Rousseau, Jean-Claude, director. 1983. *Jeune femme à sa fenêtre en lisant une letter*. Rousseau Film Production.
- Vaz, Ana, artist. 2016. *Há Terra!*.
- Zero, Grupo, director. 1977. *A Lei da Terra*. Alberto Seixas Santos, Grupo Zero.


CREDITS

*Luz, Clarão, Fulgor: Augúrios para um Enquadramento Não Hierárquico e Venturoso* [Light, Blaze, Fulgor: Auguries for a Non-hierarchical Framing and Flourishing], by Sílvia das Fadas. 16mm dual-projection film, ca. 85', color and b/w, sound, and live reading, ongoing since 2017. Shot in Alentejo, Portugal. Sound compositions: Pä (Part I), João Farelo (Part II). Soundscapes by Nora Sweeney, Robert Blatt, and Sílvia das Fadas. Masks: Joaquim Cerdeira. *Light, Blaze, Fulgor: Auguries for a Non-hierarchical Framing and Flourishing* was produced with the support of a doctoral fellowship by the Fundação para a Ciência e a Tecnologia (FCT), Portugal as well as funding from FWF PEEK: "DisPossession: Post-Participatory Aesthetics and the Pedagogies of Land," and the Akademie Schloss Solitude. All frame enlargements and film stills in this chapter: reproduced courtesy of Sílvia das Fadas, the artist.

ልብ በዝግታ ሲመታ ማዳመጥ
ጊዜ ለስፍራ ስፍራ ለጊዜ
በውኃ ውስጥ መውደቅ
ከዘለዓለማዊነት በቀር ምንም አለማወቅ



# በወንዝ ዳርቻ



## ሮሽታ ቱግሩል

ኩርዲስታን

“መረጃ ሁሉ ቢደመሰስ የልኬትን ውሎች አያጠፉም። የመናፍስትን መጋመድ ጉልህ ሆኖ እንዲታይ ለማድረግ ብዙ ስራ ይጠይቃል። ያለፈው ጊዜ የተዘጋ ጊዜ አይደለም፤ ሆኖም አያውቅም። ነገር ግን ዋናው ጉዳይ የውል መጥፋት አይደለም። ያለፈው ጊዜ የአሁኑ ጊዜ አይደለም። ‘ያለፈ’ ጊዜና ‘መጪው’ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚለዋወጡ እና በአለም ውስጣዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖሩ ጥቅልል ኩነቶች ናቸው። ባለፈው ጊዜ እና በመጪው ጊዜ እርግጠኛ ተፈጥሯዊ ግንኙነት የለም። ኩነቶች በስፍራና በጊዜ ውስጥ የሚገኙ ሳይሆኑ በቁሳዊ ቁርኝት እንዲሁም በሁለንተና (universe) የጊዜና - የስፍራ - ግዘፍ ውስጥ የሚጋመዱ ጥቅሎች ናቸው። የዲፍራክሽን (diffraction) ቀመር “መመለስ” እንኳን እንደገና መመለስን፣ የትውስታን መጥፋትንና ያለፈውን ጊዜ ዛሬ መደገምን አያመለክትም። ትውስታ በአለም ዓላባዎች ውስጥ የሚፃፍ የውስጣዊ ድግግሞሽ እንቅስቃሴዎች የዝቃጭ ድር ነው። አለም ሁሉንም የትውስታ ውሎች በውስጧ ‘ትይዛለች’ ወይም አለም እራሷ ትውስታ [የትውስታ] ጥቅል ቁሳዊነት ነች።”

— Karen Barad, “Nature’s Queer Performativity”



“ከታይግሪስ ወደ ፐርሺያ ባህር ሠላጤ የሚወስድ መንገድ እየፈለግኩ ነበር። እየዋኘሁ ብዙ ጊዜ አቅጣጫዬን ስቼ ጠፋሁ። ሚስጥራዊ መንገድ እንዳለ ስላመንኩኝ ትንንሾቹን ቆሮች እና መግቢያዎች እየተከተልኩ ከሜሶፖታሚያ ወደ ባህር ሠላጤ ፍለጋዬን ቀጠልኩ።”

ጦርነትን በሚያቅዱ ዘንድ ጂኦግራፊ መደምሰስ እና ለሠዎች መኖሪያ እንዳያገለግል መደረግ ያለበት የጦር ኢላማ ተደርጐ ይታያል። ጂኦግራፊን እንደ መሳሪያ በመጠቀም በአንድ ክልል ውስጥ የሚገኙ ዜጐችን ለማስፈራራት እና ለመቆጣጠር ሊጠቀሙበትም ይችላሉ። ከ1990ዎቹ ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ ቱርክ የሚደረገው ጦርነት በጉልበት የፀና የአካባቢ አገዛዝ (territorial governance) ሌላ ደረጃ ያደረሰ የጦርነት ስልት ነው። ከገጠር እስከ ከተማ በመስፋፋት አገዛዙ የራሱን ጥፋት እያፋጠነ መሆኑን ያሳያል። ተፈጥሮ እና ማህበራው ካባቢው በጦርነት የተጐዳ ስለሆነ ታሪክን በማጥናት የአካባቢው ህይወት (habitat) እንዴት በጊዜ ሂደት እንደተለወጠ ከታሪክ መመሪያን ማግኘት ይቻላል።

እ.ኤ.አ. በ2008 የቱርክ መንግስት ከደርዘን በላይ የሚሆኑ “የደህንነት የግድብ ኘሮጀክቶች” ብሎ የጠራቸውን ግንባታዎች አስተዋወቀ። እነዚህ ግድቦች ለመገንባት የታቀዱት በቱርክና ኢራቅ ድንበር አካባቢና በሰሜን ኩርዲስታን በሚገኙ አንዳንድ የማዕከላዊ ክልል ሸለቆዎች ውስጥ ነበር።[1] ይህ የግንባታ እቅድ በኩርዲስታን ክልል ሲደረግ ሁለተኛው ነው። በ1990ዎቹ የቱርክ መንግስት PKK የተባለውን ለኩርዳዊያን መብት የሚታገልን የፖለቲካ ድርጅት ህዝባዊ እና ቁሳዊ ድጋፍ ለማንጠፍ ሲል የክልሉ ህዝብ በሀይል እንዲነቀሉና ሰፈሮቹን በማፍረስ ህዝቡ በሌሎች አካባቢዎች እንዲሰፍሩ አድርጓል። በዚህ እርምጃ በ3000 ሰፈሮች የሚኖሩ ከ3 ሚሉዮን በላይ ሠዎች ከአካባቢያቸው ተፈናቅለዋል። ግድቦቹ የተገነቡት የPKK ተዋጊዎች መተላለፊያዎችን ለመዝጋት እና ቁሳዊ እገዛን እንዳያገኙ ለማድረግ ነው።



← Rojda Tuğrul, Tigris and Euphrates, 2019

1 Zeynep S. Akinci & Pelin Tan, “Waterdams as Dispossession: Ecology, Security, Colonisation,” in *Climates: Architecture and the Planetary Imaginary,* ed. J. Graham (New York: Columbia Books on Architecture and the City; Zurich: Lars Muller Publishers, 2016), 142–49.

ይህ “የደህንነት ግድብ” ፕሮጀክቶች ሀሳብ የመነጨው ከ “ደቡብ ምስራቅ አናቶሊያን ፕሮጀክት” (GAP) ሲሆን ምክረ ሀሳቡ የተፃፈው በ1930ዎቹ ቢሆንም ተግባራዊ እንቅስቃሴው በአዲስ መንፈስ የጀመረው ከ1970ዎቹ በኋላ ነው። አላማውም በኢፍራጢስ እና ታይግሪስ ወንዞች ላይ ትላልቅ የመስኖና የኤሌክትሪክ ማመንጫዎችን መንገባት ነው። ዛይነፕ ኤል አኪንቺ እንደሚሉት “ከ1920ዎቹ ጀምሮ የቱርክ መንግስት ህዝብን የማስፈር ፖሊሲ አካበቢውን ከኩርድ ህዝቦች ለማንፃት እና የባህል ማዕቀፋቸውን ከአካባቢው ግፅ ለመሰረዝ ግቡ አድርጐ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። እነዚህ የሠፈራ ፖሊሲዎች ሌላው አላማቸው በኢፍራጢስ ምስራቅ የሚገኙትን ኩርዶች ብዛታቸውን መቀነስ ነው። በዚህ የተነሳ አንዳንድ ኩርዶች ወደ ኢፍራጢስ ምዕራብ ክፍል እንዲሰደዱ ሲደረጉ በአንፃሩ ደግሞ የቱርክ ዝርያ ያላቸውን ሰዎች ደግሞ ወደ ምስራቅ የኢፍራጢስ አካባቢዎች በማስፈር ቁጥራቸው እንዲጨምር ተደርጓል።  ይህ እቅድ  500 ሺህ ሰዎችን ከምዕራብ ወደ ምስራቅ በ 10 ዓመት ጊዜ እንዲሰፍሩ ሀሳብ አቅርቧል።” GAP የተባለውን ፕሮጀክት በላይኛው ሜሶፖታሚያ በኢፍራጢስና ታይግሪስ አካባቢ የሚገኙ ከተሞችን የሚያካትት ሲሆን ፕሮጀክቱ 22 አዲስ ግድቦችን ለመገንባት አቅዷል።



የGAP መዘዝ በቱርክ ድንበሮች ውስጥ ብቻ ተወስኖ የቀረ አልነበረም። ምክንያቱም ታይግሪስና ኢፍራጢስ በደቡብ በኩል ወደ ሶሪያ እና ኢራቅ ስለሚፈሱ ፕሮጀክቱ እነዚህንም አገሮች በወንዞቹ የውሃ ፍሰት ላይ ምንም አይነት ቁጥጥር እንዳይኖራቸው ያደረገ መሆኑ ነው። በወንዞቹ የውሃ ቁጥጥር ዙሪያ ከእነዚህ አገሮች ጋር የተፈጠረው አለመግባባት እና አታካሮ የGAPን ስራ ከማጓተቱም ባሻገር በአሁኑ ጊዜ ለፕሮጀክቱ መቆም ምክንያት ሆኖዋል ይህም ሆኖ ግን የቱርክ መንግስት ፕሮጀክቱ ከግብ እንዲደርስ የሚያደርገው ጥረት PKKን የማዳከም ፍላጐቱ ከጐረቤት አገሮች ጋር ያለውን አለመግባባት ከመፍታት እንደበለጠበት ያመለክታል። የደህንነት ግድብ ፕሮጀክቱን በ2008 ያስተዋወቀውም በዚህ የተነሳ ነው። PKK በበኩሉ ማንኛውንም የግድብ ስራ እንደሚያጠቃ በማስታወቁ የቱርክ መንግስት እያንዳንዱ የግድብ ስራ ላይ የጦር ሰፈርና የጦር ማማ ለማቋቋም ተገዷል። እነዚህ ግድቦች የጦር ግድቦች በመባል በስፋት ይታወቃሉ፤ የጦርነቱ አካልም ሆነዋል። በ2012ም እነዚህ ግንባታዎች በተደጋጋሚ በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት እንዲቋረጡ ተገደዋል።





ከ1920ዎቹ ጀምሮ እነዚህ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነቶች ስነ-ምህዳሩን እና ማህበራዊ መስተጋብሩን የሚለውጡበት መንገድ እና እንዴት የአካባቢውን ማህበራዊ መስተጋብር እያጠፉት እንዳሉ ሳስብ ነው። ከሞላ ጎደል በቱርክ፥ ኢራቅ እና ሶሪያ ተጽእኖ የማይደረግበት የኩርዶች ክልል የለም። በዚህ ሳቢያ እንስሳት፥ አእዋፍት እና ብዝሃነት ያላቸው አዝእርት በዚህ ምክንያት እየጠፉ፤ የታሪክ ስፍራዎች እና ቅርሶች እንዲሁም የታሪክ እውቀት በስፋት እየወደመ ነው። የጥንታዊዋ የበልቂስ ከተማ (በጋዚያንቴፕ) የጎርፍ አደጋ እና ሃሳንኬይፍ ላይ የተጋረጠው ከፍተኛ አደጋ የዚህ ውድመት ማሳያዎች ተደርገው ሊጠቀሱ ይችላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታም በአካባቢው ሌሎች ብዙ ጥንታዊ ከተሞች ጠፍተዋል በውሃም ተሸፍነዋል።[2]

ይህን ምእራፍ የምጀምረው ከሜሶፖታሚያ ለስላሳ ቅርፊት ኤሊ አንጻር በተጻፈ መነባንብ ነው። ይህች ኤሊ የኢፍራጢስ ለስላሳ ቅርፊት ኤሊ ተብላም ትጠራለች። በኢፍራጢስ እና ታይግሪስ ዳርቻዎች አካባቢ የምትገኝ ለቦታው ብርቅዬ የሆነች እንስሳ ነች። በ2008 በታይግሬስ የደቡብ ዳርቻ የአርኬዎሎጂ ቁፋሮ ተደርጎ እንግዳ የሆነ ነገር ግን ትልቅ ግኝት በዲያርባኪር ክፍለ አገር ተገኝቷል። ግኝቱ የመቃብር ቦታ ሲሆን በውስጡም ከ45-55 ዓመት የሚሆናት ሴት እና ከ6-7 ዓመት የሚሆነው ልጅ ቅሪት ነው። ቅሪቶቹ 2500 ዓመት የተገመቱ ሲሆን በመቃብር ቦታው 21 ኤሊዎችም (17ቱ የሜሶፖታሚያ ለስላሳ ቅርፊት ኤሊዎች ናቸው) ተገኝተዋል።

የአርኪዎሎጂ ጥናቱ እንደጠቆመው እነዚህ ኤሊዎች ተበልተው ለሁለት ህይወት አልባ አካሎች እንደ በረከት የቀረቡት የሰዎቹን ነፍስ ከክፉ መንፈስ ለመጠበቅ እና ነፍሳቸውን ወደ ዘላለማዊነት እንድትሻገር ለማድረግ ነው።[3] ቁፋሮው የተደረገበት ቦታ በተለያየ ጊዜ እነደ መቃብር ቦታነት ያገለገለ ሲሆን እነዚህ ቅሪቶች የተገኙት ለግድብ ስራ ግንባታ በሚደረግበት ጊዜ ነው። ይህ ቅሪቶቹ የተገኙበት ቦታ በግንባታው የተነሳ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በውሃ መጥለቅለቁ አይቀሬ ነው።

በግድብ ስራው የተነሳ የሜሶፖታሚያዋ ለስላሳ ቅርፊት ኤሊ በአካባቢው የመጥፋት አደጋ ከተጋረጠባቸው እንስሳቶች ውስጥ አንዷ ናት። ኤሊዎቹ በታይግረስ ወንዝ በአሁኑ ወቅት ቢገኙም በግንባታው የተነሳ ላይመለሱ ሊጠፉ የሚችሉበት አጋጣሚ ከፍተኛ ነው። ግድቦቹ የአካባቢውን የተፈጥሮ ህይወት ለጥፋት ይዳርጋሉ። ከዚህ በተጨማሪም የኤሊዎቹና የሌሎች ህይወቶችና የእውቀቶችን ውድመት ያመለክታል። በመሆኑም ከእንስሶች እና እጽዋት ጋር

↻ Rojda Tuğrul, Ataturk Dam on the Euphrates (left); Dams and Barrages on the Tigris and Euphrates (right), 2019

2 The politics of assimilation are referenced in Akinci & Tan’s article (p. 143): “In 1924 with the establishment of the Sark Islahat Planı or Orient Reform Plan, assimilation or Turkification of Kurds found legal grounding. The assimilation policies were applied via three main tools: settlement, education, and policies to culturally ‘Turkify’ the region.” See note 1 for full reference.

3 Rémi, Berthon, Yilmaz Erdal, Mashkour S. Mashkour, and Gülriz Kozbe, “Buried with Turtles: The Symbolic Role of the Euphrates soft-shelled Turtle (Rafetus Euphraticus) in Mesopotamia,” *Antiquity* 90, no. 349 (2016): 111–25; doi: 10.15184/aqy.2015.196.

አፈታሪካዊ፥ ታሪካዊ እና አንትሮፖሎጂያዊ እውቀቶች እንደሚጠፉ ሳይታለም የተፈታ ነው።





በዚህች ለስላሳ ቅርፊት ኤሊ ተፈጥሯዊ እና አካላዊ ህይወት እና በአፈታሪካዊ ተምሳሌትነቷ መካከል ያለውን ዝምድና ስናጤን በአንድ ጂኦግራፊ ውስጥ የሚካከቱ እና የሚኖሩ ኩነቶች መካከል ያለውን ግንኙነት እንድናስተውል ያደርገናል። በወንዝና በንብ መካከል ያለው የእርስ በእርስ ትስስር (interdependence) ወይም በድምጽ ኮርድ እና በተራራ መካከል ያለውን ግንኙነት ስናጤን በጣም የተለያዩ እና የማይገናኙ በሚመስሉን ነገሮች መካከል ሳይቀር ያለው ግንኙነት አንዱ ካለሌላው መኖር አለመቻሉን ያሳገነዝበናል። ይህ ፕሮጅክት በነገሮች መካከል ያለው ቁርኝት ላይ የሚያተኩርና የስነ ህይወት መደምሰስ የሚያስከትለውን የረጅም ጊዜ አደጋ ሆነኝ ብሎ ያጠናል፤ ይመረምራል።





የመልክአ ምድሩ መደምሰስና መጎዳት የባህልና የታሪክ ውድመት ነፀብራቅ ነው። በመልክአ ምድሩ ላይ የሚታዩት ጠባሳዎች በአካባቢው ማህበረሰብ ስነ-ልቦና ውስጥ ምልክት ጥለው ያልፋሉ። የተነቀለችና የተፈናቀለችው ምድር የኩርዶች የፖለቲካ ትግል ስደት እና መፈናቀል ታሪክ ተምሳሌት ናት። በዚህ በተሰበረና በተጎዳ መልክአ ምድር ውስጥ የሚኖሩት ደግሞ አብላጫው የኩርድ ማህበረሰብ አካላት ናቸው። አብዛኛው ህዝብ ይህንን የተለወጠ ካባቢ፣መልክአ-ምድር፣ስነ-ምህዳር፣ስነ-ሰብዕ፣ታሪክ፣ፖለቲካና ባህል በለት ትዕለት ህይወቱ ይኖረዋል።

በዚህ ጥናቴ የተለያዩ ሚዲያዎችን አንድ ላይ በማምጣት እንዴት አብረው ሊሰሩ እንደሚችሉ አጠናለሁ። በስእል ደብተሬ ላይ የሰራኋቸው ስእሎች በነገሮችና የተለያዩ የጊዜ ቀመር (temporalities) ባላቸውን ስፍራዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይመረምራሉ። አንባቢዎች እነዚህን ግንኙነቶች (relationalities) በምስል ሲመለከቱ -ህፃንዋ የሜሶፖታሚያ ለስላሳ ቅርፊት ኤሊ-በተረበሸው የወረቀት ገጽ መሃል ላይ ተቀምጣ የውሃ ወጀብ በሚመታት ጊዜ ለ 10 ሴኮንዶች ወደ ታች ስትወርድ ይመለከታሉ። የማይንቀሳቀሰው የዚህ አኒሜሽን



↻ Rojda Tuğrul, Buried with Turtle; Buried with Turtle (both on left page) & Turtle and Hyena; Turtle and Boncuklu Tarla (Beaded Field), (both on right page; all from 2019)

ክፍል ወደ 200 ገጽ ነው። ይህን ያደረግኩበት ምክንያት የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባትን ይህችን እንስሳ የጊዜ ማእቀፍ (time frame) ለማሳደግ እና የህይወት ጊዜዋን ለማሰብ ካለኝ ፍላጎት የተነሳ ነው። ይህ ስራ በግድቡ ግንባታ የተነሳ ወደ ወስጥ የተሰረጎዱ መሬቶችን ያሳያል። በዘዴና በጥንቃቄ የኤሌዋን የሰውነት ክፍል የመበለቱ ሂደት የፖለቲካና ማህበራዊ ጉደዮችን ቁርኝት ያሳያል፤ አካባቢውም እንዴት በዚህ ጦርነት እንደቆሰለ ያመለክታል።

የቅጽበት ፎቶግራፍ በዚህ ስራ ሌላ የምስል ንድፍ ሃሳብ ምስረታዬን የሚያግዝ ዘዴ ነው። በሜይ 2019 በታየግርስ ቤዚን የምትገኝ የ12000 ዓመት እድሜ ያላት የሃሳንኬይፍ ክፍለ ሃገር በሊሱ ግድብ ስራ ምክንያት ነዋሪዎቿ እንዲለቁ ተደረዋል። ይህ ከመሆኑ ጥቂት ሳምንታት በፊት አካባቢውን በ200 ሜትር ዲያሜትር ላይ ሆኜ በእግሬ በመጓዝ የቅጽበት ፎቶግራፎች ወስጄ ነበረ። ፎቶግራፎቼ ጥንታዊ ሸለቆዎችን (Canyons)፣ ዋሻዎችን፣ ታሪካዊ ድልድዮችን፤የመንገድ ውሻዎችንና ብርቅዬ አዝእርትን ይዘዋል። ፎቶግራፎቹ









↑ Rojda Tuğrul, Turtle and Boat; Turtle and Hieroglif; Turtle and Boncuklu Tarla (Beaded Field); and, Turtle and Crane, all from 2019







ግድቡ ከመሰራቱ በፊት እና በኋላ በአካባቢው ላይ ያለው ልዩነት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። የዚህ ምስል ምሰረታ አላማ ከግድቡ ግንባታ አሰቃቂ ውጤት በፊት ያለውን ሁኔታ ለማሳየት ብቻ ሳይሆን የአካባቢው ውድመት ያላስቆማቸውን የህይወት መቀጠሎችን (appearing process of things) ለማሳየትም ነው። ስለዚህ የስራዬ አይነተኛ አላማ በአለመኖርና በመኖር እንዲሁም በመምጣትና በመጥፋት መካከል ያለውን ግብግብ ማሳየት ነው።

↑ Rojda Tuğrul, Turtle and Ruin; Turtle and Woman Fighter, both from 2019





↑ Rojda Tuğrul, *Knowing Tomorrow*, Hasankeyf, 2019



↑ Rojda Tuğrul, *Knowing Tomorrow*, Hasankeyf, 2019



ማንነቶች በዕለት ተለት ይሰራሉ። መከበራቸውም ተገቢ ነው። ነገር ግን ማንነቶች ሁልጊዜም በግንኙነቶች አውታር ላይ የሚውሉ ናቸው። ራሳቸውንም ዩክሊዲያን ላልሆኑ ትላንቶች፣ዛሬዎችና ነገዎች ይከፍታሉ። ተራው (የዕለት ተለቱ) ከሌሎች ጋር ወደርነትን የሚሰራ የተቆራኙ ፍጥረታት የጭቃ ዳንስ ውጤት ነው። እስከታች ድረስ ድርብርብ የባህር ኤሊዎች[1]፤ ወደረኞቹ ፍጥረታት በእያንዳንዱ የተጣጠፈና የተደራረበ የጊዜና የስፍራ የውስጥ እንቅስቃሴ ውጤት እንጂ ራሳቸውን ቀድመው የሚሰሩ በግል የቆሙ ማንነቶች አይደሉም።

— Donna J. Haraway, *When Species Meet*

1 እንደ አንድ አፈ-ታሪክ አባባል ምድር ፀንታ የቆመችው ከስር ተደራርበው በተሸከሟት ኤሊዎች አማካኝነት ነው።






መሳሪያ

# ሪ አኒሜቲንግ (Re-Animating)

በጦርነት ቀጠና ውስጥ የታቀዱ ስርአታዊ ጣላቃ ገብነቶች በተለያዩ አካላት ላይ ከፍተኛ ጥፋትና ለውጥን ያስከትላሉ። የነገሮች በፍጥነትና በተደራረበ መልኩ መከሰት ምን የት እየተካሄደ እንደሆነ በአግባቡ ለመረዳት አዳጋች እንዲሆን ያደርገዋል። በመሬት ላይ እና በመሬት በኩል በኩርድ አካባቢዎች ላይ እየተወሰደ ያለው የሃይል እርምጃ የጦርነቱን ውስብስብነት ያሳያል። ይህ እራሱ የግጭቱን ዘርፈ ብዙ እና የረጅም ጊዜ ተጽእኖዎች ከማመላከቱም በላይ ተጽእኖው በተለያዩና እንደዋዛ ሲታዩ የማይገናኙ በሚመስሉ ነገሮች ላይ ሁሉ አደጋን ይጋርጣል። የዚህ አይነት ጣልቃ ገብነት-ማለትም የግድብ ግንባታ የተለያዩ ፍጥረታትን ያጠፋል። ይህ ደግሞ የስነ-ቃል ውክልና ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል፤ የአፈ-ታሪክ ባህል መጥፋትን ያስከትላል። የእነዚህን ሁሉ ኩነቶች ግንኙነት / ትስስር መገንዘብ ብዝሃ-አቀፍ የሆነ እይታን ይጠይቃል።

ሪ አኒሜቲንግ በጊዜ እና ስፍራ አሰራር ውስጥ ጣላቃ በመግባት የመልክአ-ምድርን መረበሽ ሂደትን ያሳያል። ነገሮችን በመደራረብ፣በመጠቅለል ሪ አኒሜቲንግ በጦርነት ጊዜ "የነገሮችን" ሁኔታ ያጠናል ይተነትናል። ቦታን እና ጉዞን በጊዜ ወይንም ጊዜን እና ጉዞን በቦታ ውስጥ በማርጋት የሚሰራ የሙከራ አይነት ነው። ይህ ዘዴ የነገሮችን የቦታና የጊዜ ጉድኝትን ውል ለመከተል የሚጥር ዘዴ በመሆኑ በአንድ አሰቃቂ የውድመት ሁኔታ አማካኝነት ነገሮች ላይ የሚከሰቱ ስቃዮችን በማጉላት የአካባቢ ለውጥ በተለያዩ አካላት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ያስረዳል።

ሪ አኒሜቲንግ ጊዜን እና ቦታን የመመዝገብ ሂደት/ሙከራ አይደለም። ጊዜን በማርዘም ቦታን በማብዛት የሚሰራ ሙከራ እንጂ። ጊዜን በማርዘም ፣ በማቆምና በማቀዝቀዝ ለተለየ አይነት እይታ እድል ይሰጣል። ይህ ልዩ ሁኔታ/ለውጥ ነገሮችን ለማጤን ትእግስት ለሌላቸው እና አንዳንዴም ነገሮች የእይታ አቅማችን ከሚፈቅድልን በላይ በሚለዋወጡበት ሁኔታ ለውጥን በምልዐት እንድንረዳ ሊጠቅመን ይችላል።

ሪ አኒሜቲንግ ነገሮችን በዘዴና በጥንቃቄ የመበለት ሀሳብ ነው። ምስሎችን ሲያቀርብ የሰዎችን የቦታና የጊዜ ግንዛቤ ከፍ ያደርጋል። ሪ አኒሜቲንግ አንድን አካል ከተመደበበት ቦታ ማንሳት ብቻ ሳይሆን የቦታን መድረሻ ራሱ መለወጥ ይችላል። በዚህ ረገድ ለምሳሌ በሜሶፖታሚያ የምትገኝ አንዲት ውሃ ውስጥ የምትኖር ኤሊ ስነ-ሕይወቷ በወንዝ ውስጥ የተወሰነ ብቻ ሳይሆን አፈ-ታሪካዊ ቅርፅ ያላት ስለሆነች የዘለለትና የትውስታ (Memory) ተምሳሌትም ናት። በእንዲህ አይነት የምስል ውክልና ሪ አኒሜቲንግ አዲስ ትእይንት እና ቅደም ተከተል ይፈጥራል ብሎም ስለ ጊዜ እና ቦታ እንደገና እንድናስብና እንድንመረምር ይረዳናል።

ሪ አኒሜቲንግ ከትላንት ወደ ዛሬ እና በተቃራኒው እንድንጓዝ በማድረግ ግንኙነቶችን እና የነገሮችን የጊዜ ቀመር ውል እንድንከተል ይረዳናል። አንድ ምሳሌ ለመስጠት ያክል የጊዜ መፈራረቅ ውጤቶች የሆኑ ፍርስራሾችን በተለያየ ጊዜ የነበራቸውን ለውጥ ሊያሳየን ይችላል። ይህ ለውጥን በጊዜ

የመመደብ ሂደት የጊዜና የቦታ ሂደት ቀጥተኛ ያልሆነ እና ውስብስብ መሆኑን ያሳያል። ስእሎች፣ፎቶግራፎች፣የቃል ታሪክ ፣ቪዲዮ፣ የድምጽ ቅጂ እና ማንኛውም ሌላ የመረጃ ዶሴ (Archive) ለሪ አኒሜቲንግ ሂደት አስተወጽኦ ያደርጋሉ። እነዚህ ሚድያዎች ለሪ አኒሜቲንግ ሂደቱ ራሱ ጥቅም ላይ ሊወሉ ይችላሉ። በጦርነት አውድ ውስጥ ሪ አኒሜቲንግ ተለዋዋጭ ሂደት በመሆኑ ሁኔታዎችን እና ምስሎችን የሚቆጣጠሩትን ሳይቀር ሊጻረር ይችላል። በጦርነት አውድ ውስጥ በሚኖሩ ገደቦች የተነሳ ማንኛውም የምስል ውክልና የራሱን ሀይልና ጉልበት ይዞ ይመጣል። አንድ ተራ የምስል/ስእል ስራ ወይም ጥራት የጎደለለው ፎቶግራፍ ወይም ቪዲዮ በዚህ አይነት አውድ ውስጥ የራሱን ጉልበት ይዞ ይመጣል። (1) በዚህ የሪ አኒሜቲንግ ሙከራ ዋናው ተዋናይ የስነ-ጥበብ ሠራተኛው/ዋ ነው። ውክልና የሚሰጠው ሪ አኒሜት የሚያደርገውና ምስሎችን በመቆጣጠር የጦርነት አውድማውን ስፍራ የሚፈጥረውም አርቲስቱ ነው።

የሪ አኒሜቴኒግ መሳሪያ ጊዜን እና ቦታን ሪ አኒሜት በማድረግ የሚሰራ ሲሆን ጊዜን እና ቦታን ሪ አኒሜት ማድረግ ግለሰቦች ከመሬታቸው ጋር እንደገና የሚገናኙበትን ሂደት ሊፈጥር ይችላል። ይህ በምናብ የተሰራ ሁኔታ የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ሰዎች ከመሬት ጋር ያላቸውን የግል ግንኙነቶች ላይ ያተኩራል። መሳሪያው ደግሞ ከመሬታቸው የተነጠቁ ሰዎችን ተሞክሮ እንዲሁም የንጥቂያ ትውስታቸው ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

(1) Hito Steyerl, “In Defense of the Poor Image,” *e-flux journal* 10 (2009); online at: e-flux.com/journal/10/61362/in-defense-of-the-poor-image.



“ታሪክ የሠዎች ትርክቶች የሚነገሩበት ያለፈውን ዘመን ቅሪቶች ወደ ትርክት የምንለውጥበት ተግባር ነው። በተለምዶ የታሪክ ባለሞያዎች የሰዎችን ቅሪቶች የሚያጠኑ ሲሆን ታሪክን ለመጻፍ የሚጠቀሙት ለምሳሌ የግል ማስታወሻዎችን እና የታሪክ ዶሴን (Archive) ነው። ነገር ግን የታሪክ ባለሙያዎች ትኩረታችንን ሰዎች ያልሆኑ የጋራ መልክአ-ምድራችንን ለመስራት አስተዋጽኦ ያላቸውን አካላት ውል እና ዱካ ለማጥናት የማንጥርበት ምንም ምክንያት የለም። እነዚህ ዱካዎችና ውሎች የተለያዩ ህይወት ያላቸው አካላት ድንገተኛና አጋጣሚ በሆነ ሁኔታ የሚጋመዱበት “የታሪክ” ጊዜ አካል መሆን ይችላል። እነዚህ አካላት በዚህ አይነት የታሪክ መጋመድ (Entanglement) ለመሳተፍ የግድ በአንድ አይነት መልኩ ብቻ ታሪክን መስራት የለባቸውም። ህይወት ያላቸው አካላት ሁሉ “ትርክት ባይተርኩም” ታሪክን በታሪክነቱ እንድንረዳው የሚያደርጉን ተያያዥ ዱካዎችና ውሎች የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ስለዚህ ታሪክ ብዝሃነት ያላቸው የሰዎችም ሆነ ሰው ያልሆኑ አካላት አለምን የመስራት ጉዞ ድርሳን ነው።”

— Anna Tsing, *The Mushroom at the End of the World*

ገቢር

# ቦታን ሪ አኒሜት ማድረግ

ቦታን ሪ አኒሜት የማድረግ ገቢር ልምምድ የሚያደርጉት ተሳታፊዎች በመጅመሪያ አንድ የመልክአ ምድርን ውድመት ስለሚወክል ቦታ ይወያያሉ። ይህ የተፈጥሮ ውድመት ወንዝ፣ሸለቆ፣መንገድ ወይም ተራራ ወዘተ... ሊሆን ይችላል።

ተሳታፊዎች እይታን የመመስረት ሂደት ላይ ለመሳተፍ የተለያዩ ቁሳቁሶች ያስፈልጋቸዋል። ልምምዱ የሚደረግበትን ቦታ (ቤት ውስጥ ወይም ውጪ) እና ወቅት ግምት ውስጥ ማስገባትም ያስፈልጋል። ለሁኔታው የሚመች ተስማሚ ጫማ፣ውሃ፣ምግብ፣ዣንጥላ የአንገት ልብስ፣ ጃኬት ወዘተ... ያስፈልግ ይሆናል። ተሳታፊዎች ከታች የተዘረዘሩትን ንባቦች እና የስነ-ስዕል ስራዎች ወደ ልምምዱ ከመምጣታቸው በፊት እንዲመለከቱ ይበረታታሉ።

### በቦታው መገኘት

- ወደ ልምምዱ ቦታ ለመምጣት በእግር ወይም በብስክሌት ብትመጡ ይመከራል
- አካባቢውን ለመቃኘት ጊዜ ውሰዱ
- ስሜታችሁ ላይ በማተኮር የእግር መንገዳችሁን የምትጀምሩበትን ቦታ ወስኑ

### የእግር መንገድ

- የእግር መንገዳችሁን ጀምሩ፤ ከመሬቱ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ሞክሩ (ይህን አላማችሁ አድርጉ)
- ከአካባቢው ምልክቶች ልታገኙ እንደምትችሉ በማሰብ ለዚህ ራሳችሁን ክፍት አድርጋችሁ ጠብቁ። መሬት ምን ልትነግራችሁ እንደሚችልና እንዴት እንደምትቀበሉት አስቡ
- በአካባቢው ያሉትን ፍርስራሾችና ቅሪቶች በንቃት አስተውሉ። እነዚህ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ:- ላባ ፣ቁራጭ አጥንት፣ የመቃብር ቦታ፣የእባብ ቆዳ፣የበግ ጭንቅላት ወዘተ...
- ከምናባችሁ የምታገኙትን ምስል ለማሰላሰል ወደ ኋላ አትበሉ። ይህ ጉዞ መኖር እስከ አለመኖር ነው።



ገቢር

### መሳል/ፎቶግራፍ ማንሳት

ይህ ክፍል ምንም አይነት የስነ-ውበት ችሎታ አይጠይቅም ። አላማው ጊዜ ወስዶ የአንድን ኩነት በመኖሪያው/ በሚገኝበት አካባቢ ምን አይነት ግንኙነቶች ሊኖሩት እንደሚችሉ ማሰብ ነው። ይህን ተግባር ለመፈጸም የመሳል ችግር ከገጠማችሁ ፎቶግራፍ አንሱ

- በእግር ጉዟችሁ በአካባቢው የሚገጥሙዋችሁን እንደ እንጉዳይ፣ ቀንድ አውጣ፣ወፎች፣ድንጋዬች፣ተራሮች፣ነፍሳት፣የውሃ አካል፣ ዛፎች፣ ወዘተ... ያሉ ነገሮችን ጊዜ ወስዳችሁ አስተውሉ
- የሚያጋጥሙዋቸሁን ነገሮች ሳሉዋቸው። በዚህ የስእል ክፍለ ጊዜ የሚያጋጥሙዋችሁን ነገሮች መጻፍ ትችላላችሁ
- ከሚያጋጥማችሁ ነገሮች ጋር ግንኙነት ስላለው በአካባቢው የማታዩዋቸውን ነገሮች ጻፉ። በአካባቢው የማታዩት ነገርን ለመሳል ከተቸገራችሁ የቃል ገለጻን ተጠቀሙ
- የጉዟችሁን መንገዶች እና ግንኙነቶችን አስተውሉ። የሚያጋጥሙአችሁን ነገሮች አስቡ ባቸው። መንገዳችሁን እና የምታዩዋቸውን የተለያዩ አካላት እና ከቦታው ጋር ያላቸውን ግንኙነት አጢኑ

### ማዳመጥ እና መኮረጅ

- አካባቢውን ያዳምጡ እና የሚሰሟቸውን ድምፆች ይተንትኑ።
- በዚህ ምድር ውስጥ ተመስጦ እንዲሰማዎት የሚያደርጉትን ድምፆች ይኮርጁ። በቂ ማበረታቻ ከተሰማዎት ከአንዱ የተፈጥሮ አካል ጋር ለመነጋገር ይሞክሩ።
- ከቻሉ ድምጾቹን ይመዝግቡ።

### መመለስ

- ከእግር መንገዳችሁ፣ከስእል ስራችሁ፣ ከፎቶግራፎቻችሁ እና ከማዳመጥ ተግባሮቻችሁ ወደ መጣችሁበት የመጀመሪያ ስፍራ ተመለሱ
- በዚህ ገቢር ያጋጠሟችሁን ምስሎች፣የድምጽ ቅጂዎች እና ቃላት አንድ ላይ አምጧቸው
- እነዚህን ግንኙነቶች /ቁርኝቶች እና የነገሮችን ትርክቶች አንድ ላይ አንብቧቸው
- ያገኛችሁትን አብርሆቶች (inspirations) ፣ቅሬታዎችና ግርምቶች ለሌሎች ተሳታፊዎች አጋሩ

ገቢር

# ጊዜን ሪ አኒሜት ማድረግ

ይህ ጊዜን ሪአኒሜት የማድረግ ተግባር ቦታን ሪኒሜት ከማድረግ ጋር በመጣመር የመኖር ህልውናን ይሰጣል። ቀዳሚ አላማው የሌሎች አካላትን የጊዜ ሁኔታ (ተሞክሮ) መረዳት እና ማሰላሰል ነው።ተሳታፊዎች አንድ ሰው ያልሆነ አካልን መርጠው ቦታውን ሪ አኒሜት በማድረግ በቦታው ላይ እንዲያተኩሩ ይጠይቃል። ያለፈውን ጊዜ እና የጊዜን ሂደት እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል።

ለዚህ ገቢር ተሳታፊዎች አንድን ዘዴ (ሚዲየም) በመጠቀም ወይም በመምረጥ የዚህን አካል በጊዜ የሚያደርገውን ጉዞ እንዲወክሉ ያደርጋል። ዘዴው ስእል፣የሚንቀሳቀስ ምስል፣የታተመ ምስል ወዘተ... ሊሆን ይችላል።ለዚህ ተግባር እንደ እርሳስ፣ወረቀት፣ካሜራ እና ማስታወሻ ደብተር ያሉ ቁሳቁሶችን ተጠቀሙ።

## ያለፈው ጊዜ

- ስለነገሩ የህይወት ዑደት ተወያዩ። እንዴት ወደ አለም መጣ የለውጡ እና የህይወቱን ቆይታ ውል እና ሂደት ተከታተሉ። ሞቱንም ከግምት ውስጥ አስገቡ። ምን አይነት ሞት እንደሚያጋጥመው- ተፈጥሮአዊ ወይስ ሌላ ምክንያት መኖሩን ለዩ
- በስነ-ምህዳሩ ዝግመታዊ ለውጡን እስከ ህይወቱ ቆይታ ያለውን ውል አጢኑ። የነገሩን የለውጥ ሂደት ባለፉት የተወሰኑ አስርት አመታት ምን እንደሚመስል አስቡ/ተወያዩ
- የነገሩን የማይታይ አፈ-ታሪካዊ ውክልና እና ባህላዊ ዘይቤውን ፈልጉ

## አሁን

- የነገሩን በአሁኑ ጊዜ በስነ-ምህዳሩ/አካባቢው ያለውን ቦታ ተረዱ። በስነ-ምህዳሩ ውስጥ የሚጠብቀው ሚዛን ምንድን ነው?
- በተፈጥሮአዊ አውዱ ምን አይነት ሚና እንዳለው ምን አይነት ስነ-ህይወት ጋር ግንኙነት እንዳለው እና ማንን አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችልም አስተውሉ
- በአሁኑ ጊዜ ይህ አካል ምን አይነት ተምሳሌትና ዘዬ በራሳችሁ ቋንቋ እንዳለው አስቡ

## መጪው ጊዜ

- የዚህን ነገር /አካል በመጪው ጊዜ የሚኖረውን ህይወት ዘርዝሩ። በዚህም ላይ አንድ አንቀጽ ፃፉ
- የህን ነገር ለመወከል ምን አይነት ዘዴ (ድምፅ፣ፅሁፍ፣ስእል፣ፎቶግራፍ አኒሜሽን ቪዲዮ ወዘተ) እንደምትጠቀሙና ከዚህ ዘዴ ጋር ያላችሁን ግንኙነት አስተውሉ
- ይህ ነገር /አካል ባለፉት አስርት አመታት ያሳለፈውን የለውጥ ሂደት አስቡ፤ በዚህም ላይ ተወያዩበት




ADDITIONAL REFERENCES

- Barad, Karen. "Nature's Queer Performativity." *Kvinder, Køn & Forskning*, no. 1–2 (2012): 25–53. Doi: 10.7146/kkf.v0i1-2.28067.
- Haraway, Donna J. *When Species Meet*. Minneapolis: University of Minnesota Press, 2008.
- Tsing, Anna. *The Mushroom at the End of the World: On the Possibility of Life in Capitalist Ruins*. Princeton: Princeton University Press, 2015.


ARTWORKS

- Forensic Architecture. 2019. *The Killing of Tahir Elçi*. HD video, 26'18". Online at: forensic-architecture.org/investigation/the-killing-of-tahir-elci.
- Idris Khan, artist. 2012. *Houses of Parliament, London*. Gelatin silver print.
- Rabih Mroué, artist. 2012. Double Shooting. Installation, 72 video frames.

CREDITS

*Mesopotamian Turtle*, by Rojda Tuğrul. Animation / drawings ink on paper (234 sheets), 148 × 210 mm, 2019.

*Knowing Tomorrow*, by Rojda Tuğrul. Instant still images (40 pieces), 85.6 × 53.98 mm, 2019. Made in Hasankeyf, Turkey.

Both work cycles were produced with the support of FWF PEEK: "DisPossession: Post-Participatory Aesthetics and the Pedagogies of Land." All images in this chapter: reproduced courtesy of Rojda Tuğrul, the artist.

በህልሜ ወጣት ነበረች
በእነዚያ ጥቁር አይኖች፤ባልተዘመረላችው
ፀሃይን ወደምንጠብቅበት ኮረብታ
ለመሮጥ እጄን ያዘች



# ዴስፒና



ኢፔክ ሃምዛውግሉ

ሲኖፕ/ቱርክ

በጣም ረዥም ጊዜ ነው ካየኋት። ሁከቱ ከተነሳበት ቀን ጀምሮ በህልሜ እምብዛም አልመጣችም። በእኔና በአካባቢዬ የሚሆነውን ለመመልከት ብቻ እንደሞት መልአክ ሆና ትከሰታለች። ትላንት ግን በህልሜ መጥታ ወደ እስር ቤቱ እንድሄድ ነገረችኝ። ከብዙ አመታት በፊት አንድ እስረኛ የልብወለድ ማንነቷን ታሪክ ፅፎ ዘላለማዊ እንዳደርጋትም አጫወተችኝ። በዚህ ዘላለማዊነቷም ከእኔ ጋር መነጋገር እንደምትችል (አስረዳችኝ)። ዝንጅብል የሚመስል ረዥም ፀጉር ያላት ቆንጆ ሴት ስትሆን ዴስፒና የጋራ ስማችን እንደሆነ ነግራኛለች። እጄንም ይዛ ወደ እስር ቤቱ አምጥታኝ (ሰዎች) የሚገረፉባቸው የነበሩ የእስር ቤቱን ክፍሎች አስጎበኘችኝ። እነዚህም ክፍሎች ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ መደበቂያችን እንደሚሆኑ (አሳወቀችኝ)።



ሲኖፕ በቱርክ በሠሜን ጫፍ በጥቁር ባህር መሃል የምትገኝ ከተማ ናት። 60,000 ሰዎች በከተማዋ ይኖራሉ። በበጋ ሰዎች በስደት ለስራ ከሚሄዱባቸው ትልልቅ ከተማዎች ቤተ ዘመድ ለመጠየቅ ሲመለሱ የከተማዋ ነዋሪ ቁጥር አምስት እጥፍ ይጨምራል። ሃገር አቀፉ የቱርክ የ2014 እና 2016 ብሄራዊ መረጃ እንደሚነግረን ሲኖፕ በቱርክ በጣም ደስተኛ ማህበረሰብ የሚኖርባት ከተማ ናት። ምንም እንኳ የሃገሪቱ መንግስት ይህንን መረጃ ቢያስተዋውቅና ቢለፍፍም የከተማዋ ነዋሪዎች ስለዚህ መረጃ ሰምተው እንደማያውቁ ይነግሩናል።

የሲኖፕ መልክአ ምድር አረንጓዴና ሰመያዊ ቢሆንም ከፍተኛ የቆሻሻ ችግር ያለባት ከተማ ናት። ዋነኛው የከተማዋ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አሳ ማጥመድ ሲሆን በ2013 በቱርክና በጃፓን መንግስታት መካከል በተደረገ ውል በከተማዋ

↑ Video still, *Despina,* by İpek Hamzaoğlu, 2021

→ Sinop Fortress Prison Museum; photo by İpek Hamzaoğlu, 2019



የውሃ ተርማል ሀይል የሚያመነጩ እና የኑክሊየር ኢንዱስትሪዎችን ለመገንባት ስምምነት ተፈራርመዋል። በሁሉም እድሜ ክልል የሚገኙ በከተማዋ የሚኖሩ ሴቶች እና ወንዶች ይህን በግል ባለሃብቶችና መንግስታት መካከል የተደረገውን ስምምነትና ፕሮጀክት ቢቃወሙትም መንግስት ግን የከተማዋ የስነ ምህዳር ንቃት ሀሊና ከፍ ያለ መሆኑን በማወጅ ይህን የህዝብ ተቃውሞ ያስተባብላል። የከተማዋ ነዋሪዎች በሲኖፕ ረዥም ታሪክ ይኮራሉ። ሆኖም ግን ሲኖፕ በግሪክ እና አርመኖች እንዳይነገርና እንዲረሳ የሚፈለግ ብዙ የመከራ ታሪክን ያስተናገደች ከተማ ናት። ሲኖፕ የሚለውን ስሟን ያገኘችው ስለ ከተማዋ ከሚነገሩ አፈ-ታሪኮች እና የስነ ፍጥረት (Origin) ታሪኮች ነው። እንደ አንዱና በስፋት እንደሚነገረው አፈ ታርክ ከሆነ ከተማዋን የመሰረተቻት የአማዞን ንግስትና የውሃ አማልእክት የሆነችው ሲኖፕ እንደሆነች ይነገራል።

ይህችን ከተማ ከቅኝ ግዛት ለመጠበቅ ግሪኮች ከክርስቶስ ልደት በፊት በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ምሽግ እንደሰሩ ይነገራል። የተለያዩ ስልጣኔዎች:- ፋርሶች የፖንስ ዘውዳዊ ስርአት፣ሮማውያን፣ቤዛንቲኖች፣ሴልጁኮች እና የካንዳር ቤይሊኮች ቅኝ እንደገዟት እና የጦር ሰፈር አቋቁመው ምሽጎቿን እንዳድሱ እና እንዳስፋፉ ይነገራል። ኦቶማኖችም በ1887 የተወሰኑትን የከተማዋን ምሽጎች ወደ እስር ቤት ለውጠው "የሃሳብ ወንጀል" የፈጸሙ ጸሀፊዎችን፣ ፖለቲከኞችን እና ምሁራኖችን ከትልልቆቹ ከተሞች (ከኢስታንቡልና አንካራ) አምጥተው እንዳሰሩ የታሪክ መረጃዎች ያሳያሉ።

ባለፉት አስርት አመታት ከከተማዋ ጋር ያለኝ ግንኙነት ሴት አያቴንና ሌሎች ቤተሰቦቼን ከመጠየቅ አልፎ ሲያኖፔል የተባለውን የከተማዋን የአርት ፌስቲቫል እንደ ስነ ጥበብ ሰራተኛና የስነ ጥበብ አጥኚ ወደ መጎብኘት ተቀየረ። አንደኛው የፌስቲቫሉ አውደ ርእይ ከ1939 ጀምሮ እስር ቤት በነበረና ከ1999 ጀምሮ ደግሞ ወደወህኒ ቤት ሚውዚየምነት የተቀየረ ቦታ ነው። ቱርኮች ስለ



ከተማዋ የሚያውቁት ዋናው ነገር ሲኖፕ አሰቃቂ እስር ቤቶች ያሉባት ቦታ እንደሆነች ሲሆን ወህኒዎቹ በታፈጉ እና ዝቅተኛ ስፍራ ውስጥ በመሰራታቸው የተነሳ ክብሪት እንኳን ማቀጣጠል አስቸጋሪ እንደሆነ ይነገራል። የወህኒ ቤቶቹ አሰቃቂ መኖሪያዎች ከሚሰራጩት ብዙ ታሪኮች ባሻገር ሳባህቲን አሊ በተባለ ከኢስታምቡል ተግዞ በሲኖፕ የታሰረ ታዋቂ ገጣሚና ጸሃፊ የታሰረባቸውን ጊዜያት የሚተርኩ የወህኒ መዝሙሮች (Prison Ballades) በጽሁፍ በስፋትና በፍጥነት ተሰራጭተው ይገኛሉ። ይህ የግጥም ስራ በኋላ በከሬም ጉነይ “አልዲርማ ጎኑል” (“Heart Nevermind”) ወይንም “ግዴለም ልቤ” በተባለው ጽሁፍ ተዘጋጅተው ኤዲፕ አክባይራም በተባለው ድምፃዊ የፖለቲካ ግጭቶች በተበራከቱባቸው የ1970ዎቹ አመታት ተቀንቅነዋል። የ1970ዎቹ የሁከት አመታት በመጨረሻ በ1980 በተካሄደ መፈንቅለ መንግስት ተቋጭተዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እነኚህ ዘፈኖች በተለያዩ ሰዎች የተዘፈኑ ሲሆን ድምፃውያኑም በዘፈኖቹ የዘት የተነሳ ብዙ ዛቻ ደርሶባቸዋል።

በ2017 የስነ-ጥበብ ስራዬን እንዳቀርብ በሲኖፕ የስነ ጥበብ ፌስቲቫል (biennale) ተጋበዝኩ። ለዚህ ፌስቲቫል አጫጭር ትእይንት ያለው ድራማ በማዘጋጅበት ጊዜ ለአንድ የኑክሌር ፋብሪካ ግንባታ ሲባል እየተቆረጡ ስለነበሩ የከተማዋ ዛፎች የሰማሁት ዜና ከአይምሮዬ ሊወጣ ባለመቻሉ ስለ ጉዳዩ ማግኘት የቻልኩትን ሁሉ መረጃ ማሰባሰብ ጀመርኩ። ነገር ግን ያገኘሁት ዜና የፈረንሳዩ አቬራ እና የጃፓኑ ሚትሱቢሺ ከባድ ኢንዱስትሪ ካምፓኒዎች ከጥቂት አመታት በፊት ከቱርክ መንግስት ጋር በተፈራርሙት ውል መሰረት በአንዷት የቱርክ ሠፈር የእንዱስትሪው ግንባታ እንደሚደረግ ከማተታቸው በስተቀር ስለሁኔታው ብዙ መረጃ ማግኘት አልቻልኩም። ከታሪክ እንደምንረዳው የቱርክ መንግስት የኑክሌር የሃይል ማመንጫ ለመስራት ከ1950ዎቹ ጀምሮ ፍላጎት እንደነበረው ይታወቃል። የኒውክሌር ቴክኖሎጂ ጉዳይ እንደ ሃይል ማመንጫነትና የጦር መከላከያነት በቱርክ የተለመደ ወሬ እየሆነ መምጣት የጀመረው በአሜሪካና በሶቪየት ህብረት መካከል የነበረው የፖለቲካ ፍጥጫ እየተጋጋለ በመጣባቸው




በ1950ዎቹ ነበር። ቱርክ የሰሜን አትላንቲክ ቃልኪዳን ድርጅት (NATO) አካል በመሆኗ የተነሳ አሜሪካ “በቀዝቃዛው ጦርነት” ሀመን ከ1960 እስከ 1993 በሲኖፕ የጦር ሰፈር አቋቁማ ነበር። በሲኖፕ የባህር የላይኛው ሰርጥ አካባቢ አሜሪካ ሁለት የስለላ መሳሪያዎችን (Radars) በአንድ ኮረብታ ጫፍ ላይ በመገንባት (አሁን እነዚህ መሳሪያዎች ተነስተዋል) ሶቪየት ህብረትን በጥቁር ባህር በኩል ትሰልል ነበር። በዚህም የተነሳ ይህ የስለላ መሳሪያዎቹ የተገነቡበት





ኮረብታ የከተማዋ አይነተኛ ምልክት ሆኖ ቆይቷል። በ2017 በጋ አካባቢ በሲኖፕ በቆየሁበት ጊዜ ስለ ኒውክሌር ፋብሪካው ለማጣራት ብሞክርም አባሊ በተባለች ሰፈር ፋብሪካውን ለመስራት እንደታቀደ ከተነገረኝ ሌላ ግልጽ መረጃ ማግኘት አልቻልኩም ነበር። በመሆኑም አንዷት የምወዳት አክስቴ ፋብሪካው ሊሰራ ወደታቀደበት ትክክለኛ ስፍራ እንድትወስደኝ ጠየቅኳት። ብዙ ያልተጨበጡ መረጃዎችን ከሰበሰብን በኋላ ከአየር ሳተላይት ባገኘነው ካርታ አማካኝነት 650,000 ዛፎች የተጨጨፉበትን አካባቢ የኒውክሌር ኢንዱስትሪው የሚገነባበት ቦታ እንደሆነ ደረስንበት። ከባህር ሰርጡ ወጥተን ወደ ከተማይቱ ማእከል ነዳን። ደኑ በትልልቅ ማሽኖች ተጨፍጭፎ የተሰራውን መንገድ ይዘን ስንነዳ አቅጣጫ ስተን ጠፋን። እየነዳን መንገዳችንን ስንፈልግ ኦና እና ማንም ያልሰፈረበት ቦታ አገኘን። ስፍራው ምንም ዛፍ፣ እንስሳትና ህይወት ካለመኖሩ የተነሳ አካባቢው ከባድ የተፈጥሮ አደጋ የደረሰበት ይመስላል። መሬቱን የከፈለው ግዙፍ ግምሳት ምንም ህይወት የሌለበት በመሆኑ የሚሰቀጥጥ ስሜትንም ይፈጥራል።

በጥቁር ባህር ዳርቻ ከ400 በላይ የተለያዩ የሀይል ማመንጫ ኢንዱስትሪዎች (በውሃ ሀይል ኤሌክትሪክ የሚያመነጩ ኢንዱስትሪዎች፣ የተርማል ሃይል ኢንዱስትሪዎችና አንድ የኒውክሌር ሃይል ማመንጫ) በአሁኑ ጊዜ ለመገንባት በእቅድ ላይ ይገኛሉ። የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫዎች ባለፈው አንድ አመት ብቻ 203 ደርሰዋል። ተጨማሪ 143 ወደፊት ለመገንባት ታቅደዋል። የትኛውም ግንባታ እና እቅድ ግን ያለ ተቃውሞ አልተካሄደም። በሲኖፕ ክፍለ ግዛት የምትገኝ አንዷት ትንሽ ከተማ ግምባታ የሚያካሂዱ ሃይሎችን በተሳካ በተቃውሞ ስራቸው በ2016 እንዲቋረጥ ማድረግ ተችሎዋታል። የከተማዋ ነዋሪዎች መሬታቸውን እና የውሃ ምንጮቻቸውን ከእነዚህ ነጣቂ የንግድ እና የመንግስት ሃይሎች ለመጠበቅ ከመቻላቸውም በላይ በ2013 በጌዚ (ቱርክ) የተነሳውን አመጽ እና ሌሎች በአገሪቱ ለሚደረጉ ተመሳሳይ ትግሎች አርአያ ሆነዋል።

የዚህ “ዴስፒና” የተባለው ፕሮጀክት መነሻ ሀሳብ የመነጨው የሲኖፕ ነዋሪዎች ከወህኒ ቤቶቹ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመረዳት እንዲሁም የወህኒ ቤቶቹ አሠቃቂ ታሪክ በአካባቢው ላይ ያሳደረውን ማህበራዊ ተፅዕኖ ከመገንዘብ እና

↻ Sinop Fortress Prison Museum; photos by İpek Hamzaoğlu, 2019

“የመናፍስት ጉብኝት ስጋትን ያስከትላል። የጊዜን የተለመደ ፍሰትንም ይቀይራል። በተለምዶ ያለፈ፣ የአሁን እና የሚመጣ ብለን የጊዜን ተከታታይነት የምንቀምርበትን ስርአት ያፋልሳል። እነዚህ መናፍስት የሚመጡት የሚወክሉት መከራ እንዳይታይ ሊከለልና ሊጨቆን ሲሞከርና ሙከራው ሳይሳካ ሲቀር ነው።”

— Avery F. Gordon, “Some Thoughts on Haunting and Futurity”



በአካባቢው ስነ-ምህዳራዊ ንቃተ ህሊና የተቀሰቀሰ የሀይል ማመንጫ ግንባታዎች ተቃዎሞ አማካኝነት ነው። ይህ ፕሮጀክት በፊልም የቀረበና በሲኖፕ የሚሰራው የኑክሌር ሃይል ማምንጫ ሊያስከትለው በሚችለው ሰው ሰራሽ አካባቢያዊና ስነ ምህዳራዊ ውድመት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው። የዚህን የአካባቢ አጥኚዎች የተነበዩትን ስነ ምህዳራዊ ውድመት የድህረ-አርማጌዶንን አላባዎች በመጠቀም ያርማጌዶን ዘማች የሆነ ጣረ ሞትን የምትዋጋ ዴስፒና የምትባል ወጣትን ታሪክ ማእከል በማድረግ የተሰራ ፊልም ነው። በኒውክሌር አርማጌዶን ሳቢያ የተለያየ ህይወት ያላቸው አካላት ላይ የሚደርሰውን የብዝሃ ህይወት ውድመት የአየር እና የውሃ መበከል፣ የዘረመል እና የአፈር መመረዝ፣ የቆሻሻ ናዳ መከማቸት፣የደን ጭፍጨፋ፣ የአዝርዕት መጥፋት፣የአገር በቀል እውቀቶች፣ዘዴዎች እና ባህሎች መጥፋት እና መሬት ነጠቃ ይህ ጣእረ ሞት ወደ ህይወት እንዲመጣ እንዳደረገ በማሳየት ይህ ኩነት የአካባቢው ማህረሰብ የጋራ ንቃተ ህሊናን እንዴት እንደቀረፀ አሳያለሁ። ዴስፒና ከህልም ትውስታዋ፣ እንደ ገርዜ እና ጌዚ ህዝባዊ ትግሎች፣ የቆሰሉ የመሬት ቅሪቶች፣ ፍርስራሾችና መናፍስት እንዲሁም ከአካባቢው ትውስታ እና ሃዘን ትርክት የምታገኘውን መልእክት በማሰባሰብና የትግሏ መመሪያ በማድረግ የአካባቢ ውድመት የወለደውን ይህን ጣእረ ሞት ትዋጋዋለች። በፊልሙ ይህችን ገጸ ባህሪ እየተከተልን በመልክአ ምድሩና በሰዎች



ላይ የደረሰውን ጉዳትና ሰቆቃ ለመገንዘብ የምታደርገውን ጥረት እንከተላለን። የአሁኑን ዘመን ለመረዳት ካለፈው ዘመን ማግኘት የምንችለውን መረጃ ሁሉ እንሰበስባለን።

↑ Video still, *Despina*, by İpek Hamzaoğlu, 2021

“በአማራጭ ታሪኮች ይሆናል፣ በጨነገፉ ነገዎች ግርዶሽ፣ ሊሆኑ በሚችሉ መልካም ወደፊቶች መናፍስታዊ ጉብኝት ውስጥ ሆነን የመናፍስቱን ድምጽ ስናዳምጥ አንዳዴ መደረግ ስላለበት፣ አንዳንዴ ስለማይመለስ ትዝታ፣ ሌላ ጊዜ ስለ ጸጸት፤ ደግሞም ሌላ ጊዜ አስቸኳይ መደረግ ስላለበት ነገር ይነግሩናል። መደረግ ያለበት ነገር አስቸኳይ ሲሆን ከዚህ ቀደም ብሎ፣ በፊት፣ እንዲያውም ከረዥም ጊዜ በፊት፤ ምናልባትም ሁል ጊዜም መደረግ እንደነበረበት ይሰማናል። መደረግ ያለበት ነገር አስቸኳይ ሲሆንብን ለውጥን ነገ መጠበቅ እንደማንችል ይሰማናል። ለውጥ አሁን ያስኘናል! ነገር ግን መጠበቅ አይቀርም-- አንዳንዴ በትእግስት፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ያለ ትእግስት።”

— Avery F. Gordon, *The Hawthorn Archive*

“አንድ መንፈስ ሲጎበኝ ያ ጉብኝት እውነተኛ እነደሆነ ጥያቄ ውስጥ አይገባም። መንፈሱ የአድራጊ ምኞት ተነሳሽነት እና አቋም አለው። ምኞቱን መቀበል ግድ ይላል። ልናናግረውም ይገባል።”

— Avery F. Gordon, *Ghostly Matters*







↑ Video stills, *Despina*, by İpek Hamzaoğlu, 2021






“ምስል በተቀሰቀሰ ስሜት እና ንቁ እውቀት መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል። ቃላት ደግሞ ገመድ ሆነው ድልድዩ ተዘርግቶ እንዲቆይ ያደርጉታል። ምስሎች ከቃላት የበለጠ ቀጥተኛና ለምናባዊ እውቀት (unconscious) የቀረቡ ናቸው። የምሰል ቋንቋ በቃለት ከማሰብ ቅድሚያ አለው። ዘይቤአዊው አእምሮ ከምክንያታዊው ንቃተ እውቀት (unconsciousness) ቅድሚያ አለው።”

— Gloria Anzaldúa, *Borderlands / La Frontera*

መሳሪያ

# በፍርስራሽ ውስጥ ለመኖር የሚያገለግሉ አባሪ ካርዶች (Association Cards for Living in Ruins)

በፍርስራሽ ውስጥ ለመኖር የሚያገለግሉ አባሪ ካርታዎች የትርክት ቅስቀሳ መሳሪያዎች ናቸው። ምስልና ቃላት ያሉባቸው ካርታዎች በእጃቸው የያዙ ተሳታፊዎች የተለያዩ ትርክቶች፣ገለጻዎችና ታሪኮች ፈጥረው እንዲናገሩ የሚያደርግ መሳሪያ ነው። የፅኑ አረሞች የስነ ጥበብ እና የጥናት ሰዎች ከጥናቱ ቦታ መልከዐ-ምድር፣መናፍስት፣የነጠቃ ፕሮጀክቶች፣ የእመው እና አበው አለማት (ancestral worlds) ፣ እንስሳት፣ሰዎች፣ተቋማት እና ቁሳቁሶች ጋር የተያያዙ ቃላት እና ምስሎች የተሳሉባቸውን እነዚህን ካርታዎች ይመርጣሉ።ቃላቶቹ ወደተለያዩ የቡድኑ አባላት ቋንቋዎች ማለትም አማርኛ፣ጀርመንኛ፣ኩርድኛ፣ፖርቱጋልኛ፣ስፖኛ፣ቱርክኛ እና እንግሊዝኛ ይተረጎማሉ። ካርታዎቹ ላይ የሚገኘው ባዶ ቦታ ካርዶቹን በያዙ አባላት በራሳቸው ቋንቋ ይሞላሉ። ቃላቶች እና ምስሎች አንድ ትርጉም ብቻ ሳይሆን ብዙሃ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል። አንድን ቃል እና ምስል አንድ ላይ ካመጣነው ደግሞ ቃሉ ወይንም ምስሉ ብቻውን ሲታይ ከሚሰጠው ትርጉም ሌላ ስሜትና ትርጉም ሊኖረውና ሊገልጽ ይችላል። በፍርስራሽ ውስጥ ለመኖር የሚያገለግሉ አባሪ ካርታዎች ያልተጠበቁ የታሪክ መስመሮችን ለመክፈት የሚደረግ ግብዣ ነው። እነዚህ ካርታዎች በተሳታፊዎች ይያዛሉ ከአንዳቸው ለሌላቸው ይተላለፋሉ። ይህ የሚደረገው መልስን ለማግኘት ነው።እነዚህ ካርዶች በካናዳዊው ኢላይ ራማን በሰራቸው ኦ ኤች (OH) ካርታዎች ተምሳሌትነት የተፈጠሩ ናቸው። ኦ ኤች ካርታዎች 88 ምስሎች ያሏቸው ካርታዎችና እነሱን የሚያሟሉ ሌሎች 88 ቃላት ያሏቸው ካርታዎች ናቸው። አጠቃቀማቸው ካርታዎቹን በያዙ ሰዎች እሳቤና ገለጻ ላይ የተመሰረተ ነው። የስልጣን ተዋረድን ለሚያንጸባርቁ ጨዋታዎች እና የውድድር መንፈስ ዕድል ካለመስጠታቸውም ባሻገር አሸናፊዎችና ተሸናፊዎች የሉም። ያሉት ታሪክን እርስ በእርስ የሚደማመጡ ሰዎች ብቻ ናቸው።








ገቢር

## ገቢሮች

የተሳታፊዎች ተግባራት የተለያዩ ሲሆኑ በጋራ በወርክሾፖች ውስጥ የሚከወኑ ናቸው። ከእነዚህ ገቢሮች በፊት በንጥቂያ ፖለቲካ የተጎዱ ሰዎች ቡድን እንዲመሰርቱ ይደረጋል። ይህን ለማድረግ በፍርስራሽ ውስጥ ለመኖር የሚያገለግሉ አባሪ ካርታዎች እና የባህሪ እና ሁኔታ ካርታዎች (character and condition cards) የስፈልጋሉ። ከዚህ የገቢር መፅሃፍ ጋር በአባሪነት የተቀመጡትን ካርታዎችን ወስዳችሁ እነዚህን ካርታዎች አዘጋጁ። የእንዚህን ተግባራት ዋና አላማ ካርታ ያዦችን አንድ ላይ የቀረቡትን የምስል እና የቃላት ካርታዎች በራሳቸው መንገድ ትርጉም እንዲሰጧቸው፣ ስለትርጉሞቹ ምንነት እንዲያስቡ፣ እንዲያውጠነጥኑና ትርጉማቸውን እንዲገምቱ ማድረግ ነው። በተጨማሪም የእነዚህን ተግባራት አላማ የሰዎችን የመስማት ችሎታን ማሳደግና ለነጠቃ መልስና መፍትሄ የሆኑ ልቦለዳዊና የምንመኛቸውን አለማት ማለም እንዲያስችሉን ነው።

### ምስሎችን ማቀናጀት

ይህ ተግባር በነጠቃ ዞኑ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካላትን ከምስል እና ቃላት ካርታዎች ጋር በነፃ ቅንጅት ማገናኘት ነው።ይህ ገቢር ለ20 ደቂቃዎች ይቆያል

- ከአንድ ሌላ የቡድን አባል ጋር ተጣመሩ።እያንዳንዱ ሰው አንድ የምስል እና አንድ የቃል ካርታ ይወሰድ/ትውሰድ
- በአንድ የነጠቃ ዞን ላይ የእግር መንገድ አድርጉና በዚያ አካባቢ የደረሰ በደልና የሃይል እርምጃ ምን ያህል እንደሆነ ለ2 ደቂቃዎች አስቡ። የነጠቃ ዞኑ ሌላ ቦታ ከሆነ ስለ ቦታው ለማሰብ ሞክሩ። የምትሰሙትንና የምታሸቱትን ነገር አስተውሉ
- በአካባቢው የእግር መንገድ ስታደርጉ ስለ ቦታው ገደቦች አስቡ። ለእንዳንዱ የቡድኑ አባል ስለካርዶቻችሁ ለአመስት ደቂቃ አስረዱ
- ለመቀጠል ካርታችሁን እና ታሪካችሁን እንዲሁም ያቀናጃችሁትን ካርታ ይዛችሁ አንድ ላይ አምጧቸውና አዲስ ትርክቶችን ፍጠሩ።



↻ Left & right: Documentation from the workshop "Storytelling for the Apocalypse" in Sinop, 2019 by İpek Hamzaoğlu & Malu Blume

“ትላንት ማታም የሚመላለሰውን ህልሜን አየሁ። ምናልባትም ይህን ህልም ልጠብቀው ይገባኝ ነበር። ህልሙን የማየው ስታገል፣ የራሴን መንገድ ስስት እና ምንም አዲስ ነገር አልተፈጠረም ብዬ ራሴን ሳታልል ነው። ህልሙ የሚመጣብኝ የአባቴ ልጅ ለመሆን ስሞክር ነው። ዛሬ ልደታችን ነው። እኔ 15 ዓመት አባቴ ደግሞ 55 ይሆነናል። ነገ አባቴን፣ ማህበረሰቡን እና እግዚያብሄርን ለማስደሰት እጥራለሁ። ስለዚህ ትላንት ማታ ይህ ሁሉ ውሸት እንደሆነ እንዳስብ የሚያደርገኝ ህልም አየሁ። ስለዚህ ህልም መጻፍ ያለብኝ ይመስለኛል ምክንያቱም ይህ የውሸት ህይወት በጣም ያሰጋኛል።”

— Octavia E. Butler, *Parable of the Sower*



ገቢር

---

### የግለሰቦችን ህልም አንድ ላይ ማምጣት

እንቅስቃሴው የዳይስቶፒያን እና የዩቶፒያን ማለፊያ የወደፊት የጋራ ህልሞች የመቀየር አቅምን አንድ ለማድረግ ነው። እንቅስቃሴው ከሁለት እስከ አስር ሰዎች በቡድን ሆነው አብረው እንዲጫወቱት የታሰበ ነው።

- ከነጠቃ ዞኑ አንጻር የራሳችሁን አቋም አስተውሉ
- ስለ አንድ የግል ፍርሃታችሁ አስቡና ከነጠቃው ዞኑ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ አሰላስሉ
- ይህንን ፍርሃታችሁን በአይምሮአችሁ ይዛችሁ አንድ የቃልና የምስል ካርታ ስሩ።
- የኦክቴቪያ ኢ በትለርን Parable of the Sower የተባለው መጽሃፍ ላይ ያለውን መግቢያ የመጀመሪያ አንቀጽ አንብቡ (1)
- የኦክቴቪያ ኢ በትለርን ጀግና ህልም ከራሳችሁ ፍርሃት እና ካርታዎች ጋር አዛምዱ
- ክብ ሰርታችሁ አሳባችሁን እና የራሳችሁን የካርታ ቅንጅት ለሌሎች የቡድኑ አባላት አጋሩ።

(1) Octavia Butler, *Parable of the Sower* (New York: Grand Central Publishing, 2000.)

ገቢር

**ነፃ የጽሁፍ ልምምድ**

ይህ ገቢር የተለየ የጽሁፍ ችሎታን አይጠይቅም። ነገር ግን ተሳታፊዎችን በነጻ እንደመጣልን በሚጻፍ የፅሁፍ ልምምድ ውስጥ በመሆን በንቁ-እውቀት (conscious) እና በቅጽበታዊ የደመነፍስ እውቀት (unconscious) መካከል ያለውን ፍሰት እንድንከፍት ይረዳናል። በእስክሪብቶ እና ወረቀት ላይ ብትጽፉ ይመከራል። ነገር ግን በኮምፒውተር ላይ መጻፍ ከመረጣችሁ ይህንን ማድረግም ትችላላችሁ። ስለ ሰዋስው አትጨነቁ ነገር ግን አረፍተ-ነገሮችን ማረቅ እንዳለባችሁ አትዘንጉ። ዋናው ነገር መጻፍ አለማቆማችሁ ነው። እስክርቢቶውን አንቀሳቅሱት መጻፍ ቀጥሉ አታቁሙ። የዚህ ገቢር ዋና አላማ የነጻ ፅሁፍ ፍሰት ልምምዳችሁን ከፍርስራሽ ውስጥ ለመኖር የሚያገለግሉ አባሪ ካርታዎች ልምምዳችሁ ጋር እንድታቀናጁትና አዲስ የተለያዩ አለሞች አንድ ላይ የሚመጡባቸውን ነገዎች እንድታስቡ ማድረግ ነው።

- የራሳችሁን አቋም ከነጠቃው ዞን አንጻር አስተውሉ
- ያላችሁን አንድ ተስፋ አስቡና ከዚህ አካባቢ ጋር አያይዙት
- ይህንን በአይምሯችሁ በመያዝ አንድ የምስልና አንድ የቃላት ካርታ አዘጋጁ
- የኤን ኬ ጄሚሲንን The Fifth Season መግቢያ አንቀጽ አንብቡ (2)
- በዚህ አንቀጽ ላይ የሚገኘውን የድሮውን አለም ትውስታ እያሰባችሁ ለ15 ደቂቃዎች ነጻ ጽሁፍ ፃፉ። ይህን ገቢር ለማከናወን ሰዐት ያዙ የደቂቃ መቁጠሪያ ተጠቀሙ።
- እያንዳንዳችሁ የፃፋችሁትን ነገር ጮክ ብላችሁ ለቡድኑ አባላት አንብቡ።

(2) N.K. Jemisin, *The Fifth Season: Every Age Must Come to an End* (London: Orbit, 2015).



↑ Video stills, *Despina*, by İpek Hamzaoğlu, 2021



“ማስታወስ ያለባችሁ የአንድ ታሪክ ማብቂያ የሌላ ታሪክ መጀመሪያ እንደሆነ ነው። ሠዎች ይሞታሉ። የድሮው ስርአት ያልፋል። አዲስ ማህበረሰቦች ይወለዳሉ። “አለም አበቃች” ስንል ብዙ ጊዜ ውሸት ነው፤ ምክንያቱም ምድሪቱ ትኖራለች: ደህና ነች።

ነገር ግን አለም የሚያበቃው እንዲህ ነው።
አለም የሚያበቃው እንዲህ ነው።
አለም የሚያበቃው እንዲህ ነው።
ለመጨረሻ ግዜ።”

— N.K. Jemisin, *The Fifth Season*











ገቢር

## ሌሎች አለማትን ማሰብ

የሁኔታ እና የባህሪ ካርታዎች የተዘጋጁት የተሳታፊዎችን እሳቤ ለመኮርኮርና በእነዚህ ካርታዎች አማካይነት ሌሎች ፍፁም ጥሩ (utopian) እና ፍጹም መጥፎ (dystopian) የሆኑ አለማት እና በእነርሱ ውስጥ ስለሚኖሩ ህይወት ያላቸው እና የሌላቸው አካላት እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። (3) የዚህ ገቢር ዋናው አላማ በፍጹም ጥሩ እና ፍፁም መጥፎ አለማት መካከል ያለውን ተቃርኖአዊ (Dialectic) ሳይንሳዊ ልቦለዳዊ ሁኔታን መሳል እንዴት እንደሚቻል ለመመርመር እንድናሰላስልና ተሳታፊዎች ተቃራኒ የሆነ የጋራ ህይወትና ህልውና ትርክትን የማመንጨት እምቅ ችሎታቸውን እንዲጠይቁና እንዲለማምዱ ለማድረግ ነው። የሰው፣ስነ-ምህዳር፣መልክአ ምድር እና ምናብ ጉዳት እና ውድመትን ማእከል ካደረጉ ትርክቶች ባሻገር ሌሎች ትርክቶችን ተሳታፊዎች እንዲፈጥሩ ለማስቻል ነው።

- ከነጠቃ ዞኑ ጋራ በተያያዘ አንድ የትግል እና የተቃውሞ ታሪክ አስቡ። ይህ ታሪክ በእናንተ ላይ የደረሰ፣በሌሎች ላይ የደረሰ ወይም ከትውልድ ትውለድ ተላልፎ የሰማችሁት ታሪክ ሊሆን ይችላል፡
- አንድ የሁኔታ እና አንድ የባህሪ ካርታ ምረጡ
- የሰአት መቁጠሪያ አዘጋጅታችሁ ነጻ ፅሁፍ ለ 15 ደቂቃዎች ፃፉ። በፅሁፋችሁም በሁኔታ ካርታው ላይ ተመስረታችሁ ስለ አንድ አካል አንድ ቀን ውሎ ፃፉ። ይህን ስታደርጉ ያሰባችሁትን የትግል ታሪክ ግምት ውስጥ ክተቱ።
- ከፃፋችሁት ፅሁፍ 3 ቃላትን በዘፈቀደና በደመ ነፍስ ምረጡ።
- እነዚህን ሶስት ቃላት በመጠቀም የሰዐት መቁጠሪያችሁን በመጠቀም ለ5 ደቂቃዎች ግጥም ፃፉ
- ታሪካችሁ እና ግጥማችሁን ለተቀሩት የቡድኑ አባላት ጮክ ብላችሁ በማንበብ አጋሩ።

(3) The “Condition” and “Character Cards” were developed by İpek Hamzaoğlu & Malu Blume for their workshop “Storytelling for the Apocalypse” at the International Sinop Biennial (Sinopale 7) as part of the FWF PEEK: “DisPossession: Post-Participatory Aesthetics and the Pedagogies of Land.”



↻ All images: Video stills, *Despina*, by İpek Hamzaoğlu, 2021

መሳሪያ

# ሃሜት

ሃሜት በምናወራበት ጊዜ ጠቃሚ መረጃ እንለዋወጣለን። ሃሜት ግለሰቦችን እና ማህበረሰብን የሚያገናኝ የንግግር አይነት ነው። ሃሜት የሚያወሩትን ሰዎች ከልሎ ማህበረሰብ ስለሚያወራው ሀሜትና ታሪክ ያለውን ስሜት ግልጽ ያደርጋል።የማህበራዊ ስርአትን/ግብረገብን በዘላቂነት ያዋቅራል። ሃሜቱን የሚያዳምጡ ሰዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ሀሜቱ/ታሪኩ እንዴት እንደሚታይ በማዳመጥና እንዲሁም በመሳተፍ ሊገነዘቡ ይችላሉ። ሃሜት የመረጃ ክፍተቶችንም ይሞላል።አንዳንድ ጊዜም መረጃን በሚደበቁ እንደ መንግስት ያሉ አካላት የተሰወሩ መረጃዎችን ቀዳዳዎችን እና ውሎችን በመፈለግ በተግባር ላይ የዋሉ ውሳኔዎችንና ስልጣን ያላቸውን አካላት ለመረዳት ይጠቅማል።በማህበረሰብ ዘንድ የሚዳብርን ትብብርና አንድነትን በማጎልበት ስልጣንን እና ሃይልን ለመገዳደር መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። ይህንን ደግሞ የሚያደርገው በሃሜቱ የሚሳተፉ የማህበረሰቡን አካላት ስልጣን ካላቸው ሀይሎች ከልሎ ነው። ሃሜት ማንነትን በመደበቅ የሚደረግ ንግግር እና ትረካ ነው። ከየት እንደተጀመረ ሳይታወቅ በብዙዎች ሲነገር እና ሲሰራጭ ይታያል። ከአንድ ቦታ አይመጣም፤ ነገር ግን ሁሉም ቦታ አለ። ከስልጣን ምንጭ አካባቢ ይዘዋወራል ስልጣንንም ያደፈርሳል፣ ስም ያጠፋል፣ ይቃወማል ግን የተነቀሉትን የተጎዱትን ክፍሎች እራሳቸውን ከስልጣን ቁጣና ቅጣት እንዲከላከሉ መሳሪያ ይሆናቸዋል። የመረጃ መለዋወጫ መንገድ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ አይረቡም የተባሉ መረጃዎችን እውቀት በማድረግ ገዢ እና ዋና ትርክት ያደርጋቸዋል። ዋና እና ግዢ የነበሩትን ትርክቶችን ደግሞ አይረቤ ያደርጋቸዋል ይፈታቸዋል።

ሲልቪያ ፌዴሪቺ እንደምትለው “ሃሜት” (gossip) የሚለው ቃል አሁን ከተሰጠው በጎ ያልሆነ ትርጉም በፊት በመካከለኛው የእንግሊዝ ክፍለ ዘመን የሴቶችን ጓደኝነት የሚገልጽ ቃል ነበር (5) ። ፌዴሪቼ እንደምትለው ካፒታሊስታዊ ስርአት እና ማህበረሰብን ለመመስረት ሲባል “የሴቶችን ክብር ለማኮሰስ መሞከሩ የቱን ያህል የሴቶችን እቅም እና ማህበራዊ ቁርኝት እንደጎዳው እና (ለሃሜት) አዲስ ትርጉም” (6) በመስጠት የሃሜትን ጠቀሜታ እንዳሳነሰው የሚያሳይ ምሳሌ ነው። በመሆኑም በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን “ሃሜት” የሴቶች አጋርነት እና ጓደኝነትን ከመግለጽ ይልቅ ስራ-ፈቶች ሰውን የሚቦጭቁበት የስንፍና ተግባር አድርጎ በመሳል በአሁኑ ጊዜ ሴቶችን እርባና የላቸውም የሚለው አስተሳሰብ ለማስረገጥ መሳሪያ ሆኖአል። ሆኖም ሃሜት አስፈላጊ ቋንቋ እና ለብዙ ሴቶች ከእርስ በእርስ ግንኙነቶቻቸው የሚያገኙት እውቀትንና ትብብርን የሚያዳብሩበት መሳሪያ ነው። ሃና ብላንክ (7) እንደምትለው “የሃሜት ድሮች ማን መታመን እንደሚገባው፣የት ላይ ጥንቃቄ መውሰድ እንደሚገባ፣ማን እድለኛ እንደሆነች እና እንዳልሆነች” በማሳወቅ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ታስረዳናለች። የጭቆናንና የሃይል ግንኙነትን ለማስቀጠል ለሚጥሩ ገዢ ትረካዎች አማራጭ እና ተጻራሪ ትረካን በማቅረብ ሃሜት ለግፉአን አይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ያገላግላል። ሃሜት ገዢ ትርክቶችን በመሞገትና በማጋለጥ እንዲሁም የገዢ ትርክቶችን ለመፈረካከስ በሚያስችል እምቅ ሀይሉ የተነሳ ቁልፍ የግፉአን መሳሪያ ሊሆን ይችላል። እንደ ቫይረስ ይዛመታል፣ይስባል፣ይጣፍጣል እንዲሁም ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ይጋባል (ይተላለፋል)። በክዋኔ የተመራ እና ደረቅ ያልሆነ የመረጃ ቅብብሎሽ ዘዴ ከመሆኑም ባሻገር በሚጠቀመው ቋንቋ፣ በአማራጭ እውነትነቱና በማራኪ አቀራረቡ ሳቢያ የጭቁኖችን/ተነቃዮችን ክፈተት የሚሞላ መሳሪያ ነው።

(5) Silvia Federici, *Caliban and the Witch: Women, the Body and Primitive Accumulation* (Brooklyn: Autonomedia, 2004), 100.
(6) Ibid., 186.
(7) Hannah Black, “Witch-hunt,” *TANK Magazine* 8, no. 11 (2017); online at: tankmagazine.com /issue-70/features/hannah-black.





ገቢር

# ሃሜት ሰምቻለሁ

የተለያዩ ቋንቋዎች ሃሜትን የሚጀምሩበት የራሳቸው መንገድና ዘዬ አላቸው።በቱርክኛ ሃሜት ለመንገር ሃላፊ ጊዜ ሰዋሰውን እንጠቀማለን። ይህ ገቢር በጋራ የሚከወን ተግባር ነው።የገቢሩ ዋና አላማ የሃሜትን ክዋኔአዊነት ለማሳየት እና ይህ ባሕሪው እንዴት ሚዲያ በከፍተኛ የመንግስት ቁጥጥር ስር በሆነበት አውድ ውስጥ እንዴት ያለ አይነተኛ መረጃን የማሰራጫ መንገድ እንደሆነ እንድናጤን ማደረግ ነው። ለዚህ ገቢር ከዚህ መጽሃፍ ጋር አባሪ የተደረጉትን የሁኔታ ካርታዎችን በመመልከት በመቁረጥ አዘጋጁ።

ከታች በተለያዩ ቋንቋዎችና አውዶች የተዘጋጁ የሃሜት መጀመሪያ መንገዶች በምሳሌነት ቀርበዋል። እነዚህ ምሳሌዎች እንዴት አንድ ላይ ሊመጡና ሊቀናበሩ እንደሚችሉ ተለማመዱ

- *Sana bir şey söyleyeceğim ama kimseye söylemeyeceğine yemin et…* (ከቱርክኛ፤ ለማንም ላለመናገር ቃል ግቢ…)
- *Oh senti questa…* ((ከኢጣልኛ፤ ይህን ስማ…)
- *Valla ben söyleyenlerin yalancısıyım.* (ከቱርክኛ፤ የሰማሁትን ነው የምናገረው)
- *Ça reste entre nous.* (ከፈረንሳይኛ፤ በእኔና ባንተ/ች ይቅር…)
- *Tu me promet tu garde ça pour toi.* (ከፈረንሳይኛ፤ ካንች ጋር እንደሚቀር ቃል ግቢልኝ)
- *J’ai un dossier de ouf sur X.* (ከፈረንሳይኛ፤ ስለ እገሌ ያበደ ወሬ አለኝ)
- *Ej, słuchaj… właśnie słyszałam, że…* (ከፖሊሽኛ፤ ስሚ … ምን ሰማሁ መሰለሽ/ህ)
- *Laf aramızda.* (ከቱርክኛ፤ በኔና ባንች/ተ መሃል ብቻ)
- *Benden duymuş olma.* (ከቱርክኛ፤ እኔ አልነገርኩሽም አሉ)
- (ከሩሲያኛ፤ ወሬዎች እየተራመዱ ነው…)
- *Te tengo un chisme…* (ከስፓኒሽኛ፡- ሀሜት ደርሶኛል…)
- *Doszły mnie słuchy, że…* (ከፖሊሽኛ፤ ወሬ ደርሶኛል)
- *Ay bu kulaklar neler duydu, neler işitti.* ((ከቱርክኛ፤ እነዚህ ጆሮዎች የያዙት እና የሰሙት…)

↑ Video still, *Despina,* by İpek Hamzaoğlu, 2021



## ገቢር

- ከሁሉም ተሳታፊዎች ጋር ክብ ሰርታችሁ ተቀመጡ
- አንድ የሁኔታ ካርታ በመሳል የታሪኩን አለም የሚቀርጽ ቡድን ሁኑ
- አንድ የባህርሪ ካርታ በመሳል አለሙን የሚመራ ቡድን ሁኑ
- እንዴት አይነት አለም እነዚህ ካርታዎች ለመስራት እድል እንደሚከፍቱ፣ ማን መሪ እንደሚሆን፣የትኞቹ ህይወቶች የበለጠ ቦታ እንደሚኖራው የበለጠ አስፈላጊ እንደሚሆኑ እና የትኞቹ ስራዎች የበለጠ ዋጋ እንደሚሰጣቸው አስቡ።
- ከላይ በተጠቀሰው መሰረት “አንድ ወሬ ሰምቼ...” በማለት ከ2-3 አረፍተ-ነገሮች ያለው ታሪክ ጻፉ። በታሪኩም ውስጥ የበለጠ አስፈላጊ መሆን አለባቸው የምትሏቸውን አካላት ድምፆች ለማስገባት ሞክሩ።
- የሐሜትን አመክንዮ ተከትሎ በታሪኩ ላይ ተጨማሪ ዓረፍተ ነገሮችን ይጨምሩ።
- ታሪኩን በሚጨምሩበት ጊዜ ከተለያዩ አውዶች እና ቋንቋዎች የተጠቆሙትን ምሳሌዎች ለመጠቀም ይሞክሩ እና ከራስዎ ቋንቋ ተመሳሳይ አገላለጾችን በመጨመር ዝርዝሩን ለማበልፀግ ነፃነት ይሰማዎት።



↑ Video stills, *Despina*, by İpek Hamzaoğlu, 2021



ARTWORKS & FILMS


- Adanalı, Yaşar, Ayça Aldatmaz, Burak Arıkan, Elif İnce, Esra Gürakar,Zeyno Üstün, Özlem Zıngıl, and anonymous participants, artists. Since 2013. *Networks of Dispossession (Graph Commons)*.
- Al-Maria, Sophia, artist. 2018. *Wayuu Creation Myth*. Single-channel video. Online at: vimeo.com/282312230.
- Al-Maria, Sophia & Victoria Sin, artists. 2019. *BCE*. Single-channel video. See: dazeddigital.com/art-photography/gallery/26163/7/sophia-al-maria-and-victoria-sin-bce.
- Blume, Malu, artist. 2020. *The Book of S of I*. Video, 28’, color, English.
- Henriksson, Minna, artist. 2017. *Solidarity*. Linocuts.
- Karakaş, Gizem, artist. 2016. *The Ground Has Ears*. Performance.
- Lahire, Sandra, director. 1987. *Uranium Hex*. 16mm film, 11’, color, Magnetic, 4:3. LUX. See: lux.org.uk/work/uranium-hex.
- Marker, Chris. 1962. *La Jetée*. 35mm film, 28’, French/German. Argos Film.
- Treister, Suzanne, artist. 2009–11. HEXEN 2.0: *HISTORICAL DIAGRAMS: From Diogenes of Sinope to Anarcho-Primitivism and the Unabomber via Science-Fiction.* Diagram.
- Tsai, Charwei & Tsering Tashi Gyalthang, artists. 2012. *Lanyu: Three Stories*. Three-channel video installation.
- Utikal, Sofi, artist. 2016. *Reversal Tarot*. Performance.
- Weerasethakul, Apichatpong, director. 2009. *A Letter to Uncle Boonmee*. Shortfilm, 18’, Thai. Animate Projects.


ADDITIONAL REFERENCES


- Anzaldúa, Gloria. *Borderlands/La Frontera: The New Mestiza*. San Francisco: Aunt Lute Books, 1987.
- Gordon, Avery F. *Ghostly Matters: Haunting and the Sociological Imagination*. Minneapolis: University of Minnesota Press, 1997.

  — *The Hawthorn Archive: Letters from the Utopian Margins.* New York: Fordham University Press, 2018.

  — “Some Thoughts on Haunting and Futurity.” *borderlands* 10, no. 2 (2011): 1–21. Online at: averygordon.net/files/GordonHauntingFuturity.pdf.
- Scott, James C. *Domination and the Arts of Resistance: Hidden Transcripts*. New Haven: Yale University Press, 1990.


CREDITS

*Despina*, by İpek Hamzaoğlu. HD video, 2021. Shot in Sinop, Turkey. Performers: Ezgi Eczacıbaşı and Sinem Hekim. Set assistant and additional camera: Malu Blume. Music: Alican Çamcı. Soundmix: Cemil Hamzaoğlu. Very special thanks to Erkan Akliman, Malu Blume, T. Melih Görgün, İbrahim Hekim, Sinem Hekim, Mert Karaçıkay, Gülbahar Karaduman, Laura Nitsch, Selin Saraçoğlu, Büke Onur, and Osman Onur. Produced with the support of Sinope (International Sinop Biennial) and FWF PEEK: “DisPossession: Post-Participatory Aesthetics and the Pedagogies of Land.” All images in this chapter: reproduced courtesy of İpek Hamzaoğlu, the artist.

እሾሃማ ሽቦ
በግትር መናፍስት
የኀሉ
የወረቀት ላይ መስመሮች



# የወረቀት አውድማ



ጃኒን ጀምበሬ

በርሊን /ጀርመን

የእኔ የህይወት ልምድ ለናንተ ማስተማሪያ አይደለም፤ የእናቴን ጉሮሮ ስድስት ጫማ ወደታች ለመቅበርና ስቃዩዋን በነፃ ትምህርት እና በተሻሻለ መመሪያ ለመካስ አይሆንም። ከመረቀቃቸው በፊት አቧራ ለጠጡ መመሪያዎች። ከመፈጠራችን በፊት ለቀበረን ይህ ሃገር በስማችን ከመጥራቱ በፊት በሙት ታሪካችን ይጠራናል።
— Koleka Putuma, “EVERY / THREE HOURS”



የጥናቴ ስፍራ የጀርመን ቅኝ-ግዛት ዶሴ (archive) ነው። የምመለከተው በአፍረካውያን የተጻፉ የጀርመንን ቅኝ-አገዛዝ የሚቃወሙ ከ1880-1914 የተጻፉ መዝገቦችን ነው። ደብዳቤዎችን፣አቤቱታዎችን፣እና የጋዜጣ ፅሁፎችን በመፈለግ/በማጥናት እንደ ብዙ ሌሎች በአውሮፓ ቅኝ ስለተገዛው ሰው የተፃፉ ታሪክ ነን ባይ ተረት ተረቶችን እመራመራለሁ። የቅኝ ተገዥ አፍሪካዊ ሁሉን ቻይ ድምጽ አልባ፣ስም አልባ አድራጎትን (agency) ፣ ቋንቋን የተነፈገና የተገዛ ሰው ነው የሚለውን ትርክት በመሞገት ዝግጅቴን አቀርባለሁ።

በብዙ ምክንያት ይህ ጥናት፤ እንዲሁም ከጥናቱ የወጣው ታሪክ ሙሉ ያልሆነና የተበጣጠሰ ነው። ይህ የጽሁፍ ጅማሮ እንጂ ያለቀ ስራ አይደለም። እንዲያውም ጽሁፉ በጅምር ላይ ያለ ያላለቀ ማንነቱን ማጣት አይሻም።






↑ Janine Jembere, details of BArch 1001/4073 (2020)

“ፍራንዝ ፋኖን ስለ ቅኝ አገዛዝ አለም፣ ስለ አደረጃጅቱ ስለ መልክአ-ምድራዊ ገጽታው እና አይነተኛ ማንነቱን ስለሚሰራው የሃይል መንበር ሲያወሳ በመጀመሪያ የሚጠቅሰው የጦር ሠፈሩን እና የፖሊስ ጣቢያዎቹን ነው። ይህን የሚያደርገው ቅኝ ግዛት ከምንም በላይ የጉልበት ውስብስቢት (labyrinth) ስለሆነ ነው። እነዚህ የጉልበት ተቋማት ስርአቱ ሊገዛው፣ ሊያቀናው እና ደንብ ሊያስይዘው በሚጥረው መሬት እና ካርታ ላይ ተቀርጸው ይገኛሉ። ሌላው ፋኖን የሚያሳየው ነገር የቅኝ ግዛት በተገዢው አይን ግዳጅና ጥቃት በመዋቅሮቹና በተቋማቱ የተንሰራፋበት የጉልበት እና የአመጽ መነሃሪያ እንደሆነ ነው።”

— Achille Mbembe, *On the Postcolony*



ለጥናቴ የምፈልጋቸው ዶሴዎች በቡንደሳርቺፍ በርሊን-ሊችትርፌልድ የሚገኘው የጀርመን ፌደራል ቤተ መዛግብት ውስጥ ነው። ቀድሞ የፕረሺያ ካዴት ትምህርት ቤት የነበረና ከመጀመሪያው የአለም ጦርነት በኋላ ወደ ህዝብ ትምህርት ቤትነት የተለወጠ፤ ከ1933 በኋላ ደግሞ ኤስ.ኤስ የተባሉት የናዚ ጀርመን ያለፍርድ ሰዎችን የመግደል ስልጣን የነበራቸው ፖራሚሊታሪ ሓይሎች መቀመጫ ነበር።

እምቤምቤ እንደሚያስታውሰን የቅኝ አገዛዝ አስገዳጅነትና ጥቃት በስርአቱ ተቋማትና መዋቅሮች ውስጥ ተፅፈው የሚገኙ ናቸው።[1] በጀርመን የቅኝ ግዛት ስርአቱ ቁኝጮ በሆነችው በርሊን ደግሞ ይህ የቅኝ ግዛት ጉልበት ተራ መስሎ በየቦታው ላይ ተጽፎ እናገኘዋለን።የቤት መዛግብቱ ስነ-ህንጻ በውስጡ የተከናወነውን ሰቆቃ የሚጠራ እንደገና የሚከስት ገጽታ አለው። የቡንደሳርቺቭ ህንጻ በመዋኛ ቦታ እና በአረንጓዴ ስፌና ረጃጅም በሆኑ አፀዶች የተከበበ ነው።እነዚያ የሰቆቃ ተምሳሌት የሆኑ ህንጻዎች ባይኖሩ ፀጥ ያለ አረንጓዴ አካባቢ በመሆኑ ለማረፍ እና ዘና ለማለት የሚመች ቦታ ይሆን ነበር። ይህን ቦታ ለብዙ ጊዜ የጎበኘሁት እና የማውቀው ቢሆንም ለምን ሰውነቴ እንደማይወደው እና ለምን እነዚያ ህንፃዎች አሁንም ቆመው እንዳሉ አይገባኝም።

የማጠናቸውን የቅኝ ግዛት መዝገቦች በቪየና የስነ-ጥበብ አካዳሚ ቢሮ ወይም እስቱዲዮዬ ተቀምጭ እምረምራለሁ፤ አነባለሁ። ይህን ስራ ለመስራት መቀመጫዬ በርሊን ወይንም ቪየና መሆናቸውን ምጸታዊ ሆኖ አገኘዋለሁ። እነዚህ የማጠናቸው መዝገቦች በተለያዩ ቦታዎች የተጻፉና ከተለያየ ቦታ የመጡ ናቸው። ጽሁፎቹ በፊት በአፍሪካ የጀርመን ቅኝ ግዛቶች የነበሩ አሁን ካሜሩን፣ ቶጎ፣ ናሚቢያ፣ ታናዛኒያ፣ ቡሩንዲ እና ርዋንዳን የሚመለከቱ ሲሆን እነዚህቦታዎችን ጎብኝቼ አላውቅም በሃሳቤ ለመከሰትም አልሞክርም። ለዚህ ምክንያቴ ቅኝ ገዢዎች ስለእነዚህ የማያውቋቸው አካባቢዎች የነበሯቸው እሳቤዎችና እልም አስተኔዎች (fantasies) የመብት አለኝ ስሜትን ያዘሉ የቅኝ ተገዢዎችን ተሞክሮ እና ህይወት ያቀለሉ ስለነበሩ ነው።ይህ እሳቤ እና ቅኝ ግዛታዊ ጉልበተኝነት ክፉና አላዋቂ ቢሆንም በሳይንስ፣“በእውቀት” እና በኢኮኖሚያዊ ልማት የራሱን ትልቅነት ያውጃል፤ ይገልጣል። ኤሜ ሴዜር እና ሌሎችም እንደጠቆመት ይህ አይነቱ እሳቤ እና ትርክት ዘርፈ ብዙ ዘረፋን ለማካሄድ የሚደረግ ሠበብ ነው። በዚህም የተነሳ ነው የማላውቃቸውን አካባቢዎች በምናቤ ከመከሰት ለመቆጠብ የምሞክረውና የማውቀው የረዥም ጊዜ መኖሪያዬ የሆነውን የጀርመን ዋና ከተማን እንዲሁም የበርሊን ጉባኤ (The Berlin Conference) የተካሄደበትና የጀርመን የቅኝ ግዛት ማእከል የሆነውን የበርሊን ከተማ ላይ የማተኩረው።

1 Achille Mbembe, *Necropolitics* (Durham: Duke University Press, 2019).





↻ Janine Jembere, 1 detail of BArch 1001/4299; 4 details of BArch 1001/4308 (2020)









የማጠናቸው መዝገቦች ኤሜ ሴዜር የሚያነሳቸውን ተቃውሞዎች የሚያንጸባርቁ ሲሆኑ የመሬትና የሉአላዊነትን ጥያቄዎች የያዙ ናቸው። ምንም እንኳን መዝገብ ረቂቅ የሆነ ነገር ቢሆንም በመዝገብ ውስጥ የመሬትና የቦታ ጉዳይ ማእከላዊ ስፍራን ይይዛል። የምመለከታቸው ደብዳቤዎች ጽሀፊዎቻቸው ስለሚኖሩባቸው በጀርመን ቅኝ ግዛት የተያዙና ብዙ ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች ሲሆን ፤ ደብዳቤዎቻቸው እንዲደርሱ የታቀዱት ደግሞ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ለሚገኝ አንድ ተቋም ወይም ግለሰብ ነው።

“የቅኝ አገዛዝን ጥፋት በግልጽ ተረዳሁ። የዲተርዲንግ፣የሮያል ደች ወይንም የስታንዳርድ ኦይል መኖር ሊያጽናናኝ አይችልም።...ሁሉንም ቦታ ሳማትር ቅኝ ገዢዎችና ተገዢዎች አንድ ላይ ባሉበት ጊዜ ሁሉ የማየው ጉልበትን፣ጭካኔን፣ሰቆቃን፣አረመኔነትን፣ግጭትንና በትምህርት ስም በሚደረግ ቀልድ በችኮላ የሚፈበረኩ በሺዎች የሚቆጠሩ ጥገኛ አሽከሮችን፣ “ልጅ” (እየተባሉ የሚዋረዱ አዋቂዎችን) ፣ የእደጥበብ ሰራተኞች፣የቢሮ ጸሃፊዋችና ትርጁማኖችን ነው። እኒህ ሁሉ ለተቃና የንግድ እንቅስቃሴ አስፈላጊ ጥገኞች ናቸው።
አሁን የነገሮችን ቀመር ለመግለጽ ተራው የእኔ ነው። ለእኔ ቅኝ አገዛዝ “ከቲንጊፊኬሽን” ጋር እኩል ነው። የወሬውን ማእበል ሰምቼዋለሁ-- ስለ እድገት፣ስለ ሰኬቶች፣ስለ በሽታዎች ቁጥጥር፣ስለ የኑሮ ደረጃ መሻሻል ይነግሩኛል። እኔ ደግሞ ስለ ህብረተሰብ መንጠፍ፣ስለባህል መደፍጠጥ፣ስለ ተቋማት መርከስ፣ስለመሬት መነጠቅ፣ ስለ ሃይማኖት መዋረድና መድቀቅ፣ ስለ ድንቅ ስነ ጥበብ መውደም (እና) ታላቅ እድሎችን ስለመቀማት እነግራቸዋለሁ። እነርሱም ቁጥሮች ፊቴ ላይ ይወረውሩብኛል። ስንት ማይል መንገዶች፣ግድቦችና የባቡር ሀዲዶች እንደተሰሩ ይነግሩኛል ። እኔ ደግሞ የማወራው ለኮንጎ ውቅያኖስ ስለተገበሩ ሺዎች፣ ይህንን ጽሁፍ በማዘጋጅበት በዚህች ሰዐት እንኳን ሳይቀር እጃቸው የአቢጃንን ወደብ ስለሚቆፍሩት እና ከአማልክቶቻ ቸው፣ከመሬታቸው፣ከልማዶቻቸው፣ከሕይወታቸው፣ከጭፈራቸውና ከጥበባቸው ስለተነጠሉ ሚሊየኖች ነው። እነርሱ ስለተመረተው እና ወደ ውጭ ስለተላከው በቶን የሚመዘን ጥጥና ካካዎ፣ ስለታረሰው የወይንና የኦሊቭ ሄክታር መሬት በመንገር ሊማርኩኝ ይሞክራሉ። እኔ ደግሞ ስለተጨናገፉት ለአካባቢው ተስማሚ የሆኑ የተፈጥሮ ኢኮኖሚዎች፣ስለወደሙ የምግብ እህሎች፣ሰለማያባራ የምግብ እጥረትና እርዛት፣የቅኝ ግዛቱን ቁንጮ ለማክበር ስለተቃኘው የእርሻ ስርአት፣ ስለጥሬ እቃና ስለምረት እቃዎች ዘረፋ እነግራቸዋለሁ።”
— Aimé Césaire, *Discourse on Colonialism*









↑ Janine Jembere, 2 details of BArch 1001/4073; 1 detail of BArch 1001/4299 (2020)

የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በ1903 እና በ1913 መካከል 105,000 አፍሪካዊያን በጀርመን የጦር ዘመቻዎች እንደተገደሉ አምኗል። ይህ ቁጥር በትሮፐንኮለር በሽታ ተፅዕኖ ሳቢያ በጀርመን ነጋዴዎች እና ባለስልጣናት የተገደሉትን አፍሪካዊያንን አያካትትም።
— Gold Coast Leader, archived in BArch R 1001 (Reichskolonialamt)/4308

አዲሶቹ አገሮች (ከቅኝ ገዢው አገር ለሚመጣው) ግለሰብ የተለየ የጉልበትና የጭካኔ ልምምድን እንዲያከናውን ሠፊ ቦታ እና ዕድልን ይሰጡታል። በቅኝ ገዢው አገር እምብርት ቢፈጽሙ ብዙ ወቀሳን የሚያስከትሉና ጨዋና ስርአታዊ የሆነ ሕይወት መገለጫ አይደሉም ተብለው የሚወሰዱ ተግባሮችን በቅኝ ተገዢ አገር ላይ ለመፈጸም ከፍተኛ ነጻነት ስላለ በቅኝ ተገዢ አገር እነዚህን ተግባሮች ለማዳበርና ዋጋቸውን ከፍ ለማድረግ ቀላል ነው። በዚህ የተነሳ ቅኝ ግዛቶች ለዘመናዊ (አውሮፓዊ) ህብረተሰብ [የጭካኔ እና የልቅነት] ማስተንፈሻ ሆነው አገልግለዋል። ምንም እንኳ የቅኝ ግዛቶች ዋጋ ይህ ብቻ ቢሆንም ይህ ተግባር ያለው ጠቀሜታ ግን እጅግ ከፍተኛ ነው።
— Carl Siger, quoted in Césaire's *Discourse on Colonialism*



ይህንን የጭካኔ ልምምድ በቅኝ ግዛቱ ብቻ አምቆ ማስቀረት ግን ቀቢጸ ተስፋ ነበር። ቅኝ ግዛቶች ስርአት ላለው እና ጨዋ የቅኝ ገዢ አገር ማህበረሰብ እንዲፈጠር በማስተንፈሻነት ተገድበው ከመቅረት ይልቅ በአውሮፓ በጥቂት አስርት አመታት ውስጥ ለተካሄደው ሰፊ ጭፍጨፋ የመሞከሪያ መድረኮች ሆነው አገለገሉ። ሆኖም በቅኝ ገዢው አገር ሁሉም በእኩል ደረጃ ለግድያ የቀረበ አልነበረም። ጥልቁ መስመር (the abyssal line) መልክአ ምድራዊ ክፍፍልን የሚያሳይ ሳይሆን ንድፈ ሃሳባዊ መስመር ነው። ይህም መስመር በዘረኝነት ሳይንስ እና በካፒታሊስታዊ ስግብግብነት የታጨቀ ነው።[2] ጉልበቱም ከፍተኛ ስለሆነ በምኖርበት አካባቢ ሁሉ ተሰራጭቶ መብትን፣አደጋን፣ ስራን፣ ሀብትን ፣ሞትን በአድሏዊነት ሲያከፋፈል አየዋለሁ።

ከላይ በጠቀስኩት ቤተ መዝገብ የምመለከታቸው መዝገቦች ከመቶ አመት በላይ ያስቆጠሩ በመሆናቸው ስለ ጊዜ ማለፍ እንዳስብ እገደዳለሁ። ዛሬ፤ ማለትም በ2019፤ በዚህ ቤተ-መዝገብ አንድ ወንበር ላይ ተቀማጭ መዝገቦቹን አገላብጣለሁ።የማነባቸው ደብዳቤዎች በተጻፉበት ጊዜ የፕረሺያ ወታደሮች አንዳንዶቹ ወደ ቅኝ ግዛት ሲላኩ በእነዚህ ግድግዳዎች መካካል ተመላልሰዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ የጉልበት እና የጭካኔ ስራን በቅኝ ግዛቶቹ ተለማምደዋል። እኔም በዚህ ቤተ መዝገብ በዚህች ሰዕት ተቀምጫለሁ። ይህ የአጋጣሚ ጉዳይ ብቻ አይደለም። የቅኝ ግዛት አስገዳጅነት ተቋማትና መዋቅሮቹ ውስጥ ተጽፎ ይገኛል። የማጂ ማጂ እና በዋርሶ ከተማ ድሃ ሰፈሮች የተካሄዱ አመጾች በተመሳሳይ ምክንያቶች የተቀሰቀሱ ናቸው። የጀርመን የበላይነት ትምክህት እና አፋኝ አስገዳጅነትና ጥቃት እነዚህን ህንጻዎች እንዳቆሙ ሌሎች መዋቅሮች እና ተቋማም ሁሉ ጉልበቱን መጠቀሙን፣ ጥቃቱንና ማስገደዱን አሁንም አላቆመም። ለዚህም ነው የማጠናቸው የታሪክ ዶሴዎቹ ስለ ዛሬም ናቸው የምለው። ያለፉት ዘመናት፣ተቋማት እና መዋቅሮች ሁሉ የተያያዙና ቀጣይነት ያላቸው ናቸው።

ይህ ቤተ መዛግብት የቀብር ቦታ ነው። ብዙ ህይወት በግድግዳው፣ በወለሉ እና በጣሪያው ውስጥ ተቀብረዋል። ከዚህም ሌላ ህይወቶች፣ ሃሳቦች፣ መንፈሶች እና እድሎች በእነዚህ መዛግብቶች ውስጥ፣ በመሳቢያዎቹ እና በካቢኔዎቹ ተቀብረዋል። በመሆኑም እነዚህ ቦታዎች ላይ ያሉትን እሬሳዎች የታጀሉባቸውን መዛግብት ሳገላብጥና ሳናግራቸው ስራዬን ሞት የመቀስቀስ ስራ ያደርጉታል።ይህ ሬሳን ከሞት የማስነሳት ስራ ግን መድረሻ/ግቤ ሳይሆን የስራዬ ጅማሮ ብቻ ነው።[3]

2. Tropenkoller is an alleged medical condition; it was first reported in the 1890s in the context of court scandals around extreme violence in the German colonies, wherein Tropenkoller was said to affect mainly German men in hot tropical climates and was used to justify a loss of selfcontrol and sexual and other excessive violence.

3 Boaventura de Sousa Santos, *Epistemologies of the South: Justice against Epistemicide* (London and New York: Routledge, 2017).

4 Christina Sharpe, *In the Wake: On Blackness and Being* (Durham: Duke University Press, 2016).






በመናፍስት የንጽፈ-ሀሳብ ማእቀፍ ውስጥ ጊዜ የሚመለስም የማይመለስም አይደለም። ነገሮች እና ሁነቶች አንዳቸው ባንዳቸው ላይ ታደራርበው ይሄዳሉ።ታሪኮች የሚታወቅ መጀመሪያ ካላቸው መጨረሻ ላይኖራቸው ይችላል። ሊቋረጡ ይችላሉ፤ ነገር ግን አንድ ታሪክ ወይንም ሁነት በሌላ ታሪክ ወይንም ሁነት ውስጥ ሰርጎ ገብቶ ሊቀጥል ይችላል። ምንም እንኳ በመካከላቸው ዝምድና ላይኖር ቢችልም ግጭቶች እና ትግሎች ካቆሙበት እንደገና ሊጀምሩ ይችላሉ። ሌላ ጊዜም ወደላይ ሊፈሱ ይችላሉ ወይም ያለምንም መቀጠልን የመፈለግ ስሜት እንደገና ሊጀምሩ ይችላሉ። ነገር ግን ያለፈው ታሪክ ጥላ በአሁን ጀርባ ሁልጊዜ ይላወሳል። በእርግጥም አንዱ ሁነት የተለያዩ ጅማሮዎች ሊኖሩት ይችላል። በዚህ ሂደት አንድ አካል ህይወት ከማጣት ወደ መጎልበት ሊመጣ ይችላል። ሁሉ ነገር የሚከናወነው በፍጻሜ አልባነት መርህ ነው። በዚህ የተነሳ በትላንት፣ዛሬና ነገ ምንም አይነት ስርአታዊ ቀጣይነት የለም። በመካከላቸው የዘር ግንድ የለም፤ ያለው ከጥልቅ ውስጥ እየተፈታ የሚሰራጭ፤ ነገር ግን የተገነጣጠለ፣ በብዙ ቀጫጭን ክሮች የተያያዘ እና ተከታታይ የጊዜ ቀመር ብቻ ነው።

— Achille Mbembe, *Critique of Black Reason*



መሳሪያ

# የመዝገብ ቤት መናፍስቶችን ማናገር

አንዱ የቅኝ ግዛት መዛግብቶችን የማጥኛ ዘዴ መዛግብቱ ውስጥ ከሚርመሰመሱት መናፍስት ጋር መወያየት ነው። (1) መናፍስቶች ሰዎችና ሌሎች ኗሪ እና ንቁ ሕይወት የነበራቸው ነገሮች ናቸው። እነዚህ መናፍስት በፊት ግዳይ የተደረጉ … የተደመሰሱ እና በእያንዳንዱ ትውልድ ዘመን የሚፈጥሩ ናቸው። መናፍስት አካባቢያችንን ይወራሉ፤ አንዳንዴም ይመሩናል፣እንድናስታውስ እና እንድናስብ የደርጉናል። (2) እንደ ኤቨሪ ጎርዶን ፣አሺል እምቤቤ፣ጁዲት በትለር፣አቴና አትናሲው፣ ኢቭ ተክ እና ሲ. ሪ ያሉ ምሁራን መናፍሰትን ከመነጠቅና ነቀላ ጋር በተያያዘ እንድናስብ ይረዱናል። ንጥቂያ በእኔ ስራ ውስጥ ከሰው ያነሰ ቦታ እንዲይዙ የተደረጉ ሰዎችን እና ከታሪክ የተፋቁ፣ግዳይ የተጣሉ አካላትን እና የግፉአን ህይወትን ይመለከታል። (3)

በታሪክ ዶሴ ውስጥ መናፍስት በአንድ ጊዜ የሰቆቃ ተሸካሚዎችም የተስፋ ምንጮችም ናቸው። የመናፍስት አልጠፋ ባይነትና ሞትን አሻፈረኝ ማለታቸው ግዞተኛም ቢሆኑ መግደልና ማጥፋት የማንችላቸው የአድራጎት (agency) ሃይል ያላቸው ናቸው። ይህ ሞትን አልቀበል ባይነተቸው ጊዜን ያውካል፤ ይህ ሞትን እምቢ ባይነታቸው እንዲጠፉ እንዲቀበሩ የሚፈልገዋቸውን አካል ለመበቀል የሚያደርጉት ተግባር ነው። የመናፍስትን የሚረብሽ ቅላጼ መከተል የታሪክ ዶሴን ውስጣዊ ፍሰቶች፣ እንግዳ ግንኙነቶችና የተገነጣጠለ ጊዜን በግልጽ እንድንመለከት ይረዳናል።

ውይይት ከመናገር ማዳመጥና ሃሳብ መቀያየር ባሻገር የመበት ተሟጋች የሆኑት ግሬስሊ ቦግስ እንደሚያስተምሩን አዲስ ሃሳቦችንና ቋንቋዎችን ለመፍጠር የሚያገለግለን መሳሪያ ነው። ውይይት የተግባር ስም ነው፤ ወደ አንድ አይነት ተግባር ይጠቁማል። በአንፃሩም ከመናፍስት ጋር መወያየት የግብረገብ (Ethics)ጥያቄን ያስነሳል። (4) "ለምን የተኛችውን ሰው በሰላም እንድታርፍ አትተውዋትም" ሊያስብል ይችላል። ስለዚህ መናፍስትን እንዴት ለመወያየትና ለመነጋገር እንዲስማሙ ልንጠይቃቸው እንችላለን? እንዴትስ በታሪክ ዶሴ ካለች መንፈስ ጋር መነጋገር ይቻለናል? ከመናፍስት ጋር መነጋገር ማለት ደግሞ የመናፍስት መስፈሪያ መሆንን መቀበል ነው። ሻሮን ፓትሪሺያ እንደምታስተምረን ከመናፍስት ጋር ውይይት በህይውትና በሞት መካከል ያለውን ተቃራኒ ሁለትዮሽ ማወክና ሙታን በሕይወት ካሉ ሰዎች እልፍኝ ውስጥ መምጣታቸውንና የሙታንን መነሳት መቀበልን ማወጅ ነው። (5)

(1) See also, Naomi Rincón Gallardo's chapter "Heavy Blood," in this volume, 33–51.
(2) Eve Tuck & C. Ree, "A Glossary Of Haunting," in *Handbook of Autoethnography*, eds. Stacey Holman Jones, Tony E. Adams, and Carolyn Ellis (Walnut Creek: Left Coast Press, 2013), 639–58.
(3) Judith Butler & Athena Athanasiou, *Dispossession: The Performative in the Political* (Cambridge: Polity, 2013), 1–10; Avery F. Gordon, *Ghostly Matters: Haunting and the Sociological Imagination* (Minneapolis: University of Minnesota Press, 2011); Achille Mbembe, *Critique of Black Reason*, trans. Laurent Dubois (Durham: Duke University Press, 2017); and, Tuck & Ree, "A Glossary of Haunting."
(4) "On Revolution: A Conversation Between Grace Lee Boggs and Angela Davis," (2 March 2012); online at: radioproject.org/2012/02/grace-lee-boggs-berkeley.
(5) Sharon Patricia Holland, *Raising the Dead: Readings of Death and (Black) Subjectivity* (Durham: Duke University Press, 2000).





↻ Janine Jembere, detail of BArch 1001/4299, 2020



ገቢር

# ከመናፍስት ጋር መወያየት

ይህን ገቢር ብቻችሁን ወይም ከሌሎች ጋር ማድረግ ትችላላችሁ

- ለእኔ አስፈላጊ ነው የምትሉትን ጉዳይ መረጣችሁ ስለ ጉዳዩ ለመወያየት የምትችሉትን ሁሉ መናፍስት ዘርዝሩ።
- የመናፍስት ዝርዝር ካዘጋጃችሁ በኋላ የትኛው መንፈስ ጋር መወያየት እንደምትፈልጉና ይህ ለምን እንደሆነ ግለጹ
- ጣልቃ የሚገቡ መናፍሰት ሊገቡ እንደሚችሉ ከግምት ውስጥ ክተቱ፤ እነዚህን ለማዳመጥ እየሞከራችሁ ነው ወይንስ ገሸሽ እያደረጋችኋቸው ነው? ለምን?
- ውይይቱን የምታካሂዱበት በቂ ጊዜ ይኑራችሁ። ለውይይቱ የሚሆን ቦታም ምረጡ። ውይይን በተለያየ ጊዜና በብዙ ክፍለ ጊዜዎች ውስጥ ልታደረጉ ትችላላችሁ።በውይይቱ መሀከልም እንደአስፈላጊነቱ ሁሉም ተገቢውን እረፈት አግኝቶ እንዲመለስ አድርጉ
- ከውይይቱ ጊዜ በፊትና በኋላ ተዘጋጁ (መጠጥ ምግብ መንፈሳዊ ጽዳት ወዘተ አድርጉ…)
- ወይይቱን ስታደርጉ (ቦግስ እንደሚሉት) በውይይቱ አሳብን ለመቀየር ክፍት ሁኑ
- በውይይቱ መጨረሻ መናፍስቱ መሄድ ወደሚፈልጉበት እንዲሄዱ እና እናንተም ለብቻችሁ ወደ ምትሄዱበት እንድትሄዱ አንድ አይነት ስርአት (ritual) አድርጉ።

↻ Janine Jembere, details of BArch 1001/4202 (2020)







መሳሪያ

# ዶሴዎችን መፍጠር (Creating An-Archives)

የቤተ መዛግብቱ እና የሙዚየሙ ስብስቦች የመነቀልና የንጥቂያ ምሳሌዎች ናቸው።የነገሮችን አውድ ይከልላሉ፤ መንፈስንና ቁሶችን ይዘርፋሉ። በመሆኑም በድልደላ እና አውደ ቢስ በሆነ በነጭ አውሮፓዊ ሳይንስ ስም በሚቀምሩት እውቀት ትርጉምና ተምሳሌቶች ላይ ጥቃት ይፈጽማሉ። ቤተ መዛግብቱ እንደ መሳሪያና እንደ ተቋም ስርአትን፣ደንብን፣ድልደላን ያካሂዳል። በስብስቡ ውስጥ መካተት ያለበትን እና የሌለበትን ይወስናል። በዚህም የተነሳ መሞገት ይገባዋል።በቤተ መጻህፍቱ የሚገኙትን መዛግብት ለብዙ ጊዜ ሳገላብጥና ሳጠና ከቆየሁ በኋላ ታሪኮቹ እንዴት የተለያዩ እንደሆኑና የማያልቁ የጭካኔ ድርሳናት እንደሆኑ ተረዳሁ። ከመዝገብ ቤቱ አውጥቼ በማተም እና ኮፒ በማድረግ በፖስተሮች ላይ ቀድቼ አባዛኋቸው ከዚያም በስፋት አስራጨኋቸሁ። ይህ ግን ማንን ይጠቅማል? ከቡድናችን ጋር በነበራቸው ቀይታ ዶክተር ኢቮ ተክ እነዚህን መዝገቦች ማጋራት እና ማሰረጨት ሰዎች ከአውዳቸው ውጪ መዛግብቱን ትርጉም ሊሰጧቸው እንደሚችሉ በማሳሰብ ይህ ጉዳት ሊኖረው እንደሚችል አስገነዘቡኝ። በዚህ ጊዜ ነበር የማጠናቸውን ደብዳቤዎች የፃፉት ሰዎች አላማ ምን እንደነበር እና ለእነማን ደብዳቤዎቹን እንደፃፉ ለማሰብ የተገደድኩት። የፀሀፊዎቹን አላማ ደግሞ ልጠይቃቸው አልችልም። በመሆኑም መዛግብቱን በማጥናትና ወደፊት ሊያነቧቸው ለሚችሉ ሰዎች የተዋቸውን ምልክቶች መፈለግ ጀመርኩ፤ ፀሀፊዎቹም ደብዳቤዎቹ ምን እንዲያደርጉላቸው እንደሚፈልጉ ለማወቅ ፍላጎት ስላደረብኝ ለዚህ መልስ ለማግኘት እያንዳናዳቸውን ፋይሎች እያጠናሁ ለዚህ መልስ ለማግኘት ሞከርኩ። ደብዳቤዎቹ የተጻፉባቸው አገሮች ውስጥ ያሉ ተመራማሪዎች፣ የስነ ጥበብ ሰዎች፣ ምሁራንን፣ የመብት ተሟጋቾችን አነጋገርኩ። ፋይሎቹንም ባንድ አድርጌ ለእነዚህ ሰዎች ላኩላቸው። እነዚህ መዛግብት በተጻፉበት አካባቢ ፋይዳ ይኖራቸው ይሆን? የሚለው ጥያቄ ከእነዚህ ተማራማሪዎች፣ ምሁራን ፣ የስነ-ጥበብ ሠዎች ወዘተ… ጋር የነበረኝን ውይይት አቅጣጫ ሰጠው። ፍላጎቴም ስለ ንጥቂያ ፣ ባለቤትነትና ከ "universal history" ሌላ ትርክትን ማግኘት ሆነ።

ይህን ስራ ለማከናወን ዋናው ጥያቄዬ የነበረው "ሌላውን" (the other) መንጠቅ፣ መመደብ፣መሰብሰብ እና ማንኳሰስ አይነተኛ አላማው አድርጎ የተነሳን የታሪክ ዶሴ እንደእኔ ያለች የ "ሌላው" ("the other") ዘር አባል ይህ ዶሴ ከሚደብቃቸው መናፍስት ጋር እንዴት ተቀናጅታ መስራት ትችላለች የሚል ነው። እንዴት የነግ-ትላንት (future past) ትርክትን በዚህ ሁኔታ መስራት ይቻላል? በአውሮፓ ቤተ መዛግብት እና ተቋማት ውስጥ ካሉ የባህል ቁሶች ጋር ምን አይነት ግንኙነት እንደኔ አይነት ሰዎች ሊኖራቸው ይችላል? ለኔ የዶሴውን ውል የማግኘት ፍለጋ እንደ እኔ ያሉ በአውሮፓ የሚኖሩ የ"ሌላው" ዘር አባላት በማነነትና ቅኝ የተያዙ ሌሎች አገሮችን ለመረዳት አይደለም። የዚህ ፍለጋ ዋናው አላማ አሁን ያለንበትን ቦታ እና ጊዜ ለመገንዘብ ነው፤ ከተቻለን አንድ ላይ ተገናኝተን ለመወያየትና ሁሉንም ማንነታችንን ከተቆጣጠረው አውሮፓ ተኮር (eurocentrism) አስተሳሰብ ትንሽ ፈቅ ብለን ማንነታችንን እንድናጤን ነው። የ An-archives አላማ የዚህን የታሪክ ዶሴን ማእከሉን ማሳት እና መበተን ፣ሃይሉን መቀነስ ነው። ሳርና ሳቮር እንደሚሉት "ባህልን ማጥፋትና ባህልን መሰብሰብ የአንድ ሳንተም ሁለት ገጽታዎች ናቸው"። (6) ስለዚህ እንዴት አድርገን ነው "An-archives"ን የምንፈጥረው? መልሴ- በጥንቃቄ የተመላ ነው። የፈጠራችን አላማ ፍጻሜን ማግኘት እና መጨረስ ሳይሆን መጀመር ነው። ታሪክን ለመመዝገብ ሳይሆን ትርክቶችን ለመገዳደርና ለመሞገት ነው። የትርክቶችን ጠቅላላ ገፅታቸውን ለማስቀመጥ ሳይሆን ግንኑነቶችን ለማመቻቸት ነው።

(6) Felwine Sarr & Bénédicte Savoy, *The Restitution of African Cultural Heritage: Toward a New Relational Ethics* (November 2018); online at: restitutionre port2018.com.



→ Janine Jembere, detail BArch 1001/4308, 2020

ይህ ባህልን አመረትን የሚለው አመክንዮ የባህልን አይነተኛ መርህ የሚክድ ነው። በዘመናት ሁሉ ባህል በአውሮፓም ሆነ በሌላ አካባቢ የሚፈጠረውና እንደገና በአዲስ መልክ የሚሰራው ካንዱ ወደ ሌላው በመተላለፍ፣በመራባት፣በማልመድ፣በጥናት እና በህብረተሰብ ለባዊነት ውስጥ የሚገኙ እውቀት እና ቁሶቹን በመለወጥ ነው። ባህልን ማጥፋት እና ባህልን መሰብሰብ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።
— Felwine Sarr & Bénédicte Savoy, *The Restitution of African Cultural Heritage*

ገቢር

# ስለ An-archives ወርክሾፕ ማዘጋጀት

### መግቢያ

- እቅዱ ምን እንደሆነ አጭር ገለጻ ማድረግ
- ወርክሾፑን የሚያመቻቹትን ሰው እና የወርክሾፑን ተሳታፊዎች ማስተዋወቅ።የስብሰባ /ዶሴ ማደራጀት ስራ ላይ ስላላቸው ፍላጎት አጭር መግለጫ

### ልውውጥ

- ስለ መሰብሰብ/ዶሴ ማደራጀት ያላችሁን ተሞክሮ (የኢንስታግራም ግድግዳዎች እንደ ዶሴ ሊታዩ ይችላሉ) እና ስለምታውቋቸው ስብስቦች/ዶሴዎች ሃሳብ ተለዋወጡ

### ማቀድ

- ምስላዊ እና ምናባዊ (አን)ማህደሮችን ፣ የጥበብ ልምዶችን ፣ ገጽታዎችን ፣ ወዘተ ጨምሮ የተለመዱ እና ያልተለመዱ ፍላጎቶች።
- ወደ ካርታው / እቅዱ ይመለሱ እና ለቀኑ የሚሆኑ ግንኙነቶችንና እንቅስቃሴዎችን ይጨምሩ።
- የተለመዱ እና ያልተለመዱ ሰነዶች/ ርዕሶች / ጭብጦች / ሀሳቦች / ማጣቀሻዎችን ያካቱ።

ገቢር

### ግብአት

- በዶሴ ማደራጀት እና An-archiving መካከል ያለውን ልዩነት ምንድን ነው?
- እነዚህ ልዩነቶች ዶሴ ከማደራጀት ስነምግባርና ስነውበት አንጻር እንዴት ይታያሉ?
- በተግባራቱ አስተባባሪዎች የተዘገጁትን የ(አን)ማህደሮችን ምሳሌዎች ተመልከቱ።

### አንድን ቁስ ማብራራት

ይህን መልመጃ ከኢቭ ታክ የተዋስኩት ነው። አንድ ነገር በተሳታፊዎች መካከል ይተላለፋል; እያንዳንዱ ተሳተፊ ቁሱን በሚይዙትና እና በሚመለከቱት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው ስለ ቁሱ አንድ ነገር ብቻ እንዲናገር ይደረጋል። ይህም ሲሆን ከመጠን በላይ የመወሰንም ወይም የመቀነስም ባህሪን ማስወገድ ያስፈልጋል። (ከነገሮች ጋር ማዛመድ እና ፍርድ መስጠትም አይፈቀድም)።

ገቢር

### በነፃነት መጻፍ

- ምንም አይነት ገደቦች ባይኖሩ እናንተ ጥሩ የምትሉት an-archive ምን ይመስላል? ስራው ምንድን ነው? ምን አይነት ቁሶችን ይይዛል ወይም አይዝም? እንዴት ፣ለምን፣እና ለማን? ቁሳዊ ነው ወይንስ ዲጂታል? እንዴት አይነት የማጋራት እና የግብአት ድርጅቶች አሉት? አላማው ምንድን ነው?

### ውይይት

ቀደም ብለው የቀረቡትን የ(አን)ማህደር ምሳሌዎች እና የራሳችሁን እሳቤ ከልሱ

- ማህደሮችን መፍጠር ስለ ይዘት / ትኩረት እና አግባብነት ባለው ክምችት አስፈላጊነት (በክምችቱ ውስጥ) እና አላስፈላጊነት (ክምችቱ ውጭ) መካከል ያለውን ልዩነት ብቻ ሳይሆን ስለ አወቃቀር እና ስነ-ውበትም ግንዛቤን ይጠይቃል ፡፡ ተጨማሪ የውይይት ነጥቦች፤ የዶሴ ክምችትዎን እንዴት ማቅረብ፣ ማጋራት እና ማደራጀት ይችላሉ? ምን ዓይነት ልምዶች እና አጋጣሚዎችን፤ ምናልባትም የጭካኔ ሂደቶችን ፈብርከዋል ወይም አመቻችተዋል? እንዴት ምደባን፣ ኩረጃን፣ ቅደም ተከተሎችን ጠብቆ መመደብን ማካሄድ ይቻላል? እንዴት (በቀላሉ ሊጠፉ የሚችሉ) ዶሴዎችን ከመቀበር አትርፎ ይዘቶቻቸው እንዲታዩ ማድረግ ይቻላል?

### ግብአት

- ስለ ማደራጀት እና ማጣቀሻ ግብአት አጭር መግለጫ መስጠት፤ በተለይም ምደባን በተመለከተ ለሚነሱ የግብረገብ (ethics) ጥያቄዎች አስተያየት መስጠት።
- ስለ እለት ተእለት ተግባራት ያለ ግብ መሰብሰብ፣ የተሰበሰቡትን ዶሴዎች መልሶ መጎብኘት እና መፈተሽ፣ ነፃ ስለሆኑና በሆኑ ስብስቦች ውስጥ ማሰብ።

### ማጠቃለያ እና አስተያየት

ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጥያቄዎችን፣ እሳቤዎችን፣ ሃሳቦችን መጋራት።

ለቀጣይ ጊዜ መዘጋጀት፣ ስለ ሌላ ጊዜ የመገናኘት ዕድል መኖር አለመኖር መነጋገር፣ ስለ ግቦችና ምኞቶች መነጋገር።

ADDITIONAL REFERENCES


- Campt, Tina M. *Listening to Images*. Durham: Duke University Press, 2017.
- Césaire, Aimé. *Discourse on Colonialism* [1955]. New York: Monthly Review Press, 2000.
- Mbembe, Achille. *On the Postcolony*. Berkeley: University of California Press, 2001.
  — *Critique of Black Reason*. Durham: Duke University Press, 2017.


ARTWORKS & PROJECTS

Suggestions for the activity “Conversations with Ghosts”:

- Kazeem-Kamiński, Belinda, artist. 2017. *Unearthing: In Conversation*. HD video, 13”.
- Heinowsky, Walter and Gerhard Scheumann, directors. 1966. *Der Lachende Mann: Bekenntnisse eines Mörders* [The Laughing Man: Confessions of a Murderer]. Film, 66’, East Germany.
- Mabouna, Moise Merlin & Brigitta Kuster, artists. 2006. *2006–1892 = 114 Years* (DV video, 7’ loop).
- Savvy Contemporary, Berlin. Colonial Neighbours (participatory archive & research project). Online at: savvy-contemporary.com /en/pillars/colonial-neighbours.
- We Are Born Free. Empowerment Radio. On-going radio program. Online at: wer.oplatz.net.

Suggestions for the activity “An-Archives Workshop”:

- Kazeem-Kamiński, Belinda, artist. 2019. *The Letter*. Video.
- Each One Teach One (eoto) e.V.; initiative in Berlin. Online at: eoto-archiv.de.
- Hoffmann, Anette, Matei Bellu, and Regina Sarreiter, artists. 2012. *Unerhörter Bericht über die deutschen Verbrechen in den kolonisierten Gebieten und über das fortwährende Wirken der Gewalt bis in die Gegenwart*. Installation.
- Jafa, Arthur, artist. 2018. *Matrix 272*. Video installation.
- The Black Archives; initiative in Amsterdam. Online at: theblackarchives.nl.
- Gates, Theaster. *Black Archive*. Exhibition. Kunsthaus Bregenz, 23 April – 26 June 2017.
- Vitjitua Ndjiharine, artist. 2018. *Ikonowall / Mirrored Reality.* Digital print and mirror film.

CREDITS

*Paperlands*, by Janine Jembere, 2020. All images in this chapter: reproduced courtesy Janine Jembere and Bundesarchiv Berlin. Produced with the support of FWF PEEK: “DisPossession: Post-Participatory Aesthetics and the Pedago-gies of Land.”

እጠራሻለሁ፤ አዳኝ ሆይ
በእባብ ቅርፅ ነይልኝ
ነጎድጓድሽ ሰማዩን ይስበረው
በቀለኛ በሆነው ኃይሉ!



# የኦፖሰም ጽናት




ናኦሚ ሪንኮን ጋላርዶ

ኦክሳካ/ሜክሲኮ

በአለም ዙሪያ በራስ አገዝ አካባቢዎችና ማህበረሰቦች ብዝሃ አቀፍ ሁለንተና የሚገኙ በዕድሜ የገፉ እንዲሁም ወጣት የመብት ተሟጋቾች (ቁጥራቸው በከተማ በመጨመር ላይ ይገኛል) የአኗኗር ዘያቸውን ከጥቃት ለመከላከል በፅናት ይታገላሉ። ይህ ተጋድሎዋቸው አንዳንዴ ህይወታቸውን እስከማስከፈል ይደርሳል። የህን ትግል በረጅም የጭቆናና የተቃውሞ ታሪክ ውስጥ እየተካሄደ ያለ አካባቢያዊ ራስ ገዝንና የጋራ ይዞታን ለመታደግ፣ ተፈጥሯዊ የሆነ የመኖር ህልውናን ለማረጋገጥ የሚደረግ የፖለቲካ ተግባር እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል።

“የአበውና የእመው ስርዐትን የመገንባት ናፍቆት መለወጥን ካለመሻትና ካለፈ ጊዜ አምላኪነት የሚመነጭ ሳይሆን በህይወት ልምምድ እና ትውስታ ጠቋሚነት የሚገኝ የተለየ ነገን የሚተልም የህይወት ፍልስፍና ነው። ይህ ፍልስፍና በ “ወደፊተኝነት” (futuri-ty) የታቀኘ ህሳቤ ሲሆን የራስ ገዝ አካባቢዎችና ማህበረሰቦች በብርታት የተለየ ማንነታቸውን ጠብቀው የሚቀጥሉባቸውን ሁኔታዎች ለማመቻቸት የሚደረግ ትግል ነው።”

— Arturo Escobar, *Thinking-Feeling with the Earth*



ወደ ኦክሳካ በመጣሁ ቁጥር ወደ እሷ እመለሳለሁ። ታነፃኛለች። በአፏ ሙሉ ሜዝካል (አልኮል የሚሠሪበት ተክል) ትይዛለች ነገር ግን አትውጠውም። ግማሽ እርቃን በሆነ አካሌ ላይ ትተፋዋለች። “ሜዝካል ሀይልን ያሠራጫል” ትላለች። እኔም ቀዝቀዝ የማለት እና የእፎይታ ስሜት በሰውነቴ ሁሉ ይሰራጫል። ትንፋሿም የመደንዘዝ መንፈስ ይፈጥርብኛል። ከዚያ አዲስ በተቆረጡ የሮዝመሪና፣ ካሞሚል እና በሶ ብላ ጥቅሎች ሰውነቴን ታሸዋለች። ጥቅሎቹንም በሰውነቴና በደረቴ ላይ ትጨምቃቸዋለች። እንደገና በሜዝካል ታጥበኛለች፤ አይኖቼንም ትከድናቸዋለች። እንቁላልም በሰውነቴ ሁሉ ታንከባልላለች። ትሰብረውና በብርጭቆ አድርጋ ታነበዋለች ። ከዚህ ሁሉ በኋላ እረፍት እንድወስድ ታደርገኛለች። ከዚያም በጣሪያዋ ላይ ባለው በረንዳዋ ላይ ሆነን የፀሀይን መጥለቅ እያማተርን እናወጋለን።




↖ On the set of *Opossum Resilience,* by Naomi Rincón Gallardo; photo by Claudia López Terroso, 2019

አክሳካ በደቡብ ሜክሲኮ የምትገኝ አገረ-ግዛት ነች። ምንም እንኳ የውስጣዊ ቅኝ ግዛት አመክንዮ አስቸጋሪ ቢያደርገውም የተለያዩ ነባር ህዝቦች ለብዙ ክፍለ ዘመናት ከፊል የራስ-ገዝ አስተዳደርን በአገረ ግዛቷ ሲተገብሩ ቆይተዋል።[1] እነዚህ ከፊል የራስ አገዝ ዞባዎች የሚተዳደሩት ከሀገረ መንግስቱ በተለየ በራሳቸው አካባቢያዊ ህጐች፣ እሴቶችና እና ባህሎች ነው። የእነዚህን ዞባዎች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በተወሰነ ደረጃ የሜክሲኮ መንግስት እውቅና ቢሰጠውም በሌላ በኩል ደግሞ መሬታቸውን እና የተለያዩ ሀብቶቻቸውን በመንጠቁ የተነሳ ቅንብር የሌለው አስተዳደር እና የተለያዩ ማህበራዊና አካባቢያዊ ግጭቶች በሜክሲኮ በተለይም በአክሳከ እንዲበራከቱ አድርጓል።

ወደ አክሳካ ላለፉት አስርት ዓመታት የመጣሁት ወይ ጓደኞቼን ለመጠየቅ አልያም መደበኛ ያልሆኑ የስነ-ጥበብ ትምህርት ቤት ኘሮጀክቶች ውስጥ ለመሣተፍ ነው። በ2018 ወደ ኦክሳካ የተመለስኩት በንጥቂያ ዙሪያ የተደረገ የትረካ የስነ-ጥበብ ኘሮጀክት ውስጥ ለመሳተፍ ነበር። በ2018 ክረምት ወራት የዛፖቴክ የመሬት መብት ተሟጋች ጋር ተገናኘሁ። ለጥቃት እንዳትጋለጥ ማንነቷን ለመደበቅ ስል ከዚህ በኋላ ሌዲ ሪድ (Lady Reed) ብየ እጠራታለሁ። ሌዲ ሪድ ሌሎች ንጥቂያን የሚቃወሙ የኢ-ቅኝ ግዛታዊ ፌሚኒስት (decolonial feminists) ቡድኖች ጋር አብራ ስለምትሠራ ወደ ኦክሳካ በተደጋጋሚ ትመላለሳለች። እኔና ሌዲ ሪድ መጀመሪያ የተገናኘነው በአንድ ሙዚየም መግቢያ ላይ ነው። በመጀመሪያ የተገናኘን ቀን ሌዲ ሪድ

1 Isabel Altamirano-Jiménez, “Indigenous Movements,” Wiley Online Library (2017); doi: 10.1002/9781118430873.est0675.

የተለያዩ የማዕድን ቁፋሮ ፕሮጀክቶችን የያዙ ካርታዎች ይዛ ነበር። በኦክሳካ የሚገኙትን የማዕድን ፕሮጀክቶች በካርታው ላይ አሳየችኝ።
እኔና ሌዲ ሪድ “መሬት” ስንል በጣም ስለተለያዩ ሁለት አይነት ነገሮች ነው የምናወራው። ለሌዲ ሪድ መሬት እርስ በርስ በመረዳዳት ላይ የተመሠረተ ማህበራዊ ግንኙነት ጋር የተቆራኘ ንድፈ-ሀሳብ ነው። ህይወት የሚደራጀው በመሬት እና በዝናብ ዙሪያ ሲሆን የለያዩ ክብረ-በዓላት የዚህን ዑደት ለመዘከር ይከበራሉ። በተቃራኒው እኔ ባደግኩበት ከተማ ሜክሲኮ ሲቲ የስፔይን ቅኝ ገዢዎች ከተማዋን የቆረቆሩት የሜክሲካን ስልጣኔን ሆን ብለው በማጥፋት ሲሆን የዚህ ታሪክ አይነተኛ መገለጫው የረቀቀና በግብርና ቴክኖሎጂ የበለፀገውን ጥልቀት በሌለው የሀይቆች ገጽ ላይ የሚካሄድ የነበረውን የግብርና ስርዐት (አንዳንዴ floating islands ተብሎ ይጠራል) በማጥፋት ነው። ቅኝ ገዢዎች ነባሩን ሕዝብ በሃይል ለመግዛት እንዲያስችላቸው ይህንን የግብርና ስርዐት በማጥፋት የሀይቆቹን ክፍል ወደ የብስ በመለወጥና አስፋልት በማድረግ በማዕከላዊ ቁጥጥር ስር የዋለች ከፍተኛ እና አሰቃቂ የሀብት ልዩነት ያለባት እና ከአቅሟ በላይ በህዝብ ብዛት የተጨናነቀች የሜክሲኮ ሲቲ ከተማን ፈጠሩ። ምንም እንኳ ከተማዋ የተሰራችው ከመሬት እና ከተፈጥሮ ጋር የነባር የአካባቢው ሕዝቦች የነበራቸውን ግንኙነት በሚያጠፋ መልኩ ቢሆንም፤ አሁንም ማህበረሰባዊ ትብብር፣ አጋርነት እና በስሜት ላይ የተመሠተ የማህበራዊ ቁርኝት መንፈስ በከተማዋ እንደቀጠለ እናያለን።

ከአምስት መቶ አመታት በላይ ቅኝ ግዛታዊ ጭፍጨፋና ነጠቃን የተቀበሉ ነባር ሕዝቦች ዝግ ባለ የጊዜ ሂደት ላይ የተመሠረተና የረጅም ጊዜ ቅኝት ያለው በመረዳዳት ላይ የተመሰረተ የአኗኗር ዘዬን ለማዳበር ከፍተኛ የሆነ ችሎታን የሚጠይቅ ስርአት ዘርግተዋል። ከዚህም ጋር በተየየዘ ከተፈጥሮ ጋር የተጋመደ ማህበራዊ ህይወትን ለመመስረት ችለዋል። በዚህ ወግ አጥባቂ ፖለቲካ ራሱን በአዲስ መልክ አድሶ በመጣበት ሄትሮ ፖትሪያርካል እና ዘረኛ የሆነ የካፒታሊስት ስርዓት ከፖለቲካዊና ወታደራዊ አስገዳጅነት ጋር ተቆራኝቶ የፖለቲካ ነውጥን ፣ መፈንቅለ መንግስትን ኒዮ ሊበራል የወንጌል ሥራን እና የፍርሃት መልክአ ምድርን በሚፈጥርበት ዘመን በደቡብ አሜሪካ የብዝሀ አቀፍ ሁለንተናን የሚተልም የፖለቲካ ፍልስፍናን ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር የሞትና የሽረት ትግል ነው። ሜክሲኮ እንዲህ ያሉ ጦርነቶችን ባስተናገደችባቸው ያለፉት አስርት ዓመታት ከሜሶ አሜሪካ ባህል የሚገኘው የእውቀት ማዕቀፍ ለዘመናት የቆሰለውን ማንነቱን እንደገና ለማደስ እና ለመመለስ አይነተኛ ጥቅም እና እምቅ ሀይል አለው። በዚህም የተነሳ የነባር ማህበረሰቦች ተቃውሞ እና ትግል ለሰው ልጅ ክብር እና ደስታን ለማጐናጸፍ ለሚደረገው በአብሮነት የሚከወን ትግል የግብረገብ ህልውናውን አቅጣጫ ለግሶታል።

ከሌዲ ሪድ ጋር የነበረኝ ቅርርብ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሊጐለብት ችሏል። ከሚያፍነው ከፍተኛ ሙቀት እና ድንገተኛ ዶፍ ዝናብ ለመጠለል በቡና ቤቶች እና ግሮሰሪዎች ተገናኝተናል። በሙቀት ወቅትም ቀዝቃዛ ቢራችንን አብረን ተጐነጭተናል። በእነዚህ አጋጣሚዎች አማካኝነት ከተወለዱ ውይይቶቻችን አንዱን በድምጽ መቅረጫዬ ለማስቀረት ችያለሁ። በተጨማሪም የአለም መስራት ፕሮጀክቴን ለእሱዋ መታሰቢያነት እንዳውለው ሌዲ ሪድ ፈቃደኝነቷን ሰጥታኛለች።



አንድ የካናዳ የማዕድን አውጪ ኩባንያ ሌዲ ሪድ በምትኖርበት ትንሽ ከተማ ማዕድን ቁፋሮ በመጀመሩና ይህንን ሲያደርግ የአካባቢውን ነዋሪዎች ባለማማከሩ ሌዲ ሪድ መሬቱን ለመታደግ በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ጀመረች። ነገር ግን ይህህዝባዊ አመፅ የማዕድን አውጪ ኩባንያው ከመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የአካባቢውን መሬት እና ውሃ በመቆጣጠር አካባቢውን ለብክላ ከማጋለጥ አላዳነውም። ሆኖም የአካባቢው ነዋሪዎች አንድ ስብስብ በመፍጠር የተገፈፉትን የመናገር መብት እንዲሁም መሬት እና ውሃ ለማስመለስ ተቃውሟቸውን ተያያዙት። ከአካባቢው መንግስት አካላት ጋር በመመሳጠር ኩባንያው ማህበረሰቡን ለመከፋፈል የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ከመጀመሩም በላይ ታጣቂዎችን ሰርጐ በማስገባት ተቃውሞውን ለመስበር ብዙ ጥረት አደረገ። የሀይል እርምጃዎች መወሰድም ተጀመሩ። ሁኔታውም እየተባባሰ መጣ። ሌዲ ሪድ አንድ ምሽት ከጓዶቿ ጋር ወደምትኖርበት ከተማ እየነዱ በሚሄዱበት ጊዜ በደረሰባቸው ጥቃት አንድ ባልደረባቸው ሲሞት ሌዲ ሪድ ደግሞ ሁለት ቦታ በጥይት ተመታች። ከቁስሉ ሙሉ ለሙሉ ለማገገም ስድስት አመታት ወሰዱባት። አንድ ጊዜ ባደረግነው ውይይት ሌዲ ሪድ በአካባቢዋ ጥቃትን በጽናት አልፈው እንደገና ትግላቸውን የሚቀጥሉ ሰዎች ትንሽ ኦፖሰሞች እንደሚባሉ ነገረችኝ። የሜሶ አሜሪካ የስነ ፍጥረት ታሪኮች ኦፖሰምን እንደ ዘለአለማዊ ህይወት ተምሳሌት ይመለከቷታል። ኦፖሰም የሞተች መስላ እንደገና እንደምታንሰራራ ይተርካሉ።

ይህ የኦፖሰም ፅናት የሚባለው ሥራ የሜሶ አሜሪካን አፈታሪኮች ከአሁን ዘመን ጉዳዩች ጋር በማያያዝ የተፈጠረ አዲስ ታሪክ (fabulation) ነው። ታሪኩ አራት ገፀ-ባህሪዎች (አንድ ኮረብታ፣አንድ አፖሰም፣ ሌዲ ሪድ እና ብዙ ጡቶች ያሏት የአጌቭ ተክል) ያሉት ሲሆን እነዚህ በተለያዩ የጊዜ ቀመሮች የሚኖሩ ገፀ ባህርያት አንድ ላይ የሚመጡበትን የአለም ፍጥረት እና አሁን በኦክሳካ እየተካሄዱ ያሉ ንጥቂያዎችን የሚቃወሙ ተጋድሎዎችን በአንድ የታሪክ ንድፍ ውስጥ በማምጣት የሚደረግ ትርክት ነው። አራቱ ገፀ-ባህርያት የንጥቂያ እና የጥቃት ስርዓቱን በመቋቋም እንዲሁም አንድ ላይ በመምጣት አንድ ክብረ በዐል አዘጋጅተው ከፊል ድላቸውን ያከብራሉ። ይህን የሚያደርጉት የአካባቢው ሰዎች ለግል ጥቅማቸው ማዕድን ማውጣት በተከለከሉበት አውድ ነው።



← On the set of *Opossum Resilience*, by Naomi Rincón Gallardo; photo by Claudia López Terroso, 2019

“በአብዛኛው የሜሶ አሜሪካ አፈ-ታሪክ ምድር የተቀደሰች ቦታ ናት። ሃብታም የሆነች አድባር ናት። መከራና እርኩሰትም ምድርን በሞሉ በሰዎች ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ። ምድርም አዳላጭ እና የአደጋ ስፍራ ናት።ስርአቷም ብሉያዊ በሆነ የክፋት እና የደግነት ሁለትዮሽ ውስጥ ነው።እንደ አድባር ሰዎችን እንደ ስራቸው ልትሸልምም ልትቀጣም ትችላለች የ EZLN ንዑስ ኮማንደር እንደሚያትተው እነዚህ ነባር ሰዎች እንደሚሉን ምድሪቱ እናታችን ናት፤የባህል ስሌት ሰሌዳ ነች። በውስጧም ታሪክ እና ሙታን ይኖራሉ።”
ጉዳዩ የነባር ሴቶች ምድርን በተመለከተ የሚያቀርቡትን ሰፊ የሆነ ትንታኔን ማዳበር ነው።ለእነርሱ ምድር/መሬት ለእርሻ ጉዳይ የምትውል ቁራጭ ቦታ አይደለችም። የመሬት ጥያቄያቸውንም እንዲህ ባለ በደጎየ መልኩ ማቅረብ የለብንም (…) የመሬት መብት ጥያቄያቸው ምድርን እንደ እትብታቸው መቀበሪያ ስፍራ፣እንደ ቅዱስ ቦታ፣ማንነታቸውን የምትሰራ ተምሳሌት መመልከት ስለሚገባው የቁራጭ መሬት መብት ፍለጋ ተደርጎ መተርጎም የለበትም። (…) ኮማንደር ኤስተር እንደምትለው ምድር ሕይወት፣ ተፈጥሮ እና የኛ አካል ናት።ይህ ቀላል የሚመስል ሀረግ በሜሶ አሜሪካ ስነ-ትእይንተ አለም (Cosmology) ህልውና ያላቸው ነገሮች ሁሉ ቁርኝት እንዳላቸው ያመለክታል። ህልውና ያላቸው ነገሮች አንዱ ከሌላው የተነጠሉ አይደሉም። ይህ መሰረታዊ የህልውና መርህ በነባር የህክምና ስርአቶች እና የመጀመሪያዎቹ የታሪክ ምንጮች መረጃ ጋር ስምሙ ነው። ይህ መርህ የሰዎችን ስብስብ/ማህበር በተለየ መልኩ በመስራቱ የተነሳ ምንም ነገር በነፍስ-ወከፍ ሊቆም እንደማይችል ያስረዳል።አለሙም ከኛ ውጪ እና ከሰዎች ተለይቶ የሚገኝ ነገር አይደለም--በውስጣቸው እና በነሱ በኩል የሚወለድ እንጂ። “እኔ” ከአከባቢው ተነጥሎ አይገኝም። የ“ቁስ” አለሙ ውንፍትነት (permeability) የኑረትን ባህሪ ቁሳዊ እና ቁሳዊ ባልሆኑ ነገሮች እንዲሁም በውስጥ እና በውጪ መካከል ያለውን ቀጣይ ተላላፊነት ይቀርፃል።”
— Sylvia Marcos, *The Borders Within*



በሜሶ አሜሪካ ስነ-ትእይንተ አለም ኮረብታዎች እና ተራሮች ቅዱስ ስፍራዎች ተደርገው ይታያሉ።የቅድስና ተምሳሌትነታቸው የሚመጣው ከዋሻዎችና በመሬት ውስጥ ለውስጥ በሚተላለፉ የውሃ አካላት መነሻ ምንጮች ስለሆኑና ወደ ሙታን አለም የሚያደርሱ የመሬት አካላት ተደርገው ስለሚታዩ ነው።፡ ኦፖሰም ደግሞ እሳትን፣ትምባሆን እና አልኮልን ሰርቃ ለሰዎች የምትጋብዝ እንስሳና አማልክት ናት።አጌቩ የምትባለው ተክል ደግሞ የናሃው ህዝቦች ሴት አማልክት የሆነችው ማያሁዌል የተገኘችባት የተቀደሰች ተክል ናት። ማያሁዌል የሴት ፍሬያማነት (fertility) ተምሳሌትና 400 ጡቶች ያሉዋት አማልክት ናት። በሚክስቴክ (የሜሲኮ ሜሶ አሜሪካ ነባር ህዝቦች) ብሂል ሌዲ ናይን ሪድ ደግሞ እበቦችን እንደ ጸጉር በራሷ ላይ የምትጎነጉን በእጇ ቢለዋ ይዛ የአጌቩ ቅጠሎችን የምትቆርጥ ሴት ናት።

በኦፖሰም ጽናት ውስጥ ኮረብታው የተለያዩ ህልውና ያላቸውን አካላትን የጊዜ ቀመር በመመልከት ስለነርሱ ታሪክ የሚተርክ አካል ነው። ይህ አፈ-ታሪካዊ ንድፍ አስፈሪ በሆነ ጨለማ ውስጥ በሚንጨላጨል የብርሃን ትርኢት ይጀምራል። ይህ ትርዒት በእጅጉ ከተለወጠ-ከተጎዳ መልክአ ምድር እና ብልጭ ድርግም በሚል ብርሃን አማካይነት በነጎድጓድ ሲናጥ ከሚታየው ኮረብታ ምስል ጋር በመለዋወጥ ይታያል።

Yo soñé con los naguales
Porque ando eriza de ancestros
Ante los planes siniestros
De las zonas especiales:
Conflictos territoriales,
Extracción rapiñadora
¡Yo te invoco protectora,
Ven en forma de culebra,
Que tu trueno el cielo quiebra
Con su fuerza vengadora!

አበውና እመውን ስለናፈቅኩ
ናጉዋሌዝን በህልሜ አየሁ
በእርኩስ እቅድ ፊት
የተለያዩ የኢኮኖሚ ዞኖች በሰሩት
ልክ የለሽ-ስግብግብ ነጣቂነት
እጠራሻለሁ አዬ ጠባቂዬ እልሻለሁ
በእባብ መልክ ነይ
ይስበር ነጎድጓድሽ ሰማይ
ቂም በወለደው ሃይል



← On the set of *Opossum Resilience*, by Naomi Rincón Gallardo; photo by Claudia López Terroso, 2019

ኦፖሰሟ በሌዲ ሪድ አጋዥነት የአጌቯን ወተት (ፐልክ) ትፈልጋለች። ከፍለጋዋ ስትመለስ በመንገዷ ያገኘችውን ሁሉ ትሰርቃለች፤ በጀርባዋም ልጇን አዝላለች። ሌዲ ሪድ ደግሞ በቆንጨራዋ የአጌቩን ቅጠሎች ትቆርጣለች።



¿Cuál será aquel animal
Que en figurilla de barro
En el pecho lleva flores
Y en la trompa un torzal?

¿Qué criatura trepadora
Roba el fuego con su cola
Traza el curso de los ríos
Y aparece con la aurora?

Ponle un jarro de aguamiel
Pa que venga y se emborrache
En los tiempos de despojo
Que no haga falta el tepache
Aticen todos los fuegos
¡Y que regrese el tlacuache!

ማናት ይህች እንስሳ እንደ ሸክላ ምስል
አበቦችን በደረቷ ገመድን በሾለ አፍንጫዋ
ማናት ይህች ተንጠልጣይ ፍጥረት እሳት
በጭራዋ የምትሰርቅ

የወንዞችን ፈለግ ተከትላ በፀሃይ ንጋት ብቅ
እምትል?
አጉሜል በእንስራ አኑሩ መጥታ
እንድትጠጣ።

በንጥቂያው ዘመን ቴላፓቼው እንዳያንስ
እሳቱን ቆስቁሱት
ኦፖሶምዋ እንድትመለስ!
ማነች ይህች ነባር ህይወት
ሁለት ማህጸን ሁለት እምስ ያላት?
በሚፈውሱ ጭራዎችዋ ሰውነትን የምትከፍት



¿Cuál es la especie nativa
Dos úteros y vaginas
Cuya cola curativa
Cavidades desopila?

¿Cuál será el mítico ser
Que con sus crías al lomo
Se hace el muerto, aguanta golpes
Para después renacer?

¡Ponle un jarro de aguamiel!
Pa que venga y se emborrache
En los tiempos de despojo
Que no haga falta el tepache
Aticen todos los fuegos
¡Y que regrese el tlacuache!

¿Quién es ladrona mañosa
Con manitas de persona
Que deguella las gallinas
Por su sangre deliciosa?

¿Cuál es aquel marsupial
Dueño frío de la noche
Que en su panza de costal
Guarda tabaco y mezcal?

ማነች ይህች አፈ-ታሪካዊ ህይወት
ልጆችዋን በጀርባዋ የምታዝል?
እንደገና ለመወለድ
ጡጫን ቀምሳ ሞትን የምታታልል
አጉሜል በእንስራ አኑሮ መጥታ
እንድትጠጣ።
በንጥቂያው ዘመን ቴላፖቼው እንዳያንስ
እሳቱን ቆስቁሱት
አፖስሟ እንድትመለስ!
ማነች እሷ ይህች አድቢ ሌባ?
የሰው እጆች ያሏት
ዶሮዎችን አርዳ ጣፋጭ ደማቸውን
የምትጠጣ
ማነች ይህቺ ማርሱፒያል
የቀዝቃዛቀው ሌሊት ባለቤት
በቋት መሳይ ሆዷ ትንባሆና ሜዝካል
የምትይዝ?



ብዙ ጡቶች ያሏት አጌቭ ፍጥረታትን ለመማረክ ትመጣለች፤ ለሰዎችም ዳንስና ፌሽታን እንዲሁም ለስካር አለም መንገድ ትከፍታለች። አጌቹ በብዙ ማዳበሪያና በአንድ እህል የበላይነት ስር በመሆኑ ቀጥኗል፤ የአልኮል ሃይሉም ነጥፏል።

↻ On the set of *Opossum Resilience,* by Naomi Rincón Gallardo; photos by Claudia López Terroso, 2019

Déjame ablandar tu cuerpo
Yo te ayudaré a llorar
Niño otra vez te volverás
Ya no serás individuo
Sacando eructos y pedos
Irradiarás puro cariño
Te acordarás de tus muertos
Te despojarás de tí mismo
Fermentos sacramentales
Hígado luminiscente
Te diluirás dulcemente
Abriéndote a un caos profundo
De intoxicantes rituales
Cachondo mareo rotundo
Fuerzas sobrenaturales
Te harán viajar a otro mundo
Mi tierra esta amenazada
Forzada al monocultivo
Por el empresario altivo
Cuyo credo es el capital
Mi sangre sobre-explotada
Antes era medicinal
Hoy hiper-fertilizada…
¡Han gentrificado el mezcal!

አካለችሁን ላለስልሰው
እንደገና ማልቀስ ትችሉ ዘንድ ላግዛችሁ
እንደገናም ልጆች ትሆኑ ዘንድ ላስችላችሁ።
ግለሰብ ብቻ ከእንግዲህ አትሆኑም
ከእራሳችሁ ላይ እራሳችሁን ትገፍፋላችሁ
የተባረኩ እርሾዎች
የማያቃጥሉ እሳቶች
የሚያበሩ ጉበቶች።
በጣፋጭነት ትቀጥናላችሁ
እራሳችሁንም ጥልቅ ለሆነ የስካር ሁከት
ትእይንት ትከፍታላችሁ
ሻፋዳ ለሆነ የሚያስተጋባ ድንዛዜ
(እና) አማልክታዊ ሃይል
(ይህም) ወደ ሌላ አለም ይወስዳችኋል።
መሬት በአደጋ ላይ ነች
በአንድ እህል ግዳጅ
ቀኖናቸው ገንዘብ በሆነ
በንግድ ባላባቶች።
ደሜ ከመጠን በላይ ከመበዝበዙ በፊት
ለፍጥረታት መድሃኒት ነበር
ዛሬ በማዳበሪያ ነጥፏል
ሜዝካሉም ተፈጥሮውን ቀይሮ ሁሉን
አጥቷል!







ኮረብታው የመሬት መብት ተሟጋቾዋን ሌዲ ሪድን ለመግደል የተደረገውን የአድፍጦ ማጥቃት ሙከራ ይተርካል። ተከተሏት-- ደረሱባትም-- አድፍጠውም በመስቀለኛ ቦታ ላይ አጠቋት። እሷንም ሊያጠፉ ሞከሩ።ወደ ብጥሥጣሽ ሊቀይሩዋት፤ ዶግ አመድ ሊያደርጉዋት።የተሳካላቸውም መስሏቸው ነበር። እሷም የሞተች መስላ እንደ አፖስም አሳሳተቻቸው። ሲሄዱም አካላቷን ቆዳዋን፣ጸጉርዋን፣ልቧን፣ጫማዎችዋን፣ልብሷን፣እግርዋን እና ሁለመናዋን ሰብስባ ሁሉን ቦታው መለሰች። ከተነሳች በኋላ ጥንካሬዋም ተመለሰ።

ኦፖሰሟ ሌዲ ሪድን እንዴት እንደምታንሰራራ አስተማረቻት። ሌዲ ረድም ምርኩዟን ይዛ በዋሻው ደነሰች።



↻ On the set of *Opossum Resilience*, by Naomi Rincón Gallardo; photos by Claudia López Terroso, 2019

Naciste bajo ciclos de lluvias constantes
Temporadas de siembras y cosechas regulares
Creciste bajo un manto de saberes ancestrales
Un mundo ordenado por las fiestas patronales
Aprendiste a usar la yunta y pastear al ganado
Sembrando calabaza, maiz, frijol, garbanzo
Te formaste rodeada de estructuras agrarias
De ejidos y de tierras comunitarias
Enmedio de asambleas, decisiones colectivas
Organización apartidaria para gestionar la vida
Tus padres te inculcaron el amor por la tierra
¡Por eso la defiendes en tiempos de guerra!

Tiempos de guerra llamada despojo
Catástrofe ecológica en disfraz de desarrollo
Empresas extractivas contratando sicarios
Destrucción a sangre y fuego de mundos milenarios

በማያቋርጥ የዝናብ ዑደት ውስጥ ተወለድሽ
በማያቋርጡ ወቅቶች
አዝእርት እና ሰብሎች
በእመው እና አበው ከለላ አደግሽ።
በቅዱሳን በአላት በተዋጀ አለም
ተማርሽ ቀንበርን መጫን ከብቶችን መመገብ
መዝራት፤ ዱባን፤ በቆሎን ባቄላን ሽምብራን
በግብርና መዋቅራት በኤጂዶስ እና በጋራ መሬት ተከበሽ።
ህይወትን ለማስተዳደር በማህበራት
በምክር ጉባኤዎች
በጋራ ውሳኔ ስርአቶች ተከበሽ።
ያለ ፖለቲካ ፓርቲዎች

ወላጆችስ መሬቱን እንድትወጂ አስተማሩሽ
ለዛ ነው በዚህ ጦርነት ስዓት የምትታደጊ መሬት
በእነዚህ የንጥቂያ የጦርነት ጊዜያት
የስነ-ምህዳር ውድመት--ሲባል ልማት




Los chismes se esparcieron creando confusión
Visitas aisladas, fases de exploración
Contubernios corruptos con las autoridades
Concesiones sin consulta a las comunidades

Te uniste a la brigada para tomar la mina
Llevaron tinaco, cobijas, cocina
Como los compañeros se iban a trabajar
Cerca de cien mujeres fueron a ocupar

የስነ-ምህድር ውድመት--ሲባል ልማት
ነጣቂ ኢንዱስትሪዎች ነፍሰ ገዳይ የሚቀጥሩበት
የሺዎች አመታት ደምና እሳት የሚወድሙበት።
ሃሜት ሲነዛ ሰዎችን ሊፈታ

ጉብኝቶች ግኝትን ፍለጋ
ብልሹ ውሎች የባለስልጣናት
ጀማው የማይመክርበት።
ቁፋሮውን የማዕድኑን ለመያዝ



La policia estatal llegó a desalojarlos
Helicópteros y perros, elementos armados
Carros antimotines, detenciones arbitrarias
Despliegue coercitivo para intimidar la banda
Tiempos de guerra llamada despojo
Fuerzas paramilitares forzando el desalojo
Cinturones estratégicos, zonas especiales
Depredación masiva de bienes naturales

Frente a las amenazas y represión abrumadora
Se juntaron para formar la coordinadora
Gestiones para el pueblo
Brigadeos de información
Animar con festejos el espíritu de organización
Pusiste ahi tu tiempo, energía y pensamiento
Tu presencia y voz encendieron el firmamento
Joven mujer indígena defensora de la vida
Constelación de fuerzas tejiendo alternativas
Una noche de regreso en un cruce de caminos
Rafaguearon su nave un grupo de asesinos
Uno de tus compas cayó en el atentado
El coche en el que iban terminó destrozado

En estos tiempos de guerra llamada despojo
Tu sigues de pie resistiendo con arrojo
La herida de tu pierna memoria del agravio
Sigue irradiando rabia y deseo libertario

ብርጌዱን ተቀላቀል ማዕድኑን ለመውረር
የውሃ ታንክ ፣ብርድልብስ፣ ተንቀሳቃሽ ኪችን ያዝሽ
ወንዶች ወገኖችሽ ስራ
መቶ ሴት ጓደኞችሽ ማዕድኑን ያዙ
ፖሊሶችም ለማፈናቀል መጡ
ሄሊኮፕተሮች ውስጥ የታጠቁ ወታደሮች
አመጽ መበተኛ መኪኖች
የዘፈቀደ እስሮች
ሀይል፣ ማስገደድ
ህዝብን ለማስፈራራት።
ይህ ንጥቂያ የተባለ የጦርነት ጊዜ
ቅጥር ህገወጥ ወታደሮች ሃገር ሲያስለቅሱ
ስትራቴጂያዊ መስመሮች ልዩ ዞኖች
የተፈጥሮ ውድመት
በዚህ ሁሉ ሽብር እና ሀይል
የመረጃ ብርጌዶች።
አንድ ላይ መጥታችሁ ስብስብ በመፍጠር
ለህዝቡ ሀብትን ለማስተዳድር
በፌሽታ የስብስቡን መንፈስ ማስደሰት
ጊዜሽን ሀይልሽን እና ሃሳብሽን በመሰዋት
መኖርሽ ፣ድምጽሽ ገነትን አበራት
ወጣት ነባር ሴት የመሬት ተሟጋች
ብዙ አካላት አማራጮችን በመፍተል
ወደ ቤትሽ በተመለስሽበት ምሽት
ቅጥር ገዳዮች መኪናሽን አጠቁ
አንድ ጓድሽ በጥቃቱ ሞቱ
መኪናውም ከጥቅም ውጪ ሆነ
በዚህ የንጥቂያ የጦርነት ዘመን
አሁንም ቆመሻል፤በድፍረት ቅዋሜ
የእግርሽ ቁስል የነውሩ ማስታወሻ
ቁጣን እና የነጻነት ምኞትሽን ያቀጣጥላል።

← On the set of *Opossum Resilience*, by Naomi Rincón Gallardo; photo by Claudia López Terroso, 2019








# የተዳቀሉ አፈ-ታሪኮች ከደቡብ ንፍቀ-ክበብ

በሜሶ-አሜሪካ ስነ-ትእይንተ አለም ጊዜ እርስ በእርሱ የሚጠላለፍ ጠመዝማዛ አውዳዊ (cyclical) እና ሁልግዜ የሚለወጥ ተደርጎ ይታያል። በሜሶ አሜሪካ ስነ-ግጥምና ስነ ቃልም ይህ ተጠላላፊነትና ተደጋጋሚነት ይታያል። በግጥም ላይ ለምሳሌ ተከታታይነት ያላቸው የግጥም አንጓዎች በመካከላቸው ያለው የቃላት ልዩነት ትንሽ ስለሆነ የሃሳብና የስሜትን ተደጋጋሚነት ከማሳየቱም በላይ በተለያዩ መንዶች አንድን ሃሳብና ስሜትን የመግለጫ ዘዴ ነው። የዘዬዎች እና የአባባሎች ተደጋጋሚነት ሃሳብን ውስብስብ፣የሚቀያየር፣ አንድ ላይ በተመሳሳይ ጊዜ ሊፈጠር የሚችል እና አንዱ ሌላውን የሚያግዝ እና የሚያዳብር ያደርገዋል። (1) ይህ የተለያዩ ሃሳቦችን በተቃራኒነት ከሚያስቀምጥ የአስተሳሰብ ስርአት እና ስነ-ትእይንተ አለም በእጅጉ የለየ ነው። በሜሶ አሜሪካ ስነ-ትእይንተ አለም እያንዳንዱ ህልውና ያለው አካል ሕይወት ያለው (animated) ሲሆን በተለያየ ግዜ ማንነቱን የሚለወጥ ነው። በዚህ የሀሳብ ስርአት ህይወት የተለያ "ቆዳ" እና አካልን ይወስዳል፤ የተቸከለ ሳይሆን በተለያዩ ማንነቶች የዳበረ እና አንዱ ከሌላው ጋር በእጅጉ የተቆራኘበት ተላዋዋጭ (fluid) ስነ-አለም ነው።

የአለም ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ በተለያዩ አፈ ታሪኮች እና የስነ ፍጥረታት ትርክቶች ሃብት የዳበረ የአለም ክፍል ነው። ይህም ጥንታዊ የሆነ ንፍቀ ክበብ ህብረተሰባዊ ድርጅትን፣ እሳቤን እና ተምሳሌታዊነትን የሚመሰክር ነው። ሰው ያልሆኑ አካላትና ህልውናዎች በብዝሃ ንፍቀ አለም ውስጥ የሚኖሩበት እና አድራጎታዊ (agency) ማንነት የተላበሱበት ንፍቀ ክበብ ነው። የተለያዩ እሳቤዎች፣ በአብሮነት (co-presence) የሚኖሩበትና የተለያዩ ህልውናዎች እርስ በርስ የመረዳዳት ግንኙነት ያዳበሩበት ስነ-አለም ነው። ምንም እንኳን የረጅም ዘመን ቅኝ ግዛት የንፍቀ ክበቡን የእውቀትና የእሳቤ ማእቀፍ አድኖ በመግደል (epistemicide) ላይ ቢሰማራም እነዚህ ስነ-አለሞች በነባር ህዝቦች ስነ-ቃል፣ስነ-ትእይንት፣የህክምናና የፈውስ ስርአቶች፣ሙዚቃ፣ክወና፣ስእላዊ ተምሳሌቶች፣በአላትና የትረካ ስርአት ውስጥ ተጠብቀው ይገኛሉ።

ነገር ግን አፈ-ታሪኮች አንደንድ ጊዜ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን፣አካላትን፣ጾታዎችን እና ወሲባዊ የማንነት ስርአቶችን ሊያገሉ እና በብሂል ውስጥ ያሉ መገፋቶችን ሊያጠናክሩ ስለሚችሉ አፈ-ታሪኮችን በማዳቀል ሂደት ጨቋኝ እና ኢፍትሃዊ ይዘታቸውን ማስወገድ ይቻላል። በዚህ ስራ ላይ የተዳቀሉ አፈ-ታሪኾች ኢ-ቅኝ ግዛታዊ (decolonial) አመለካከት እና (ኲዊር) ማንነትን እንደ መሳሪያ ተጠቅመው መብታቸውን እንዲያስከብሩ ይረዳቸዋል።

ከደቡባዊ ምስራቅ ሜክሲኮ የዛፓቲስታ ታጋዮች ብዝሀ አቀፍ ሁለንተናን ለመገንባት የስነ ዖታ ግንኙነት ሚዛናዊነትን ፣ ከተፈጥሮ ጋር ያለ ቁሳዊ ቁርኝትን እና አማራጭ የፍትህ ስርአትን በመገንባት ላይ ይገኛሉ።እንደ ፖለቲካዊ እና ስነ ጥበባዊ እስትራቴጂ ዛፓቲስታዎች የማያን ጥንታዊ ስልጣኔን እና የስነ ጥበብ እሳቤዎቹን በመጥቀስ የምንኖርበትን የውድመትና የጨለማ ዘመን ለማለፍ የሚያስችል የህይወት ኡደት መታደስን ለመተለም ይጥራሉ። በንዑስ ኮማንደር ማርቆስ (አሁን ጋሌያኖ ነው የሚባለው) ከቀደምት አካላት ጋር በመነጋገር የተጋድሎ እንቅስቃሴውን እንደሚያበረታታ ከፅሁፉ መረዳት እንችላለን። ኮማንደሩ በዚህ ፅሁፉ ከአንድ ትንሽ ጥንዚዛ (beetle durito) ጋር በሚያደርገው ውይይት ኒዮ ሊበራልሊዝም በደቡብ አሜሪካ ላይ እያስከተለ ስላለው ተፅዕኖ ይገልፃል።

**በውስጣዊ ቀኝ ግዛት (internal colonialism) ሙሉ ለሙሉ ያልተመታውና ያልታፈነው የነባር ህዝቦች የድሮ ዘመን ታሪክ በሌሎች ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ውስጥ ባሉ ቅኝ በተያዙ ህዝቦች ውስጥም ታምቆ ለመገለጥ ይጠባበቃል። ይህን የድሮ ዘመን ታሪክ መፈለግና እሳቱን መቆስቆስ የሚስትዜክስ ህዝቦች ወደፊት ለምንገነባው ኢ ቅኝ ግዛታዊ አለምን የመስራት ተግባር አይነተኛ አስተዋፅኦ አለው። የነባር ህዝቦችን አፈ ታሪኮች እንደ መሳሪያ በመጠቀም ስሜታዊ ማንነትን በማነቃቃት የሚወጠንን አለምን የመስራት ጥረት በአለም ዙሪያ እያንሰራራ የሚገኘውን ፋሽዝምን ለመታገል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው።**

(1) Sylvia Marcos, "The Borders Within: The Indigenous Women's Movement and Feminism in Mexico," in eds. Marguerite Waller & Sylvia Marcos, *Dialogue and Difference: Feminisms Challenge Globalization* (London: Palgrave Mcmillan, 2005), 81–112.

# መስተጋብሮችና የተዳቀሉ አፈ-ታሪኮች

ይህ ገቢር አፈ-ታሪኮች ላይ የተመሰረቱ አካባቢ ተኮር ትርክቶች እንደ ታሪክን መንገሪያ መሳሪዎች በመጠቀም በዘመናችን እየተከናወኑ ያሉ ንቅናቄዎችን እና እነርሱን የሚቃወሙ እንቅስቃሴዎችን ይመለከታል። ይህ የትርክት ገቢር የመሸነፍን ትርክት ከማራባት ይቆጠባል።

ኦፖሰሞች በሜሶ አሜሪካ አከራካሪ ውክልና እና ስም ያላቸው እንስሳት ናቸው።በጨለማ የሚሰክሩ እና ሌቦች ተደርገው ይወከላሉ። ነገር ግን ለሰዎች ደስታን እና የሚቀጣጠል ስሜትን፣ ምግብ ለማብሰል አስፈላጊ የሆነውን እሳትን፣ፈንጠዝያን እንዲሁም ለሰውነት ሙቀትን የሚሰጡ ፍጡራን ተደርገው ይሳላሉ። በዚህ አፈ ታሪካዊ ውክልናቸውም እሳትን በጭራቸው ጠልፈው በመስረቅ በሆዳቸው ቋት ደግሞ ትንባሆና አልኮልን በመያዝ ችሎታቸው ይወሳሉ።

በሜሶ አሜሪካ አፈ-ታሪኮች ኦፖሰሞች የማይሞቱ እና ቢሞቱም መልሰው እንደገና የሚያንሰራሩ ተደርገው ይሳላሉ። በአንዳንድ የኦክሳካ መንደሮች ጉልበታም እና ፅኑ ሰዎች ባላቸው አቅምና ብርታት እንዲሁም ከጉዳት የማገገም ችሎታ የተነሳ “ትንሽ አፖሰም” (tlacuachitos) ይባላሉ። ኦፖሰሞች ከተመቱ፣ ከተጎዱ በኋላ ያለ የሌል ሀይላቸውን አሰባብበው እንደገና በማንሰራራት ይታወቃሉ።

ኦፖሰሞች ስለ መትረፍ፣ብርታት፣እና ጽናት ምን ያስተምሩናል? እነዚህ ችሎታዎችስ እንዴት ንጥቂያን ለመታገል ሊያገለግሉን ይችላሉ?

ተቀባዮች፡- የስነ-ጥበብ ተማሪዎች፣ የስነ-ጥበብ ሰዎች (የክዋኔ፣ሙዚቃ፣የስእል፣የቪዲዮ፣ፊልም፣ ስነ-ግጥም ወዘተ)፣ የባህል ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች፣የመብት ተሟጋቾች፣የመሬት መብት ታጋዮች በዚህ ገቢር ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

ዝግጅቶች:- የገቢሮቹ አመቻች የተመረጡ ንባቦችን በተሳታፊዎቹ ቋንቋዎች ከገቢሮቹ በፊት ማዘጋጀት ኖርባቸዋል። በተጨማሪም በዚህ አካባቢ እየተከናወኑ ስላሉ የነጠቃ ፕሮጀክቶች የተጻፉ ጽሁፎችን ማዘጋጀት ይበረታታል። (ታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች ተመልከቱ)

ስፍራ፥- በደንብ ብርሃን የሚገባበት ክፍል፣ ጠረጴዛዎች፣ትላልቅ ወረቀቶች፣ማርከሮችና ማጣበቂያ፣ ከተቻለ የምስል ማስፈንጠቂያ (projector)፣ ከተቻለ የድምጽ ማጉያ መሳሪ፣ ከተቻለ ላፕቶፕና አዳፕተር፣ ውሃ፣ ኩኪስ፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ ሻይ ቡና፣ እና ሌሎች በአካባቢው የተለመዱ መጠጦችን።



እኛ እነማን ነን? እኛ ሉላዊ ደቡባዊያን ነን። ትልቁ የፍጡራን እና የፍጥረታት ስብስብ ለማይበቃው የካፒታሊዝም የቅኝ ግዛት፣የአባታዊነት ስርአት እና ሌሎች የእነርሱ ተቀጣሪ የሆኑ ጨቋኝ አካላት መስዋዕት የቀረብን። በሁሉም ትላልቅ የታሪክ ሁኔታ ላይ ነበርን ምክንያቱም መልክአ-ምድራችን የኢፍትሃዊነት እና የጭቆና መልክአ-ምድር ነው።ሁሉም ሰው አይደለንም፤ እኛ ተስፋ በመቁረጥ ለመስዋእትነት ራሳችንን አናቀርብም። በመሆኑም (ሁሌ) እንቃወማለን፤ የሰው ልጅ ክብር አለን።

— Boaventura de Sousa Santos, *Epistemologies of the South*




## ገቢሮች

### መድረስ

- በጠረጴዛ ዙሪያ የተቀመጡ መጠጥ እና ቀለል ያሉ ምግቦችን ተካፈሉ
- ለምትሰሩት ስራ እና ለህይወታችሁ ትልቅ ቦታ ያለውን ስፍራ በመተረክ እራሳችሁን ለሌሎች ተሳታፊዎች አስተዋውቁ። ይህ ቦታ ከነባር ህዝቦች ጋር ያለውን ግንኙነት ለሌሎች አጋሩ። ስለቦታው የጋራ ትግሎች፣ስለአባለቱ፣ ስለ ፈውሱ እና ለውጡ የምታውቁት ምንድን ነው? እረፍት ውሰዱ።

### በተሳታፊዎች ዘንድ የሚገኙ እውቀቶችን እና ሊዳብሩ የሚችሉ ትብብሮችን ዘርዝሩ

- ትልቅ ወረቀት፣ማርከሮች እና እርሳሶች ጠረጴዛው ላይ አስቀምጡ። ለተሳታፊዎች ምን ምን ነገር ላይ ጥሩ እውቀት እና ክህሎት እንዲሁም ፍላጎትና ፍቅር እንዳላችሁ አጋሩ።
- የተሳታፊዎቹን እውቀቶች፣ፍላጎቶችና ፍቅሮች ስብስብ ዘርዝራችሁ ፃፉዋቸው።በመካከላቸው ያሉትን ትስስሮች አጢኑ።
- ወረቀቱን ግድግዳ ላይ ስቀሉት እና ወርክሾፑ እስኪጠናቀቅ እዛው ተውት።

↑ This and all following photos in this section document the workshop “Mythico-critical Fabulations in Times of Dispossession”, at IAGO, Oaxaca by Naomi Rincón Gallardo, 2019



## ገቢሮች

### አንድ ላይ ማንበብ

- ከዚህ ምእራፍ በታች የተዘረዘሩትን ማጣቀሻ ንባቦች ተመልከቱ፤ ከነርሱም ውስ ጥዕሁፎችን መርጣችሁ ጮክ ብላችሁ ለተሳታፊው አንብቡ
- በቡድን በመከፋፈል ስለራሳችሁ አስፈላጊ ናቸው ብለችሁ የምታስቧቸውን ቃላት መርጣችሁ ተወያዩባቸው

### የንጥቂያ ውሎች እና ስንጥቆች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶቻቸውን ፃፉ፡-

በዚህ አካባቢ ስለተበራከቱ የንጥቂያና የገፈፋ ፕሮጅክቶች ምን ታውቃላችሁ? በዚህ ሂደት ከሰዎች ሌላ የተጎዱ ህልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡ ምን ምን አካላት አሉ?

- እነዚህን ፕሮጅክቶች ለመቃወም እና እምቢ ለማለት ሰዎች ምን እያደረጉ ነው?
- መልሶቻችሁን አንድ ላይ ተወያዩባቸው በትልቅ ወረቀት ላይ መዝግቧቸው።
- አንድ ላይ ሆናችሁ እነዚህን የንጥቂያና የገፈፋ እርምጃዎችን ለመገዳደር ስለተቋቋመሙ ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎቻቸው ዘርዝሩ።ሰዎች እንዴት እየተደራጁ ይገኛሉ? ትግሎቻቸው ምን አይነት መልክ አላቸው?
- ስለእነዚህ ጉዳዮች ለመነጋገር ማንን መጋበዝ እንደሚያስፈልጋችሁ በጋራ ተወያዩ
- የስም ዝርዝራቸውን አዘጋጁ ግብዣውን የሚያደርጉ ሰዎችን መድቡ።





## ገቢሮች

### የአፈ-ታሪኩ የታሪክ ንድፍ:-

አንድ ጊዜ ነበር፤ ሌላ ጊዜ፤ አፈታሪኩ (There was a time, another time. The myth)

- ከአካባቢው የሰማኋቸው አፈ-ታሪኮች ውስጥ ገፀ ባህሪን ምረጡ። እነዚህን ከስነ ቃል (ከዘፈኖች፣ውይይቶች፣የፈውስ መዝሙሮች እና አባባሎች)፣የተፃፉ ምንጮች(የነባር ህዝቦች የተሰበሰቡ አፈ-ታሪኮች፣ተረቶች )፣የምስልእና ሌላ ቁሳዊ ምንጮች(የሸክላ ስራዎች እና ሌሎች አካባቢያዊ ቁሳዊ ውጤቶች)እና ማህበራዊ ክዋኔዎች (ትርኢቶች እና ክብረ በአላት)ልታገኗቸው ትችላላችሁ።ከአካባቢው ስለ አፈ-ታሪኮች የሚያውቁ ሰዎችን አነጋግሩ አፈ-ታሪካዊ ንድፍን ለማዘጋጀት የተለያዩ ቁሳቁሶችን አንድ ላ አምጡ (ለምሳሌ ማስታወሻ ደብተር መመዝገቢያ ዶሴ፣የኮምፒውተር ፎልደር፣ጠረጴዛ፣ካርቶን ሳጥን ወዘተ...)
- በግላችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ንድፈ ሃሳባዊ ዝርዝሮችን አዘጋጁ። እነዚህ አፈታሪካዊ ህልውናዎች (አካላት) እነማን ናቸው? የአድራጎት እና የችሎታቸው መጠን ምን ያህል ነው? በአካባቢው ተፈጥሮ ላይ ያላቸው ሚና ምንድ ነው? ከእነማን ጋር ግንኙነት አላቸው? ግንኙነቶቻቸውስ እንዴት ያሉ ናቸው? በንጥቂያው ዞን ውስጥ በምን መልኩ ተጽእኖ ይደረግባቸዋል? በመካከላቸው ያለው ግጭት እና ምኞቶቻቸው ምንድን ናቸው? እንዴትስ እነዚህን ተግዳሮቶችን ይወጧቸዋል? በመጪው ሩቅ ዘመን ለእነርሱ ህየወት ምን አይነት ራእይ አላችሁ?
- የአፈ-ታሪኩ ጨቋኝ ጎኖች ምንድን ናቸው? አፈ-ታሪኩን በማዳቀል በአፈ-ታሪኮቹ እንደልብ ነጻነትን የማምጣት ችሎታቸውን እንዴት ማሳካት ይቻላል?
- የአፈ-ታሪኩን የአሁንና የመጪውን ጊዜ የጊዜ ቀመሮች አንድ ላይ አምጡ
- የተሳታፊዎችን የአፈ-ታሪክ ንድፍ በመዘርዘር በመካከላቸው ያሉ ትስስሮችን ፈልጉ
- በመካከላቸው ያለ አስተጋብኦን ፈልጉ፤ ከዛም በቡድን ተከፋፈሉ
- የታሪካችሁን አጭር መግለጫ ጽሁፍ (synopsis) አዘጋጁ፤ ታሪኩ ቡድኖቹ ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ላይ መመስረት አለበት



## ገቢሮች

### በምስል መከሰት (visualization)

- ከተለያዩ ምንጮች ያገኛችኋቸውን ምስሎች (ከኮዴክስ፣ ባህላዊ ቁሶች ወዘተ) በማደራጀት ገጸ ባህሪዎቻችሁን ሳሉ።
- በቡድን በመከፋፈል የራሳችሁን አካል በመጠቀም ሶስት የተለያዩ ገጸ-ባህሪያት በእንቅስቃሴ ላይ እያሉ የሚያሳዩ ምስሎችን ፍጠሩ። እነዚህንም ምስሎች ፎቶ አንሷቸው እነዚህን በመጠቀም ታሪክ መፍጠር ትችላላችሁ። ታሪኩን የሚተርክ “voice over” (የበላይ ድምጽ) እና ለታሪኩ የድምጽ አውድ (sound scape) መፍጠር ትችላላችሁ።

### አካል መንሳት (materialization)

- ይህን ታሪክ በምን ዘዴ (በኮኒክ፣በፎቶ-ልቦለድ በክዋኔ፣በአሻንጉሊት ትያትር፣በቪዲዮ፣በድምጽ በዘፈን/መዝሙር ወይምን በእነዚህ ዘዴዎች ቅንብር) መተረክ እንደምትፈልጉ አስቡ
- በመጀመሪያ የወርክሾፖቹ ቀን ተሳታፊዎች ያዘጋጁትን የእውቀትና የክህሎት ዝርዝር ተመልከቱ። ታሪካችሁን እውን ለማድረግ ከማን ጋር መተባበር እንዳለባችሁ ወስኑ።
- የታሪኩን ፕሮዳክሽን አቅዱ
- በእቅዳችሁ መሰረት ፕሮዳችሽናችሁን አካሂዱ

### በአፈ-ታሪክ ላይ አፈታሪክ በመደረብ ማዳቀል

ከማን ጋር በመተባበር እና በምን አይነት ዘዴ ስራችሁ በአጋዥነት ደረጃ በውስን ቦታ ላይ የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚትችሉ አስቡ። ስራችሁ ለተደራሹ የህብረተሰብ ክፍል እንዴት እነደሚዳረስና በእነርሱም እንዴት ሊጎለብት እንደሚችል አጢኑ።ከየትኞቹ የተደራሹ ማህበረሰብ የአኗኗር ዘዬ፣ ኩነት እና ድርጅት ጋር ታሪካችሁ ሊናበብ እንደሚችል ለዩ።ተደራሹን ማህበረሰብ በማግኘት እና ከእነርሱ ጋር በማስብ ታሪካችሁ እንዴት ሊዳብር እንደሚችል አስቡ።
















↑ Sketches for *Opossum Resilience*, by Naomi Rincón Gallardo, 2019



ADDITIONAL REFERENCES

- Gil, Yásnaya Elena A. *¿Nunca más un México sin nosotrxs?.* Oaxaca: Fusilemos la Noche, 2018.
- Rivera Cusicanqui, Silvia. *Ch'ixinakax utxiwa: Una reflexión sobre prácticas y discursos descolonizadores.* Buenos Aires: Tinta Limón, 2010.

ARTWORKS

- A Tribe Called Red, artist. 2016. *We are the Halluci Nation.* Studio Album. Radicalized Records.
- Caycedo, Carolina, artist. 2014. *Land of Friends: Descolonizando la Jagua.* Video, 38'10".
- Huichaqueo, Francisco, director. 2011. *MENCER Ñi Pewma.* Video, 32'34". Online at: vimeo.com/284993347.
- The Karrabing Film Collective, director. 2018. *The Mermaids, or, Aiden in Wonderland.* Video, 26'29". Karrabing Indigenous Corporation.

CREDITS

*Opossum Resilience*, by Naomi Rincón Gallardo. HD video, 16'00", 2019. Shot in Oaxaca, Mexico. Performers: Hill – Luis Enrique García; Agave – Chichis Glam; Opossum – Naomi Rincón Gallardo; Lady Reed – Diana Gómez Córdoba. Cinematography: Masha Godovannaya. Photo documentation: Claudia López Terroso. Electronic sound effects: Enrique Arriaga. Direct sound: Konk Balam Díaz. Voice-over for Hill: Claudia López Terroso. Voice-over for "I dreamt about the *naguales*": Naomi Rincón Gallardo. Lyrics of "Opossum": Naomi Rincón Gallardo. Music: Fernando Guadarrama. Voice: Paulina Jiménez. Jaranas (small guitars): Oliver Martínez Kandt and Fernando Guadarrama. Lyrics of "Fermented, adulterated, hyper-fertilized": Naomi Rincón Gallardo. Music and vocals: Chichis Glam. Lyrics of "Rosy": Naomi Rincón Gallardo. Rappers: Yadhi Boz ft. Doma. Props: Naomi Rincón Gallardo. Opossum's Mask: Ezequiel Marín "Máscaras". Seamstress: Mayra Angélica Cernas. Lighting: Jakob Aguilar. Thanks to: Tepelmeme Community Organization, Pollos Bar, Pablo Arellanes, Lorena Ancona, and Moisés García. Produced with the support of FWF PEEK: "DisPossession: Post-Participatory Aesthetics and the Pedagogies of Land" and Parallel Oaxaca.

ማዘን መቆርቆር፤
መቆርቆርም ልበሙሉነት፤
በስስት እና በስጋት ከመራድ፤
እዚህም እዚያም ልብ እንዲነካ መፍቀድ፤



# መቆርቆር እና መሆን




## ብርሃኑ አሻግሬ

አዲስ አበባ / ኢትዮጵያ

**“በሉላዊ ደቡብ ውስጥ የምንኖር ሰዎች የምንጋራው ነገር ቢኖር በክብር ለመኖር ከብዙ እንቅፋቶች ጋር መላተም ግዴታችን መሆኑ ነው። ይህም ማለት በደህንነት ለመኖር እንቅፋቶቻችን ሊወገዱ የሚችሉ ናቸው በሚል ብርቱ እምነት ስንታገል መኖራችን ማለት ነው። ከምንም በላይ ግን፤ የትግላችን ልቀት መሠረት ያደረገው ከዓላማችን ምንነት በላይ በሂደቱ ውስጥ በምናከናውናቸው ድርጊቶች ብቃትና በስሜታችን ፅናት ነው።”**

— Boaventura de Sousa Santos, *Epistemologies of the South*



አዲስ አበባ በአፍሪካ ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ካሉ ከተሞች ውስጥ አንዱ ነው። ከተማው የኢትዮጲያ የፖለቲካ ማዕከል ሆኖ ከማገልገሉም ባሻገር፣ ከ1963 ዓ.ም. ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት (ኋላ አፍሪካ ህብረት የተባለው) መቋቋም ጀምሮ የአሕጉሩ ማዕከል በመሆንም ሲያገለግል ቆይቷል። እኔም ከአዲስ አበባ ጋር ያለኝ ቁርኝት ከሁለት አስርት አመታት በላይ የዘለቀ ነው። ከዚያ ቀደም የተወሰኑ የክረምት ጊዜያትን በከተማው ያሳለፍኩ ቢሆንም፣ በዚያን ጊዜ በነበረኝ ግንዛቤ ተለቅ ያሉ  ነገሮች በቀላሉ የሚከናወኑበትም የሚደናቀፉበትም ቦታ መሆኑን ከማስተዋል ያለፈ ስለከተማው ብዙ ዕውቀት አልነበረኝም። ጠቅልዬ በአዲስ አበባ ለመከተም ወስኜ  ከመጣሁ በኋላ ግን በሂደት የተሻለ ልረዳው የምችል ቦታ ሆነ። መቼም ያገር ልጅነት ነገር ተለዋዋጭ ነውና፤ ከጊዜ በኋላ ተወልጄ ካደግኩበት ቦታ ይልቅ አዲስ አበባ ቤቴ ሆነ። የአዲስ አበባ ከተማ ኑዋሪነት ከሚሰጠው እድልም እየተቋደስኩ፤ የሚፈጥረውን የመከራ ገፈትም እየቀመስኩ እኖራለሁ። ከዕለት ዕለት የከተማው ለውጥ ጋር ራሴን ለማጣጣም እየሞከርኩ፤ ከሚቀረው ያገር ልጅ ስሜት ጋር  መቼም የማይሞላ፤ ጎድሎም የማይንጠፈጠፈውን፤ ነገር ግን ሁሌም የሚደምቀውን  የአዲስ አበባን ህይወት ከኑዋሪው ጋር እየተጋራሁ እኖራለሁ።

የአዲስ አበባ መልክዓምድር ወጥነት የሌለው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የከተማው አደረጃጀት፤ የዕለት ተዕለት የከተማው ኑሮ እንዳይሰለች እግዞታል። የአካባቢው አቀማመጥ ሊሰጥ የሚችለውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በመገንዘብ፤ በ1886 ዓ.ም. ገደማ ዳግማዊ ንጉስ ምኒልክ ከእንጦጦ ተራራ አሁን አራት ኪሎ ተብሎ ወደሚጠራው ስፍራ ቤተ መንግስታቸውን ገንብተው ወረዱ።[1] በመቀጠልም የንጉሱ ጦር፣ ሹማምንቱ፣ የነገስታት ቤተሰቦች፣ እንዲሁም አገልጋዮቻቸው በቤተመንግስቱ ዙሪያ መስፈር ጀመሩ። ቀስ በቀስም ሰፈራው ወደ ትንሽ መንደርነት፥ እየቆየም ወደ ቀበሌነት፤ ቀጥሎም ወደ ደመቀ ከተማነት በመሸጋገር እያደገ የመጣ ማንነትን ገንብቱዋል። ከከተማው ምስረታ ጀምሮ ቦታው ከአገሪቱ የተለያዩ ስፍራዎች የመጡ ሰዎች መገናኛም መሰባሰቢያም ማዕከል ሆነ። ይህ ሁኔታ እስከ አሁኑ ጊዜም በመቀጠሉ ከተማው ከፍተኛ የህዝብ ብዛት ያለው፤ የ130 ዓመት እድሜን ይዞ አራተኛ ትውልድ በማስተናገድ ላይ ይገኛል።

የመጀመሪያው ሰፋሪዎች በመጡ ሰሞን ነበር ከተማው ‘አዲስ አበባ’ የሚለውን ስም ከንጉስ ምኒልክ ባለቤት ከንግስት ጣይቱ የተጎናጸፈው።[2] ይህ ከተማ በዘመናዊነት መባቻ ላይ ይቆርቆር እንጂ፤ ጅማሮው ከተሜነትን ለማቀፍ ታቅዶ የተደረገ አልነበረም። ከተለመደው የከተማ መልክዓምድር አቀማመጥ ይልቅ፤ ዝብርቅርቅና ደንብ የለሹ አደረጃጀት የተለየ ማንነት ስጥቶታል። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ማንነት በከተማው ውስጥ ለሚንጸባረቀውም ማህበራዊ ግንኙነትና ጥምረት መሰረት ሆኖ አገልግሏል። ከአስርት ዓመታት ወዲህ፤ መንግስት የማከተምና የማዘመንን ስራ በስፋትና በተቀናጀ ሁኔታ ሲጀምር፤ ይህ በጋራ የመኖር ዘዬ ታሪክ ሆኖ መቆጠር ጀመረ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ብዙና ተከታታይ የከተማ መፈናቀሎች የከተማዋ መገለጫ ሆነዋል። ቁጥር ስፍር የሌላቸው ቤተሰቦች ከለመዱትና ከኖሩበት የመኖሪያ አከባቢ እየተነቀሉ፤ ጨርሶ አዲስና ግር ወደሚል የከተማ ዳርቻ መዳረሻዎች ተገፍተዋል። የፈራረሱና የወደሙ መንደሮችን ረግጠው የሚጀመሩ የግንባታ ቦታዎችን መመልከት የከተማዋ የዕለት ተዕለት ኑሮ አካል ሆኗል። ታሪካዊ ሰፈሮች፣ መንደሮች፣ የጋራ መናሓሪያ ስፍራዎች፣ ሀውልቶችና የግንባታ ቅርሶች ሳይቀሩ ለዚሁ የመንግስት የልማት አጀንዳ ቦታ መልቀቅ እጣ ፈንታቸው ሆኖ ቀስ በቀስ ከኗሪው የጋራ ትውስታዎች እየጠፉ መምጣታቸው ሃቅ ነው።

ከተማው በጠቅላላው ወደ አንድ ትልቅ የግንባታ ስፍራነት በፍጥነት እየተለወጠ የመማጣቱ ነገር በራሱ ብዙ አጥጋቢ መልስ ያላገኙ ጥያቄዎችን

1 Emperor Menilek II was King of Showa during the establishment of Addis Ababa; he became an Emperor of Ethiopia in 1889.

2 Empress Taytu was highly involved in many political, diplomatic, and leadership matters, which made her one of the most powerful women in Africa during her time. See Chris Prouty, *Empress Taytu and Menilek II: Ethiopia 1883–1910* (Trenton: The Red Sea Press, 1986).

ሲያስነሳ ቆይቷል። የከተማው ነዋሪ መሰረታዊ ፍላጎትና መንግስት ለማቅረብ በቻላቸው ነገሮች መካከል ያለው አለመጣጠን፤ ቀጣይ የሆነ የመረበሽና የውጥረት ስሜትን አስፍኗል። እኔም፤ የተለያዩ የከተማ ኑሮ እውነታዎችን በአትኩሮት ለመገንዘብ እንደሚሞክር የጥበብ ሰው፤ ከዚህ ፈጣን የከተማ ከባቢ ለውጥና ተያያዥ የሆነውን የኑሮ ሁኔታ የሚመለከቱ ብዙ የጥበብ ስራዎችን ላለፉት ጥቂት ዓመታት ስሰራ ቆይቻለሁ። በነዚህ ስራዎች ውስጥ፤ በተለይ አትኩሮት ሰጥቸ የተንቀሳቀስኩት የከተማው ሰው መፈናቀል፣ የመሬት ቅሚያ እና የቦታዎችን በፍጥነት መለዋወጥና መቀያየር ያማከለ ነበር። ይሁን እንጅ፤ ባለፉት ስራዎቸ ውስጥ በዋነኛነት መሰረት አድርጌ የቆየሁት አሁን ያለውን የከተማ ለውጥና የከተማ ኑሮ በማጤን ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን የጋራ ተግዳሮት በማጠየቅ እንጅ፤ ወደሁዋላ የነበረውን የከተማው ታሪክ መሰረት በማድረግ አልነበረም።

አዲስ አበባ በኢትዮጵያ ውስጥ በህዝብ ቁጥር ከፍተኛውን የሚይዘው የኦሮሞ ማህበረሰብ በሚገኝበት ክልል ውስጥ የሚገኝ ከተማ ነው። ስለዚህም፤ በከተማው እድገት ውስጥ ቀጣይ ሆኖ በቆየው የጎንዮሽ መስፋፋት ምክንያት፤ በከተማው ዙሪያ የሚኖሩና በዋነኛነት የዚሁ ማህበረሰብ አካል የሆኑ ገበሬዎች ከሚያርሱትና ከሚኖሩበት መሬታቸው በግዴታ ሲገፉ ቆይተዋል። ይህ ለአስር አመታት ከተማዋን የሰፈረባት የጎንዮሽ መስፋፋት አባዜ የከተማው ድንበር ላይ በመድረሱ መስፋፋቱን ለማስቀጠል የቦታ እጥረት መከሰት እንደጀመረ ለመረዳት ብዙ ድካም አይጠይቅም። ኋላም በ2014 ዓ.ም. የከተማ አስተዳደሩ የተቀናጀ የከተማ ማስተር ፕላን ብሎ የሰየመውን በከተማው ዙሪያ ያሉ ትንንሽ ከተማዎችና መንደሮች የሚያካትት አዲስ የከተማ ፕላን አስተዋወቀ። ይህን አዲስ የከተማ ልማት ሃሳብ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ፤ የከተማውንና በዙሪያው ባሉ መንደሮችና ከተሞች ውስጥ የሚኖረውን ማህበረሰብ ተገቢ በሆነ መልኩ በውይይት ያሳተፈ አልነበረም።

ይህ እንግዲህ የልማታዊ ፈላጭ-ቆራጭ የሆነው መንግስት ማናለብኝ ባይነት፤ እንዲሁም መሬትን ሀይል በመጠቀም በባለቤትነት መያዝ የሚቻል ነገር ነው ብሎ የማመን የተዛባ አመለካከት ማሳያ ነው። የኢትዮጲያ ህዝብ በአብዛኛው በግብርና የሚተዳደር ማሕበረሰብ ነው። ለዚህም ህዝብ መሬት ከንብረትነትም በላይ የተወሳሰበ ትርጉም ያለው ነገር ነው። መሬት ይዞታ ነው፣ መሬት ማንነት ነው፣ መሬት በጊዜ ሂደት ውስጥ የዳበረ የዕውቀት ክምችት ነው። ይህንን ውስብስብ የመሬት ውክልና ያለመረዳት የታየበት የመንግስት ውሳኔ በክልሉ ውስጥ ባለው ህዝብ፤ በተለይም በወጣቱ ላይ ቁጣንና አመጽን አጫረ። ይህም ቁጣ ከክልሉ ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በፍጥነት ተስፋፋ። የተነሳውም የወጣቶች አመጽ ለሶስት ዓመታት ቀጥሎ በመጨረሻም ሀገሪቱን ለ27 ዓመታት አንቆ ይዟት ከነበረው የፖለቲካ መዋቅር ለማላቀቅ በተደረገው የለውጥ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚናን ያዘ። በዚህም ለዓመታት በዘለቀ የትግል ሂደት ውስጥ፤ እጅግ በጣም ብዙ ቁጥር ያለው ወጣት ለሞትና ለእስር ተዳርጉዋል።

በኦሮሚያ ክልል ለዓመታት በቆየው አመጽ ሲንጸባረቅ የነበረውን የወጣቶች ንቅናቄና የቁጭት መጠን በአትኩሮት ስከታተል ቆይቻለሁ። ከዚህም የተረዳሁት፣ ምንም እንኳን የተቀናጀው አዲስ የከተማ ማስተር ፕላን ጉዳይ የሁኔታው መንስኤ ቢሆንም፣ ቀጣይነት ለነበረው የወጣቶች አመጽ ብቸኛው ግፊት ግን እሱ ብቻ አልነበረም። ይልቁንም ከከተማዋ ምስረታ ጀምሮ የተከማቸ በደል፣ ቸል የተባለ ብሶት፣ የመሬት ቅሚያ፣ መፈናቀል እና የአከባቢው ሰው ላይ የነበረ የባህል ተጽእኖ ላይ የቆመ መሰረት ያለው ትርክት ውጤትም መሆኑን ለማስተዋል ችያለሁ። ነገር ግን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ይህ የከተማዋ በበደልና ጥቃት ላይ የመመስረት ትርክት በመንግስት ደረጃም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ በይፋ ውይይት ሲደረግበት ያልቆየ ከመሆኑ የተነሳ፤ በደፈናው ተከድኖ ይብሰል ተብሎ የተተወ ጉዳይ ይመስላል። ከከተማው መቆርቆር በፊት














↑ Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Walking together to Mount Entoto; handwritten newspaper for *Care & Mourning;* "Maintaining" (sharing meals with collaborators); poem-reading performance inside a moving public bus; poetry-reading performance; all in Addis Ababa, 2019













የነበረውን ከተማው ያረፈበት ቦታ ሁኔታ ትርክት ለብዙዎች ግልፅ ሳይሆን የቆየ ሲሆን፤ እስካሁንም ቢሆን የጋራ ስምምነትን ለመፍጠር የቻለ ተጨባጭ የታሪክ መረጃ ሲቀርብ አይታይም። አንዳንድ ጊዜ ሳስበው፤ በሽዎች ከሚቆጠሩ አመታት በፊት ለተከናወኑ ታሪኮች ተጨባጭ መረጃን ሰብስባ ባቆየች ትልቅ አገር ውስጥ፤ የመቶ ሃምሳ ዓመት ታሪክ እንቆቅልሽ መሆን ይገርመኛል። ለማንኛውም፤ ከከተማው ምስረታ በፊትና በኋላ የነበረውን የመሬት ጉዳይ የተወሰነው የክልሉ ሕብረተሰብ ክፍል ብቻ በቃላዊ ትርክቱ ሲገልፀውና ሲያፀና የቆየው ታሪክ መሆኑ ግልፅ ነው። ይህም ትርክት በከተማዋ ምስረታ ወቅት የተፈጠረን ተጠቂነት የሚያወሳ ነው። ይህ የበደልና የመነጠቅ ታሪክ በተገቢው ሁኔታ በስፋት ግንዛቤ ውስጥ የሚገባበት ሁኔታ ሳይፈጠር ቀርቷል። ይህ በተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የምናየው ትርክቱን በመረዳት ላይ ያለ ልዩነት፤ ከንጉሡ ነገስቱ ማህበረሰባዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አስተዋፅኦ እንዲሁም ሀገርን በመገንባት እና በማቆየት ሂደት ውስጥ ከነበራቸው ሚና ጋር ከሚኖረው ታሪካዊ ግጭት የመነጨ ሊሆን ይችላል።

በሀገሪቱ በቅርብ ከተካሄደው የፖለቲካ ለውጥ በኋላ፤ የክልሉ ተወላጅ የሆኑ ታሪክ አዋቂዎች፣ ፖለቲከኞች፣ የመብት ተሟጋቾች እንዲሁም ወጣቶች ይህንን ከከተማው ምስረታ ጋር የተያያዘ የጭቆና ትርክት በግልጽ ማንሳትና መወያየት ጀምረዋል። ከዚህም በላይ የከተማውን ባለቤትነት ከክልሉ ማህበረሰብ ጋር በማቆራኘት ጥያቄ የማንሳት አዝማሚያም ተስተውሏል። ይህ ለዘመናት ሳይነሳ የቆየና በቅርቡ በግልፅ መሰላሰል የጀመረ ጥያቄን ተከትሎ፤ ከተነሳው የጥቃት ታሪክ ጋር የሚቃረኑ የተለያዩ ትርክቶችን ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስነስቷል። ይህም ሁኔታ፤ በክልሉ ማህበረሰብ ውስጥ ተጨማሪ ንዴትን፣ ጥላቻን፣ ቁጭትን የመሳሰሉ አጥፊ ስሜቶች በመፍጠሩ በማህበረሰቦች መካከል የባሰ ንትርክና ግጭት የቀሰቀሰ ሆነ። በሰከነ ሁኔታ መወያየትና መደማመጥ በጠፋበት በዚህ ጊዜ የክልል ድንበሮች ይበልጥ ጎልተው መታየት ጀመሩ። የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች እኛን አይመስሉም ያሏቸውን ቡድኖች በመፍጠር ከክልላቸው እስከ ማፈናቀል ደረሱ። ይህም አንዳንድ ቦታዎች እንደፈለገ የሚነጠቁ፣ ያዳንዶች ሕይወትም እንደዘበት የሚታዩ አስመስሎ አቀረባቸው። የጸጉረ ልውጦች ፈጠራው፤ የምንጋራውን ታሪክ እንድንክድ በማድረግ አብሮ መኖርን ማዕከል ያደረገን የጋራ ተስፋ የሚያሳጣ ጉዳይ ነው።[3] ይህ አስቸጋሪ ሁኔታም ሀገሪቱን በ2018 ዓ.ም. በሀገር ውስጥ በተፈናቀሉ ሰዎች ቁጥር በዓለም የመጀመሪያ ደረጃ ላይ እንድትቀመጥ አደርጋት።[4] የተለያዩ የማሕበረሰብ ክፍሎች ለሁሉም የጋራ ውድቀትን ብቻ በሚያቀዳጅ አለመግባባትና ግጭት ውስጥ ተጠምደው የጋራ ህልም የሆነውን ማለፊያ ኑሮ በማምከን ላይ ይገኛሉ።[5]

በአሁኑ ጊዜ የማህበረሰቡ የጋራ ሕይወት ከመሃል እስከዳር በጥላቻ መናፍስት እየታመሰ ይገኛል። በዚህ ወቅት ግለሰቦችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ምላሽ ከጥልቅ ሀዘን እስከ ሚንተከተክ ቁጣ ባሉ ስሜቶች እየተናጠ ይገኛል። ቁጣው ወደማንመለስበት የጥፋት መንገድ ሊወስድ የሚችል አደጋን ሊያመጣ የሚችል ሲሆን፤ የሚታየው የሀዘን ስሜት ግን ልዩነትን ማዕከል ያደረገና በዚሁም ላይ የተመሰረተ አብሮ የመምጣት (Coming together) እድል ለመፍጠር ወደሚያስችል ሃይል ሊቀየር ይችላል። ይህ አብሮ መምጣት ያለፈውን የታሪክ አጋጣሚ በመርሳት ሳይሆን አንዳችን የሌላችንን ጉዳት በመረዳትና በውጤታማ መደማመጥ ላይ የተመሰረተ የጋራ የሆነ የድሕነት ወይም የፈውስ መንገድ ማለት ነው። ስለዚህም፤ ይህ አብሮ መምጣት መጀመር ያለበት የታሪክን ጠባሳ ለማጥፋት በማሰብ ሳይሆን፤ አሁን ያሉብንን ትኩስ ቁስሎች ከማዳን ነው። እዚህ ላይ መታወስ ያለበት፤ እንደ እኛ አይነት ባህልና ታሪክ ባለው አገር ውስጥ ምንም ዓይነት ለውጥና ዕድገት ቢመጣ፤ አብሮ ማዘን

← Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Ritual-making performance at Mount Entoto; “Maintaining” (Nifro, one of the common snacks for periods of mourning); discussing mourning rituals; mourning performance in public space (on Menilek Square); mourning performance in public space (on Arat Killo); all in Addis Ababa, 2019

3 Zygmunt Bauman, *Liquid Modernity* (Cambridge: Polity, 2000), 95.

4 The internal displacement ranking is taken from the global 2018 midterm report of the Internal Displacement Monitoring Center; online at: internal-displacement.org.

5 The concept of *buen vivir* [good living] derives from the Quechua word “sumak kawsay.” I use it here in the way that it has been adapted by Boaventura de Sousa Santos.

ያልቻለ ማህበረሰብ አብሮ ሊደሰትና እድገቱን ሊያጣጥም አይችልም፤ ምንም እንኳዋን እድገት በሩቅ የተሰቀለ ዳቦ ሆኖብን ብንቆይም።

የመቆርቆር እና የመሆን እሳቤ፤ የሀዘንን ሀሳብና ገቢር በመመርመር ፍላጎት ላይ ተመስርቶ፤ ይህንንም እንደ አስተውሎት፣ የዕውቀት መንገድና የፖለቲካ አካሔድ አድረጎ በመገንዘብና በመተግበር ወደ ጋራ ሽረት ለመሄድ የሚደረግ ጥረት ነው። ሀዘንን በጥልቀት ለመመርመርና ለመገንዘብ መወሰን፤ የስጋትን ጊዜ በማሳጠር አንዱ የሌላውን ቁስል ህመም በመረዳት፥ የሌሎችን ስሜት በመልካም መንካትና የራስም ልብ በሌሎች ሁኔታ እንዲነካ የመፍቀድ ሂደት ነው። ይህ ሂደት ደግሞ አንድ ላይ መምጣትን እና አብሮነትን ይጠይቃል። አብሮነትና የጋራ ሽረት የሚገኙት ደግሞ በተለመደ የፖለቲካ ቋንቋና ዲስኩር ሳይሆን፤ ባህላዊ የሆነውን ማህበረሰባዊ እውቀት፥ አካላዊ የሆነውን ልምድ እና የማህበረሰብ ተሞክሮን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው። ስለዚህ በጋራ የማዘን ፅንሠ ሃሳብ ላይ ማተኮር ማለት፤ ማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ መሰረቱን በመረዳት በሂደቱ ንቁ ተሳታፊና ብቁ ምስክር ለመሆን መወሰንና መፍቀድ ያስፈልጋል። ኢትዮጲያን ጨምሮ በብዙ የአፍሪካ ባሕሎች ውስጥ፤ ማንም ሰው ብቻውን ማዘን የለበትም የሚል የጋራ መረዳት አለ። እንደ ኢትዮጲያ ባሉ ሀገራት በከተማም በገጠርም ቦታዎች ቀብርንና ሀዘንን በጋራ ለመወጣት የተደራጁ ማህበራት (እድሮች) አሉ። እንዲህ ያሉ ሀዘን ላይ ተመስርቶ ማህበረሰብን የማደራጀት መዋቅሮች የተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ትግሎችን በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜያት ፈጥረዋል። ለምሳሌ ያክል በአርጀንቲና፤ “Mothers of the Plaza de Mayo”፣ በእስራኤል፣ በሰርቢያና በአለማቀፍ ደረጃ “Women in Black”፥ እንዲሁም በአሜሪካና አለማቀፍ በሆነ ደረጃ “Black Lives Matter” የመሳሰሉት ይገኙበታል።

በመቆርቆር እና መሆን ፕሮጀክት ውስጥ ዋና የለውጥ ምሕዋር ሆኖ የሚያገለግለው በመላበስ የመሆን (embodiment) እሳቤ ነው። በመላበስ የመሆን እሳቤ ስለ ሕይወት፣ ተጋላጭነት እንዲሁም መተባበርን ስለማምጣት በስነ-ምግባር፣ በስነ-ውበትና በፖለቲካ ውስጥ የሚደረጉ እና ቀጣይነት ያላቸው የድርድር አቅጣጫዎችን ለመፈተሽ ዓቅም ያበረክትልናል።[6] በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ፤ በመላበስ የመሆንን እሳቤ መሰረት በማድረግ አሳታፊ በሆነ መልኩ የተለያዩ የስነ-ጥበብ ፈጠራ፣ የስነ-ትምሕርት እና ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ስራዎች ተሰርተዋል። ለምሳሌ ያክልም ለመጥቀስ በተለያዩ የፈጠራ ዘርፎች የተሰማሩና የተለያየ ባህላዊ መሰረት ያላቸው ባለሙያዎች ተሳታፊ የሆኑበት የስድስት ቀናት የውይይትና የተግባር እንቅስቃሴ ተጠቃሽ ነው። የዚህም የጋራ መድረክ ዝግጅት እና መዋቅር የተዘረጋው መቆርቆር እና ማዘን በሚለው የፕሮጀክቱ ዋና ፅንሠ-ሃሳብ ዙሪያ ሲሆን፤ የተለያዩ የሀዘን ባህሎችንና ወጎችን መሰረት ያደረጉ የተግባር እንቅስቃሴዎችና ሙከራዎች ተካሂደዋል፤ ከነዚህም ውስጥ የሚዛመዱ የተረክ መመስረቻ ካርዶችን በመጠቀም ስለነጠቃ ትርክት መመስረት፣ በግፍ፥ ሰቆቃ እና ትግል ዙሪያ ላሉ ቃላቶች ትርጉም የመስጠት ሂደት፣ የሀዘን እንጉርጉሮ መፃፍና ማንበብ፣ የእግር ጉዞ ወደ እንጦጦ ተራራ፣ የሀዘን ድምጸት ልምምድ፣ በሰውነት እንቅስቃሴ የመተረክ ሂደት፣ የተለያዩ ቋንቋዎችን በመጠቀም ያለመግባባት ልምምድን ማካሄድ፣ የግልብጥ ድርሰት አፃፃፍና የመሳሰሉ የተለያዩ የማቀራረቢያና የመማማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተካሔደ ነበር።

ይህን አብሮ የመምጣት (Coming together) እና የመሰባሰብን ሀይል በመጠቀም ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ስነ-ጥበባዊ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ የከተማው ቦታዎች በጋራ ፈጽመዋል። የሀዘን እንጉርጉሮ የማንበብ ክዋኔ በጉዞ ላይ ባለ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ውስጥ፣ የከተማው ዋናና ታሪካዊ የህዝብ ማዕከል በሆነው መስቀል አደባባይ ላይ የተቀናጀና ስልታዊ በሆነ መልኩ

6 Ben Spatz, “Notes for Decolonizing Embodiment,” *Journal of Dramatic Theory and Criticism* 33, no. 2 (2019): 9–22; doi: 10.1353/dtc.2019.0001.



በድምፀትና በአካል እንቅስቃሴ ብቻ የታጀበ ሰላማዊ ተቃውሞ፣ ከሃዘንና ከሰቆቃ መናፍስት ጋር ለመደራደር የተዘጋጀ ልዩ የለቅሶ ስነ-ስርዓት በእንጦጦ ተራራ ላይ፥ እንዲሁም መቆርቆር እና ማዘን ላይ ያተኮረ በእጅ የተጻፈ ጋዜጣም ተዘጋጅቷል።[7] አብሮ የመምጣት ተግባሩ ዋና ውጤት ተድርጎ ሊቆጠር በሚችል ሁኔታም የጋራ ለቅሶ ክዋኔ ስነ-ጥበባዊና ፖለቲካዊ ይዘት ባለው መልኩ ከጭቆና ጋር በተያያዘ የሚጠቀሱ ሶስት የከተማው ስፍራዎች ላይ በይፋ ተከውነዋል።






↖ Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Mourning performance in public space (at National Palace); gesture exercise in pair (problematizing gestures); both in Addis Ababa, 2019

7 Meskel Square is the major public square in Addis Ababa; it is a very important space in the everyday urban life and the socio-political history of the city, as well as a renown site across the country.







↑ Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Discussing scores for mourning gestures; rehearsal for mourning performances; vocal exercise (systemic protest) at Meskel Square; all in Addis Ababa, 2019





በክብርና በደህንነት መኖራችን ላይ የሚመጣ እንቅፋትንና አስቸጋሪ ሁኔታን መቀየር የሚቻለው ራስን ከመቀየር በመጀመር ነው።

— Boaventura de Sousa Santos, *Epistemologies of the South*

“በመላበስ የመሆን እሳቤ ውስጥ የሚከወኑ የጥበብ ዝግጅቶች ትርዒት ተብለው ብቻ ሊታለፉ የማይችሉ ከባርነት/ጭቆና ነጻ የመውጣት ጥረትን የሚደግፍ አንዳች ሃሳብ አላቸው። ትርዒት ሊለካ የሚችል ፍካሬያዊ ሀይልና እዚያው በዚያው የምናየውና የምንበይነው ሲሆን፤ ከዚህ በተለየ በመላበስ መሆን ግን ሕይወት፣ መትረፍ፣ ተጋላጭነት እና ስነ ምሕዳርን ማዕከል ያደረገ የግብረገብ ፖለቲካን እውን ሊያደርግ የሚችል ሓይል ያለው ነው። ባጠቃላይ፤ ትርኢት መስሎ መገኘትን መሰረት ያደረገ ሲሆን፤ መላበስ ደግሞ ሆኖ መገኘትን የሚያበረታታ እሳቤ ነው።”

— Ben Spatz, “Notes for Decolonizing Embodiment”





# የሀዘን አካላዊ ምልክቶች (Gestures for Mourning)

ስንንቀሳቀስ - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስንናገር - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስንመኝ - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስንራራ - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስንቆረቆር - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስንካፈል - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስናገኝ - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስናጣ - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስናዝን - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስንቃወም - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስንጋጭ - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ስንታገል - አካላዊ ምልክት እናሳያለን፤ ...ሁሌም አካላዊ ምልክት እናሳያለን።

አካላዊ ምልክት ወይም ቋንቋ መልዕክትን ወይም ትርጉምን የመለዋወጥ እምቅ ሀይል አለው። አካላዊ ቋንቋ የትርጉም ግብዣና የአንብቡኝ ጥሪ ነው፤ ውይይትን የማነሳሻ ጉትጎታ ነው፤ የሰውነት አካል ጋር የሚደረግ ግንኙነት ነው። አካላዊ ምልክት በባህሪው ውስብስብ ነው፤ ተግባራዊና ትርጉም ያለው ከመሆኑም ባሻገር አካላዊና ፖለቲካዊም ነው። በአንድ ጊዜ ብዙ መልእክቶችን/ትርጉሞችን ይገልፃል። በመሆኑም ፈጠራዊና ትምህርታዊ በሆነ መንገድ ስኬታማ መግባቢያ የመሆን እምቅ ሀይል አለው። በተለያዩ የስነ-ጥበብ ስራዎች እንደተመለከተው እካላዊ ምልክት ፈተራ የተሞላባቸው ፖለቲካዊ ሀሳብን ለማንሳት አይናተኛ ጥቅም አላቸው፤ ለምሳሌ በአይ ዌይዌይ “Study of Perspective” በተባለው ተከታታይ ስራው ላይ ይህን በግልፅ እናያለን።

አካላዊ ምልክት በፖለቲካ ተቃውሞና ሰልፎች ውስጥም ትልቅ ሚና ይጫወታል። ለምሳሌ “Hands up! don’t shoot!” የሚለው እጅን ወደ ላይ የማድረግ ምልክት በአፍሪካ-አሜሪካውያን ላይ የሚደርሰውን የፖሊስ ጭካኔ የተሞላበት እርምጃን በመቃወም በተደረጉ ሰልፎች ላይ ሀይል ያለው የተቃውሞ ምልክት ሆኖ አገልግሏል። አኑሻ ከድሀር እንደምትለው “አካላዊ የእንቅስቃሴ ቅንብር እና አካላዊ ምልክት በተቃውሞ ፖለቲካ ውስጥ ማዕከላዊ ቦታ ያላቸው እንጂ ተጓዳኝ እላባዎች አይደሉም” (1) ። በሁሉም ባህሎች ውስጥ የተለያዩ የመግለፅ ሀይል ያላቸውና ወደ ፖለቲካ ቋንቋነት መለወጥ የሚችሉ አካላዊ እንቅስቃሴዎችና ምልክቶች አሉ።

የሀዘን ወይም የለቅሶ ጊዜ አካላዊ ምልክቶችና እንቅስቃሴዎች ስነ-ጥበባዊ አቅም ከመያዛቸውም በላይ ገላጭና ስሜታዊ የመማማር ሂደትን የሚፈጥሩ፣ ትርጉምና ለውጥን የሚሰሩ፣ ደንብና ሚስጥርን የሚያቀናብሩ እንዲሁም በአዲስ መልክ ትርጉምን የሚፈጥሩ ናቸው። እንደ አካላዊ ቋንቋነታቸው ድርጊትን መሰረት ባደረገ መልኩ ጥያቄን የሚያጭሩና መልስን የሚጠቁሙ ፖለቲካዊ አቅም ያላቸው የመግባቢያ መሳሪያዎች ናቸው። በሀዘን ጊዜ ዘካላዊ ምልክቶች የርሕራሄና የመቆርቆር ውጤት ሲሆኑ፤ በአሳዛኝ ነገሮችና በሰው ልጅ ስሱነት ለመነካትና በአካላችን ስሜታችንን ለመግለፅ እንችል ዘንድ ለራሳችን መፍቀድ እንዳለብን ያሳስቡናል። በተጨማሪም በአብዛኛው የደቡባዊው የዓለም ክፍል የህዝብ ተብለው የሚታሰቡ ስፍራዎች ላይ ፈጠራዊና ፖለቲካዊ ለሆነ ምክንያት መጠቀም ቀላል አይደለም። እንዲህ አይነት ቦታዎች ላይ የሚደረጉ ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች ለአካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ሊያጋልጡ ይችላሉ። በመሆኑም፤ የለቅሶ ጊዜ አካላዊ ምልክቶች ስሜታዊና ያልተንዛዛ የፖለቲካ ቋንቋን የያዙ መገለጫዎች ስለሆኑ ወሱን ዕድልን በሚሰጡ የንጥቂያና የሰቆቃ ስፍራዎች ላይ ሃሳብን ስነ-ጥበባዊና ፖለቲካዊ በሆነና ስልታዊ መንገድ ለመግለፅ ሁኔታዎችን ያቀላሉ።

ይህ የተግባር እንቅስቃሴን መምሪያ በጋራ መምጣትንና በጋራ መስራትን ይጠይቃል። ስለዚህ፤ እንደዚህ ስነ-ጥበባዊና ፖለቲካዊ በሆነ ምክንያት የተለያየ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አንድ ላይ በሚመጡበት ጊዜ አለመግባባት ሊኖር እንደሚችል ግምት ወስጥ በማስገባት በጋራ ሆኖ ችግሮችን መፍታት ለክዋኔው መሳካት ወሳኝ ነው።

(1) Anusha Kedhar, “Choreography and Gesture Play an Important Role in Protests,” *The New York Times* (15 December 2014); online at: nytimes.com/roomfordebate/2014/12/15/what-does-the-style-of-a-protest-say-about-a-movement/choreography-and-gesture-play-an-important-role-in-protests.



← Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Mourning performance around the National Palace in Addis Ababa, 2019







### ገቢሮች

የሚከተሉት አራት ገቢሮች ዓላማቸው የሚኖር ልዩነትን አውቆ፥ አክብሮና አቻችሎ እንዲሁም በልዩነት ምክንያትም ጭምር በጋራ በመምጣት የሚፈፀም ስነ-ጥበባዊና ፖለቲካዊ ተግባርን ለማደራጀት፥ ለመምራትና ለመከወን ነው።

#### አካላዊ ቋንቋን ማጤንና ማጠየቅ

የዚህ ገቢር ፍላጎት አካላዊ ምልክትን ለመከወን ብቻ ሳይሆን፤ ለሂደቱ ትኩረት ለመስጠትና ለማጠየቅ ነው።

- እያንዳንዱ ግለሰብ እንድ ርሕራሄን፣ ሀዘንን፣ ወይም ለቅሶን የሚገልፅ እካላዊ ምልክት ይዞ ይመጣል።
- አካላዊ ምልክቶቹን የሚያሰዩ ምስሎች ያሉባቸው ካርታዎችን እስከ ማብራሪያቸው አዘጋጁ።
- አንዳንድ እነዚህ ምልክቶች የተካተቱባቸውን ካርታዎች አንድ አንድ ተከፋፈሉና የምልክቱን ምንነትና ትርጉም ምን እንደሆነ አስቡ።
- ጥንድ ጥንድ በመሆን እርስ በእርሳችሁ አካላዊ ምልክቶቹን እየተለማመዳችሁ ተማማሩ።
- የተማማራችሁትን አካላዊ ምልክቶች በራሳችሁ መንገድ ድርጊቶቹን በቃላት እየገለፃችሁ አካላዊ ምልክቶቹን ከውኑ።




↑ Berhanu Ashagrie, *Care & Become*: mourning gesture cards, 2019





### ገቢሮች

#### አካላዊ ቋንቋዎችን መተርጎም

ይህ ገቢር አካላዊ ምልክቶችን ወደ ሌላ የምስል ወይም ትዕይታዊ ቋንቋ ለመተርጎም የሚያስችል ስፍራን ስለመፍጠር ነው። ይህን ገቢር ለማከናወን ማግኘት የምትችሉትን የፅሁፍና የስዕል መስሪያ ቁሳቁሶች በቅድሚያ አዘጋጁ።

- እያንዳንዱ ግለሰብ ቀደም ባለው የገቢር እንቅስቃሴ ውስጥ የተለማመዱትን አንድ አካላዊ ምልክት መሰረት በማድረግ ይህን ገቢር ይፈፅሙ።
- ምልክቱን ወደ ምስል ቋንቋ ለመተርጎም ዘዴዎችን አስቡ፤ የምስላዊ ፈጠራ ስራውን ሂደት ወስኑና አካላዊ ምልክቱን ወደ ትዕይታዊ ምስል ቀይሩት።



↑ Berhanu Ashagrie, *Care & Become*: score for mourning gesture, 2019





## ገቢሮች

### የስጋት ስፍራዎችን ማመላከት

ይህ ገቢር በአካባቢው ያሉ የሰቆቃና የስጋት ስፍራዎችን በመለየት፥ በማመላከትና በመወያየት ግንዛቤን የማስፋት ሂደትን ያመቻቻል።

---

- ሁለት ቡድኖችን አዋቅሩ፤
  - የመጀመሪያው ቡድን: በአካባቢው የሚገኙ የነጠቃና የስጋት ስፍራዎችንና ታሪካቸውን በማሰብ ይዘጋጃል፤
  - ሁለተኛው ቡድን: የሚጠቀሱ ስፍራዎችን ካሉበት ቦታ ሆነው እንዴት አቅጣጫ እንደሚያመላክቱ ያስባል፤

---

- የመጀመሪያው ቡድን አባል የሆነ እያንዳንዱ ሰው አንድ ስፍራን ትጠቅስና/ይጠቅስና ከዚያ ቦታ ጋር ተያያዥ በሆነ መልኩ የተፈፀመ ወይም እየተፈፀመ ያለን የንጥቂያ ወይም የሰቆቃ ትርክት ይገልፃል።

---

- እያንዳንዱ የሁለተኛው ቡድን አባል የሆነ እያንዳንዱ ሰው ወደተጠቀሰው ስፍራ እንዴት መድረስ እንደሚቻል ካሉበት ቦታ ሆኖ አቅጣጫን ያመላክታል።

---

### አካላዊ ምልክቶችን በይፋ መከወን

ይህ የገቢር ክፍል በአካባቢው በሚገኙ የነጠቃ፥ የስጋትና የሰቆቃ ቦታዎች ላይ የሚደረግ አካላዊ ቋንቋዎችን በተደራጀና ስልታዊ በሆነ መንገድ በመቀመር ተቃውሞን ለመግለፅ የሚያመቻች ነው። ደህንነትን ለመጠበቅ ሲባል ምንጊዜም የክዋኔው ስፍራዎችን ሁኔታ ቀድሞ ማጣራትና በተገቢው መልኩ መረዳት ተገቢ ነው።

---

- የተወሰኑ ከንጥቂያና ከስጋት ጋር የሚያያዙ ፖለቲካዊ ስፍራዎችን ወይም የህዝብ ተብለው የሚታሰቡ ቦታዎችን በመለየት ታሪካቸውንና የአሁን ያሉበትን ሁኔታ በሚመለከት ተወያዩ።

---

- የለቅሶ/ሀዘን አካላዊ መገልጫዎችን ለመከወን የሚያመች ቦታ በመምረጥ በቦታው ላይ በቡድን ተገኙ።

---

- ቀደም ብሎ በገቢር ክፍል አንድ እና ሁለት ድርጊቶች ላይ እያንዳንዱ ታሳታፊ የመረጡትን አካላዊ ቋንቋ በመጠቀም ለሌሎች የቡድኑ አባላት ያለማምዱ።

---



↑ Berhanu Ashagrie, *Care & Become*: mapping exercise on Mount Entoto, Addis Ababa, 2019

→ Berhanu Ashagrie, *Care & Become*: gesture exercise at Meskel Square (systemic protest), Addis Ababa, 2019



“ስለተለያዩ  የምስክርነት አይንቶች ማሰብ ይቻላል። ይሁን እንጅ፤ የምስክርነትን ሃይል በወጉ ለመረዳት ከተምሳሌታዊ ፋይዳው ባሻገር መመልከት ተገቢ ነው። ይህ አይነት ምስክርነት እርስ በርስ ዕውቅና መሰጣጠት ጋር አንድ አይደለም። ምናልባትም ተመሳሳይነቱና ህብረቱ ስጋት ጋር ሲሆን፤ ስጋት በዚህ አግባብ ልክ እንደ መሸበር፤ ነባራዊ ዕውነታን በትክክል ከመረዳት የሚመነጭ የህይወት ተሞክሮ ነው። ይህ ተሞክሮ ከእውነታው ሊነጥል ከሚችል ‘እውቀት’ (ወይም እልም አስተኔ) በእጅጉ ይለያል።”

— Margarita Palacios, *Radical Sociality*



መሳሪያዎች

# የሀዘን ክዋኔ ድርሰት

ድርሰት በተለያዩ የጽሁፍ አቀራረቦች የሚደራጅ ለአንድ ንግግር፣ ክዋኔ፣ ተውኔት ወይም ትርዒት እንደመርህ የሚያገለግል የድርጊት መምሪያ መረጃ ነው። ድርሰት ብዙ ነገሮችን ማለት ሊሆን ቢችልም በተለመደው የክዋኔ ጥበባት ዘርፍ፤ ድርሰት በተውኔት ውስጥ የሚነገሩ ቃላትን፥ የሚካሄዱ ንግግሮችንና የታሪክ ፍሰቱን የሚመራ እና እንዲሁም በተውኔቱ ውስጥ ያሉትን ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎችን የሚጠቁም ሆኖ የሚያገለግል ጽሁፍ ማለት ነው። ከዚህም አንጻር የድርሰት ጽሁፍ ለተውኔት ተረክ ፍሰትና በክዋኔዎቹ ውስጥ ያሉትን እንቅስቃሴዎች በግልፅ የሚያመላክት በጽሁፍ የተቀነባበረ መምሪያ ሆኖ የሚያገለግል ዶሴ ነው።

ድርሰት ታሪኮችን በተወሰነ መንገድና የክወና ደርዝ ለመተረክ የምንጠቀምበት የተለያዩ ይዘቶችና የታሪክ አወራረድ ዘዴዎች ያሉት በባለሙያ የሚደራጅ ፅሁፍ ነው። እዚህ ጋር ዋናው ጥያቄ ጥቃትንና ጭቆናን የሚተርክ ድርሰት እንዴት ነው በተሳካ ሁኔታ ለመፃፍ የሚቻለው? እንዴት ነው የሰቆቃ ኩነቶችን በትረካ መልክ፤ ፍራንክ ዊልደርሰን እንደሚለው “በቃል ሊገለፅ የማይችል የስቃይ ሰዋሰው” ሊገለፁ የሚችሉት? (2) እንዴትስ አድርገን ነው ብዙና የሚጋጩ ትርክቶች ያሉባቸው ህብረተሰቦች ውስጥ የጥቃትና የመከራ ታሪክ በሚያስማማ መልኩ ሊተነተን የሚችለው? በምን ዘዴስ ነው በዘመናችን ያሉ ማህበራዊ ቅሬታዎችን፥ ያልተፈቱ ማንነቶችንና የተወጠሩ ግንኙነቶችን የሚያጠናክሩ መናፍስቶች ጋር መግባባትና መገዳደር የሚቻለው? በዚህ ሁኔታስ ስለ “እኛ” አፍ ሞልቶ መናገር የሚቻለው? “የለቅሶ ክዋኔ ድርሰት” ከላይ በተገለፁት ጉዳዮች አማካኝነት ለምስክሮች አስቸጋሪ የሆኑ ማህበራዊ ሁኔታዎችን እውቅና የሚሰጥ ለገቢር መገልገያነት የቀረበ እሳቤ ነው። በመሆኑም በተለምዶ ከሚታወቀው የገቢር ድርሰት ሚና በተለየ መልኩ፤ በግልባጭ ድርሰት አግባብ የሚዳብር እና በርሕራሄና መቆርቆር ላይ የተመሰረተ መላበስን ተከትሎ የሚመጣ ፅሁፍ ነው። በዚህ ሁኔታ የድርሰት ፅሁፉ የሚዘጋጀው ለከዋኒዎቹ እና ክዋኔው ለሚካሄድበት ስፍራ ቀጥተኛ ተሳትፎ እድል በመስጠት ነው። ስለዚህም፤ “የሀዘን ክዋኔ ድርሰት” ከፅሁፉ ይልቅ የንጥቂያንና የጭቆናን ታሪክ ተላብሶ በመምሰል ሳይሆን በመሆን ለመተረክ ለፈቀደው ከዋኒ የህይወት ተሞክሮ የበለጠ ቦታ ይሰጣል። “የሀዘን ክዋኔ ድርሰት” በንጥቂያና በጭቆና ምክንያት በጥልቅ ሀዘን እና ለቅሶ ውስጥ ያለውን እካላዊ እውቀትና አካላዊ ልምድ በጥበብና በአንክሮ ለመረዳትና ለመግለጽ የሚረዳ ስነ-ጥበባዊና ፖለቲካዊ ሂደት ነው። ከዚህም ሌላ፤ የክዋኔ ሂደቱ አካላዊ ድርጊቶችን በመላበስ ፅንሰ-ሃሳብ ውስጥ በጋራ በመከወን የህይወት ተሞክሮዎችንና እውቀቶችን በማካፈልና በመማማር ግንዛቤን ማስፋትና ጭቆናን ለመተረክ የነጠረ ቋንቋ ለማዳበር ሁኔታዎችን ያመቻቻል። በተጨማሪም፤ የመላበስን ክዋኔ እንደ ስነ-ውበት፣ ስነ ዕውቀት/ትምህርት እና ፖለቲካዊ ድርጊት አድርገን እንድንገነዘብ የሚረዳ ልባዊ የመጋራት፣ የርሕራሔና የመቆርቆር ስሜቶችን ለማዳበር እድሎችን የምናገኝበት መንገድም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በዚህ መሰሪያና የገቢር እንቅስቃሴዎች ውስጥ፤ “የሀዘን ክዋኔ ድርሰት” የሚከናወነው በተለመደው የድርሰት አወቃቀር ሂደት ሳይሆን በግልብጥ ድርሰት (Reverse script creation) ነው። (3)

“የሀዘን ክዋኔ ድርሰትን” የማዘጋጀት ሂደት አንዱ አላማው ብዝሃነት ያላቸውን ማንነቶችና ግንኙነቶች እውን ለማድረግና የጋራ ምናብ ለመገንባት እንዲሁም ይህ ራዕይ ለብዙዎች እንዲደርስ በማድረግ፤ ሰዎች ከተጨቆነ ነባራዊ ሁኔታ ባለፈ የሆነ አይነት ነፃነትን እንዲያገኙ መሻት ነው። በተጨማሪም ፖለቲካዊ በሆኑ ቦታዎች ላይ በንጥቂያ ክዋኔ ገቢር ላይ የሚሳተፉ የተለያዩ ማንነቶች እንዲቀራረቡና በመካከላቸው እምነት እንዲደረጅ የሚያስችል ስትራቴጂዎችን ያቀፈ ከመሆኑም በላይ፤ በአንድ አውድ ላይ ብቻ እንዲሰራ ብቻ ሳይሆን፤ ተራማጅ በሆነ መልኩ የምናከናውነውና ለሌሎች አውዶች ልናጋራው የምንችለው “የሀዘን ክዋኔ ድርሰት” የመፍጠር ብቃትን የማመቻቸት ሃሳብ ሰንቆ የተዘጋጀ የገቢር ማደራጃ ነው።

(2) Frank B. Wilderson, *Red, White & Black: Cinema and the Structure of US Antagonisms* (Durham: Duke University Press, 2010), 1–32.

(3) Reverse script creation based on a certain form of performative engagement is not a simple summary or synopsis of the performance. See Adam Andrzejewski & Marta Zareba, “Theatrical Scripts,” *Rivista di estetica* 65 (2017): 177–94; doi: 10.4000/estetica.2169.



ገቢሮች

ይህ የገቢር ክፍል የተለያዩ ልምምዶችን ክወኔዎችን የያዘ ሲሆን፤ ከእያንዳንዱ እንቅስቃሴ በኋላ በተሳታፊዎች መካከል የሚደረጉ ውይይቶችና ልምድ ልውውጦች እጅግ ወሳኝ መሆናቸውን መገንዘብ ያሻል።

## የሃዘን እንጉርጉሮ ማደራጀት

ይህ ገቢር ከሀዘን፣ ከመገፋት፣ ከመነጠቅና ከጥልቅ መከፋት ጋር በተያያዙ ጠቃሚ ለሆኑ ቃላት የነጠረ ትርጉም በማበጀትና የጭቆና ቋንቋን ሃይል በማስፋት፤ የቃላቶቹን ትርጉም መሰረት ባደረገ መልኩ የሀዘን እንጉርጉሮዎችን (4) ለመጻፍና ሃሳብን በተለየ መልኩ ለመግለፅ ያመቻቻል።

- ከመነጠቅ፥ ከመገፋት፥ ከሀዘን፣ ከርህራሄ፣ ከመቆርቆር፥ ከለቅሶ እንዲሁም ከትግልና ከእምቢ ባይነት ጋር የተዛመዱ ቃላትን መዘርዘር፤
- እያንዳንዱ ቃል ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ለቃላቱ ከአካባቢው እውነታ ጋር የሚገናኝ መልኩ ተጨማሪ ትርጉም መስጠት፤
- እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ትርጉም ከተሰጣቸው ውስጥ የተወሰኑ ቃላትን በመውሰድ እና እንደ መሪ ቃል በመጠቀም የሀዘን እንጉርጉሮ መጻፍ፤
- ከግሩፑ የተሰበሰቡትን እንጉርጉሮዎች በመቀጣጠል አንድ ወጥ የሀዘን እንጉርጉሮ አድርጎ ማቀናበር፤
- ከዚያም ከመነጠቅ፥ ከመገፋት፥ ከሀዘን፣ ወይም ከትግልና ከእምቢተኝነት ጋር በተያያዘ አንድ ስፍራን መርጦ በጋራ የሀዘን እንጉርጉሮ ንባብ ማካሄድ።

(4) Lamentation poems are a style of non-narrative poem expressing deep grief or sorrow over a personal loss. In the Amharic language, they are referred to as “Ye hazen enguguro,” and are counted among the popular expressions of loss and grief in Ethiopian mourning traditions.



↻ Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Mourning performance in public space (on Menilek Square); lamentation poem writing exercise; both in Addis Ababa, 2019



## ገቢሮች

### ድምፀትን ማዋቀር

ይህ ልምምድ ድምፀትን በማዋቀር በተለየ ሁኔታ እራስን የመግለፅ ሂደት የሚፈጥር ሲሆን፤ በተቻለ መጠን ክፍት በሆኑ ስፍራዎች ወይም የህዝብ ተብለው በሚታወቁ ቦታዎች ላይ ቢካሄድ፤ የተቀናጀ በጋራ የማዘን ሂደት ወይም ስልታዊ የሆነ የተቃውሞ ድምፅ እንደሆን ሊታሰብ ይችላል።

- እያንዳንዱ ተሳታፊ የሀዘን፣ የመነጠቅ፣ የለቅሶ፣ የበደል ወይም ደግሞ የተቃውሞ መገለጫ ሊሆን የሚችል አንድ ድምጽ ያወጣል፤
- ተሳታፊዎች አንድ በአንድ የፈጠሩትን ድምጽ ለሌሎቹ ተሳታፊዎች በጋራ ማለማመድ።

### ልዩ የሀዘን ስነ–ሥርዓት መፈጸም

ይህ ልዩ የሀዘን ስነ–ሥርዓት የመፈጸም ሂደት፤ በጭቆና ምክንያት የጠፉ ነፍሶችን ከማስታዋስና ከመዘከር በዘለለ፤ ከስቃይ መናፍስቶች ጋር በመደራደር ክፉ ጊዜያትን ለማስቀረትና መልካም ህይወትን ለማስፈን የሚደረግ መልካም ስነ–ሥርዓት ነው። (5)

- የተለያዩ የለቅሶ ባህሎች ላይ ተዋያዩ፤ ከዚያም ከተለያዩት ባህሎች ውስጥ አንድ አንድ ቃል፥ ድምጽ፣ አባባል፥ ቁሳቁስ፣ አካላዊ ምልክት፤ እንቅስቃሴ፥ ተፈጥሯዊ ቁስ መምረጥ፤
- ከተለያዩት የለቅሶ ባሕሎች የመረጣችኋቸውን መገለጫዎች በማካተትና በማዋቀር አንድ ልዩ የሆነ ስነ–ሥርዓታዊ ክዋኔ ማዘጋጀት
- ሀዘንና ሰቆቃን ከመፍጠር ጋር ታሪካዊ ተያያዥነት ያለው የጭቆና ቦታ መርጦ የተዘጋጀውን ልዩ ስነ–ሥርዓት መፈፀም።

(5) Most cultures in Africa have mourning traditions involving rituals; in the Ethiopian context, mourning rituals are mainly seen as ways to communicate with the dead, and to honor, celebrate, and sustain the memory of the deceased.



↻ Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Vocal exercise; ritual-making performance at Mount Entoto; both in Addis Ababa, 2019





## ገቢሮች

### ይፋዊ የወል ሀዘን ክዋኔ

ይህ የተግባር ክፍል ይፋዊ የሆነ በጋራ የማዘን ክዋኔን በተወሰኑ ቦታዎች አቀናብሮ የመከወንን ሂደት የሚያመቻች ሲሆን፤ የጋራ ክዋኔውም ከመገፋት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ስፍራዎች እንዲካሄዱ በማበረታታት አካላዊ ምስክርነት እንዲንፀባረቅ ያበረታታል። (6) ይህንን ክዋኔ ለመፈፀም ከመንግስት የፀጥታ አካላት ጋር አላስፈላጊ እሰጥ-አገባ ውስጥ ላለመግባት አስቀድሞ ስለቦታው አስፈላጊውን መረጃ ማግኘትና ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል።

- በአካባቢው ሰዎች ስለተነጠቁባቸውና ለሀዘን ምክንያት ስለሆኑ ቦታዎች ታሪክ እንዲሁም ጊዜያዊ ሁኔታ መወያየት። ከዚያም የተወሰኑ ስፍራዎችን ለክዋኔ መምረጥ፤
- ከዚህ ቀደም ሲል በነበሩት የተለያዩ የክዋኔ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተገኙ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን እንደ ግብዓት በመጠቀም የጋራ የሀዘን ክዋኔ ማዋቀር፤
- ቅድሚያ ልምምድ በማድረግ የሀዘን ክዋኔውን በተመረጡት ስፍራዎች በጋራ በይፋ መከወን።

(6) Involve gestures and movements that have different performative qualities. The project *Care & Become* has tried to further develop these performative elements as aesthetic and political acts.

↑ Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Rehearsal for mourning performance, Addis Ababa, 2019

## ገቢሮች

### የግልብጥ ክዋኔ ተረክ መጻፍ

ይህ የገቢር ክፍል ቀደም ብሎ የተከወነውን ይፋዊ የሀዘን ክዋኔና አካላዊ ተሞክሮዎች ዋና መሰረት በማድረግ የግልብጥ ትርክት በፅሁፍ ማደራጀትን ያመቻቻል። የግልብጥ ትርክት መፃፍ ማለት ጊዜና ቦታን መሰረት በማድረግ የተካሄደን ተግባር ወይም ክወኔ መነሻ በማድረግ የሚደራጅ የክወኔ ምምሪያ ፅሁፍ ማለት ነው። ይህም ማለት ግን፣ የተከወነውን ተግባር የመዘርዘርና የመተረክ ሂደት ሳይሆን፣ በክዋኔው ሂደት ውስጥ የተፈጠሩ አካላዊ እውቀቶችን፥ ተሞክሮዎችንና ምናቦችን በማዋቀር ትርጉም የሚሰጥ ተረክ የመፍጠር ሂደት ነው።
ለተከወነው ይፋዊ የሀዘን ክዋኔ የግልብጥ ትርክቱን በፅሁፍ ከማስፈር በፊት፣ የሚከተለውን አጭር ልምምድ ማድረግ የሚመከር ሲሆን፣ ይህም ልምምድ የግልብጥ ትርክቱን ለፅሁፍ እንደ መግቢያና መለማመጃ ሆኖ ያገለግላል።

---

- ተሳታፊዎችን በጥንድ በጥንድ ማዋቀርና ለልምምዱ ቦታ እንዲይዙ ማድረግ፣
- ጥንዶቹ በየተራ ለአጋራቸው ቃላትን ሳይጠቀሙ በፊትን ገፅታ፥ በምልክት እና በሰውነት እንቅስቃሴ ብቻ በመጠቀም የሆነ ዓይነት ተረክ ይነግራሉ።
- እያንዳንዱ ተሳታፊ ከባልንጀራቸው አካላዊና ምልክታዊ ገለፃ የተረዱትን ተረክ በፅሁፍ ያሰፍራሉ፣
- ከዚያም በየተራ ለተሳታፊው ያደራጁትን ተረክና ተሞክሮ ያካፍላሉ።

---

በቀጣይነት፣ ተሳታፊዎች በሶስት ቡድን ይዋቀራሉ። እያንዳንዱ ቡድን ከታች ከተጠቀሱት ሶስት መሰረታዊ አቅጣጫዎች ውስጥ አንዱን በመውሰድ፣ በቀደመው ክፍል በጋራ የተከወነውን ‘ይፋዊ የሀዘን ክዋኔ’ መሰረት በማድረግ የግልብጥ ትርክ በፅሁፍ ያዘጋጃሉ።

---

- ይፋዊ የሀዘን ክዋኔው በጋራ የተደረገበት ስፍራ ታሪክ ምንድን ነው? ስፍራው አሁን ያለበት ሁኔታና ምን ይመስላል? ምን ዓይነት አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው?
- ምን ዓይነት የክዋኔ ስልቶች፥ ዘዴዎችና አቀራረቦች በክወኔው ውስጥ ተካተወል? ለምን?
- ክዋኔውን በመከወን ሂደት ውስጥ ምን ዓይነት ተሞክሮዎች፥ ልምዶች፥ ዕውቀቶችና ተግዳሮቶች ነበሩ?

---

በተቀመጡት አቅጣጫዎች ተረኮች ከተፃፉ በሁዋላ ሶስቱም ቡድን በአንድ ላይ እንዲመጣ ማድረግና ከቡድኖቹ የመጡትን ተረኮች በማንበብ ውይይት ማድረግ። በመቀጠልም፣ ከሶስቱም ቡድን የመጡትን ተረኮች በአንድ ላይ በማዋቀር ወጥ የሆነ ተረክ ማደራጀትና ተጨማሪ ውይይት ማድረግ። በመጨረሻም፣ የተገኙ ተሞክሮዎችና ልምዶች፣ እንዲሁም የተወቀረውን የክዋኔ ተረክ ለሌሎች ማካፈል የሚቻልበትን መንገድ መቀየስና ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ።



↑ Berhanu Ashagrie, *Care & Become:* Reverse scriptwriting exercise in pairs, Addis Ababa, 2019




ADDITIONAL REFERENCES

- Cobbina, Jennifer E. *Hands Up, Don't Shoot: Why the Protests in Ferguson and Baltimore Matter, and How They Changed America*. New York: New York University Press, 2019.
- Kedhar, Anusha. "'Hands Up! Don't Shoot!': Gesture, Choreography, and Protest in Ferguson." *The Feminist Wire* (6 October 2014). Online at: thefeministwire.com/2014/10/protest-in-ferguson.
- Palacios, Margarita. *Radical Sociality: On Disobedience, Violence and Belonging*. London: Palgrave Macmillan, 2013.
- de Sousa Santos, Boaventura. *Epistemologies of the South: Justice against Epistemicide*. Boulder: Paradigm Press, 2016.
- Spatz, Ben. "Notes for Decolonizing Embodiment." *Journal of Dramatic Theory and Criticism* 33, no. 2 (2019): 9–22. Doi: 10.1353/dtc.2019.0001.


ARTWORKS

- Brown, Trisha, artist. 1971. *Accumulation.* Choreography.
- Mawimbi, Alex (Ato Malinda), artist. 2013. *Mourning a Living Man*. Performance.
- Nkanga, Otobong, artist. 2012. *Contained Measures of Kolanut*. Mixed-media performance.
- Norment, Camille, artist. 2016. *Prime*. Haptic sound installation composed for benches and four voices.
- Wei Wei, Ai, artist. 1995–2017. *Study of Perspective.* Series of photographs.
- Wilcox, Noelle Awadallah Hui Niu & Mihret Kebede, artists. 2018. *An Intimate Exile*. Video, poetry, and dance.

STRUGGLES & PROTESTS

- Las Tesis, Las Tesis, *Un violador en tu camino* [The rapist is you], Chile (2019).
- *Hands Up, Don't Shoot!* Ferguson, USA (2014).
- *Women in Black,* Israel (1988) and internationally.
- *Madres de Plaza de Mayo,* Buenos Aires, Argentina (1977–2006).

CREDITS

*Care & Become*, by Berhanu Ashagrie Deribew. Mourning performances in public space, Addis Ababa, Ethiopia, 2019. Collaborators: Berhanu Ashagrie, with Brook Teklehaimanot, Helen Zeru, Kassahun Hailu, Mihret Kebede, Martha Haile, Meron Hailu, Robel Temesgen, Tesfaye Bekele, and Zerihun Berhanu. Contributors: Ameneshewa Admassu, Dr. Elizabeth W. Giorgis, Julien Schmid, Lucie Strecker, Dr. Netsanet G. Michael, Dr. Surafel Wondimu, and Tassew Wondim. Supporters: Agegnehu Adane, Eyob Kitaba, Ashenafi Mestika, Bekele Mekonnen, Desalegn Worku, Henok Melkamzer, Liya Girma, Meseret Hailu, and Emuye Majet. Documentation: Habtamu Gebremeskel. Produced with the support of FWF PEEK: "DisPossession: Post-Participatory Aesthetics and the Pedagogies of Land."

# በዘመናችን ባለው የሉላዊ ደቡብ ወቅታዊ እውነታ ላይ የቀረበ ሂሳዊ ቁዘማ

በኤልሳቤጥ ወልደጊዮርጊስ

በሉላዊ ደቡብ የአለም ክፍል ውስጥ በመገዛት እና በስልጣን መካከል በሚገኙ ብዙሃነት ያላቸው ተቃርኖዎች ላይ በማውጠንጠን ይህ ከንጥቂያ ባሻገር የተባለው የገቢር መጽሃፍ አዳዲስ የስነ-ውበት እሳቤዎችን እንድንመለከት ከማስቻሉም በላይ ለአዲስ አይነት የሰው ልጅ የማንነት ምስረታ (humanist subjectivity) ስነ-ውበትና ስነ-ጥበብ ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽኦ እንድንገነዘብ ያግዘናል። ምንም እንኳ የሉላዊ ደቡብ የአለም ክፍል የወደፊት እጣ ፋንታ በብዙ እርግጠኛ ባልሆኑ ሂደቶች የተመላ ቢሆንም፤ እነዚህ የስነ-ጥበብ ምሁራን በተለያዩ መንገድ ያቀረቡዋቸው እሳቤዎችና ያዘጋጁዋቸው የተግባር ሂደቶች ይህን እርግጠኛ ያልሆነ ነገ በአዲስ መልክ ለመቅረጽ ያላቸውን ቁርጠኝነት በግልጽ ያሳያል።

የስነ-ጥበብ ተመራማሪዎቹ በመግቢያው ላይ እንደሚያመለክቱት፤ ለዚህ ስራ አንዱ ቆስቋሽ የሆናቸው "ከደቡባዊ የእውቀት አደረጃጀት ማእቀፍ (epistemologies of the South) የተገኙ እና ገዢ የሆነውን የአውሮፓ ተኮር የእውቀት ምርት ማእቀፍን ለመሻገር ትግል የሚያደርግ የሃሳብ ስርዓት ነው"። በዚሁ የመፅሃፉ መግቢያ ላይ እንደሚያመለክቱት "ግባቸው በነባርና የአካባቢ እውቀቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ከተለያዩ አለማት የመነጩ ንድፈ ሃሳቦችን በመለየት በሉላዊ ደቡብ የአለም ክፍል ላሉ የተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች የተለያዩ መልሶችን ማግኘት ነው"።

እነዚህ የስነ ጥበብ ሰዎች የሚያቀርቡት ዋነኛው እና በሰፊ መሰረት ላይ የታነፀው ትርክት ውስብስብ፥ ብዝሃ አቀፍ እና ብዝሃ ንብርብርነት ያለው በፆታ፣በመደብ እና በዘር ላይ የተመሰረተ በአገራዊ ድንበር እና ከዚያ ባሻገር የሚሰራ የማንነት ግንባታ ትርክት ነው። በዚህ ስራ ዓለማቀፋዊ ካፒታል (global capital) ይሞገታል፤ ብሎም በሰዎች መካከል የሚፈጥረውን ልዩነት የትኞቹ ሰዎች መታቀፍ እና የትኞቹ መገለል እንዳለባቸው የሚያበጅበትን ስርአት እና ድንበር ፀሀፊዎቹ ይሞግታሉ። እነኚህን የመሰሉ ልዩነቶችና መገለሎች በሉላዊ ደቡብ የአለም ክፍል በጎላ መልኩ እንደሚገኙ በስነ-ጥበብ ስራዎቻቸው ከማሳየታቸውም በላይ ክህሎትን በተመላ እና ምናባዊ በሆኑ መንገዶች በተለያዩ ስፍራዎች ላይ የሚከሰቱ የችግር እና የቀውስ ሁኔታዎችን ያጤናሉ። በተለይም የ"Dispossession" ወይንም የንጥቂያን ፅንስ ሃሳብ በሚመረምሩበት ጊዜ፤ ጉልህ በሆነ መልኩ ንጥቂያ ድንበር ዘለል የሆኑ የኢኮኖሚ እና የመሰረተ አውታሮች ትስስር ምክንያት በየደረጃው እየተስፋፋ የሚሄድ እንደሆነ በአግባቡ ያሳያሉ። በገቢር መፅሃፉ እንደተጠቀሰው "ብርቱ ጭካኔ እና አውዳሚ ዝርፊያ በሚያስጨንቁት ዓለም ውስጥ፤ ምን አይነት ታሪኮችን መዘከር እና ደጋግመን መናገር እንዳለብንና ከሕይወት ዓለም የመጥፋት አደጋ ከተጋረጠባቸው ታሪኮች የትኞቹን መስማት እንፈልጋለን?" የሚለውን ጥያቄ ወሳኝነት ያሰምሩበታል።

የንጥቂያ ንድፍ-ሀሳብ በሁሉም የስነ-ጥበብ ስራዎች ውስጥ በጉልህ ተገልፆ የምናገኘው ነው። የመሬት እና ሌሎች ንጥቂያዎች በሚያስከትሉት ጉዳት አማካኝነት ሁል ጊዜ ግልፅ ያልሆኑ፣የሚለዋወጡ እና ብዥታን የሚፈጥሩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው የነጻነት፣የፍትህ እና የፖለቲካ መብቶች ትርጉምና ልምምድ ያልጠራና ውሉ የማይያዝ ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። በዚህም የተነሳ ስለ ሁሉም አይነት ንጥቂያዎች የምንወያይባቸው እና የምንከራከርባቸው አማራጭ መድረኮችን መፍጠር እንደሚያስፈልግ መገንዘብ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እነዚህ ስራዎች ያስረግጡልናል።

1 The Willful Weeds Research Group, "Dispossession Matters: An Invitation," in this volume, 9.

2 Ibid.

3 Ibid., 10.

በዚህ የገቢር መጽሃፍ ውስጥ የምናገኘው የንጥቂያ ፍልስፍናዊ መሰረትን ተንተርሶ የሚደረግ ሂሳዊ መጠይቅን በመያዝ በኢትዮጲያ ውስጥ ባለፉት ጥቂት አመታት ሲደረግ የቆየውን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ፅሁፌ ውስጥ በመጠኑ ለማንሳት እሞክራለሁ። ይህ የተቃውሞ እንቅስቃሴ የዛሬይቱን ኢትዮጲያን ገዢ የፖለቲካ ስርዓት ከመሰረቱ ያናጋ እንቅስቃሴ ነው። ሆኖም ግን የተቃውሞው ዋና ተዋንያን ትግላቸውን መሰረታዊ እና አዎንታዊ ወደሆነ ፖለቲካዊ ህይወት ለመለወጥ አስችሏቸዋል ብሎ በእርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም። ትግላቸው “በጂኦግራፊ እና በብሄር ማንነት ላይ የተመሰረተ አዲስ የዜግነት እና የማንነት ጥያቄ በኢትዮጲያ ውስጥ መገንባት” ላይ መሆኑ ግልጽ ነው። የግዛታዊ ሉዓላዊነት ጥያቄ እየተነሳበት በመሆኑ ዜግነት በአገር አቀፍ ደረጃ ከመበየን ይልቅ አማራጭ በሆኑ አዲስ እና ብዝሃነት ባላቸው የባለቤትነትና የማንነት ጥያቄዎች ሲቀመር ይታያል። በእነዚህ የብዝሃ ማንነት እና የባለቤትነት ስሜቶች ላይ በመመርኮዝም ተፎካካሪና ተወዳዳሪ የፖለቲካ አመለካከቶች የመብት እና የይገባኛል ጥያቄዎችን ሲያንጸባርቁ ይስተዋላል። በሉአላዊነት እና የተለያዩ የዜግነት አይነቶች መካከል ያለው ግጭት ከአለም አቀፍ ገዢ የሆነ የኢኮኖሚ ስርዓት ጋር የተቆራኘ ነው። ድንበር ዘለል የሆነ ካፒታል በኢኮኖሚዎቻችን ላይ በሚያሳድረው ተፅእኖ እና እየጨመረ በመጣው ቁጥጥር የተነሳ ስርዓታዊ አድሎ እና መገልገል ከመባባሱም በላይ የፖለቲካ ማንነቶች ቀውስ ውስጥ እንዲገቡ ሆነዋል።

ምን አልባትም የኢትዮጲያ ተሞክሮ በሉላዊው ደቡብ የአለማችን ክፍል የሚገኙ በንጥቂያ አውድ እንዲሁም በዜግነት መብት ብያኔዎች ዙሪያ የሚነሱ ያጋራ ተግዳሮቶችን ለመረዳት ሊጠቅመን ይችላል። ለምሳሌ ለመጥቀስ ያክል እስከ 2019 መጨረሻ ኢትዮጲያ 1.4 ሚሊዮን ሰዎች በስደት እና በአገር ውስጥ መፈናቀል የተነሳ (1.2 ሚሊየን የተፈናቀሉባትን ሶሪያን በማስከተል) አለምን ስትመራ ቆይታለች። ምንም እንኳን የግጭቶች መንስኤ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩትም በክልላዊ ድንበር አለመግባባት፣ እንዲሁም ማነው ትክክለኛው የመሬት ባለቤት በሚል የሚነሳ የብሔር መልክ የያዘ ግጭት ለተከሰቱ መፈናቀሎች፣ ንጥቂያዎች፥ የደቦ ብያኔዎች እና የሃይል እርምጃዎች እንደ አይነተኛ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በእነዚህ ውስብስበና ዘርፈ ብዙ የንጥቂያ እና መፈናቀል ሁናቴዎች የተነሳ የዜግነት ጥያቄ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጣም አንገብጋቢ እና ወሳኝ ጥያቄ እየሆነ መጥቷል። የታሰበ እና በእቅድ በየደረጃው የተደረገ የመሬት ንጥቂያ ታይቶ የማይታወቅ መፈናቀልን አስከትሏል። በንጥቂያ አማካኝነት የተከሰተው መፈናቀል እኩል የሆነ የዜግነት መብት መርህን ሸርሽሯል። ያለፉት ዓመታት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችም የዚህ ንጥቂያ እና መፈናቀል ቀጥተኛ ውጤቶች ናቸው ማለት ይቻላል።

የሚያሳዝነው ነገር ግን ይህን የመሬት ንጥቂያና ከአካባቢ መፈናቀል የተቃወሙ ህዝባዊ ተዋንያን ስለ ዓለም አቀፋዊ ኒዮ ሊበራል የሃይል እንቅስቃሴዎች እና ፕሮጅቶቶች፥ እንዲሁም በመሬት ላይ እያካሄዱት ያሉትን ጭካኔ የተመላ ወረራ፣ በኢንቨስትመንት እና የአገር አንድነትን ለማምጣት በሚል ሰበብ በሚደረግ የመሬት ዘረፋ እና የሰዎች እና የህዝቦች መብት ገፈፋ ዙሪያ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ ነው። የባለቤትነት ስሜት እና አመለካከት የሚገነባው መሬትን ለመያዝና ለመቆጣጠር በሚደረግ የቡድኖች ድርድር አማካኝነት ነው። በመሬት ዙሪያ ቡድኖች የሚሰማቸው የእርግጠኝነት መንፈስ እጦት አለመረጋጋትን ፈጥሯል። ከዚህም በተጨማሪ ምሁራንም የርዕዮተ-ዓለማዊ ቀውስ ውስጥ በመሆናቸው የተነሳ በተለያዩ የብሄር ቡድኖች መካከል ባሉ የድንበር እና የይገባኛል አለመካከቶች በመጠመድ እና አንዱን ደግፎ የሌላውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ሂደት ላይ በማተኮራቸው የተነሳ ከነዚህም ግጭቶች በስተጀርባ ያለውን ፍትሃዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ እኩልነት እና የፍትህ ጥያቄ እንዳይመረምሩ ሆነዋል። በዚህ የተነሳ የቀደመ የጭቆና ታሪክን ከዛሬው ታሪክ እና ጭቆና ጋር በማያያዝ የጋራ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እና ትንታኔ ተንጠልጥሎ እንዲቀር ምክንያት ሆነዋል። አቅም የሌላቸው ግፉአን ፋላጎቶች እና ምኞቶች ዛሬም እንቆቅልሽ ሆነዋል።

የኒዩ ሊበራል ርእዮት አለም ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር ያለው ግንኙነት ገሸሽ በመደረጉ የተነሳ በዚህ ዘመን የመሬት ይገበኛል እና የመብት ጥያቄን የሚወስኑ ሁኔታዎች ከእኛ ተከልለውብን እንዲቆዩ ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም ስር የሰደደ የማንነት ፖለቲካ የኒዮ ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ የፈጠረውን ኢ-ፍትሃዊ እኩልነት እንቆቅልሽ ለመፍታት ኒዮ ሊበራሊዝምን በአግባቡ መረዳት እና መተንተን እንደሚገባው ይዘነጋል። የተለያዩ ብሄርተኝነቶች የሚያቅፏቸው አመለካከቶችና ስሜቶች (sensibilitiess) ከመስፋፋታቸው እና ገዢ ከመሆናቸው የተነሳ የመሬት ይገባኛል ጥያቄን እና መብትን ለመፍታት አገራዊ ብሄርተኝነትን መጠቀም ፋይዳ እንደሌለው መዋቅር መመልከት የተለመደ ሆኗል።



የዓለም አቀፋዊ ካፒታል ፖለቲካ እና ጂኦግራፊ እንዲሁም የካፒታልን መስፋፋት የሚያግዘው የመንግስት ጭቆና የፅኑ አረሞች ፕሮጀክት የሚተልመው አይነት የተደራጀ ዓለም አቀፋዊ ድምጽና መጠይቅ ይሻል። የጽኑ አረሞች መፅሃፍ አዘጋጆች የሚጋብዙን የጊዜውን አንገብጋቢነት በተለየ ሁኔታ እና ንቃት እንድናጤን ነው። እውነትም ይህ የገቢር መጽሃፍ እንደሚያሳየው የከተማ ጂኦግራፊ ፖለቲካ፣ ንጥቂያ፣ መፈናቀል፣ የዜግነት ልዩነት እና ተዋረድ፣ የባለቤትነት እና የማንነት ጥያቄ፣ የመገለል እና እነዚህን የመሳሰሉ በዚህ ዘመን የሚነሱ ክርክሮች፣ እንቅስቃሴዎች እና ትግሎች በሉላዊው የደቡብ የአለም ክፍል ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። እንደዚህ ያሉ በድህረ ቅኝ ግዛት ሀገረ መንግስት ውስጥ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በማተኮር በጽኑ አረሞች የገቢር መፅሃፍ  ዝግጅት ውስጥ የተሳተፉት የስነ-ጥበብ ተመራማሪዎች የሉላዊ ደቡብ የተለያዩ ተሞክሮዎችን በጋራ መድረክ ለውይይት የሚያመጣ ሰፋ ያለ የሃቲት አድማስ (discursive sphere) እንድንፈጥር ያበረታቱናል።

ጽኑ አረሞች

# አብሮ የመስራት ፕሮቶኮል

በመጨረሻም የፖለቲካ ሥነ-ምህዳር ምሁራን የንጉሠ ነገሥቱን ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት (epistemologies) ባልተማሩበት እና የእውቀት ምርትን በጋራ የመለወጥ ዘዴ በማድረግ ለፖለቲካ አቋማችን ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ጥሪ ያቀርባል።

— Juanita Sundberg, “Ethics, Entanglement, and Political Ecology”



*መሳሪያ*

ይህ የስራ ፕሮቶኮል ረቂቅ የተዘጋጀው ሁሉም የቡድኑ አባላት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉበትና እንዲያጎለብቱት በማሰብ ነው።ብዙዎቻችን የተዘረዘሩትን አብዛኞቹን ሂደቶች ልናውቃቸው ብንችልም እዚህ ላይ በድጋሚ ጥራታቸውን ጠብቀው ቀርበዋል። ተጨማሪ ግብአት፣ ግብረ መልስ፣አስተያየቶችና ሃሳቦች እንዲሁም ሂስ መስጠትም ይበረታታል።

## I. የጥናትና የምርምር ስብሰባዎች

### 1. ስብሰባውን ማደራጀት

ለያንዳንዱ የምርምር ስብሰባ ሁለት ሰዎች ዋና አደራጅ የመሆን ሃላፊነትን ይወስዳሉ

- ዝርዝር እቅድ ያዘጋጃሉ፣ የምንሰራባቸውን ቦታዎች ይወስናሉ (ለምሳሌ ከማክሰኖ እስከ አርብ፣ በየሁለት ወሩ)
- ካለፈው ስብሰባ ጋር ቀጣይነት መኖሩን አረጋግጡ።ያልተቋጩ ጉዳዮች መቋጨታቸውን አረጋግጡ
- በቡድኑ አባላት መካከልም ሆነ በተጋባዥ እንግዶች መካከል ተግባቦትን (communication) አመቻቹ
- ከስብሰባው በፊት እና በኋላ ተገቢውን የስራ ክፍፍል አድርጉ ወይም ምደባ አድርጉ (ማስታወሻ ማን ይወስዳል፣ ሰዐት ማን ይይዛል፣ ነገሩን ለመሰነድ ኃላፊነት ማን ይወስዳል)
- ውጤታማ የማነቃቂያ፣ የማወያያና ልውውጥ ማድረጊያ መንገዶችን አቅርቡ

### 2. እያንዳንዱ ስብሰባ የሚጀምረው

- የሳምንቱን የስራ እቅድ በመወያየት (ይሄ በዋና አዘጋጆቹ ቀድሞ ይሰራጫል)
- የስራዎቹን አላማ መወያየት
- የስብሰባውን ግብ (ግቦች) መወሰን
- የሚሰሩትን ተግባራት ዝርዝር ማሰራጨት (መበተን)

### 3. እያንዳንዱ ስብሰባ የሚያልቀው

- የሳምንቱን ግበረ መልስ (feedback)፣ አስተያየት እና ግምገማ በማቅረብ
- ለቀጣዩ ስብሰባ ጠቅለል ያለ እቅድ መወያየትና ማርቀቅ
- የሚሰሩትን ተግባራት ዝርዝር ማሰራጨት (መበተን)
- ዋና ዋና የዝግጅቱን ማጠቃለያ ሃሳብ በድምጽ ማስቀረት (ይሄ ስብሰባ ያመለጣቸው ሰዎች ዋና ዋና ሀሳቡን እንዲያደምጡ እድል ይሰጣል)

### 4. እረፍቶች

ዋና አዘጋጆቹ የሳምንቱን ስብሰባ ሲያቅዱ፣ የግማሽ ቀን ዕረፍትን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ። የዚህ የእረፍት ጊዜ ፋይዳ የስራችንን ሂደት በተመለከተ ወደ ኋላና ወደፊት ለመመልከት የትኩረት ግዜ እንዲኖረን እድል ይሰጣል።

### 5. የስብሰባ ቦታዎች

የስብሰባ ቦታዎች: እስካሁን ብዙ ስብሰባዎችን በአካዳሚው ቅጥር ውስጥ አዘጋጅተናል። ይህ ምቹ ቢሆንም የቢሮው አካባቢ ብዙውን ግዜ የቡድኑን መንፈስ የሚያነቃቃ አልነበረም። ከአካዳሚው ግቢ ውጪም ውስጥም ያሉ ሌሎች ለቡድን እንቅስቃሴዎቻችን የሚመቹ ቦታዎችን በማሰብ የሥራ ክፍለ ጊዜዎችን እናዘጋጃለን። ለምሳሌ ወደ ጫካ በመሄድ እንጉዳይ መሰብሰብ፣ በእግር እየተጉዋዝን መወያየት፣ በጫካ ውስጥ ታሪኮችን ማውራት፣ ወዘተ ያሉ ነገሮችን እናደርጋለን።

## II. ተግባቦቶች

### 1. የኢሜል ግንኙነት

እስካሁን ቡድኑ በኢሜል ለመመለስም ሆነ ውይይቶችን ለማስፋፋትና ለማዳበር ዝግታ ይታይበታል። የላኪውን ተነሳሽነት ካለማበረታታቱም በላይ ሀይሉንም ይጨርሳል። ይህ ሁኔታ ተግባቦትን ዝግ ያለ ሂደት እንዲይዝ አድርጎታል። መሰረታዊ መረጃን በተመለከተ በኢሜይል የሚላክ ጥያቄን በሁለት ቀናት ለመመለስ እንሞክራለን

### 2. ቀነ-ገደብ

እስካሁን የምርምር ስራዎቻችን የዘገዩበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ተጨማሪ ጉልበት እና ጥረት አክለንበት በሰአቱ የጥናት ውጤቶቻችንን በጊዜ ለማቅረብ እንፈልጋለን። በተመሳሳይ ሁኔታ ስራዎቻችንን ማስረከብ የቆረጥነውን ቀነ ገደብ ለመወሰንን ተጨባጭ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ ውሳኔ እናደርጋለን።

## III. አስተዋጽኦዎች

